## የዐውደ ዓመት መዝሙራት

1. ዓመቱን አሳልፈህ
2. ባርክ ለነ
3. ወአንተኒ ሕፃን
4. ርዕሰ ዐውደ ዓመት
5. ዐውደ ዓመት
6. የእለተ የዓመት
7. እናመስግን
8. አበባዮሽ
9. የአዋጅ ነጋሪ ቃል
10. በመንፈስ የሐውር
11. እምሄሶ ለሄሮድስ
12. ለዮሐንስ አንገት
13. መጽአት ወለታ
14. ዮሐንስ ክቡር

## የመስቀል መዝሙራት /ለመስከረም 16 - 25 ቀን/

15. መስቀሉን ተሸክመን
16. መስቀል ቤዛችን ነው
17. መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ
18. መስቀል ተመርኩዘን
19. ኀበ ቀራንዮ
20. መስቀል አበባ
21. ዕፀ መስቀል
22. አየኸው ደመራ
23. መስቀል ኃይላችን
24. ወሪዶ እመስቀሉ
25. ከመ ትባርከነ
26. በመስቀልከ
27. ይትቀደስ ስምከ
28. ዕሌኒ ንግሥት
29. መስቀል ብርሃነ
30. ዮምሰ
31. መስቀል ኃይልነ
32. ጸጋ ነሣእነ
33. ጥልን በመስቀሉ
34. መስቀል ሕይወት
35. ለእጸ መስቀሉ
36. ዘእጣን አንጸረ
37. በመስቀሉ ወበቃሉ
38. በወንጌሉ ያመናችሁ
39. ይቤሎሙ ኢየሱስ
40. ኃይልነ
41. በኃይለ መስቀሉ
42. መስከረም ጠባ
43. መስቀሉሰ ለክርስቶስ
44. ኀበሩ ቃል
45. ዮም በዓለ መስቀሉ
46. ልዑል እግዚአብሔር
47. እንተ ተሐንፀት
48. ርእዩ ዕበዩ
49. መስቀል አብርሃ
50. መስቀል አስተርአየ
51. መስቀል ብርሃነ
52. ርእዩ ዕበዩ
53. መርሕ በፍኖት
54. ሶበ አእመረ.
55. የመስቀል አመላለስ /ወረብ/
56. ኃይለ መስቀሉ
57. ብርሃን ወጣ

## የመስቀል መዝሙራት (በኦሮምኛ ቋንቋ)

58.. ፈኖ ኢፋ (መስቀል ብርሃን አጭሩ)
59. ሎላ ፈኖሣ ቲን (ጥልን በመስቀሉ ገደለ)
60. ፈኖ ኩኒ (ዝንቱ መስቀል )
61. አርሳቱ አገርሲሴ (ዘእጣን አንጸረ).
62. ኮታላላ (ርእዩ ዕበዩ)
63. ኖራ (በመስቀሉ ወበቃሉ)
64. ፈኖ ኬተኒ (መስቀል ብርሃን ረጅሙ)
65. ፈኖ ኬተኒ (በመስቀልከ ርድአነ)
66. ፈኖ ኢፋ (መስቀል አብርሃ )
67. ኤዩ ፈኖ ዳኒ. (ኧኸ በመስቀልከ )

68. እምገቦከ

## የወርኃ ጽጌ መዝሙራት

69. ርሃበ ወጽምአ
70. እስከ ማእዜኑ
71. ተፈጸመ
72. ከማሁ ኀዘን
73. ዮም ጸለሉ
74. መአዛሆሙ ለቅዱሳን
75. ንዒ ርግብየ
76. አክሊለ ጽጌ
77. እምነ እምነ ንኢ
78. አሠርገዋ
79. ማርያም ኅየኪ
80. እስመ ውእቱ
81. እንዘ ተሐቅፊዮ
82. ምንም ሳትበድል
83 ውድስት አንቲ
84. ንግሥተ ሰማያት
85. ክበበ  ጌራ ወርቅ
86. ከመጽጌ ሮማን
87. ብክዩ ኅዙናን
88. አዘክሪ ድንግል
89. ድንግል መከራሽን
90. ሰቆቃወ ድንግል
91. ወደ ምሥራቅ እዩ
92. ምስለ ሚካኤል
93. አፈንብ
94 ኦ ድንግል
95. ለምኚ ድንግል
96. መዓዛ አፈዋት
97. ክበበ ጌራ ወርቅ
98. ንዒ ርግብየ
99. ምዕረ በዘባንኪ
100. እንዘ ተአቀፊዮ (ወረብ)
101. ትመስል እምኪ
102. እመቤቴ የአምላክ እናት
103. ሠናይትየ
104. ንዒ ማርያም
105. እሴብሕ ጸጋኪ

## የመድኃኔዓለም (የአማኑኤል) መዝሙር

106. መድኃኔዓለም አዳነን
107. አማኑኤል ጌታ ሆይ
108. ኑ ደስ ይበለን
109. ዘሰማየ ገብረ
110. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር
111. አማን በአማን
112. ሠላም ሀበነ
113. ዝንቱ ኩሉ
114. እግዚአብሔር ይመስገን
115. እሳተ ጽርሁ
116. ቸሩ መድኃኔዓለም
117. ኩሎ ዘፈቀደ
118. እንዘ የአምር
119. የኃያላን ኃይል
120. በደሙ ቤዘዋ
121. ኢትግድፈነ
122. ፍቅር ሰሐቦ
123. እንዘ ይብሉ
124. ንሴብሖ
125. እስመ አልብነ ረዳኢ
126. መድኃኔዓለም
127. ስብሐት ለአምላክ
128. መድኃኔዓለም
129. ሠራዊተ
130. ወበጽጌያተ
131. አባ አባ
132. መንክረ ግርማ
133. እንደ ዓይንህ ብሌን
134. በመስቀሉ ወበቃሉ
135. ኩሉ ከንቱ
136. እስመ ውእቱ
137. ሰላም ለዝክረ ሥምከ
138. መርሕ በፍኖት

139. ንአ ንአ አማኑኤል
140. ወመኑ መሀሪ
141. መድኃኔዓለም
142. አልቦ ዘከማየ
143. እናመስግን አማኑኤልን
144. መድኃኒት
145. ሰማየ በአብ
146. እግዚአብሔር ብርሃኔና
147. አማኑኤል አዳነን
148. መድኃኔዓለም ክርስቶስ
149. እንዘ ይብሉ
150

## የቅዱስ ሚካኤል መዝሙራት

151. ውእቱ ሊቀሙ
152. ሊቀ መላዕክት
153. ሚካኤል ስዩም
154. ሚካኤል ሊቅ
155. ምስለ ሚካኤል
156. ሰፊሆ ክነፊሆ
157. ከመትባርከነ
158. ሐመልማለ ወርቅ
159. ባሕራንኒ
160. እግዚኡ ረስዩ
161. ዓይኑ ዘርግብ
162. ነዋ ሚካኤል
163. አንተኑ
164. መልአከ ሰላምነ
165. አመ ይሰቅልዎ
166. በእደ መልአኩ
167. ዓይኑ ዘርግብ
168. ሚካኤል መጽአ
169. ዘአውረድከ መና
170. ሊቀ መላዕክት
171. ዝኬ ውእቱ
172. ተወከፍ ጸሎተነ
173. ቅዱስ ሚካኤል
174. ቀዋምያን
175. ውእቱ ሚካኤል
176. በአምሳለ ርግብ
177. ሚካኤል
178. ቅዱስ ሚካኤል
179. ሚካኤል አማልደን
180. አንተ ቅዱስ ሚካኤል
181. ኃያል ኃያል
182. ፈተና ቢገጥማት
183. ከሚካኤል በቀር
184. ዝንቱ አስማተ

## የኅዳር ጽዮን መዝሙራት

185. አብርሂ ጽዮን
186. ዘካርያስ ርእየ
187. የኪዳን ጽላት
188. ታቦተ እንተ ውስቴታ
189. ውስቴታ ታቦተ
190. ታቦተ ሕጉ
191. ሙሴኒ ርእያ
192. ሐመልማላዊት
193. ጽላት ዘሙሴ
194. ዘይሃይድ ዓይነ
195. እንተ ክርስቶስ
196. ጽላት ዘሙሴ
197. ኢትዮጵያ ታበጽህ
198. ተመጠወ ሙሴ
199. ሙሴ ዘርእያ
200. አብርሂ ጽዮን (ወረብ)
201. እዝራኒ
202. ሃሌ ሃሌ ሉያ
203. ዘበሰማይኒ
204. ወባዕዳነ ነቢያት
205. በምን በምን
206. የኅዳር ጽዮን አንገርጋሪ
207. ጽዮን

208. ዕዝራኒ ተናገራ/2/
209. ዘርእየ

## የልደት እና የጥምቀት መዝሙራት

210. በኮከብ መጽኡ
211. በጎለ እንስሳ
212. ውስተ ማኅፀነ
213. መጽአ ከመይቤዙ
214. በጎል ሰበከ
215. ሖረ ኢየሱስ
216. ምድርኒ ርእይቶ
217. ወወለደት
218. በፍሥሐ ወበሰላም
219. ወረደ
220. ወቅድሳት
221. በእደ ዮሐንስ
222. ኢየሱስ ሖረ
223. እንዘ ሕፃን
224. ኀዲጎ ተሰአ
225. ወተመሰሎ
226. ክርስቶስ ተወልደ
227. እምሰማያት
228. መድኃኒነ ተጠመቀ
229. አማን በአማን
230. ሃሌ ሃሌ ሉያ
231. እንዘስውር
232. ክርስቶስ ተወለደ
233. ዮሐንስኒ
234. ሶበ መጽአ
235. ዮም ሰማያዊ
236. ስብሐት ለእግዚአብሔር
237. ወጽአ ወገብአ
238. ንሕ ናንሶሱ
239. መጽአ ቃል
240. ፈለገ ዮርዳኖስ
241. ቅዱስ
242. የምሥራች
243. በበረት የተኛው
244. ከእመቤታችን ተወለደ
245. ኦንፈራፆ
246. የዓለምን በደል
247. የምሥራች
248. ደስ ይበለን
249. ሳር ቅጠሉ
250. እሰይ ተወለደ
251. አንቺ አንቺ
252. እስመ እምዘርዓዳዊት
253. ሶበ ሰማዕነ
254. በክንፉ ጋርዷት
255. ተልኮ መጥቶ
256. ርኢኩዋ
257. በፍሥሐ ወበሰላም
258. ተነሥ እንዘምር
259. ሖረ ኢየሱስ
260. በመንፈስ የሐውር
261. ኑኑ እንደሰት
262. ኢየሩሳሌም
263. ዮም ፍሥሐ
264. ተወልደ
265. ቤዛ ኩሉ
266. ወነዋ ተወልደ
267. ለዘተወልደ
268. ቤዛ ኩሉ
269. በዛሬው ጥምቀቱ
270. በቤተልሔም ተወልደ
271. ይቤላ መልአክ
272. ሃሌ ሃሌ ሉያ

273. በቤተልሔም ተወለደ
274. የምስራች ተወለደ
275. ወአንተኒ
276. በወንጌሉ ያመናችሁ
277. ልዑል እግዚአብሔር
278. ኢየሱስ ክርስቶስ
279. እግዚኡ መርሐ
280. ወነዋ ተወልደ
281. ውእቱ ኢየሱስ
282. መጽአ ወልድ
283. ኸኸ ኀዲጎ
284. ዮሐንስ አጥመቀ
285. ቤተክርስቲያን
286. መንክረ ግርማ
287. በቃና ዘገሊላ
288. ዘበዳዊት
289. አንክርዎ
290. ለክብረ ቅዱሳን
291. ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ/2/
292. ግነዩ ለእግዚአብሔር
293. ተአምረ
294. በጎል በጎል
295. ዮሐንስ አጥመቀ
296. እኅትየ መርዓት
297. እኅትየ ይብልዋ
298. እርሱ ባይወለድ
299. የጥበብ ሰዎች መጡ
300. አብሠራ
301. ማርያም
302. ከነቢያት ሀገር
303. ተወለደ
304. እምሰማያት

**የአስተርእዮ ማርያም መዝሙራት**

305. እንበይነዝ አእምሩ
306. ጊዜ እረፍታ
307. ተናገራ ዕዝራ
308. ዘድንግል መናስግት
309. ድንግል ወላዲተ ቃል
310. እስመ እምዘርዓ ዳዊት
311. ክርስቶስ ተወለደ
312. አስተርእዮ
313. ጊዜ ዕረፍታ
314. ሞትሰ

**የሠርግ መዝሙራት**

315. መጽአ ዘመጽአ
316. ደስ አላት ቤ/ክ
317. ሕገ ሰብእናሁ
318. መርዓዊ ሰማያዊ
319. ይደሰት ሙሽራው
320. ካህናት ተንሥኡ
321. አድርገህልኛልና
322. ድንቅ ነው በጣም
323. እግዚአብሔር ፈቅዶ
324. ደስ ይበለን
325. ቃና ዘገሊላ
326. አጅቡት በዕልልታ
327. ሙሽራዬ
328. በሠርጋችን ዕለት
329. ደመቀ አበራልን
330. መርዓዊ ስቡሕ
331. ዳዊት ይሴብሕ
332. መጽአ መርዓዊ
333. ሁለቱም አንድ ሆነ ዛሬ
334. ደስ አለው ጌታ
335. መጽአ መርዓዊ
336. የምስራች ደስ ይበላችሁ

337. ኢያቄም ወሐና
338. ደስ አላቸው
339. ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ
340. ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ
341. የማነ ተሐቅፊኒ
342. በምድራዊ ሕይወት
343. በክብር ዙፋኑ
344. በቃና ዘገሊላ ቁ.1
345. በቃና ዘገሊላ ቁ.2
346. ኑ ተመልከቱልኝ
347. ሥላሴ
348. የኢትዩጵያ ኦርቶዶክስ
349. ተፈጸመ
350. ንጽሕት ድንግል
351. ወእመአኮ
352. ንሴብሖ ለአምላክ
353. እልል እልል/1/
354. እልል እልል/2/
355. ይትባረክ
356. የሀብከ ዩም
357. እጹብ ድንቅ ሥራ
358. ዘተመነያ
359. ግነዩ ለእግዚአብሔር
360. ደስ አላቸው/2/
361. ሙሽራው ሙሽራ
362. የቃናው ደስታ
363. ሶበ ሰማዕነ
364. እንደአብርሃም
365. ተፈሥሒ
366. አምሮ ሲያበራ
367. እሰይ እሰይ
368. አሐዱ አካል
369. አዳም ሆይ
370. ሙሽራው ደስ ይበልህ
371. ንሴብሖ ለሥላሴ
372. የቤታችን ራስ
373. ቤታችን ይቀደስ
374. ደስ ይበለን /የሠርግ/
375. ለበጐ ፈቃዱ
376. እልል በይ
377. ሙሽራው ከሙሽሪት ጋር
378. የክብሯ መግለጫ
379. ተነሥ ሙሽራዬ
380. ከመጽጌ
381. አንሶሰወ
382. የኢትዮጵያ
383. ትብሎመርዓት
384. አብርሂ
385. አማዕኩኪ
386. ወአንቲኒ

<u>የኪዳነ ምሕረት መዝሙራት /የካቲት 16 ቀን/</u>

387. አምላክ ለእኛ ብሎ
388. ኪዳንኪ ኮነ
389. ክነፈ ርግብ
390. አንቲ ምሥራቅ
391. ሶበሰ ኪዳንኪ
392. አንቺ ነሽ ተስፋው
393. መርሕ ዘገነት
394. ተናዘዘ ብኪ
395. ሰላም ለኪ
396. አማን በአማን
397. አማልጂን ከልጅሽ
398. አዳም ንባብኪ
399. እንበለ ምግባር
400. ኪዳንኪ ኮነ
401. አመ ወርኃ ነጊድ
402. ነይ ነይ ማርያም
403. ልቤን አነሳስቶ

404. ዕርገታ
405. ተበሃሉ
406. ዐረገች
407. ማርያም ዐረገች
408. ጴጥሮስ
409. አእረግዋ
410. እኽ ማርያምስ
411. ኦ ምርአግ
412. ኦ ርኅርኂተ

<u>የንስሐ መዝሙራት</u>

413. በጌቴ ሰማኔ
414. የአብርሃም አምላክ
415. መስክረ ቀራንዮ (1)
416. መስክረ ቀራንዮ /2/
417. አዘነች
418. ሞተሃልና ስለኔ
419. ዘጠኝ ሠዓት ሲሆን
420. ኪርያላይሶን
421. ጌታ ሆይ
422. በዕጸ መስቀል ላይ
423. ለእኛ ብሎ ተንገላታ
424. ኦ የማይሞተው ሞተ
425. በትዕግሥቱ ብዛት
426. በእለተ ዓርብ
427. ድንግል የዚያን ጊዜ
428. ዓለምን ለማዳን
429. ምደረ ቀራኒዮ
450. አምላክ ለእኛ ብሎ
451. አልፋና ዖሜጋ
452. ቅዱስ (3) እግዚአብሔር
453. አቤቱ በመንግሥትህ
454. አባታችን ሆይ
455. ወንበዴ ነበርኩኝ
456. በኢየሩሳሌም
457. የዳዊት ሐዘኑ
458. ልቤ አቤት በል
459. አቤቱ አቤት ኃጢአቴ
460. አደባባይ ቆሜ
461. በከሃሊነቱ
462. ወደ ሕይወት መንገድ
463. ለእኛ ብሎ
464. ነነዌን ሊያቃጥል
465. እስራኤል ሠለቸው
466. አዝናለሁ አለቅሳለሁ
467. ሞቼ ስለማልቀር
468. የጥበብ ሀገሯ
469. አማኑኤል ሆይ
470. ዋ ለነፍሴ
471. ተይ ተመከሪ
472. ዓለም ወረተኛ
473. ለውለታህማ
474. እርዳኝ ዝም አትበል
475. በመከራ ጽና
476. የሰው ልጅ በኃይልህ
477. የሰማዩ አባት
478. አቤቱ ልንበርከክ
479. ላይቀር መሞት
480. በኢያሪኮ መንገድ
481. ማረን አባታችን
482. በሥራዬ የት ይሆን
483. ልመናዬን ስማኝ
484. ሁላችን እንጸልይ
485. ሰው ለሰው
486. መጽሐፍ ቅዱስን
487. ኑ እንቅረብ
488. ነፍሴ ሆይ

489. ወደአንተ እሰግዳለሁ
490. አንድ ጊዜ
491. መቼነው ጌታ
492. እስከመቼነው
493. ከወገኔ ጋራ
494. እያለፈ ነው ዘመኔ
495. አማኑኤል ሆይ
496. እግዚአብሔር መልካም ነው
497. አታውኪኝ ነፍሴ
498. ነብዩ ዳንኤል
499. የነፍሳችን ቤዛ
500. ፍቅርና ሰላምን
501. አሐዱሰ
502. ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ
503. እኔስ በምግባሬ
504. የእመቤታችን አማላጅነቷን
505. ከፈጣሪ በታች
506. ድንግል ሆይ ስለአንቺ
507. እናት አለኝ
508. አድኝኝ እናቴ
509. ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም
510. ኃጢአቴ በዛ
511. ነፍሴ ሆይ
512. ዓይኑ ዘርግብ
513. ምድር ጸዳች
514 እንደተቆጣኝ
515. ስለ እኔ የሞተው
516. የጌታዬ እናት ጸለየች
517. እግዚአብሔር አለኝታችን
518. ከዳዊት አብራክ
519. ስሜ ተለውጦ
520. ተሰቀልክ ወይ
521. ዛሬ ተይዣለሁ
522. ስምህ በሁሉ ተመሰገነ
523. ማን ነው እርሱ
524. ስምሽ ማርያም
525. በዘር አንድ የሆነው
526. ተስፋ አለኝ
527. አልፈርድም እኔ
528. ምስጋና ጀመረ
529. ዮሐንስ ሄደ ዮርዳኖስ
530. ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ
531. እንዲህ አለው ጴጥሮስ
532. አምላካችን ቅዱስ ነው
533. አስተርአያ ገብርኤል ግብተ
534. ነፍሴ ሆይ
535. እግዚአብሔርን ጥራው
536. አምላክ ሆይ
537. ሞትን ድል አድርጐ
538. አንጻኝ
539. ተይ ተመከሪ
540. ነይ ነይ
541. ስምሽ ጣዕም አለው
542. እመቤቴ ስልሽ
543. መልእክተ ወንጌል
544. አባታችን ሆይ
545. የሰው ልጅ ሁል ጊዜ
546. ዕዳ አለብን
547. አቤት የዚያን ጊዜ
548. በአምሳሉ ፈጥሮናል
549. ጊዜዬ እስኪደርስ
560. ጌታ ያለው
561. ከእምነት አደባባይ
562. ንሴብሖ
563. የአብ ቃል አክብሮሽ
564. ማነው የሚያድነኝ
565. ቅያሜው ይቅርና
566. የሀብከ ዮም
567. ኢትዮጵያ ሆይ
568. እሰይ እሰይ
569. የእኛ ጌታ
570. ለእኤስ ልዩ ናት

571. እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ
572. የመስቀሉ ፍቅር
573. ኑ ተመልከቱልኝ
574. ኪዳነ ምሕረት
575. ከወገኔ ጋራ
576. ከካራን ውጡ
577. ኪዳነ ምሕረት ሩኅሩኅ
578. የአርያም ንግሥት
579. ለንስሓ ሞት አብቃኝ
580. ጊዮርጊስ በዚያች ቀን
581. አልተወኝም ጌታ
582. አምላካችን ተመስገን
583. ባርከን
584. የቅዱሳን አምላክ
585. ድንግል ሆይ
586. ስለድንግል ብሎ
587. አምላክ አለ መሃላችን
**588.** ዴማስ ሆይ ተመለስ
**589.** ባሰማት ጊዜ
590. አባታችን
591. ሰላም ላንቺ ይሁን
592. የዓለም ንግሥት የሆንሽው
593. እመቤታችን ላንቺ
594. ማርያም እመቤቴ
595. የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
597. ክርስቶስ በስምህ
598. አቤቱ ማረን ይቅር በለን /2/
599. አቤቱ ማረን
600. እስመ ለዓለም ምሕረቱ
601. ተገርፎ ተሰቅሎ
602. ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል
603. ስብሐት ለአብ
604. በሞት ጥላ ወድቀን
605. በዓለም ጥላ ማረፍ
606. ኑ እንቅረብ
607. የሰው ልጆች ሁላችን እንማር
608. ላይቀር መሞት
609. መመኪያዬ አንተ ነህ
610. አምላክ ሆይ ወደኛ
611. የብርሃን መውጫ
612. ድንግል ሆይ ስላንቺ
613. ድንግል ማርያም እናታችን

## <u>የሆሣዕና መዝሙራት</u>

614. ሆሣዕና እምርት
615. ሰላምሽ ዛሬ ነው
616. እምአፈ ደቂቅ
617. ቅድስት ሀገር ሆይ
618. ሆሣዕና በአርያም
619. ደቂቅኒ
620. አብርሃነም ነስአ
621. በትፍሥሕት
622. ይባዕ ንጉሠ
623. አርዎ ኖኀተ
624. ሆሣዕና በሉ

## <u>የትንሣኤ መዝሙራት</u>

625. ትንሣኤከ
626. አማን በአማን
627. ወምድርኒ
628. እምእቶነ እሳት
629. ጌታ ተነሥቶአል
630. ተስፋ ሕይወት ተሠርዐ
631. ሠርዓ ለነ
632. ፈኑ ዲቤኒ
633. መድኃኒተ ኮነ
634. ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን
635. ንሴብሖ
636. እሰይ ተነሣ
637. ብርሃን ወጣ

638. የሕያዋን አምላክ
639. እልል /6/ አማኑኤል
640. ክርስቶስ ተነሣ
641. እሰይ አገኘነው
642. ገብረ ሰላመ
643. ሰላም ሰላም
644. ኑ እናመስግን
645. ፋሲካ
646. ተንሥአ

## የዕርገት እና የጰራቅሊጦስ መዝሙራት

647. አንትሙስ
648. አምላካችን ዐረገ
649. ኀበ አቡሁ
650. ዐርገ በስብሐት
651. አማን በአማን
652. ዐቢይ ዜማ
653. ዐርገ እግዚእነ
654. ዐረገ በስብሐት
655. ዘምሩ ለአምላካችን
656. ወይቤሎሙ
657. መንፈስቅዱስ ወረደ
658. እየባረካቸው
659. ሐዋርያት ተባበሩ
670. እሰይ አገኘነው

## የግንቦት 1. መዝሙራት

671. ዮም ኮነ
672. እስመ እበውእ
673. እምሐና
674. ዓምደ እሳት ጾርኪ
675. አማን በአማን
676. የምስራች ተወለደች
677. ኦ ማርያም መንክር
678. ተወልዳለችና
679. አእይንታ ዘርግብ
680. አልብኪ ነውር
681. ከሊባኖስ
682. አማን በአማን
683. እኀትየ መርዓት
684. ኢያቄም ወለዳ
685. ሐመልማላዊት
686. ኢያቄም ወሐና
687. ማኅደረ መለኮት
688. ኢያቄም ወሐና
689. ኦ ድንግል አምሳል
690. የሐና ልጅ ነሽ
691. ማርያምሰ ተንቱ
692. ማርያም ድንግል
693. እስመ እምዘርዓ ዳዊት
694. ምርያም ንጽሕት
695. ንጽሕተ ንጹሐን ከዊና
696. ዮም ፍሥሐ ኮነ
697. እንተ በምድር
698. አማን በአማን
699. ሰላም ለኪ ማርያም
700. ሰላም ለኪ
701. ኮነ ዮም
702. ዮም ፍሥሐ ኮነ /ጽፋት/

## የመላእክት መዝሙራት

703. እንደ አናንያ
704. ሚካኤል ገብርኤል
705. ገብርኤል አብሠራ
706. ውእቱ ሩፋኤል
707. አማልደን ስንልህ
708. ኦ ገብርኤል
709. ሩኅሩኅ መልአክ
710. የራማው ልዑል

711. ገብርኤል
712. የብርሃናት አለቃ
713. ቅዱስ ገብርኤል እርዳን
714. ገብርኤል መጽአ
715. ገብርኤል ነው
716. ቀዋምያን
717. ይቀልል
718. ገብርኤል ምልአኒ
719. ራጉኤል
720. ጸሊ ኀበ አምላክ
721. ንቁም በበህላዌነ
722. ናና ገብርኤል
723. ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ
724. አዕርግ ጸሎተነ
725. መልአከ ሰላምነ

## የቅዱሳን ጻድቃን መዝሙራት

726. ሐዋርያው
727. ገድሉ ተአምራቱ
728. ንዌጥን ዜማሁ
729. ተነግሮ የማያልቅ
730. አባ አቡነ
731. ለሳውል ወኬፋ
732. የአምላክን በረከት
733. የጸጋ ምስጋና
734. ማርቆስ ዘአንበሣ
735. ተክለሃይማኖት
736. ዘከመ ጻለየ
737. ማርቆስ ሐዋርያ
738. ባርከን አባታችን
739. ታማልደናለች
740. ፊልጶስ
741. አምላክ ባከበራት
742. እቀቡኒ
743. የቅዱሳን በአት
744. በድፍረትና
745. ይትፌሥሑ
746. ተክለሃይማኖት ፀሐይ
747. ተክለአብ
748. ዜና ውዳሴከ
749. ቅዱሳን አባቶች
750. ትዌድሶ
751. ጼና አልባሲሁ
752. ያሬድ ማህሌታይ
753. ሰማየ በአብ
754. በኢትዮጵያ ምድር
755. የጻድቃን ከተማ
756. ጻድቃንሰ ኢሞቱ
757. ቅዱሳን በሙሉ
758. ቅዱሳን መስክሩ
759. ምስጋና ጀመረ
760. ኦ መዓርኢረ ቃል
761. ጽድቅ ተክለ አልፋ
762. ግሩማን መላእክት

## የሰማዕታት መዝሙራት

763. አማን በአማን
764. ሰማዕታት
765. ዮሐንስ
766. ቅዱስ ጊዮርጊስ/1/
767. ሕፃን ወእሙ
768. በእምነታቸው ዳኑ
769. ጊዮርጊስ ብርሃኑን
770. ምስክረነቱን ገለጸ
771. መጥመቀ መለኮት
772. አርሴማ
773. መፅሐፈ ዜናሁ ለቂርቆስ
774. ፀሐይ ዘልዳ

775. ስብሐት ለአብ ወወልድ
776. ከመፀበል
777. መክብበ
778. ቅዱስ ጊዮርጊስ
779. ሕፃን ቂርቆስ
780. ኦ እስጢፋኖስ
781. ኦ ፍጡነ ረድኤት
782. አርአዮ ለቂርቆስ
783. ዐፀደ ወይን
784. ሰአለ ሥረይ
785. ይቤላ ሕጻን
786. አምላኮሙ
787. ገባሬ መንክራት
788. ጊዮርጊስ ግሩም
789. ጊዜ እረፍቱ

**ለቤተክርስቲያን እና ለአባቶች የሚዘመሩ መዝሙራት**

790. አመ ትትሐነጽ
791. ሃሌ ሉያ
792. ዝንቱ ኵሉ
793. ሰላም ለክሙ
794. ባርከኒ
795. ከመ ትባርከነ
796. አባ አባ
797. ኦ አባ ቅዱስ
798. ከጌታዬ ፍቅር
799. ቤተክርስቲያን
800. ለዛቲ ቤት
801. ይትባረክ
802. እንኳን ደኅና መጣችሁ
803. የድሆች መጠጊያ
804. ሰላም ለኪ
805. ተዋሕዶ
806. ተዋሕዶ ንጽሕት
809. ተዋሕዶ ሃይማኖት
810. ጽንዑ በተዋሕዶ
811. እግዚአብሔር የሀበነ
812. በሃይማኖት
813. አንድ እምነት
814. ውድ ሃይማኖታችን
815. የቅዱሳን አበው

**የምስጋና መዝሙራት**

816. ዋይ ዜማ
817. ስምአኒ
818. የሥላሴን መንበር
819. ሥላሴን አመስግኑት
820. ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን
821. ኵሎ ዘፈቀደ
822. ይትባረክ እግዚአብሔር
823. ይትባረክ
824. እንደ እግዚአብሔር ያለ
825. ልዑል እግዚአብሔር
826. እግዚአብሔር ብርሃኔና
827. እንደ አባቶቻች
828. እናምናለን በአብ
829. በበጎ ፈቃዱ
830. እልል በሉ
831. እግዚአብሔር አመስግኑት
832. ኢትግድፈነ
833. የወደደኝ ጌታ
834. ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር
835. ድንቅ አደርጎልኛል
836. ስሙ በክብር
837. በገና አንሥተን
838. በመስቀል ተሰቅሎ
839. ሳይገባኝ አምላክ

840. አምላካችን
841. ዘመኔ በከንቱ
842. እኔስ እዘምራለሁ
843. አማን በአማን
844. እግዚአብሔርን ጠራሁት
845. ኑ ወደ ቤቴል
846. ተነሡ እንዘምር
847. ለምትቀር ዓለም
848. ሰአሉ ለነ
849. ስብሐት ለአብ
850. እውነተኛ ሰላም
851. ጌታ ሆይ ለስምህ
852. ዓይኖቼ
853. አደርገህልኛልና
854. የነገሥታት ንጉሥ
855. አድሬኒ
856. ዝም አትበሉ
857. ስምህ በሁሉ ተመሰገነ
858. አንደበቴም ያውጣ
859. ወደ ቤተ እግዚአብሔር
860. እግዚአብሔር ሆይ
861. ብርሃን የለበሰው
862. አሁንስ ተስፋዬ ማነው
863. ሞት ነው ረሀብ
864. ሃሌ ሉያ
865. እንደአብርሃም እንሁን
866. ኃይልን በሚሠጠኝ
867. ሰዎች እንዘምር
868. እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ
869. አትተወኝ አትጣለኝ
870. ስለማይነገር ስጦታው
871. ቸርነትህ ብዙ
872. ንዓ አማኑኤል
873. ኦ አንትሙ
874. እንዘ ይብሉ
875. እምኩሉ
876. ስብሐት ለሥላሴ
877. ስብሐት ለአምላክነ
878. ለጌታዬ
879. ሰላመ ሀበነ
880. ኖላዊ
881. ያከብርዋ
882. ሀበነ
883. እንዘ የአምር
884. ያልጠፋነው
885. ዘሰማየ ገብረ
886. አንሰ ወቤትየ
887. ሊተስ ይኄይሰኒ
888. የአብ ጸጋ
889. አንቺ የወይን ሐረግ
890. የአምላክ እናት
891. እንድናለን
892. ሰአሊለነ ቅድስት
893. ማርያምሰ ተሀቱ
894. ዛሬም አለችን መማፀኛ
895. እመአምላክ ሙሽራ ነሽ
896. እንተ በምድር
897. ስምሽን ጠርቼ
898. ዮም ፍሥሐ ኮነ
899. ወእንዘ ትፈትል
900. የጠፉሽ አንቺን ተማጽነው
901. አንቲ ዘበአማን
902. በክብር ዙፋኑ
903. ሰላም ለኪ
904. ድንግል ማርያም የእኛ አማላጅ
905. ተወልዳለችና

906. ትውልድ ሁሉ
907. አንቀጸ ብርሃን
908. እመብርሃን መመኪያችን
909. ቃልን ለመውለድ
910. እመብርሃን (ትምህክቴ)
911. ጎሥዓ ልብየ
912. የሐና ልጅ ነሽ
913. ማርያም ድንግል ምክሆን
914. እሰይ ተከበረች
915. ማርያም ንጽሕት
916. የጽድቅ በር ነሽ
917. ለማርያም ድንግል
918. ደስ ይበልሽ
919. ማርያም
920. በምን በምን
921. ድንግል እመቤቴ
922. ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
923. የጌታዬ እናት ጸለየች
924. ቃል ኪዳን ግቢልኝ
925. እሴብሕ ጸጋኪ
926. ታማልደናለች
927. አብሠራ
928. ወይቤላ
929. በዝናመ ንጽሕኪ
930. ወደ ምሥራቅ እዩ
931. አዘክሪ ድንግል
932. እንደ ኤልሳበጥ
933. ትጎትናሽ ግሩም ነው
934. ለማርያም
935. በኃጢአት ያደፈ
936. እመቤቴ የአምላክ እናት
937. ከሊባኖስ
938. ያመሰገናት
939. ውዳሴ ማርያም
940. ኦ ድንግል
941. ማርያም
942. በመኑ በአምሣለ መኑ
943. ማርያም ተዐቢ
944. የኖኅ ቃል ኪዳኑ
945. ማኅደረ መለኮት
946. ማርያም ፊደል
947. ሰላም ለኪ
948. አስታርቂኝ
949. ደስ ይበለን
950. በሐዘኔ
951. ባክኛለሁና
952. የገነት ደጃፍ
953. ማርያም እንወድሻለን
954. ለውዳሴሽ ልትጋ
955. ያመሠገናት
956. በሀዘኔ በጭንቀቴ
957. ማርያም ማርያም በሉ
958. ማርያም ኩኒ
959. እመቤታችን ማርያም ሀገራችንን
960. ሰላም ለኪ ማርያም
961. እስኪላግንሽ
962. ናርዶስ ቀጺመታት
963. ልዑል ሠምራ
964. እንዘ ዘልፈ
965. መሶበ ወርቅ
966. ወእንዘ ትፈትል
967. ወዳጄ ሆይ
968. የሰማይ የምድር
969. ማርያም ተዐቢ
970. ነይ ነይ
971. በልዑል መጠጊያ

972\. ወትቀውም

973\. ሰአሊ ለነ ማርያም

974\. ንጽሕተ ንጹሐን

975\. አቀድም

976\. ሰላም ሰላም

977\. ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ

978\. ማን እንደእርሱ

979\. ድንቅ ነው

## <u>የሕጻናት መዝሙራት</u>

980\. መድኃኔዓለም ወሀቤ ሠላም

981\. እስጢፋኖስ ሰማዕት

982\. ኢየሱስ ክርስቶስ

983\. ኢያቄም ወሐና

984\. መሶበ ወርቅ

985\. ወእንዘ ትፈትል

986\. እመቤታችን ለአንቺ

987\. እመአምላክ ሙሽራ ነሽ

988\. ተልኮ መጥቶ

989\. ማርያም ደስ ይበልሽ

990\. እመቤቴ ጥላ ከለላዬ

991\. አባ አቡነ

992\. አንቺ ቤተልሔም / በመቀባበል /

993\. የጥበብ ሰዎች መጡ

994\. ሣር ቅጠሉ ሰርዶው

995\. እሰይ እሰይ ተወለደ

996\. ግነዩ ለእግዚአብሔር

997\. በጎል በጎል

998\. አምላክ ለእኛ ብሎ

999\. አንቺ ነሽ ተስፋው

1000\. ሰላም ለኪ

1001\. በዮናስ ስብከት

1002\. የነፍሳችን ቤዛ

1003\. ፍቅርና ሰላምን

1004\. ጾም ታድናለች

1005\. የአብርሃም አምላክ

1006\. እም እቶነ እሳት

1007\. የድሆች መጠጊያ

1008\. ያከብርዋ ለሰንበት

1009\. ኩሎ ዘፈቀደ

1010\. የሥላሴን መንበር

1011\. ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ

1012\. ልዑል እግዚአብሔር

1013\. እናመስግን አማኑኤልን

1014\. ወደ ቤተ እግዚአብሔር

1015\. ቅዱስ

1016\. ተናገሩ

1017\. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር

1018\. የተዘጋች መቅደስ

1019\. ቀስተ ደመናው

1020\. ሰላም ለኪ

1021\. የወርቅ መሰላል ነሽ

1022\. አንቺ የወይን ሐረግ

1023\. እናታችን ጽዮን

1024\. መሠረተ ሕይወት

1025\. እንተ በምድር

1026\. ማርያም ንጽሕት

1027\. የኪዳን ጽላት

1028\. ማርያም ተዐቢ

1029\. እምነ እምነ ንኢ

1030\. የጠሩሽ

1031\. ነይ ነይ

1032\. በምድራዊ ሕይወት

1033\. ኪዳነ ምሕረት እመቤት

1034\. ማርያም ድንግል

1035\. ማርያም ፊደል

1036\. ማኅደረ መለኮት

1037\. በመኑ

1038\. በምን በምን እንመስላት

1037\. የመላእክት እህት

1038\. እመቤታችን

1039\. ይዌድስዋ

1040\. የአርያም ንግሥት

1041\. ድንግል አማልጅን

1042\. ታማልደናለች

1043\. መልአክ ሰላምነ

1044. ኃያል ኃያል
1045. የጻድቃን ከተማ
1046. ጻድቃን ቅዱሳን
1047. ምስጋና ጀመረ
1048. ኦ መዓርዒረ ቃል
1049. ኦ ፍጡነ ረድኤት
1050. ኦ እስጢፋኖስ ሰማዕት
1051. ወደ ሕይወት መንገድ
1052. የሰው ልጅ በኃይልህ
1053. እግዚአብሔርን ጥራ
1054. ይህንን ጉባኤ
1055. ቃልህ ሲነገር ልስማ
1056. ሰአሊ ለነ ማርያም
1057. ወደ ምሥራቅ እዩ
1058. ለምኚ ድንግል
1059. መዓዛ አፈዋት
1060. እሴብሕ ጸጋኪ
1061. ኦ ሚካኤል
1062. ቅዱስ ሚካኤል
1063. ሚካኤል አማልደን
1064. አንተ ቅዱስ ሚካኤል
1065. ፈተና ቢገጥማት
1066. የኃያላን ኃይል
1067. ንዓ ንዓ አማኑኤል
1068. እግዚአብሔር ብርሃኔና
1069. ኦ. ድንግል ደስ ይበልሽ
1070. እናት አለኝ
1071. ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም
1072. ዓለምን ለማዳን
1073. እንዲህ አለው ጴጥሮስ
1074. መልእክተ ወንጌል
1075. ንሴብሖ
1076. ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን
1077. ውዳሴ ማርያም
1078. ኦ ድንግል
1079. ማርያም
1080. በመኑ
1081. ማርያም ተዐቢ
1082. ተወልዳለችና
1083. የዕለት የዓመት
1084. አበባዮሽ
1085. የአዋጅ ነጋሪ ቃል
1086. ምስክርነቱን ገለጸ
1087. መጥምቀ መለኮት
1088. ጊዮርጊስ ብርሃኑን
1089. ቤተክርስቲያን
1090. ሰአሊለነ ማርያም

## የደብረ ታቦር

1091. ደብረ መቅደሱ
1092. አሐደ ለከ
1093. አማን በአማን
1094. በስመ ዚአከ
1095. በደብር
1096. ቡሄ በሉ
1097. ወረዶሙ
1098. እንዲህ አለው
1099. የታቦር ተራራ

### 1. ዓመቱን አሣልፈህ

ዓመቱን አሳልፈህ ለዚህ ያደረስከን/2/
ስለ ቸርነትህ ጌታ ሆይ ተመስገን/4/

### 2. ባርክ ለነ

ባርክ ለነ እግዚኦ ዘንተ ዓመተ ምሕረትከ
በብዝኃ ኂሩትከ ለሕዝብከ ኢትዮጵያ
ከመንገኒ ለስምከ ቅዱስ/2/
በከመ ይኩን ንብረትነ በሰላም
ወበዳኅና ለዝንቱ ዓመት/2/

ትርጉም፡- ባርክልን አቤቱ ይህንን የምሕረት ዓመታችንን በቸርነትህ ብዛት ለሕዝቦችህ ኢትዮጵያ እንድንገዛ ለቅዱስ ስምህ /2/

እንዲሆንልን ኑሮአችን በሰላም

በደኅና በዚህ ዓመት /2/

3. ወአንተኒ ወረብ ዝማሜ ጽፋት

ሃሌ ሉያ ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ

አርኮ ለመርዓዊ ትሰመይ ወአዝማዱ በሥጋ

ትሰመይ ተፈኖከ ተዐርዉ አናቅጸ ጽድቅ

በመንፈስ የሐውር ወበኃይለ ኤልያስ

አልቦ ዘየአብል ዮለ ዮሐንስ

<u>ወረብ</u>

ወአንቲኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል/2/

አርኮ ለመርዓዊ ትሰመይ/2/ ነቢየልዑል/2/

**ሰላም**

ተሰአልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ

ዮሐንስ ክቡር ነቢየ ልዑል ብእሴ ሰላም ዘንብረቱ ገዳም/2/

3. ርዕሰ አውደ አመት

ርዕሰ ዐውደዓመት ዮሐንስ ወላዲ መጥቅዕ/2/

ወላዴ መጥቅዕ/2/ ወአበቅቴ/2/

ርዕሰ ዐውደዓመት ዮሐንስ ወላዴ መጥቅእ/2/

ወላዴ መጥቅዕ/2/ ዮሐንስ

4. ዐውደ ዓመት

ዐውደ ዓመት ለባርኮ ባርኮ ዐውደ ዓመት/2/

ንዒ ማርያም ለምህረት ወሣልህ/2/

5. የዕለት የዓመት

የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ

ከዚህ ካደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ

አቀርብልሃለሁ የክብር ሰላምታ ያክብሮት ሰላምታ

ኑ እናመስግን ከልባችን

የሰማዩን አባታችን

ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ላደረሰን ሁላችንን /2/

የሰው ልጆች እድሜ ጥንቱንም ሲጀመር

ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር

አንድ ቀን አይሞላም <u>እንደአንተ አቆጣጠር</u> /2/

አዝ . . .

ስለዚህ አምላክ ሆይ ክቡር ነው ቅዱስ ነው

ወደአንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው

ደካማ ነውና <u>ሰው እድሜ ከራበው</u> /2/

አዝ . . .

እጅግ አደንቃለሁ የአምላክን ጥበብ

ምድርን በአበባ ሰማይን በኮከብ

እንዳሸበረቃት <u>አስተውዬ ሳስብ</u> /2/

አዝ . . .

ከንቱ ካሳለፍኩት ጊዜዬን በዋዛ

ምን ያደርግልኛል ዘመኔ ቢበዛ

ደግሞም በጠቅላላ <u>ዓለምን ብገዛ</u> /2/

አዝ . . .

በከንቱ ጊዜያችን ፈጽሞ እንዳይጠፋ

በርትተን ከሠራን ያለአንዳች ነቀፋ

አምላክ የሚሰጠን <u>አለን ፍጹም ተስፋ</u> /2/

አዝ . . .

6. እናመስግን

እናመስግን አምላካችንን

እናመስግን ፈጣሪያችንን

ለዚህ ያደረሰንን

ጨለማውን ወስዶ ብርሃንን የሰጠን

ምስጋና ለእርሱ ይሁን

ለኃያሉ ንጉሣችን

ዘመናትን በዘመናት ያፈራርቃል

ስለ ሁሉ ሁሉ ያውቃል

ሳንለምነው የወደድነውን ይሰጠናል

ከፈቃዱ ይሰማናል

ውዳሴውን አዘጋጁ ያለ እረፍት

አዲስ ቅኔ ተቀኙለት

አዲስ መዝሙር ዘምሩለት

እንደ ወዳጁ እንደ ዳዊት

ዝናማትን ይሰጠናል በጊዜያቱ

ፍጥረቱንም ይመግባል በየዕለቱ
ኀልፈት የለው ለመንግሥቱ
አዝ . . .
ስሙ ታላቅ ኃያል ንጉሥ
የሚሉለት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
መላእክቱ በሰማያት
ምስጋናውን ያቀርባሉ ያለእረፍት
የተቤዠሽን ፍጥረትህን
ክብር ምስጋና ላንተ ይሁን
አዝ . . .

7. አበባዮሽ

እሰይ ደስ ደስ ይበላችሁ/2/
ቅዱስ ዮሐንስ መጣላችሁ
ደስ ደስ ይበላችሁ
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን/2/
ጌታ አለ ብለን ደስ ብሎን
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን/2/
ድንግል አለች ብለን ደስ ብሎን
አበባዮሽ ቅድስት/2/
ባለእንጀሮቼ ቅድስት
ቁሙ በተራ ›ቅድስት ›
በጎ ምግባርን ››ቅድስት
በእምነት እንሥራ ቅድስት ››
ዛሬ ነው ቀኑ ቅድስት ›
መመለሻችን ቅድስት ››
ይቅር እንዲለን ቅድስት ››
ቸሩ አምላካችን ቅድስት ››
አደይ የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ በራ/2/

ድንግል ማርያምን ቅድስት
እንለምናት ቅድስት
ምሕረት የሚያሠጥ ቅድስት
ቃልኪዳን አላት ቅድስት
ጭንቀት ይርቃል ቅድስት
ይቀርባል ሰላም ቅድስት ›

ስሟ ሲጠራ ቅድስት
የድንግል ማርያም ቅድስት
አደይ የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ በራ/2/
በሕገ ልቡና ጥንቱን
ፈጣሪን አውቀሽ ጥንቱን
ሕገ ነቢያት ከዓለም
ቀድመሽ ተቀበልሽ ከዓለም
በብሉይ ኪዳን ለጌታ
መሥዋዕት አቀረብሽ ለጌታ
ተስፋ ካደረጉት ከአይሁድ
ከእስራኤል ቀድመሽ ከአይሁድ
ሕገ ወንጌልን በፊት
ይዘሽ ተገኘሽ በፊት
ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ ትልቅ ጸጋ አለሽ/2/
ስለፈጸምሽ ሥስቱን ሕግጋት የፈጣሪሽን
ካለፈው ስህተት ሁላችን
እንድንመለስ ሁላችን
አዲሱ ዓመት ለሁሉ
መጣ ማቴዎስ ለሁሉ
ይህም ያልፍና በጊዜ
ይመጣል ማርቆስ በጊዜው
ሌላው ይተካል በጊዜው
ዘመነ ሉቃስ በጊዜው
ወልደ ነጎድጓድ በጊዜው
ሲደርስ ዮሐንስ በጊዜው
በየዓመቱ መጥምቁ
ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ

አደይ የብርሃን የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ አበራ-2/
ኢትዮጵያ ባህል ቋንቋሽ የሚያኮራሽ/2/
ዘመኑ አልፎ ቅድስት
ሲሄድ ማቴዎስ ቅድስት
አዲሱ ዘመን ቅድስት

ሲመጣ ማርቆስ ቅድስት
እድሜን ጨምሮ ቅድስት
ለሠጠን ጤና ቅድስት
ለመድኀኒዓለም ቅድሰት
ይድረስ ምስጋና ቅድስት
አደይ የብርሃን ጮራ በማርቆስ በራ
እቴ አበባ እቴ አበባዬ አዬ ቅድስት እናቴ
እቴ አበባ ስትለኝ ከርማ አዬ ቅድስት እናቴ
መከረችኝ ደግማ ደጋግማ አዬ ቅድስት
እናቴ
ቃሉን ሰማው አድምጥው ብላ እዬ ቅድስት
እናቴ
አዬ ቅድስት እናቴ አዬ ቅ. እናቴ/2/
ይሸታል የእጣኑ ጢስ ሲታጠን ከመቅደሱ
በመላእክት ዜማ ካህናት ሲቀድሱ ሲታጠን
ከመቅደሱ/2/
ከብረው ይቆዩን ከብርው
ከዓመት ዐውደ ዓመት ደርሰው
በእምነት በምግባር ጸንተው
ነጽተው ንስሓ ገብተው
ለሥጋ ወደሙ በቅተው
ከብረው ይቆዩ ከብረው
ከብረው ይቆዩ ከብረው
ከዓመት እከሰ ዓመት ደርሰው
ቅን ታዛዥ ልጅን ወልደው
ትጉት ሠው አክባሪ ሆነው
የፍቅርን ሸማ ለብሰው
ከብረው ይቆዩ ከብረው
አበባው ለምለም ቁጤማው ለምለም
ኢትዮጵያ እንዳንቺ የለም
አበባው ለምለም ቁጤማው ለምለም
ተዋሕዶ እንዳንቺ የለም
አበባው ለምለም ድንግል ማርያም
ያለአንቺ እመቤት የለም

8. **የአዋጅ ነጋሪ ቃል**

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሀ አየለ
የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካክሉ እያለ
ምስክርነቱን ዮሐንስ ካስረዳን
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
ዐውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም

ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንጥረግ ሁላችን
ማለፊያ እንዲሆነን ወደ አምላካችን
አዝ . . .
ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርኅራኄ በእኛ ላይ ይስፋፋ
ሥጋና ደምህን በክብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆን አምላክ ተማጽነናል
አዝ . . .
ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም አንጻን አደራህ
በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህ
አዝ . . .

10. **በመንፈስ የሐውር**

በመንፈስ የሐውር እመ ኃይል ውስተ ኃይል/2/
ካህን/2/ ወነቢይ ዮሐንስ መጥምቅ/2/

11. **እምሄሶ ለሄሮድስ**

እምኄሶ ለሔሮድስ ይብላዕ መሐላሁ (2) እም
ያምትር ርዕሶ ለዮሐንስ/2/
ዐቢይ ነቢይ ዐቢይ ነቢይ ሰባኬ ጥምቀት /2/
**ትርጉም፡-** ሔሮድስ የጥምቀቱ አስተማሪ
/መምህር/ የዮሐንስ ራስን ከሚያስቀርጥ ይልቅ
መሐላውን ቢበላ በተሻለው ነበር

12. **ለዮሐንስ አንገት**

ለዮሐንስ አንገት ለተቆረጠው
ሳይበድል ታስሮ ለተሰቃየው

ወዮልሽ ላንቺ ሄሮድያዳ
ደም አፍስሰሻል ሄሮድያዳ ወለተ ሄሮድያዳ /2/
ወዮልሽ አንቺ ዘፈንሽበት
በዮሐንስ ላይ ልትከብሪበት
አዝ . . .
ዓለምን ዞረች የእርሱስ አንገቱ
ዞራ አስተማረች ደርሶ ትንቢቱ
አዝ . . .
አንቺ አቀነቀንሽ ዘፈንን ዘፈንሽ
በወርቅ ፈንታ አንገት ተሰጠሽ
አዝ . . .
የወጌልን ቃል እናትሽ ዘንግታ
አጎትሽን ወዳ በፍቅር አግብታ
አመነዘረች ልትኖር በደስታ
አዝ . . .

### 13.መጽአት ወለታ

መጽአት ወለታ ለሄሮድያዳ ኀበ ንጉሥ ወትቤሎ
ሀበኒ በጻሕል /2/
ሀበኒ በጻሕል ርዕሰ ዮሐንስ ወንጌላዊ (3) ክቡር /2/
**ትርጉም፡-** የሄሮድያዳ ልጅ መጣችና እንዲህ አለችው ክቡር የሆነውን የወንጌላዊው የዮሐንስን ራስ በወጪት አድርገህ ስጠኝ አለችው

### 14.ዮሐንስ ክቡር

ዮሐንስ ክቡር ነቢየ ልዑል /2/
ብእሴ ሰላም /4/ ዘንብረቱ ንብረቱ ገዳም /2/
**ትርጉም፡-** የከበረ የልዑል ነቢይ ዮሐንስ ሆይ መኖሪያው በገዳም የሆነ የሰላም ሰው ነው

**የመስቀል መዝሙራት**
**/ለመስከረም 16 - 25 ቀን/**

### 15.መስቀሉን ተሸክመን

መስቀሉን ተሸክመን በእምነት እንራመድ
ለሰማያዊው ክብር እንንዝ (2) ወደእርሱ ዘንድ
እግዚአብሔር አብ ላከ አንድያ ልጁን /2/
እርሱ ወዷልና እንዲሁ ዓለሙን/2/
አዝ . . .
ከኃጢያት ያዳንከን ደምህን አፍስሰህ /2/
የሰላም ባለቤት አምላክ አንተ ነህ /2/
አዝ . . .
ይቅር ባይ መሐሪ ሰው ወዳጅ አምላክ /2/
በመንፈስህ አጽናን እንዳንታወክ /2/
አዝ . . .
አንተ ነህ ሕይወት መንገድና እውነት/2/
አብቃን የእኛ ጌታ ለዘላለም ሕይወት /2/
አዝ . . .

### 16.መስቀል ቤዛችን ነው

መስቀል ቤዛችን ነው ድል መንሻ ኃይላችን /2/
ከኃጢአት በሽታ የሚፈውሰን /2/
በኃጢአት ጨለማ ተውጠን ሳለን
የክርስቶስ መስቀል ብርሃን ሆነልን/2/
እንድንመስለው ጌታችንን /2/
እንሸከመው ዕፀ መስቀሉን /2/
እንድንሸከም ዕፀ መስቀሉን /2/
ሰውነታችንን ማንጻት አለብን

### 17.መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ

መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ /2/
ይኩነነ ቤዛ /4/ መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ/2/
**ትርጉም፡-** መስቀልህ ቤዛ (መድኃኒት) ይሁነን

### 18.መስቀል ተመርኩዘን

መስቀል ተመርኩዘን ወንጌል ተጫምተን
ሃይማኖትን ሰብከን በክርስቶስ አምነን
ማን ያሸንፈናል እኛ ክርስቲያን
ክርስቶስ አለልን
ንግሥቲቷ ዕሌኒ በጣም የታደለች
በዕጣን ጢስ ተመርታ መስቀሉን አገኘች
መስቀሉን ስትፈልግ ኪራኮስን ይዛ
መስቀሉን አገኘች የዓለሙን ቤዛ
አዝ . . .
ሙታንም ተነሥተው ያመሰገኑት
ዕፀ መስቀሉ ነው የእኛ መድኃኒት
መስቀል ምርኩዛችን ጎዳና ወንጌል
ወደገነት እንጂ አንሔድም ሲዖል
አዝ . . .

ንኡ ንወድሶ ለእፀ መስቀል
የተሸከመውን የአምላክን ቃል
ንኡ ንወድሳ ለማርያም ድንግል
አክሊለ ምዕመናን ምክኃ ደናግል
አዝ . . .

**19.ኀበ ቀራንዮ**

ኀበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት
<u>ቀራንዮ</u> (2) ኀበ ቀራንዮ
የመስቀሉ ቃል ለእኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው /2/
ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ግን ሕይወት ነው /2/
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ
እንመነው አንካደው ፈጣሪያችን ቸር ነው /2/
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የአማኑኤል እናት ናት /2/
ኀበ ጥበባት ኀበ ልሳናት /4/
<u>ዮሐንስ</u> /2/ ወንጌለ ስብከት /2/

**20.መስቀል አበባ**

መስቀል አበባ ነህ ውብ አበባ
አደይ አበባ ነሽ ውብ አበባ

መስቀል አበባ ተቀብሮ ሲኖር አደይ አበባ ሥነ ስቅለቱ
መስቀል አበባ ዕሌኒ አገኘች  አደይ አበባ ደገኛይቱ
አዝ . . .
መስቀል አበባ ጥራጊ ሞልተው አደይ አበባ አይሁድ በክፋት
መስቀል አበባ ጢሱ ሰገደ አደይ አበባ መስቀል ካለበት
አዝ . . .
መስቀል አበባ ወንዙ ጅረቱ አደይ አበባ ሸለቆ ዱሩ
መስቀል አበባ አሸብርቀው ደምቀው አደይ አበባ ላንተ መሰከሩ
አዝ . . .

**21.ዕፀ መስቀል**

ዕፀ መስቀል የክብር መውረሻ
ሰይጣንን ድል መንሻ

የክብር ባለቤት ዕፀ መስቀል የተሠዋበት ዕፀ መስቀል
ዕፀ መስቀሉ ነው ዕፀ መስቀል የዓለም መድኃኒት ዕፀ መስቀል
አዝ . . .
እንደ ዕሌኒ ንግሥት ዕፀ መስቀል ፍጹም አክብራችሁ ዕፀ መስቀል
ሁላችሁ ገስግሱ ዕፀ መስቀል መስቀሉን ይዛችሁ ዕፀ መስቀል
አዝ . . .
ያለ ኃይለ መስቀል ዕፀ መስቀል የሰላም ዓርማችን ዕፀ መስቀል
ሊሸነፍ አይችልም ዕፀ መስቀል ሰይጣን ጠላታችን ዕፀ መስቀል
አዝ . . .
እሳተ መለኮት ዕፀ መስቀል ያላቃጠለው ዕፀ መስቀል
ሰይጣንን የሚያነድ ዕፀ መስቀል ዕፀ መስቀሉ ነው ዕፀ መስቀል
አዝ . . .
እንደተባረከው ዕፀ መስቀል ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ ዕፀ መስቀል
በመስቀል ብርሃን ዕፀ መስቀል ወደ እውነት እንገስግስ ዕፀ መስቀል
አዝ . . .
የተዋሕዶ ልጆች ዕፀ መስቀል ገሥግሡ በተስፋ ዕፀ መስቀል
ዕፀ መስቀል ያዙ ዕፀ መስቀል  ጠላት እንዲጠፋ ዕፀ መስቀል
አዝ . . .

**22.አየኸው ደመራ**

አየኸው ደመራ መስቀል ሲያበራ
አየሺው ደመራ መስቀል ሲያበራ

መስቀል አለ ወይ? ቆሟል ወይ?
አለ እንጂ ለምጽ ያነጻል እንጂ
ያው ቆሟል ድውይ ይፈውሳል

አምነዋለሁ የት አገኘዋለሁ?
አለልሽ እሰሪው በአንገትሽ
ከልብሽ ተሳለሚው አምነሽ

እኮራለሁ በዕፀ መስቀል
ይፈውሳል ሙታንን ያስነሣል
ድል ያደርጋል ሰይጣንን ይመታል

**23.መስቀል ኃይላችን**

መስቀል መስቀል ኃይላችን ጠላትን ማጥፊያችን
በመስቀል እንመንለን እንድንበታለን
የክርስቲያን ጋሻ መስቀል ኃይላችን የክርስቲያን ጦር መስቀል ኃላችን
እፀ መስቀሉ ነው መስቀል ኃይላችን የማያስደፍር መስቀል ኃይላችን
አዝ . . .
መድኃኒት የሚሆን መስቀል ኃይላችን ደሙ ፈሶበታል መስቀል ኃይላችን
መስቀሉን ጥግ አድርጉ መስቀል ኃይላችን እርሱ ይፈውሳል መስቀል ኃይላችን
አዝ . . .
ክርስቶስ በደሙ መስቀል ኃይላችን ስለቀደሰው መስቀል ኃይላችን
መስቀል ላመነበት መስቀል ኃይላችን ድል ማድረጊያ ነው መስቀል ኃይላችን
አዝ . . .
የክርስቶስ ሥጋ መስቀል ኃይላችን የተፈተተበት መስቀል ኃይላችን
መስቀል ኃይላችን ነው መስቀል ኃይላችን የምንድንበት መስቀል ኃይላችን
አዝ . . .
ሕይወትን ለማግኘት መስቀል ኃይላችን ከሞት ለመዳን መስቀል ኃይላችን
መመኪያ ኃይላችን መስቀል ኃይላችን መስቀል አለልን መስቀል ኃይላችን
አዝ . . .

**24. ወሪዶ እመስቀሉ**

ወሪዶ እመስቀሉ /2/
እመስቀሉ አብርሃ ለኩሉ /2/
**ትርጉም:-** ከመስቀሉ ወርዶ ለሁሉ አበራ

**25.ከመ ትባርከነ**

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ (2) /2/
ተዋነይ በጽድቅ (4) እስጢፋኖስ ሐመልማለ ወርቅ /2/
**ትርጉም:-**

**26.በመስቀልከ**

በመስቀልከ ርድአነ /2/
ወበኃይልከ ተማኅጸነ /2/
**ትርጉም:-** በመስቀልህ እርዳን በኃይልህ ተማጽነናልና

**27. ይትቀደስ ስምከ**

ይትቀደስ ስምከ በኃይለ መስቀልከ በዕፀ መስቀልከ ክቡር ዘአዕበይኮ ለስምከ /2/
ስብሐት ለከ ለባህቲትከ ልዑል /4/
**ትርጉም:-** ክቡር የሆነ ዕፀ መስቀልህ በመስቀልህ ኃይል ስምህ ይመስገን ዘንድ ልዑል አምላክ ሆይ ለአንተ ለብቻህ ምስጋና የሚገባው ስምህን ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ

**28.ዕሌኒ ንግሥት**

ዕሌኒ ንግሥት ሐሰሰት መስቀሉ /2/
እንባቆም ነቢይ ዘአንከረ ግብሮ /2/
**ትርጉም:-** ነቢዩ እንባቆም ተአምራቱን ያደነቀው መስቀል ንግሥት ዕሌኒ ፈለገችው

**29. መስቀል ብርሃነ**

መስቀል ብርሃነ ለኩሉ ዓለም /2/
መሠረተ /3/ ቤተክርስቲያን /2/
**ትርጉም:-** ለዓለም ብርሃን የሚሆን መስቀል የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው

**30. ዮምሰ**

ዮምሰ ለእሊያየ /2/
አበርህ በመስቀልየ /4/
**ትርጉም:-** ዛሬ ለወገኖቼ በመስቀሌ አበራለሁ

**31. መስቀል ኃይልነ**

መሰቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ /2/
መድኃኒትነ ለዕለ አመነ /2/
**ትርጉም:-** መስቀል ኃይላችን ነው መስቀል ብርታታችን ነው መስቀል ቤዛችን ነው ለእኛ ለምናምነው መድኃኒታችን ነው

**32. ጸጋ ነሣእነ**

ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ በኃይለ መስቀሉ /2/
ኪያከ እግዚኦ ነአኩት ወንሴብሐከ እግዚአብሔር /2/
ጸጋን ተቀበልን ሕይወትንም አገኘን በመስቀሉ ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል /2/
አቤቱ አንተን (2) እናመሰግንሃለን እግዚአብሔር /2/

**33. ጥልን በመስቀሉ**

ጥልን በመስቀሉ ገደለ /2/
በመስቀሉ ለሰው ልጅ ሰላምን አደለ /2/

**34. መስቀል ሕይወት**

መስቀል ሕይወት
መግቢያ ለገነት
ዲያብሎስ በመስቀል
ተመቶ ወድቋል
ዲያብሎስ ድል ተመታ
በመስቀል ተረታ
ዲያብሎስ ኃይልም የለው
መስቀል አስጨነቀው

**35ለእፀ መስቀሉ**

ለዕፀ መስቀሉ እናቅርብ ምስጋና /2/
ክርስቶስ በደሙ ቀድሶታልና /2/
ጎልጎታ ሲኖር አፈር ተንተርሶ /2/
ይኸው ተገኝልን በዕሌኒ ልቅሶ /2/
አጋንንት አይቀርቡም ከሩቅ ይሸሻሉ /2/
እኛ ስንባረክ በዕፀ መስቀሉ /2/
አዝ . . .
ክርስቶስ በደሙ የቀደሰው መስቀል /2/
ድል መንሻ ሆነልን የሰይጣንን ኃይል /2/
በመስቀል ተሰቅሎ ደሙ ባይሆን ቤዛ /2/
ወድቆ ይቀር ነበር አዳም እንደዋዛ /2/
አዝ . . .
ብርሃን ነው ለዓለም የጌታ መስቀል /2/
የድሆች መጽናኛ የደካሞች ኃይል /2/
አይሁድ ይክዱታል የጌታን መስቀል /2/
ለምናምን ድኅነት የሚሆነን ኃይል /2/
አዝ . . .
አምነው ለተጠጉ ለተከተሉት /2/
መስቀል ፈውስ ነው ይሆናል ድኅነት /2/
የዲያብሎስን ኃይል የምንመክትበት /2/
መስቀል ነው ቤዛችን ዓለም የዳነበት /2/
አዝ . . .

**36. ዘእጣን አንጸረ**

ዘእጣን አንጸረ /4/
በጎልጎታ ተረክበ ዕፀ መስቀል /4/
**ትርጉም፡-** እጣኑ ያመለከተው መስቀል በጎልጎታ ተገኘ

**37.በመስቀሉ ወበቃሉ**

በመስቀሉ ወበቃሉ /2/
አዕበዮሙ ለአበዊነ /4/
**ትርጉም፡-** በመስቀሉና በቃሉ አባቶቻችንን ከፍ ከፍ አደረጋቸው

**38.በወንጌሉ ያመናችሁ**

በወንጌሉ ያመናችሁ /2/
እንካን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ /2/

**39. ይቤሎሙ ኢየሱስ**

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ እመኑ ብየ
ወእመኑ በአቡየ አበርህ /2/ በመስቀልየ
**ትርጉም፡-** ኢየሱስ አይሁድን ዛሬስ በመስቀሌ ለወገኖቼ አበራለሁና በእኔ እመኑ በአባቴም እመኑ አላቸው

**40. ኃይልነ ወጸወንነ**

ኃይልነ ወጸወንነ <u>ወሞገስነ</u> (2) /2/
ዝንቱ ውእቱ መስቀል /2/
**ትርጉም፡-** ኃይላችን መጠጊያችን መኪያችን ይህ መስቀል ነው

**41. በኃይለ መስቀሉ**

በኃይለ መስቀሉ /4/
ድል ሆነው ወደቁ አጋንንት በሙሉ
ዘምሩ ሁላችሁ ለኃይለ መስቀሉ
ድል መንሻ ነውና ላመነበት ሁሉ
አዝ . . .
ሁላችሁ በአንድነት ዘምሩ በእልልታ
ለዕፀ መስቀሉ ለሕይወት መከታ
አዝ . . .
እልል እልል በሉ በያላችሁበት
በኃይለ መስቀሉ ጠላት ለጠፋበት
አዝ . . .
እኛ እንዳንጠቃ በርጉም ጠላታችን
መስቀሉን እንያዝ ክርስቲያን ሁላችን
አዝ . . .
እንሰግድለታለን የጸጋ ስግደት
በእርሱ ላይ ስላለ ኃይለ መለኮት

አዝ . . .

**42. መስከረም ጠባ**

መስከረም ጠባ ኢዮሀ አበባ/2/
መስከረም ጠባ ኢዮሀ አበባዬ
ኢዮሀ መስከረም ጠባ ለእኛ ኢዮሀ አበባ
መስቀል አበራ ኢዮሀ አበባ
ለእኛ ሊሆነን እድገትና ልማት
ኢዮሀ ኢዮሀ አበባዬ ኢዮሀ
መስከረም ጠባ ለኛ ኢዮሀ አበባ
በተዋሕዶ የከበረች እናታችንን
የጥበብ ልጆቿ እናከብራታለን
ሃይማኖት ከምግባር ወንጌል መግባ
ስላሳደገቸን የድኅነት መሠረት
ቤተክርስቲያን እናታችን
ጥንትም መሪና አስተማሪ በመሆኗ
በዓለም ላይ ታውቋል ዜናዋ
እየተወሳ በዓለም ዜና ያኮራናል
መስቀላችን ኢዮሀ አበባ
መስከረም ጠባ ኢዮሀ አበባዬ /3/

**43. መስቀሉሰ ለክርስቶስ**

መስቀሉሰ ለክርስቶስ ብርሃንነ ለእለ ነአምን ትብል ቤተክርስቲያን/2/
ዛህኑ ለባሕር ወመርሶ ለአእማር ዝንቱ ውዕቱ መስቀል /2/
**ትርጉም:-** ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መስቀል ለእኛ ለምናምን የባሕር ጸጥታ የመርከቦች ወደብ ነው ትላለች

**44.ኅበሩ ቃል**

ኅበሩ ቃለ ነቢያተ/2/
ወይቤሎ መስቀል ብርሃነ /2/ ለኩሉ ዓለም /2/
**ትርጉም:-** ነቢያት በአንድ ቃል ተናግረው መስቀል ለዓለም ሁሉ ብርሃን ነው አሉ

**45. ዮም በዓለ መስቀሉ**

ዮም በዓለ መስቀሉ በሰማያት በላዕሉ /2/
ወዘነግሠ በምድር (2) ለአሕዛብ /2/
**ትርጉም:-** ዛሬ ከምድር ከፍ ባለ በሰማያት የመስቀል በዓል ነው በምድርም ለአሕዛብ የነገሠበት ነው

**46.ልዑል እግዚአብሔር**

ልዑል እግዚአብሔር (2) ምስጋና ይገባሃል /2/
ለመስቀል በዓል (2) በሰላም በጤና አደረስከን /2/

**47. እንተ ተሐንፀት**

እንተ ተሐንፀት በስሙ ወተቀደሰት በደሙ ቤተክርስቲያን /2/
ወተአትበት (2) በዕፀ መስቀሉ እስመ ኃይለ እግዚአብሔር ላዕሌሃ /2/
**ትርጉም:-**

**48.ርዕዩ እበዩ**

ርእዩ ዕበዩ ለቅዱስ ዕፀ መስቀል /2/
እውራን ይሬእዩ ወጽሙማን ይሰምዑ እለ ለምጽ ይነጽሑ እለመጹ ሀቤሁ /2/
ኑ እዩ የመስቀሉን ተአምራት/2/
እውሮችም ያያሉ ደንቆሮዎች ይሰማሉ ለምጻሞችም ይነጻሉ ወደእርሱም ይመጣሉ /2/

**49.መስቀል አብርሃ**

መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ኢትዮጵያ /2/
እምኩሉሰ ጸሐየ አርአየ እግዚአብሔር /2/
**ትርጉም:-**

**50. ዮም መስቀል አስተርአየ**

ዮም መስቀል አስተርአየ እለማሰኑ ፍጥረተ አሠነየ /2/
ዮም መስቀል ተኬነወ ወዘተጼወወ ሕዝብ በደሙ ቤዘወ /2/
**ትርጉም:-**

**51. መስቀል ብርሃነ**

መስቀል ብርሃነ ለኩሉ ዓለም መሠረተ ቤተክርስቲያን /2/
ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም መስቀል መድኅን ለዕለ ነአምን /2/
መስቀል ብርሃን ነው ለመላው ዓለም መሠረት ነው የቤተክርስቲያን /2/
ሰላምን ሰጪ ነው መድኃኔዓለም መስቀል አዳኝ ነው ለምናምን ሰዎች /2/

**52.ርዕዩ እበዩ**

ርእዩ ዕበዩ ለዕፀ መስቀል /2/

ዘመጠነዝ /2/ ትርሲተ ክብር ትኅትና ወፍቅር

**ትርጉም:-**

**53.መርሕ በፍኖት**

ሃሌ ሉያ መርሕ በፍኖት ሞገሶሙ ለጻድቃን ሞገስ /2/

ዝንቱ መስቀል ለአዳም ዘአግብኦ ውስተ ገነት /2/

ሃሌ ሉያ መሪ ነው በመንገድ ሞገሳቸው ለጻድቃን ሞገስ /2/

ይኸ መስቀል ነው አዳምን የመለሰው ወደ ገነት /2/

**54.ሶበሰ አዕመረ**

እስመ ለዓለም ምሕረቱ ሶበሰ አዕመረ ሰይጣነ በመስቀሉ

ለወልድ ከመይሰደድ እም ኢያመክሮሙ ለአይሁድ

ዕፀ መስቀል ከመይትክሉ ናዝራዊ ከመይስቅሉ ማሕየዊ

ከመይስቀሉ በዘመከረ ተአኩረ ወበዘአትከለ ተሰደ ወዕምዝ

ኀለየ ከመይሰውር ፀሐየ ግበ እሙቀ ለጸፊነ መስቀል አፍረየ

መስቀል ብርሃን ከመይሰውርዎ ኀቤየ

ዝንቱ መስቀል ኅብስተ ሕይወት አፍረየ አውኃዘ

ለነ ደመ ወማየ ጽዋዓ መድኃኒት ጽሩይ

ዘኢይነጽፍ ቀላይ ከመ ጌራወርቅ

ጽሩይ ሥርግው በባሕርዪ መስቀል ነቢሮ ላዕለ ርዕስየ

ታስተርኢ ጊዜ ትወጽዕ ነፍስየ

**55.የመስቀል አመላለስ /ወረብ/**

ዝንቱ መስቀል ሕብስተ ሕይወት አፍረየ አውኃዘ

ለነ ደመ ወማየ አውኃዘ ለነ /2/

ከመ ጌራወረቅ ጽሩይ ሥርግው በባሕርይ መስቀል ነቢሮ ያስተርኢ ላዕለ ርዕስያ /2/

**ትርጉም :-**

**56.ኃይለ መስቀሉ**

ኃይለ መስቀሉ አብርሃ (2) በኢትዮጵያ /2/

እስመ መስቀል ሞአ ሞተ ተሞአ /2/

**ትርጉም :-** የመስቀል ኃይል በኢትዮጵያ አበራ መስቀል ድል ነስቷልና ሞት ድል ተነሣ

መስቀል አሸንፏልና ሞት ተሸነፈ

**57.ብርሃን ወጣ**

ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንጸባርቅ

የአምላክና የሰው ልጆች እውነተኛ እርቅ

ደስ ይበለን በመስቀሉ ብርሃን

እልል እንበል በአንድነት ሆነን

ድኅነት ሆነ ለመላው ዓለም

ከፊት ለፊት በመሳሉ የመስቀሉ ነገር

የሚወደው ሐዋርያ የወንጌል መምህር

ዮሐንስም ስቅለቱን በማየቱ

ሲያዝን ኖረ በምድራዊ ሕይወቱ

ቢያሰቅቀው ሞቱ ግርፋቱ

አዝ . . .

ሞኝነት ነው ለሚጠፉት መሰናከያቸው

በዓለም ጥበብ ለሚኖሩት እውነት ተስኗቸው

ለጠቢብ ሰው በመንፈስ ለሚኖረው

የመዳን ቀን እውነተኛ አርማ ነው

ከገሃነም እሳት የሚያድን ነው

አዝ . . .

እስከ መስቀል ላልተለየው ቅዱስ ሐዋርያ

ለዮሐንስ የወንጌል ሰው የፍቅር ባለሞያ

ምስጋናችን ከምድር ይድረሰው

እንድናለን በሰጠን ምሳሌው

ሰዎች ሁሉ እንከተለው

አዝ . . .

**የመስቀል መዝሙር ( በኦሮምኛ ቋንቋ)**

**58.ፊኖ ኢፋ** (መስቀል ብርሃን አጭሩ)

ፊኖ ኢፋ አዱኛ ሁንዳፊ/2/

ኤዮን በሁራዳ /3/ ወልዳ ኬኛፊ /2/

**59.ሎላ ፊኖ ሣቲን** (ጥልን በመስቀሉ ገደለ )

ሎላ ፊኖ ሣቲን አጆሴ /2/

ፊኖ ሣቲን ነሞታፍ ነጉማ ሒሬ /2/

**60.ፊኖ ኩኒ** (ዝንቱ መስቀል )

ኩኒ ፈኖኒ ጋዲሳዳ ቆርቻዳ /2/

ኩኒ ፈኖኒ ጋዲሳዳ ቆርቻዳ /2/

**61.አርሳቱ አገርሲሴ** (ዘእጣን አንፀረ)

አርሳቱ አገርሲሴ (4)

ጎልጎታቲ አርገሜ ፈኖን ዋቀዮ /4/

**62.ኮታላላ** (ርእዩ ዕበዩ )

ኮታላላ ፈኖ ዋቀዮ ራጂሳ /2/

ጀዋማኒ ኒአርገኒ ጉሪ ኢነኔኜ ኒደጋኒ ዱኩባ ጎጋ ኒቁልቁላ /2/

**63.ፈኖራ** (በመስቀሉ ወበቃሉ)

ፈኖራ ቡኤቶ /2/

ፈኖሳቲን ሁንዳፋ ኢብሴ /4/

**64.ፈኖ ኢፋ** (መስቀል ብርሃን ረጅሙ )

ፈኖ ኢፋ አዱኛ ሁንዳፊ ቡሁራዳ ወልዳ ኬኛፊ /2/

ነገኢ ኬኛዳ ፈይሳ አዱኛ ፈኖ ፈይሳዳ ኒማቲ ሁንዱፍቲ /2/

**65.ፈኖ ኬተኒ** (በመስቀልከ ርድአነ)

ፈኖ ኬተኒ ኑገርጋሪ /2/

ሁምና ኬተኒ ሲከደና /2/

**66ፈኖ ኢፋ መስቀል አብርሃ )**

ፈኖ ኢፋ ኡርጂዳኒ ዋቃ በሬቼ ኢትዮጵያ /2/

ሁንዱ መራ ዋቀዮ አአዱ አገርሲሳዳ /2/

**67.ኤዮ ፈኖዳኒ** (ኧሽ በመስቀልከ )

ኤዮ ፈኖዳኒ ኤዮ ዱንና ኤብሴቴ /2/

ኤዮ ፈኖዳኒ ኤዮ ዱአዋና ናሰቴ

ኤዮን ነማረከቴ ፈኖዳኒ ኒቀርቃርቴ /2/

**68.እም ገቦ**

እምገቦከ ውኂዘ ነቅዓ ማይ ዘቀደሶ ለፈያታይ/2/

ለነዳይ ምስካይ መስቀልከ እግዚኦ ለነዳይ ምስካይ

**የወርሃ ጽጌ መዝሙራት**

**69. ርሃበ ወጽምአ**

ርሃበ ወጽምዓ አዘክሪ ድንግል ርሃበ ወጽምዓ /2/

ምንዳቤ ኀዘን አዘክሪ ድንግል /2/

ትርጉም፡- ርሃቡንና ጥሙን ችግሩንና ሐዘኑን እመቤታችን አሳስቢልን

**70. እስከ ማእዜኑ**

እስከ ማዕዜኑ እግዝእትየ ውስተ ምድረ ነኪር ትሄልዊ /2/

ገሊላ እትዊ /4/ ሀገረኪ ገሊላ እትዊ /2/

ትርጉም፡- እስከ መቼ ድረስ እመቤቱ ሆይ በባዕድ ሀገር ትኖሪያለሽ ወደ ሀገርሽ /4/ ወደ ገሊላ ግቢ፡፡

**71. ተፈጸመ**

ተፈጸመ ማኅሌተ ጽጌ ስሙር /2/

ንግሥተ ሰማይ /3/ ወምድር /4/

ትርጉም፡- የሰማይና ምድር ንግሥት የሆንሽ የእመቤታችን የጽጌ መዝሙር ተፈጸመ፡፡

**72. ከማሁ ኀዘን**

ከማኀ ሐዘን ወተስዶ ሶበ በኩለኄ ረከቦ /2/

ርእዮ ለይብኪ አይነ ልብ ዘቦ /5/

ትርጉም፡- እንደእርሷ ሐዘን መከራ ቢያገኘው ኖሮ ልብ ያለው ሰው ከኀዘኑ ባልተቆጠበ ነበር፡፡

**73. ዮም ጸለሉ**

ዮም ጸለሉ መላእክት ላዕለ ማርያም ወላዕለ ወልዳ ክርስቶስ በደብረ ቁስቋም /2/

እንዘይብሉ ስብሐት /2/ በአርያም ስብሐት በአርያም /2/

ትርጉም፡- እነሆ መላእክት ማርያም ከልጇ ጋር በቁስቋም ተራራ ላይ ከለሏት በእግዚአብሔር በሰማይ ምስጋና እውነትም በምድር ይሁን

**74. መአዛሆሙ ለቅዱሳን**

መአዛሆሙ ለቅዱሳን ከመጽጌ ደነላት ዘውስተ ቆላት /2/

ጸገዩ ቀንሞስ ሞስለ ናርዶስ /4/

**75. ንዒ ርግብየ**

ንዒ ርግብየ ወንዒ ሠናይትየ /2/

ምስለ ሚካኤል /4/ ወገብርኤል /4/

ትርጉም፡- መልካሟ ርግብ እመቤቴ ሆይ
ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር ነይ።

**76. አክሊለ ጽጌ**

አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀጸላ
መንግስቱ ለጊዮርጊስ /2/
ክበበ ጌራ ወርቅ /2/ አክሊለ ፅጌ /4/
ትርጉም፡- ማርያም በጊዮርጊስ ንግሥ /ክብሩ/
ጊዜ የአበባ ዘውዱ ናት የክብ
የንግሥና አክሊል ናት የአበባ
ዘውድ እሷ ክብነት ያለው
የወርቅ ስቁር ናት።

**77. እምነ እምነ ንኢ**

እምነ እምነ ንኢ /4/
በሰላም /2/ ንኢ ማርያም /2/
እናታችን ነይ ነይ /4/
በሰላም /2/ ነይ ማርያም /2/

**78. አሠርገዋ**

አሠርገዋ ለምድር አሠርገዋ ለጽጌ /2/
እስመ ውእቱ ክብሮሙ ለቅዱሳን
መድኃኔዓለም /2/
ትርጉም፡- ምድርን በአበባ አስጊጣት
መድኃኔዓለም የቅዱሳን ክብራቸው ነው።

**79. ማርያም ኀየኪ**

ማርያም ኀየኪ እም ገጸ ሄሮድስ /2/
ለአርእዩ /4/ ተአምረ ግፍኪ /2/
ማርያም ሸሸች ከሄሮድስ ፊት /2/
ለማሳየት /4/ የግፍ ተአምርሽን /2/

**80. እስመ ውእቱ**

እስመ ውእቱ ክብሮሙ ለቅዱሳን መድኃኔዓለም
/2/ አሠርገዋ ለምድር አሰርገዋ ለጽጌሃ /2 /
ትርጉም፡- ምድርን በአበባ አስጌጣት
መድኃኔዓለም ለቅዱሳን
ክብራቸው ነው።

**81. እንዘ ተሐቅፊዮ**

እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ ድንግል /2/
ምስለ ሚካኤል /4/ ፍሡሕ ወገብርኤል /3/
ትርጉም፡- ድንግል ሆይ ልጅሽን ታቅፈሽ
ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር

**82. ምንም ሳትበድል**

ምንም ሳትበድል ኃጢአት ሳይኖርባት
አንድዬ ልጇን ሄሮድስ ሊገድልባት
ሀገር እንደሌለው ከሀገር ሲያሳድዳት ምን በድላ ይሆን
ምን ኃጢአት ኖሮባት

የአዳም መዳኛ ድንግል ማርያም
አንድ ልጇን ይዛ ዞረች በዓለም /2/

ሄድሮስ ምቀኛ የዲያብሎስ ወዳጅ
ሊገድለው አስቦ የድንግልን ልጅ
መቼ ለእርሷ አዘነ ጨከነባት እንጂ
ስትሆን ለፍጥረት የዓለም አማላጅ
አዝ -------------

የሲና በረሃ እግሯን እየፈጀው
አንጀቷ ተርቦ ውኃ ጥም ሲፈጀው
መቼ ለእርሷ አዘነች የርሷን መንገላታት
ሐሰቧ ለእርሱ ነው እንዳይገድሉባት
አዝ -------------

አቤት መከራሽ አቤት ስደትሽ
እኔ ልካፈለው ወራዳው ልጅሽ
መሰደድ ያለብኝ እኔ ነበርኩኝ
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፍኩኝ
አዝ -------------

**83 ውድስት አንቲ**

ውድስት አንቲ በአፈ ነብያት /2/
ወስብሕት /5/ በሐዋርያት /2/
ትርጉም፡- በነቢያት አፍ የተመሰገንሽ
በሐዋርያትም የተመሰገንሽ ነሽ

**84. ንግሥተ ሰማያት**

ንግሥተ ሰማያት ወምድር ማርያም ድንግል /2/
ተፈጸመ/ 4/ ማኅሌተ ጽጌ /2/
ትርጉም፡- የሰማይ የምድር ንግሥት የሆንሽ
እመቤታችን ሆይ የአንቺ ማኅሌት
ጽጌ ተፈጸመ።

### 85. ክበበ /2/ ጌራ ወርቅ

ክበበ /2/ ጌራ ወርቅ
አክሊለ ጽጌ ማርያም /4/
ትርጉም፡- በወርቅ አክል የተሸለመች እመቤታችን
የጊዮርጊስ የሰማዕትነቱ አክሊል አበባ ናት፡፡

### 86. ከመጽጌ ሮማን

ከመጽጌ ሮማን ከመጽጌ /2/
አበባዬ /2/ ወላዲተ አምላክ ሲሣይ /2/
ትርጉም፡- እንደ ሮማን አበባ ያማረች የአምላክ
እናት ማርያም ሲሣይ ናት፡፡

### 87. ብክዩ ኅዙናን

ብክዩ ኅዙናን ሃልየክሙ ስደታ ለማርያም /2/
ማርያም ተአይን ባህቲታ ውስተ አድባረ ግብጽ
ከመ ኦፍ /2/
ትርጉም፡- አልቅሱ ምዕመናን አስባችሁ
የማርያምን ስደቷን /2/ ማርያም
ስትዞር
ብቻዋን በግብጽ በርሃ እንደወፍ /2/

### 88. አዘክሪ ድንግል

አዘክሪ ድንግል አዘክሪ
ለልጅሽ አሳስቢ አዘክሪ
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን /2/

ካንቺ መወለዱን አዘክሪ
በቤተልሔም »
በጨርቅ መጠቅለሉን »
መኝታው ግርግም »
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን »

በዚያ በብርድ ወራት አዘክሪ
የገበሩለትን »
የአድግና የላም »
እስትንፋሣቸውን »
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን »

በግብጽ በረሃ አዘክሪ
መሠደድሽን »
የአሸዋውን ግለት »
ርሃቡና ጥሙን »
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን »

በመቃብሩ ዘንድ አዘክሪ
ባነባሽው እንባ »
አሳስቢ ድንግል ሆይ »
ገነት እንድንገባ »
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን »

### 89. ድንግል መከራሽን

ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታሰው
በሄሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው
አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት
እንደ ችግረኛ ተነሳሽ ስደት

ኸረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሃውን አቋርጠሽ
ይገሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ
በሔሮድስ ዘመን መከራሽን አየሽ /2/

አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ
እንድትደርሽልኝ በመከራ ጊዜ
መከራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኝብኝ አደራሽን ማርያም /2/

የአማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
እድሜሽን ጨረስሽው ሆነሽ ሐዘንተኛ
መከራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኝብኝ አደራሽን ማርያም /2/

### 90. ሰቆቃወ ድንግል

ሰቆቃወ ድንግል /4/
ርእዮ ለይብኪ አዳነ ልብ ዘቦ /4/
ትርጉም፡- ልብ ዓይን ያለው ሰው የድንግልን
ልቅሶ አይቶ ቢያለቅስ አግባብ ነው፡፡

### 91. ወደ ምሥራቅ እዩ

ወደ ምሥራቅ እዩ ወደ ፀሐይ መውጫ
ድንግልን ክበቧት እንበል ሃሌ ሉያ
ለአምላክ እናት ለአዛኝት /2/
እልል እንበል እንዘምርላት /2/
ወገኖች ተነሡ እናታችን መጣች
ስሟን ስንጠራ መቼ ትቀራለች
የተከዘን ልታጽናና ነይ ሰንላት ትመጣለችና /2/

የጽጌው ማኅሌት በጸሎት ሲጀመር
ማርያም ትመጣለች በደመና አየር
ንዒ ስንል በሠዓታት ልትባርከን ትመጣለች በእውነት /2/

አዝ ----------------

ፍልሰታ ሲጀመር ቃል ኪዳን ገብታለች
የሌሊት ውዳሴን ንዒን ትሰማለች
ሕጻናትን በበረከት ልትጎበኝ
ትመጣለች በእውነት /2/

አዝ ----------------

በፍጹም ቸርነት እንዲምረን ጌታ
በአማላጅነትሽ ሁኚልን መከታ
እናታችን አለኝታችን እንድናለን
ድንግል አንቺን ይዘን /2/

አዝ ----------------

ሃሌ ሃሌ ሉያ /2/
እስመ ዝንቱ ዑራኤል እስመ ዝንቱ ለዓለም
ብርሃን /2/

## 92. ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንኢ ሠናይትየ
ማርያም /2/
ንኢ /6/ እመ አምላክ ንኢ ማርያም /2/
ትርጉም፡-

## 93. አፈንብ

አፈንብ ማቱሳላ ወልደ ሄኖክ እመአፈ ልምላሜ
ቡሩክ አፈ መላእክት /2/
ቀስመ ጽጌ ጽጌ /2/
ጽጌኪ እመ አምላክ /2/
ትርጉም፣ የአምላክ እናት እመቤታችን ሆይ
የንብ አፍ የሄኖክ ልጅ የሚሆን
ማቱሳላ ከተባረከ (ከተቀደሰ) ልምላሜ
መልአክ አፍ ልጅሽ አበባን ቀሰመ

## 94 ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አዘክሪ ርሃበ ወጽምዓ /2/
ርሃበ ወጽምዓ /2/ ወሐዘን ምንዳቤ ወሐዘን /2/
ትርጉም፡- ድንግል ሆይ አሳስቢ ርሃብ ጥሙን /2/
ርሃቡን ጥማቱን /2/ በበረሃ የደረሰብሽን /2/

## 95. ለምኚ ድንግል

ለምኚ ድንግል ለምኚ /2/
ለኃጥአን /3/ አይደለም ለጻድቃን /2/

ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ
» አዛኝ ሩኅሩኅ ነሽ
» የጌታዬ እናት
» ጸጋን የተሞላሽ
» የአምላክ ማደሪያ
» ለምነሽ አስምሪን
» አማናዊት ጽዮን
» ከእኔ አትለይኝ

ለምኚ ሐዘንሽ አዘኜ
» ለእኔ ይሁን ድንግል
ለምኚ የተንከራተትሽው
» በሀገረ እስራኤል
» ትእግስትሽን ሳየው
» ልቤ ይመሰጣል
» የሐዘን እንባ ጎርፍ
» ዓይኔን ይሞላዋል

ለምኚ በቀራንዮ አምባ
» በዚያ የፍቅር ቦታ
» በእግረ መስቀሉ ስር
» ከክርስቶስ ጌታ
» ለእኛ ተሰጥተሻል
» እናት እንድትሆኝን
» ልጆችሽ ነንና
» ምልጃሽ አይለየን

ለምኚ አንደበቴን ጌታ
» በምስጋና ምላው
» ደስ ይበልሽ ብዬ
» እኔም ላመስግናት
» አንደበቴን ጌታ
» በምስጋና ምላው
» ደስ ይበልሽ ብዬ
» እኔም ላመስግናት

## 96. መዓዛ አፈዋት

መዓዛ አፈዋት ማርያም /2/ ጽጌ መንግሥት
ቡርክት /2/
ጽጌ ጽጌ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሐ ወአጽብሐ
/2/

## 97. ክበበ ጌራ ወርቅ

ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ እምእንቁ ባሕርይ /2/
ዘየሀቱ /5/ እም እንቁ ባህርይ /2/
ትርጉም፡- ከእንቁ በሚያበራ አክሊል የተሸለመች
እመቤታችን የጊዮርጊስ አክሊል

## 98.ንዒ ርግብየ

ንዒ ርግብየ ወንኢ ሠናይትየ /2/
ትናዘዚኒ /2/ ሐዘነ ልብየ /2/
ትርጉም ፡- ከልቤ ሐዘን ታረጋጊኝ ዘንድ
መልካምዋ ርግብ ሆያ ነይ፡፡

## 99.. ምዕረ በዘባንኪ

ምዕረ በዘባንኪ ወምዕረ በገቦኪ /2/
በአዚለ ሕፃን /4/ ደከምኪ ማርያም ብዙኃ /2/
ትርጉም፡- አንድ ጊዜ በጀርባሽ አንድ ጊዜ በጎንሽ
/2/
ሕፃንን በማዘል /4/ ደከምሽ ማርያም በብዙ /2/

## 100..እንዘ ተአቀፊዮ (ወረብ)

እንዘ ተዓቀፊየ ለሕፃንኪ ጽጌ ጸዓዳ ወቀይሕ /2/
ንዒ ርግብየ ምስለ ገብርኤል ንዒ ሠናይትየ ምስለ
ሚካኤል /2/

ትርጉም፡-ብሩህ አበባ የምትሆኚ መልካሚትዋ
ርግብ ሆይ ልጅሽን ታቅፈሽ ከሚካኤልና
ከገብርኤል ጋር ነይልን ፡፡

## 101.ትመስል እምኪ

ትመስል እምኪ ማርያም ዕለተ ሣልስተ
ወርህብእተ ትመስል እምኪ /2/
ዘወለደት ጽጌ /3/ ወፀሐየ ዓለም
ትርጉም፡-

## 102.እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘወትር ነፍሴ /2/

ልቤ ተነሣሣ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍጹም ትኅትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመብርሃን
የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና
ክብር ይገባታል ዘወትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስራቆት
ያንን የእሳት ባሕር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

## 103.ሠናይትየ

ሠናይትየ /2/ ርግብ /2/
ንዒ ማርያም /4/ ሠናይትየ ንኢ ማርያም
ትርጉም፡- መልካም ርግብ ማርያም ነይ

## 104.ንዒ ማርያም

ንዒ ማርያም /3/ /2/
በሰላም /3/ ንዒ ማርያም /2/
ነይ ማርያም /3/ /2/
በሰላም ነይ ማርያም

## 105.እሴብሀ ፀጋኪ

እሴብሐ ጸጋኪ ኦ እግዝእትየ ማርያም
እጽ ልምልምት ወፍሬ ጥዕምት /3/
ሐረገወይን /3/ አንቲ ማርያም
አጸደ ወይን /3/ አንቲ ማርያም
ትመስሊ ፊደለ ወትወልዳ ወንጌለ ወታገምሪ መስቀለ
አዝ---------------
ትመስሊ ሰማየ ወትወልዳ ፀሐየ ወታገምሪ አዶናየ
አዝ

ትመስሊ መሶበ ወትወልዲ ኮከበ ወታጸግቢ ርሁበ

አዝ---------------

ትመስሊ መቅደሰ ወትልዳ ንጉሠ ወታገምሪ መንፈስቅዱስ

አዝ---------------

ትመስሊ ታቦተ ወትወልዳ ጽላተ ወታገምሪ መለኮተ

አዝ---------------

ትመስሊ ደመና ወትወልዳ ሕብሰተ መና መታገምሪ ጥኢና

አዝ---------------

ትመስሊ ገራህተ ወታፈርሂ ስዊተ ወታጸድቂ ነፍሳተ

አዝ---------------

ትመስሊ ስኒነ ወትወልዲ መድኅነ ወትፌውሲ ድውያነ

አዝ---------------

ትመስሊ ምሥራቀ ወትወልዲ መብረቀ ወታለብሲ ርሁቀ

አዝ---------------

ለአብ መርዓቱ ለወልዱ ወላዲቱ ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሐ ቤቱ

አዝ---------------

### 106. <u>መድኃኔዓለም አዳነን</u>

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ /2/
ሸሸ ደስ ይበለን /2/ እልል በሉ /2/
አዳነን በማይሻር ቃሉ /2/

### 107. አ<u>ማኑኤል ጌታ ሆይ</u>

አማኑኤል ጌታ ሆይ በምሕረትህ ተቀበለኝ /2/
ኃጢአት እኔን ልጅህን ዳግም እንዳይገዛኝ /2/
ኃይልህን አንተ አልብሰኝ /2/

### 108. <u>ኑ ደስ ይበለን</u>

ኑ ደስ ይበለን በአምላካችን /2/
አማኑኤል ሰምቷል ልመናችንን ሸሸ
ደስ ይበለን /2/

### 109. <u>ዘሰማየ ገብረ</u>

ዘሰማይ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድር ሣረረ /2/
አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ /4/
ትርጉም፡- ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና /2/
ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለአንተ
ማን አለና /2/

### 110. <u>ለጌታዬ ለእግዚአብሔር</u>

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን
እከፍለዋለሁ /2/
ምስጋና ነው እንጂ /2/ ሌላ ምን እላለሁ /4/

### 111. <u>አማን በአማን</u>

አማን በአማን /4/
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅር ምን ልክፈልህ /2/
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጸው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደሰው በደል ቢቆጥር ጌታ
ለእኔስ ኃጢአት የለውም ቦታ

አዝ ---------------

በየደቂቃው ኃጢአት ስሠራ
ስሠርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም

አዝ --------------

የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መርሮ ፍጹም አይጥምም
እንደበደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

አዝ---------------

### 112. <u>ሠላም ሀበነ</u>

ሠላም ሀበነ /4/
አምላክነ /3/ ሰላም ሀበነ /2/

ትርጉም፡- ሰላምን ስጠን /4/
አምላካችን /3/ ሰላም ስጠን /2/

### 113. <u>ዝንቱ ኩሉ</u>

ዝንቱ ኩሉ ኮነ /2/ በማኅደረ ስብሐት
(በደብረመድኃኒት) /2/

በፈቃደ /4/ እግዚአብሔር

ትርጉም፡- ማኅደረ ስብሐት በደብረመድኃኒት
በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ
ሁሉ ነገር ሆነ

**114. <u>እግዚአብሔር ይመስገን</u>**

እግዚአብሔር ይመስገን ይህቺን ቀን ቀድሶ
የሠጠን /2/
ከእያለንበት <u>ሰብስቦ</u> /2/ ለዚህ ያደረሰን /4/

**<u>115.እሳተ ጽሩህ</u>**

እሳት ጽሩህ ማየ ጠፈሩ /2/
ደመና መንኮራኩሩ ለመድኃኔዓለም /4/
ትርጉም፡-

**116. <u>ቸሩ መድኃኔዓለም</u>**

ቸሩ መድኃኔዓለም አንተ ቀረበን <u>ተለመነን</u> /2/
በምሕረትህና በቸርነትህ እንዳትለየን /4/

**<u>117.ኩሎ ዘፈቀደ</u>**

ኩሎ ከፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር /2/
በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ ወበኩሉ
ቀላያት ቀላያት /2/
ትርጉም፡- በሰማይና በምድር በባሕርና
በፈሳሾች እግዚአብሔር
የወደደውን አደረገ

**<u>118.እንዘ የአምር</u>**

እንዘ የአምር እምቅድመ ኅሊና ዘይሄሊ
ልበ <u>የአምር</u> /2/
አርአየ ኃይሉ በላዕሌነ ወጸገወይነ እኸ ሠናይቶ
እግዚአብሔር /2/
ትርጉም፡- ልብ የሚያስበውን ከማሰቡ በፊት
የሚውያቅ እግዚአብሔር ኃይሉን
አየን አየን በጎ ሥራን በላያችን
ላይ ገለጠ (አሣየ)

**<u>119.የኃያላን ኃይል</u>**

የኃያላን <u>ኃያል</u> /2/ ልዑል እግዚአብሔር /2/
ተአምራተ ብዙ <u>በሰማይ</u> /2/ በምድር /4/
ለአብና ለወልድ /2/ ለመንፈስ ቅዱስ /2/
መስገድ ይገባናል <u>በሥጋ</u> /2/ በነፍስ /4/
ለእግዝእትነ <u>ማርያም</u> /2/ ለአምላክ እናት /2/
መስገድ ይገባናል <u>የጸጋ</u> /2/ ስግደት /2/
ለጻድቁ <u>አባት</u> /2/ ለተክለሃይማኖት /2/
መስገድ ይገባናል <u>የጸጋ</u> /2/ ስግደት /2/
ለጻድቁ <u>አባት</u> /2/ ለአቡነ አረጋዊ /2/
መስገድ ይገባናል <u>የጸጋ</u> /2/ ስግደት /4/

**<u>120. በደሙ ቤዘዋ</u>**

በደሙ ቤዘዋ በዕፀ መስቀሉ አተባ /2/
ዘበእንቲሃ /4/ ተሰቅለ መድኃኔዓለም /2/
ትርጉም፡- በደሙ ዋጃት በመስቀሉ ባረካት
ስለእርሷ መድኃኔዓለም ተሰቀለ።

**<u>121. ኢትግድፈነ</u>**

ኢትግድፈነ /2/ ወኢትመንነነ /2/
አምላክ ሰላም ተራድአነ /4/
እግዝእትነ /2/ ነጽሪ ኀቤነ /2/
ሰላመ ወልድኪ የሀሉ ምስሌነ /4/
ትርጉም፡- አቤቱ አትተወን አትጣለን የሰላም
አምላክ ሆይ ተራዳን ፡፡
እመቤታችን ሆይ ወደ እኛ ተመልከቺ
የልጅሽም ሰላም ከእኛ ጋር ይሁን

**<u>122. ፍቅር ስሐቦ</u>**

ፍቅር ስሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ /2/
ወአብጽሖ /2/ እስከ ለሞት / 2/
ትርጉም፣ ፍቅር ሳበው ኃያል ወልድን
ከዙፋኑ /2/
አደረሰው /3/ እስከ መሞት /2/

**<u>123. እንዘ ይብሉ</u>**

እንዘ ይብሉ ይዜምሩ በልሳን ዘኢያረምም /2/ አማን
በአማን /2/ መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም /2/

ትርጉም፣ የሥላሴ መንግሥት ለዘለዓለም ነው
እያሉ በማያቋርጥ አንደበት ይዘምራሉ

**124.<u>ንሴብሖ</u>**

ንሴብሖ /2/ ለእግዚአብሔር /2/

ስቡሐ ዘተሰብሐ /4/ ኸኸ

ትርጉም፣ የተመሰገነ እግዚአብሔርን
እናመሰግናለን

**125. እስመ አልብነ ረዳኢ**

እሰመ አልብነ ረዳኤ በጊዜ ምንዳቤ ወሐዘን /2/
እስመ ዘእንበሌከ ባእደ ኢነአምር /2/

ትርጉም፣ በችግርና በሐዘን ጊዜ ያለ አንተ
የሚረዳን ዘመድ አናውቅም(የለንም)

**126.መድኃኔዓለም**

መድኃኔዓለም ወሀቤ ሠላም /2/
ይክበር ይመስገን ለዘለዓለም /4/
ትርጉም፣ ሰላምን ሰጪ የሆነ መድኃኔዓለም
ለዘለዓለም ይክበር ይመስገን

**127.ስብሐት ለአምላክ**

ስብሐት ለአምላክነ ወመድኃኒነ /2/
ወአድኅንከ ኀሊናነ /4/
ትርጉም፣ ለመድኃኒታችን ለፈጣሪያችን
ምስጋና ይገባዋል
ሐሳባችንን ከክፉ ነገር ስለመለሰልን

**128.መድኃኔዓለም**

መድኃኔዓለም እግዚአብሔር ኀደረ ላዕሌሃ /2/
ኪያሃ ዘሠምረ ማኅደረ ስብሐት
ኪያሀ ዘሠምረ ደብረ መድኃኒት /2/
ትርጉም፣ ሰው ሁሉ ከሚወዳት
በደብረ መድኃኒትና በማኅደረ
ስብሐት እግዚአብሔር አደረ፡፡

**129.ሠራዊተ**

ሠራዊተ /2/ መላዕክቲሁ /2/
ለመድኃኔዓለም /2/ ይቀውሙ /4/
ትርጉም፣ የመድኃኔዓለም መልእክተኞች
ከፊቱ ይቆማሉ

**130.ወበጽጌያተ**

ወበጽጌያተ ምድር አሰርጎከ /2/
ወበመስቀልከ ለጻድቃን አብራእከ /2/
ትርጉም፣በአበቦች ምድርን አስጌጥካት በመስቀልህም
ለጻድቃን አበራህ፡፡

**131.አባ አባ**

አባ አባ ባርከነ መብዓ ጽዮን በትረ ማርያም /2/
ከመ ባርኮ አብርሃም ለጹስሐቅ ወልዶ /4/
ትርጉም፣ አባታችን መብዓ ጽዮን በትረ ማርያም ሆይ
አብርሃም ልጁን ይስሐቅን
እንደባረከው ባርከን

**132.መንክረ ግርማ**

መንክረ ግርማ ኃይለ ልዑል ጸለላ /2/
አማን /2/ መላእክት ይኬልልዋ /4/
ትርጉም፣ በሚያስደንቅ ግርማ የልዑል
ኃይል ጋረዳት /2/
በእውነት /2/ መላእክት አመሰገኗት /2/

**133.እንደ ዓይንህ ብሌን**

እንደ ዓይንህ ብሌን አምላክ ሆይ ጠብቀን /2/
በክንፈ ረድኤትህ ከመዓትም ጋርደን /4/

**134. በመስቀሉ ወበቃሉ**

በመስቀሉ ወበቃሉ /2/
አዕበዮሙ ለአበዊነ /4/
ትርጉም፣ በመስቀሉ ቃል
አባቶቻችንን ከፍ አረደጋቸው

**135. ኩሉ ከንቱ**

ኩሉ ከንቱ ከንቱ ንብረቱ እስመ ኩሉ ኃላፊ ውእቱ /2/
መድኃኔዓለም /2/ አድኅነኒ እሞተ ከንቱ
ትርጉም፣ ሁሉም ከንቱ ነው መድኃኔዓለም
ከከንቱ ሞት አድነኝ

**136. እስመ ውእቱ**

እስመ ውእቱ ክብሮሙ ለቅዱሳን /2/
መድኃኔዓለም /2/
አሠርገዋ ለምድር አሰርገዋ ለጽጌሀ
ትርጉም፣ መድኃኔዓለም ለቅዱሳን
ክብራቸው ነው
ምድርን በአበባ አስጌጣት

## 137. ሰላም ለዝክረ ሥምከ

ሰላም ሰላም ለዝክረ ስምከ /2/
ጥዑመ ዜና /6/ መድኃኔዓለም ጥዑመ ዜና /2/
ትርጉም፣ ጥሩ ጣፋጭ ነገርን ለሆነው
ስምህ ሰላም ይሁን

## 138. መርሕ በፍኖት

መርሕ በፍኖት ሞገሶሙ ለጻድቃን ሞገስ /2/
ዝንቱ መስቀል ለአዳም ዘአግብኦ ውስተ ገነት /2/
ትርጉም፣ መሪ ነው ለመንገድ ሞገሳቸው
ለጻድቃን ሞገስ /2/
ይህ መስቀል ነው አዳምን
የመለሰው ወደ ገነት /2/

## 139. ንዓ ንዓ አማኑኤል

ንዓ ንዓ አማኑኤል ንዓ ንዓ መድኃኔዓለም
በፍሥሐ ወበሰላም ና ወደ እኛ መድኃኔዓለም
ቅዱስ ጌታ አማኑኤል ቸር አምላክ
መድኃኔዓለም
ለእኛ ብለህ አማኑኤል ተሰቀልክ
መድኃኔዓለም
ልትባርከን አማኑኤል ና በሰርክ
መድኃኔዓለም /2/
ሥጋህና አማኑኤል ደምህን መድኃኔዓለም
ብሉ ብለህ አማኑኤል ሰጠኸን መድኃኔዓለም
ህይወት ሆኖ አማኑኤል አዳነን /2/
መድኃኔዓለም
በኃጢያት ሞት አማኑኤል ወድቀን ሳለን
መድኃኔዓለም
ከጥንት ሀገር አማኑኤል ኑሩ አልከን
መድኃኔዓለም
ሞገስ ልበል አማኑኤል ሞገስ ላውራ
መድኃኔዓለም
ግሩም ብቻ አማኑኤል የአንተ ሥራ /2/
መድኃኔዓለም

## 140.ወመኑ መሀሪ

ወመኑ መሐሪ ዘከማከ /2/
ወኩሎ ይሴፎ ኪያከ /4/
ትርጉም፣ እንደአንተ ይቅር ባይ ማን አለ
ሰው ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋልና

## 141. መድኃኔዓለም

መድኃኔዓለም ወሀቤ ሰላም /2/
ይክበር ይመስገን ለዘለዓለም /4/

## 142. አልቦ ዘከማየ

አልቦ ዘከማየ /2/ አበሳ ኃጢአት ገባሬ /2/
ወአልቦ ዘከማከ /3/ እግዚአብሔር መሐሪ /2/
መድኃኔዓለም ክርስቶስ ዓለማተ ኩሉ ፈጣሪ /2/
በደመ ገቦከ /3/ ኃጢአትየ አስተሠርይ /2/

## 143. እናመስግን አማኑኤልን

እናመስግን አማኑኤልን የሞተልንን ጌታ /2/
በሞቱ ሞትን ሻረልን እንዳንረታ /4/

## 144. መድኃኒት

መድኃኒት እፀ ሕይወት /2/
ዝንቱ ውእቱ መስቀል /4/
ትርጉም፣መድኃኒት እና የሕይወት ዕፅ የሚሆን ይህ
መስቀል ነው፡፡

## 145. ሰማየ በአብ

ሰማየ በአብ ወበልደ አርያም ወመንፈስቅዱስ አበ አርጉ
አነ /2/
ሰማዕኩ እምመላእክት ዝማሬ በአድንኖ
ወበአትኑቶ ቦ ዘያሰርእጾ ወቦ ዘይዜምሩ /2/
ትርጉም፣

## 146.. እግዚአብሔር ብርሃኔና

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው /2/
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማን ነው /2/
አምላኬ መመኪያዬ ነው /2/

## 147. አማኑኤል አዳነን

አማኤል አዳነን በማይሻር ቃሉ /2/
ኸኸ ደስ ይበለን /2/ እልል በሉ /2/
አዳነን በማይሻር ቃሉ /2/

## 148. መድኃኔዓለም ክርስቶስ

መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቀራንዮ ስቁል /2/

በለኒ መሐርኩከ በለኒ መሐርኩኪ /2/

በእንተ ማርያም ድንግል እስመ /2/

ሐር አልቦ እንበሌከ ቃል /2/

149. እንዘ ይብሉ

እንዘ ይብሉ አይሁድ ስቅልዎ /2/ /2/

ለወሀቤ ዝናም ክርስቶስ /2/ ማየ ከልዎ /2/

ትርጉም፣ ዝናብም ለሚሰጥ ክርስቶስ

ውኃ ከለከሉት ስቀለው ስቀለው ተባባሉ

150. በለኒ መሐርኩከ

በለኒ መሐርኩከ /2/ በእንተ ማርያም

እስመ አልቦ ዘእንበሌከ ዘይሜሕር ቃል

መድኃኔዓለም /2/

ትርጉም፣ በለኝ ምሬሀለሁ ስለማርያም /2/

የለምና የሚምር ቃል ያለ አንተ

መድኃኔዓለም /2/

51.ውእቱ ሊቆሙ

ውእቱ ሊቆሙ ለመላእክት ወመልአኮሙ

ስሙ ሚካኤል /2/

ልብሱ ዘመብረቅ ዓይኑ ዘርግብ ሊቀ መላእክት /2/

ትርጉም፣ ለመላእክት አለቃቸው እርሱ ነው

ስሙ ሚካኤል ነው የሚካኤል

ልብሱ የመብረቅ አይኖቹም የርግብ

ዓይኖቹ ይመስላሉ

152.ሊቀ መላእክት

ሊቀ መላእክት ሚካኤል መልአክ ምክሩ ለልዑል /2/

ኃያል /2/ ሰዳዴ ሳጥናኤል ኃይል ገባሬ ኃይል /2/

ትርጉም፣ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ለልዑል

አማካሪ ነው ሰይጣንን ያሳድዳል

(ያባርራል)

153.ሚካኤል ስዩም

ሚካኤል ስዩም /2/ ሊቀ መላእክት /2/

መዝገበ ርኅራኄ /3/ የዋህ /2/

ትርጉም፣ የመላእክት አለቃ ሚካኤል

የዋህ የርኅራኄ መዝገብ ነው

154.ሚካኤል ሊቅ

ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ /2/

ዓይኑ ዘርግብ /2/ ዓይኑ ሚካኤል

ሐመልማለ ወርቅ /2/

ትርጉም፣ አለቃ የሆነ ሚካኤል ልብሱ መብረቅ

ነው ዓይኖቹም የርግብ ዓይን ይመስላሉ

ሚካኤል የወርቅ ሐመልማል ነው

155.ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንዒ ሠናይትየ ማርያም /2/

ንዒ /9/ እመ አምላክ ንዒ ማርያም /2/

ትርጉም፣ የአምላክ እናት እመቤታችን ማርያም

ሆይ ከቅዱስ ሚካኤል ገብርኤል

ጋር በሰላም ወደ እኛ ነይ

156.ሰፊሆ ክነፊሁ

ሰፊሆ ክነፊሆ /2/

ክንፊሆ ይጸልል ዲቤነ /2/

ትርጉም፣ ክንፉን ዘርግቶ እኛን ይጋደን ይጠብቀን

157.ከመትባርከነ

ከመትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ /2/

ተዋነይ በጽድቅ /4/ ሚካኤል ሐመልማል ወርቅ /2/

ትርጉም፣ የወርቅ ሐመልማል ሚካኤል ሆይ በወርቅ

መስቀልህ ትባርከን ዘንድ በእውነት

በመካከላችን ተገኝ

158.ሐመልማለ ወርቅ

ሐመልማለ ወርቅ /6/

ሚካኤል /3/ ሐመልማለ ወርቅ /2/

159.ባሕራንኒ

ባሕራንኒ ይቤ ዘነገደ ባሕር /2/

ርኢኩዎ /2/ ለሚካኤል ወስእንኩ ጠይቆ /2/

ትርጉም፣ ባሕርን አቋርጦ የሄደ ባህራን

ሚካኤልን ለይቼ መረዳት ተሳነኝ አለ።

160.እግዚኡ ረስዩ

እግዚኡ ረስዩ ለውእቱ ሚካኤልን

እምኩሎሙ መላእክት /2/ መላእክት

ይትለዓል መንበሩ /2/

ትርጉም፣ ከመላእክት ሁሉ ይልቅ መንበሩ
ከፍ ይል ዘንድ ሚካኤልን ጌታው ሾመው

**161.ዓይኑ ዘርግበ**

ዓይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ /2/
ሐመልማለ ወርቅ /3/ ሚካኤል ሊቅ /2/
ትርጉም፣- ሊቀመላእክት ቅዱስ ሚካኤል ዓይኑ
የርግብ ልብሱም የመብረቅ ነው፡፡

**162. ነዋ ሚካኤል**

ነዋ ሚካኤል መልአከክሙ /2/
ይስአል ለክሙ በእንተ ምሕረት /2/
ትርጉም፣ እነሆ ሚካኤል መልአካችሁ
ይለምንላችሁ፡፡

**163. አንተኑ**

አንተኑ ሚካኤል መና ዘአውርድከ /2/
ወአንተኑ ለእስራኤል መና ዘአውድርከ /2/
ትርጉም፣ ለእስራኤል መናን ያወደርክ አንተ ነህ

**164. መልአከ ሰላምነ**

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ሚካኤል /2/
ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎትነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም /2/
ትርጉም፣ የይቅርታ መልአክ ሚካኤል
ሆይ በመድኃኔዓለም ፊት ስለኛ
ለምንልን

**165. አመ ይስቅልዎ**

አመ ይስቅልዎ አይሁድ ለእግዚእነ /2/
ሚካኤል እርመመ ወገብርኤል ተደመ /2/
ትርጉም፣ አይሁድ ጌታን በሰቀሉት ጊዜ
ሚካኤል ዝም አለ ገብርኤልም ተደነቀ

**166. በእደ መልአኩ**

በእደ መልአኩ /2/ ይዕቀበነ /2/
በእደ መልአኩ /3/ ይዕቀበነ /2/
ትርጉም፣ በመልአኩ እጅ ይጠብቀን

**167.ዓይኑ ዘርግብ**

ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ/2/
ሐመልማለ ወርቅ /2/ ልብሱ ዘመብረቅ /2/

**168.ሚካኤል መጽዓ**

ሚካኤል መጽዓ ይርድአነ ወያድኅነነ /2/
ተፈኒዎ /2/ እምአርያም /2/ ከመ ያድኅነነ /2/
ትርጉም፣ ሚካኤል መጣ ሊረዳን ሊያድነን /2/
ተልኮ /2/ ከሰማይ /2/ እኛን ሊያድነን /2/

**169. ዘአውረድከ መና**

ዘአውረድከ መና /6/
ሚካኤል /3/ ዘአውረድከ መና
ትርጉም፣ መናን ያወረድክ /6/
ሚካኤል /3 / መናን ያወረድክ

**170.ሊቀ መላዕክት**

ሊቀ መላእክት /6/
ሚካኤል /3/ ሊቀ መላእክት /2/
ትርጉም፣ የመላእክት አለቃ /6/
ሚካኤል /3/ የመላእክት አለቃ
ለምንልን ለእኛ

**171.ዝኬ ውዕቱ**

ዝኬ ውእቱ ሚካኤል ኅብስተ መና ዘአውረድከ /2/
ወከመ አያያተ መአር /2/ ጥዑም ፈድፋደ ሊቀ
መላአክት /2/
ትርጉም፣

**172.ተወከፍ ጸሎተነ**

ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኑኃ ሰማይ /2/
ከመ መዓዛ ሠናይ /4/ ሊቀ መላእክት /2/
ትርጉም፣

**173.ቅዱስ ሚካኤል**

ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ልዑል /2/
መኑ ከመ እግዚአብሔር ሚካኤል ኃይል /4/
ትርጉም፣ የልዑል መልአክ ቅዱስ ሚካኤል
የስምህ ትርጓሜ ማን
እንደ እግዚአብሔር ነው

**174. ቀዋምያን**

ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት ሚካኤል ወገብርኤል/2/

ይትፌነዉ ለሳህል /2/ እም ኀበ ልዑል /2/

ትርጉም፣ ለነፍሳት የቆሙት እነዚህ መላእክት
ሚካኤልና ገብርኤል /2/
ከልዑል ዘንድ ለይቅርታ /2/ ይላካሉ
ከልዑል

### 175. ውእቱ ሚካኤል

ውእቱ ሚካኤል ኃይል ልዑል ውእቱ ልዑል
መንበር /2/
ይስአል ለነ ረዳኤ ይኩነነ ይስአል ለነ አመ ምንዳቤ /2/
ትርጉም፣ ይህ መቀመጫው ከፍ ያለ ኃይል
መልአክ ሚካኤል በችግራችን ጊዜ
ይልምንልን ረዳት ይሁነን፡፡

### 176.በአምሳለ ርግብ

በአምሳለ ርግብ ወረደ መልአክ ወረደ /2/
ወረደ /4/ ሚካኤል መልአክ ወረደ /2/
ትርጉም፣ መልአኩ ሚካኤል በርግብ አምሳያ
ወረደ እነሆ ወረደ መልአኩ ወረደ

### 177. ኦ ሚካኤል

ኦ ሚካኤል /2/ ሊቀ መላእክት
በኃጢአት እንዳንወድቅ እንዳንሞት ፈጥነህ
ተራዳን አጽናን በእምነት /2/

ለያዕቆብ ነገድ ሚካኤል
ለእስራኤል »
ጠባቂያቸው ነህ »
መልአከ ኃይል »
ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል
የእኛ አባት /2/

ነጸብራቃዊ ሚካኤል
ተክህኖ ልብስ »
ሐመልማለ ወርቅ »
ዓይኑ ዘርግብ »
ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል
የእኛ አባት /2/

በስእልህ ፊት ሚካኤል
እቆማለሁ »
ፈጥነህ ተራዳኝ »
አለሁ በለኝ »
ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል
የእኛ አባት /2/

### 178.. ቅዱስ ሚካኤል

ቅዱስ ሚካኤል /3/ ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ሥጋዬ
ፈጥነህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ

አንተ ስለሆንክ ሚካኤል
የአምላክ ባለሟል »
ልመናን ፈጥኖ »
ከአምላክ ያቀርባል »
የዋኅ መልአክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው /2/

ደዌ የጸናበት ሚካኤል
በአንተ ይድናል »
በአደባባይህ »
ምስክር ሆኗል »
ከቤቱ መጥቶ የተማጸነ
በቃልኪዳንህ ሕይወቱ ዳነ /2/

ከአምላክ ተሰጥቶህ ሚካኤል
ክብርህ ያበራል »
ለጎስቋላው ሰው »
መጠጊያ ሆኗል »
ትልቅ ትንሹ ደሃው ሀብታሙ
ለምኖ አግኝቷል ከአምላክ በስሙ /2/

በብሉይ ኪዳን ሚካኤል
ከአምላክ ተልከህ »
ህዝበ እስራኤልን »
ነጻ ያወጣህ »
በአዲስ ኪዳንም ድንቅ ሥራ አለህ
በተአምራትህ ትፈውሳለህ /2/

ባለ መድኃኒት ሚካኤል
ያቃተውን »
ፈዋሽ ጠበልህ »
ሆኖኛል ኃይል »
እንደ መጻጉ ድኅነት አገኘን

ፈውሰኸናል በአንተ ተመካን /2/

**179.. ሚካኤል አማልደን**

ሚካኤል አማልደን ከአምላካችን /2/
እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን
አደራህን አማልደን ከአምላካችን

**180. አንተ ቅዱስ ሚካኤል**

አንተ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት የአምላክ ባለሟል /2/
አገራችንን ጠብቅልን ዛሬም በአማላጅነትህ ፈጥነህ ድረስላት ለኢትዮጵያ /2/

**181. ኃያል ሀኃያል**

ኃያል /8/ ሰዳዴ ሳጥናኤል
ኃያል ገባሪ ኃይል /2/
ባሕራንን የረዳው ከተላፊለኖስ እጅ ያዳነው/2/
መልአኩ ሚካኤል ነው /2/
የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው
ከዕደ ረበናት /4/ ሶስናን ያዳናት
ሚካኤል መልአክ ምሕረት
ዲያቢሎስን ያዋረድከው በእሳት ሰይፍ
የቀጣኸው 2/ ሚዛንህ ትክክል ነው /2/
ሚካኤል ክብርህ ድንቅ ነው
ምሕዘን በትካዜ ያለሁትን ብላቴና
አጽናናኝ አረጋጋኝ /2/ ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና

**182. ፈተና ቢገጥማት**

ፈተና ቢገጥማት /2/ ቅድስት አፎምያ
ሚካኤል /2/ ብላ ስትጠራ /2/ ፈጥኖ አዳናት ከጭንቅ ከመከራ /2/
ነውና እምነቷ /2/ ጽኑ ከምግባሯ
ሚካኤል መጣላት /2/ ተአምሩን ሊሠራ
ሚካኤል መጣላት /2/ ለአፎምያ
ተአምሩን ሊሠራ
ፍጡነ ረድኤት መጣላት /2/ ገስግሶ /2/
እንደ ኃያልነቱ ኃይሉን አፈራርሶ /2/
በመጣበት ሄደ ተመልሶ
በእምነት ለጠሩህ /2/ ጸንተው በሃይማኖት
ቶሎ ይደርስልናል ፍጡነ ረድኤት /2/
ሚካኤል ሊቀ መላእክት

**183. ከሚካኤል በቀር**

ከሚካኤል በቀር የሚያጽናናኝ የለም
ረዳቴ እርሱ ነው በመከራዬ ቀን /2/

ሐዘኔ እጅግ በዝቶ ከሚካኤል በቀር
የሚያጽናናኝ ሳይኖር ከስደቴ ዘመን
ሰላም ከእኔ ርቆ ከሚካኤል በቀር
ጭንቀት አስጠብቦኝ በዙሪያዬ ከቦኝ
ዛሬ ግን አጽናኜ ከሚካኤል በቀር
ሚካኤል ደረሰ ጠላቴ አፈረልኝ
ሚካኤል ነው የዳዊት ረዳት ከጎልያድ ያዳነው
ሚካኤል ነው መንፈሳዊ ብርታት ኃይልንም የሠጠው /2/
አዝ ----------------
ቃልኪዳኑ ግሩም ከሚካኤል በቀር
ዝክሩን ለዘከሩት ሥሙንም ለጠሩት
አጋንንት አይቀርቡም ከሚካኤል በቀር
ሥዕሉ ባለበት ድርሳኑን ቢደግሙት
በረከት ይገኛል ከሚካኤል በቀር
እርሱን ሲማጽኑት ከለመኑት በእውነት
ሚካኤል ነው በትረ መስቀል ይዞ የሚጠብቀኝ
ሚካኤል ነው ከአንበሶች መንጋጋ የሚታደገኝ /2/
አዝ --------------
በኑሮአችን ሁሉ ከሚካኤል በቀር
እርሱ ይመራናል እርሱ ይረዳናል
ፈርኦንን ድል ነስቶ ከሚካኤል በቀር
ከግብጽ አውጥቶናል በብርሃን መርቶናል
የኤርትራን ባሕር ከሚካኤል በቀር
ከፍሎ እንዳሻገረን ከነዓን ገብተናል
ሚካኤል ነው ከበልዓም እርግማን
እስራኤልን ያዳነው
ሚካኤል ነው ዛሬም በአዲስ ኪዳን ክብሩ የገነነው /2/

**184.ዝንቱ አስማተ አቢይ**

ዝንቱ አስማተ ዘክቡር ወልዑል

ዘወሀቦ/2/ እግዚአብሔር/2/ ለቅዱስ ሚካኤል/2/

## የኅዳር ጽዮን መዝሙር

**185.አብርሂ ጽዮን**

አብርሂ ጽዮን

ማርያም /3/ አብርሂ ጽዮን/2/

**186.. ዘካርያስ ርእየ**

ዘካርያስ ርእየ ተቀዋመ ማኅቶት ኩለንተሃ ወርቅ በየማና ወበጸጋማ አዕጹቀ ዘይት/2/

ነቢያት ይትፌሥሑ ሐዋርያት ይትሐሰዮ በውስቴታ ወዳዊት ይዜምር በውስተ ማኅፈዲሀ /2/

ትርጉም፡- በቀኝም በግራዋም የዘይት ጫፍ ያላት

የመብራት መቅረዝ

ዘካርያስ አየ ነቢያትና ሐዋርያት

በውስጧ ደስ ይላቸዋል

ዳዊትም በውስጧ ያመሰግናል

**187.የኪዳን ፅላት**

የኪዳን ፅላት የተሠወረ መና ያለብሽ ደብተራ ድንኳን አንቺ ነሽ /2/

ይህውም መና የተባለው /2/ በድንግል ማርያም

ያደረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው/2/

**188.ታቦተ እንተ ውስቴታ**

ታቦተ እንተ ውስቴታ ኦሪት እንተ ውስቴታ /2/

ውቱረ ይኬልልዋ በወርቅ ውቱረ ይኬልልዋ በወርቅ ይኬልልዋ

**ትርጉም፡-** የኦሪት ቃል ያለባት ታቦትን ፈጽመው በወርቅ ይጋርዷታል፡፡

**189. ውስቴታ ታቦተ**

ውስታቴ ታቦት በውስቴታ ኦሪት

በውስቴታ/2/

ይኬልልዋ በወርቅ ይኬልልዋ

**190.ታቦተ ሕጉ**

ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት

ሕጽርት ወበመንፈስቅዱስ ክልልት /2/

ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየኃደጋ ለሀገር/2/

**ትርጉም፡-** በካህናት የታጠረች

በመንፈስ ቅዱስ

የተከለለች የእግዚአብሔር የሕጉ

ታቦት ጽዮን ሆይ

ንጉሥሽ ለጠላት

አይሸነፍም ሀገርንም

አይተዋትም፡፡

**191.ሙሴኒ ርዕያ**

ሙሴኒ ርእያ /2/ ሀገር ቅድስት

ኢትዮጵያ /2/

እዝራኒ ተናግራ ተናግራ ዘምራ ዳዊት/2/

ትርጉም፡- የተባረከች ሀገር ጽዮንን

ሙሴ አያት እዝራም ተናገራ ዳዊትም አመሰገናት፡፡

**192.ሐመልማላዊት**

ሐመልማላዊትሐመልማላዊት ሐመልመላዊት /2/

ሙሴ ዘርእያ ዘርእያ በደብረ ሲና ማኅደረ ስብሐት/2/

**193. ጽላት ዘሙሴ**

ጽላት ዘሙሴ ጽላት/2/

ጽላት ዘሙሴ ጽላት /2/ ማርያም ቅድስት/2/

ሙሴ ከፈጣሪው የተቀበላት አሠርቱ

ትዕዛዛት የተጻፈባት ጽላት ዘሙሴ ጽላት/2/

ይዕቲ ዕፀ መድኃኒት /2/ ይዕቲ ዕፀ መድኃኒት ማርያም ቅድስት/2/

**194. ዘይሃይድ ዓይነ**

ዘየሃይድ አይነ/2/ ልብስ ክብር ለቢሶ ዳዊት /2/

ቅድመ ታቦተ ሕግ ኃለየ ቅድመ ታቦት ሕግ/2/

ትርጉም፡- ንጉሥ ዳዊት ዓይንን የሚንፀባርቅ
የክብር ልብስ ሰብሶ ከሕግ
ታቦት ፊት አመሰገነ፡፡

**195.እንተ ክርስቶስ**

እንተ ክርስቶስ መሠረት ፀሐየ ጽድቅ ያበርህ
ለኪ ፀሐየ ፅድቅ/2/
ለሰማዕት ሥርጉት በስብሐት ሥርጉት
በስብሐት /2/
ትርጉም፡- ክርስቶስ መሠረትሽ የሆነ ቤ/ክ
የጽድቅ ፀሐይ ያበራልሻል
ለሰማዕት በስብከት
የተሸለምሽላቸው፡፡

**196.ፅላት ዘሙሴ**

ጽላት ዘሙሴ እፀ ጳጦስ ዘሲና/2/
ጸናጽል ዘውስተ ልብሱ ለአሮን ካህን /2/
ትርጉም፡- የሙሴ ጽላት የሲና እፀ ጳጦስ
የአሮን
የልብሱ ውስጥ ጸናጽል

**197. ኢትዮጵያ ታበጽህ**

ኢትዮጵያ ታበፅህ እደዊሀ ኀበ
እግዚአብሔር.2/
እንዘ ትብል አምላኪየ/2/ ነጽረኒ ወአድኀነኒ
እምኃይል ፀላኢ ወፀር/2/

**198.ተመጠወ ሙሴ**

ተወጠወ ሙሴ ተመጠወ ሙሴ/2/
ኦሪት ጽላት ተመጠወ አሥሮነ ቃላተ/2/

**199.ሙሴ ዘርዕያ**

ሙሴ ዘርእያ /2/ በደብረሲና
ሐመልማላዊት ዕፅ /2/ ሐመልማላዊት/4/
ትርጉም፡- ሙሴ ያያት
በደብረ ሲና የለመለመች ዕፅ/2/
የለመለመች /4/

**200.አብርሂ ጽዮን (ወረብ)**

አብርሂ ጽዮን/2/ ጽዮን አብርሂ/2/
እንቁ ዘጳዝዮን ዘኀረየኪ ሰሎሞን
ንጉሥ/2/
አብርሂ ጽዮን /4/
ማርያም/3/ አብርሂ ጽዮን /2/

**201.እዝራኒ**

ሙሴኒ ርእያ ለጽዮን ቅድስት/2/
ለጽዮን ቅድስት ሰላማዊት/4/
ትርጉም፡- ሰላማዊት የሆነች
ቅድስት ጽዮንን ሙሴ አያት፡፡

**202.ሃሌ ሃሌ ሉያ**

ሃሌ ሃሌ ሉያ በጾም ወበጸሎት/2/
ተመጠወ መሴ ኦሪት አሥሮነ ቃላት/2/
ትርጉም፡- አለም ሳይፈጠር የነበረ
ዓለምን አሳልፎ የሚኖር
በጾምና በጸሎት ሙሴ
አሥርቱን ቃላትን
ጽላትን ተቀበለ፡፡

**203.ዘበሰማይኒ**

ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ በቃለ ዳዊት
ይሴብሕዎ/2/
ወይብሉ ኩሉሙ ሃሌ ሉያ/2/
ትርጉም፡- በሰማይም በምድርም
በዳዊት ቃል ያመሰግናሉ፡፡

**204.ወባዕዳነ ነቢያት**

ወባዕዳነ ነቢያት እለከማሆሙ አቀቡ ሕግየ/2/
ከመ በላዕሌሆሙ እሰባሕ እስከ ለዓለም ዓለም/4/
ትርጉም፡- እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ በላያቸው
ይመስገን ዘንድ የተለዮ ነቢያት
ለእነርሱ ሕጌን ጠብቁ፡፡

**205.በምን በምን ምን ንመስላት**

በምን /2/ እንመስላት ድንግል ማርያም/2/
ምሳሌ የላትም /2/ ክብሯን የሚመጥን/2/
የሙሴ ጽላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
የመላዕክት እኅት የርኅሩኃን ርግብ/2/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የእዝራ መስንቆ የጌድዮን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃን በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር/2/
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግሥት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨላማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ/2/

206.የኅዳር ጽዮን አንገርጋሪ

ሃሌ ሉያ አይቲ ዛቲ እንተ
ታስተርኢ እምርሁቅ
ከመ ማኅቶት ብርሀት ከመፀሐይ
ሙሴኒ ርእያ ሀገር ቅድስት
ዕዝራኒ ተናገራ ዳዊት ዘመራ

207.ጽዮን

ጽዮን ቅድስት እሞሙ ለሰማዕት/2/
ወእኅቶሙ ለመላዕክት/4/
**ትርጉም፡-** ጽዮን የተባለች ቅድስት
ድንግል ማርያም የሰማዕታት እናታቸው
የመላዕክት እኅታቸው ናት፡፡

208.እዝራኒ ተናገራ/2/

እዝራኒ ተናገራ/2/
ተናገራ ዳዊት ዘመራ ተናገራ ዳዊት/2/

209ዘርዕየ

ዘርዕየ ተቀዋመ ማኅቶት/2/
ዘካርያስ ካህን ነቢይ ወሰማዕት/2/
**ትርጉም፡-** መቅረዝን ያየ ነቢያት ካህን የሆነ
ዘካርያስ የመብራት መቅረዝን አየ

**<u>የልደት እና የጥምቀት መዝሙር</u>**

**<u>210.በኮከብ መጽኡ</u>**

በኮከብ መጽኡ /2/ ሰብአሰገል/2/
ለአማኑኤል /4/ ይስግዱ ለአማኑኤል
/2/
ትርጉም፡-የጥበብ ሰዎች
ለአማኑኤል ይሰግዱ ዘንድ
በኮከብ እየተመሩ መጡ

**<u>211.በጎለ እንስሳ</u>**

በጎለ እንስሳ /2/
በጎለ እንስሳ ተወለደ አማኑኤል/4/
ትርጉም፡
በእንስሳት በረት አማኑኤል ተወለደ

212.ውስተ ማኅፀነ

ውስተ ማኅፀነ ድንግል ኀደረ ማኅፀነ
ድንግል/2/
ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ ሰማይ ወምድር
በማይ ተጠመቀ
ትርጉም፡-
ሰማይና ምድር የሚይችሉት አምላክ
በእመቤታችን ማኅፀን አደረ በውኃም
ተጠመቀ

**<u>213.መጽአ ከመይቤዙ</u>**

መጽአ ከመይቤዙ ዓለም/2/
የሀበነ ሰላመጋዳ ያበውዑ ቁርባን /2//
ትርጉም፡-
ዓለምን ለማዳን መጣ አንድነቱንም
ይስጠን ዘንድ እጅ መንሻም ያቀርቡ
ዘንድ

**<u>214.በጎል ሰበከ</u>**

በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ /2/
ቤዛ ኩሉ ዓለም/2/ ዮም ተወለደ /4/

ትርጉም፦ በበረት ተኛ በጨርቅ ተጠቀለለ
የዓለም መድኃኒት/2/ ዛሬ ተወለደ/2/

215.ሖረ ኢየሱስ

ሖረ ኢየሱስ /4/
እምገሊላ /3/ ኀበ ዮሐንስ /2/
ትርጉም፡ሄደ ኢየሱስ/2/
ከገሊላ/3/ ወደ ዮሐንስ

216.ምድርኒ ርእይቶ

ምድርኒ ርእይቶ ወአኮቴቶ/2/
ባሕርኒ ሰገደት ሎቱ/4/
ትርጉም፦ ምድርም አየችው አመሰገነችው
ባሕርም ሰገደችለት

217.ወወለደት

ወወለደት ወልደ ዘበኩራ /4/
መንጦላዕት ደመና ሰወራ /4/
ትርጉም፦ የበኩር ልጇን ወለደች
የደመና መጋረጃ ጋረዳት

218.በፍሥሐ ወበሰላም

በፍሥሐ /2/ ወበሰላም/2/
ወረደ ወልድ/4/ ወልድ ውስተ ምጥማቃት
ትርጉም፡ ወልድ ክርስቶስ
ሊጠመቅ ወደ ወንዝ ወረደ

219.ወረደ

ወረደ ወልድ/6/
እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት/4/
ትርጉም፦
ወልድ ክርስቶስ ወደ ወንዝ ሊጠመቅ ወረደ

220.ወቅድሳት

ወቅድሳት መንፈስ
ወሀበነ ማየ መንጽኤ ዚአነ
ትርጉም፡ መንፈስ ቅዱስ በመቅደስ
ለኃጢአታችን ማንጫ ውኃን ሰጠን

221.በእደ ዮሐንስ

በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ/2/
ሰማያዊ /5/ ኢየሱስ ናዝራዊ/2/
ትርጉም፦ ናዝራዊ ኢየሱስ ክርስቶስ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

222.ኢየሱስ ሖረ

ኢየሱስ ሖረ ሀገረ እሴይ
ዮሐንስ አጥምቆ በማይ ወለደነ ዳግመ እማይ /2./
ትርጉም፦ ኢየሱስ ወደ እሴይ ሀገር ሄደ
ዮሐንስም በውኃ አጠመቀው
እኛንም ከውኃ ዳግመኛ ወለደን

223.እንዘ ሕፃን

እንዘ ህፃን ልህቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/
በዮርዳኖስ /4/ ተጠምቀ በእደ ዮሐንስ /2/
ትርጉም፦ እንደ ሕፃን ሆኖ በትንሽ
በትንሹ አደገ በዮርዳኖስ
ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

224.ኀዲጎ ተሰአ

ኀዲጎ ተሰአ ወተሰአተ ነገደ /2/
ማእከለ ባሕር /4/ ቆመ ማዕከለ ባሕር/2/
ትርጉም፦ ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክትን ትቶ
በባሕር መካከል ቆመ

225.ወተመስሎ

ወተመስሎ ስብአ ዓይን አባግዓ ላባ ወማይ/2/
ወጥምቀተ አባይ/2/ አባይ/2/
መጥምቀተ አባይ /2/
ትርጉም፡ ውኃን የጠጡ የላባ በጎች ምልክትን
አይተው አንድ እንደሆኑ በጥምቀት አንድ ሆኑ
ለተባሉ ለዛሬዎቹም ምዕመናን ምሳሌ ሆኑ

226.ክርስቶስ ተወልደ

ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀ በማይ /2/
ወለደነ ዳግመ እማይ /2/
ደግመ /2/ ወለደነ ዳግመ እማይ /2

ትርጉም፡- እስይ ክርስቶስ ተወለደ እሰይ ክርስቶስ
በውኃ ተጠመቀ ዳግመኛ በመንፈስ ቅዱስ
በጥምቀት ወለደን

## 227.እምሰማያት

እምሰማያት ወረደ ወእምማርያም ተወልደ /2/
ከመይኩን ቤዛ /2/ ለኩሉ ዓለም/2/
ለብሰ ሥጋ ማርያም /2/
ትርጉም፡
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ/2/
እንዲሆነን ቤዛ/2/ ለዓለሙ ሁሉ/2/
ለበሰ የማርያምን ሥጋ/2/
ቤዛ ለዓለም ሁሉ
ለበሰ የማርያምን ሥጋ

## 228.መድኅኒነ ተጠመቀ

መድኃኒነ ተወለደ ነዋ
መድኃኒነ ተጠመቀ ነዋ/2/
ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ
ትርጉም፡- መድኃኒታችን እነሆ ተወለደ
መድኃኒታችን ተጠመቀ
አሁንም እነሆ ሰላምን እንከተላት

## 229.አማን በአማን

አማን በአማን /4/
መንክር ስብሐተ ልደቱ
አማን በአማን /4/
መንክረ ስብሐተ ጥምቀቱ
ትርጉም፡-እውነት እውነት የክርስቶስ
መወለድ መጠመቅ አስደናቂ ነው

## 230.ሃሌ ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሃሌ ሉያ /2/
ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ /4/
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ/2/
ትርጉም፡- የነበረ በማዕከለ ዓለም ያለ
ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ሰማያዊ
ክርስቶስ በምድራዊ እጅ ተጠመቀ

## 231.እንዘስውር

እንዘስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ /2/
ተአምረ ወመንክር ገብረ መድኃኒነ በቃና /2/
ዘገሊላ ከብካበ ኮነ ማየ ረስየ ወይነ
ትርጉም፡- ጌታችን መድኃኒታችን ከእኛ ተሰውሮ
የነበረው አሁን ተገለጠ በቃና ገሊላ
ውኃውን ወይን ጠጅ
በማድረግ ተአምራትን አደረገ

## 232.ክርስቶስ ተወለደ

ክርስቶስ ተወልደ ወተጠመቀ /2/
አስተርእዮቱ አማን አሰትርእዮቱ /4/
ትርጉም፡- ኢየሱስ ክረትስቶስ ተወለደ
ተጠመቀም በእውነት መገለጹ እውነት ነው

## 233.ዮሐንስኒ

ዮሐንስኒ ሃሎ ያጠምቅ/2/
በሄኖን በቅሩበ ሣሌም/4/
ትርጉም፡- በዮሐንስ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ
በዮርዳኖስ ያጠምቅ ነበር

## 234.ሶበ መጽአ

ሶበ መጽአ ቃል እምሰማይ ለተናብቦ/2/
ከበቦ /4/ ለማይ ባሕር ነድ በማይ ከበቦ/4/
ትርጉም፡- ቃል ከሰማይ ለመናገር በመጣ
ጊዜ እሳት የዮርዳኖስን ባሕር ከበበው
ውኃውም የሚሄድበት ቦታ ጠበበው

## 235.ዮም ሰማያዊ

ዮም ሰማያዊ በጎል ሰከበ
ለዘተወልደ እምቅድስት ደንግል/2/
ርእይዎ ኖሎት/2/ አእኩትዎ መላእክት /2/
ትርጉም፡- እነሆ ዛሬ ሰማያዊ ንጉሥ
በበረት ተኛ ከቅድስት ድንግል
ማርያም የተወለደውን ሰማያዊ

ንጉሥ እረኞች አዩት

መላእክትም አመሰገኑት

## 236.ስብሐት ለእግዚአብሔር

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት

ወበሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ/2/

ሃሌሉያ/3/ አሜን ሃሌሉያ

ትርጉም፡- በሰማያት ለእግዚአብሔር

በምድርም ለሰው ልጆች ሰላም ይሁን

## 237.ወጽአ ወገብአ

ወጽአ ወገብአ በሰላም /2/ ወገብአ በሰላም/2/

ትርጉም፡-በሰላም ወጥቶ በሰላም ገባ

## 238.ንኡ ናንሶሱ

በብርሃኑ ንኡ ናንሶሱ

በብርሃኑ ንኡ ናንሶሱ

ትርጉም፡- በብርሃኑ እንመላለስ

## 239.መጽአ ቃል

መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል/2/(2)

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር/4/

ትርጉም: የምወደው ልጄ ይህ ነው

የሚል ቃል ከደመና መጣ

## 240.ፈለገ ዮርዳኖስ

ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣእሙ

ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ

ቅድስት/3/ ዮርዳኖስ ሆይ የጌታ ሀገሩ

አብ ወልድ መንፈስቅዱስ በአንቺ ላይ አደሩ

## 241.ቅዱስ

ቅዱስ /3/ አልፋ ሕያው አምላካችን ክብሩ

ይስፋ/2/

እስይ ተጠመቀልን እኛ እንዳጠፋ

## 242.የምስራች

የምሥራች ተጠመቀ እስይ /2/(2)

የዓምለም ቤዛ /2/ የጽድቅ ፀሐይ /2/

ተጠመቀ አምላክ አዶናይ /2/

## 243.በበረት የተኛው

በበረት የተኛው ቅዱሱ ሕፃን

ልብስም አለበሰ ነበረ ዕርቃኑን

የምታለብሰው ልብስ ባታገኝ እናቱ

ትንፋሽ አለበሱት ከበው እንስሳቱ

እሰይ የምሥራች ሃሌ ሃሌ ሉያ

ጌታ ተወለደ ሊሆነን አርዓያ

## 244.ከእመቤታችን ተወለደ

ከእመቤታችን ተወለደ ሥጋን የለበሰው

እኛን ሊያድነን ነው/2/ ከሞት እኛን ሊያድነን ነው

በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ሞትን ድል ያደረገው

እኛን ሊያድን ነው/2/ ከሞት እኛን ሊያድነን ነው/2/

## 245.ኦንፈራጾ

ኦንፈራጾ ሰብአ ሰገል/4/

አምኃሆሙ አምጽኡ መድምም /2/

## 246.የዓለም በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ

ዘጠና ዘጠነኙን መላእክቱን ትቶ

ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ

አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ/2/

የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ

ተወለደ ሲጠመቅ እኛ ለመቀደስ

ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደፈረስ

ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ

ዮርዳኖስ ሸሸ ለመቆም ከፊቱ

እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ

እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ

መንፈስቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ

በርግብ ምሳሌ ክንፋን አሰይፎ

ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት

መጣ በዳመና ሰማያዊ አባት

እየመሰከረ የልጁን ጌትነት
ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲጨፍር
ሰማይ ሲከፍት ደመናው ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምስጢር

247.የምስራች

የም፦ራች ደስ ይበለን/2/ እንበል ሃሌ ሉያ/2/
አምላክ ተጠመቀ ሊሆነን አርዓያ/2/
አምላክ ተጠመቀ ከዚህ ሁሉ ክብሩ
ስለእኛ ነውና እንዘምር ዘምሩ
ከድንግል ተወለዶ ወልድ ሲጠመቅ
ተራሮች ዘለሉ ዮሐንስ ሲያጠምቅ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
ወልድ አምላክነቱ በግልጽ መታየቱ
ከገሊላ ወንዝ ወደ ዮርዳኖስ
ሊጠመቅ ወደደ በእደ ዮሐንስ
እንዴት ይቻለኛል አንተ ለማጥመቅ
ብሎ መለሰለት ዮሐንስ መጥምቅ

248ደስ ይበለን

የምስራች ደስ ይበለን/2/
የዓለም መደኃኒት ተወለደልን/2/
የምስራች ደስ ይበለን
አዳም ሆይ ደስ ይበለህ
የዓለም መድኃኒት ተወለደልህ
ሔዋን ሆይ ደስ ይበልሽ
የዓለም መድኃኒት ተወለደልሽ
ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት /2/
በኮከብ ተመርተው ሕፃኑን አገኙት
ሰግዱለት ከመሬት ወድቀው
ወርቅ እጣኑን ከርቤ በረከቱን ሰጥተው
ንጉሥ ሄሮድስ ይህንን ሲሰማ
ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ

249.ሳር ቅጠሉ

ሳር ቅጠሉ ሰርዶ ሰንበሌጥ ቀጤማ
በዚያች ቀን በዚያች ወር ለምለም የነበረው
እልልታ ዘመሩ በደስታ ተሞልተው
ጌታ መወለዱን የምስራች ሰምተው
እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ /2/
ያ ትጉት እረኛ ያ ትጉት አባት
ብርሃንን ለበሰ በእኩለ ለሊት
ጥሪ ተልኮለት ከሰማይ ሠራዊት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
እረኝነት ትንሽ የወራዳ ግብር
ብሎ ሰው በግምት ተናግሮ ነበር
የብዙ ሰው ራስ መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ

250.እሰይ ተወለደ

እሰይ ተወለደ የአለም መድሀኒት /3/
ይኸው ተወለደ የአለም መድኃኒት/3/
ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ ሁሉ/3/
አምላክ ቀዳማዊ ይመጣል እያሉ/3/
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ/3/
እስራኤል ንጉሥ ወዴት ነው እያሉ
ሰብአ ሰገል መጡ ይዘው እጅ መንሻ /3/
ወርቅ እጣን ከርቤውን ለማርያም እጅ መንሻ/3/
ሕፃናት እንሂድ ከልደቱ ቤት/3/
ውኃው ሆኗልና ማርና ወተት/3/

251.አንቺ አንቺ

አንቺ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ መሬት
ባንቺ ተወለደ የአለም መድኃኒት /2/
አዳም ክብር ሲሻ ቤተልሔም
ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም
ጌታ ተወለደ ቤተልሔም
ከድንግል ማርያም ቤተልሔም
እስራኤል ህዝቤን ቤተልሔም
የሚጠብቃቸው ቤተልሔም

ካንቺ ይወጣል ብሎ ቤተልሔም
እንደ ነገራቸው ቤተልሔም
እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም
የምስራች ነገስታት ቤተልሔም
ህፃኑን ከእናቱ ቤተልሔም
ተኝቶ አገኙት ቤተልሔም
ቅዱሳን መላእክት ቤተልሔም
ያሸበሸቡለት ቤተልሔም
ስብሀት ለእግዚአብሔር ቤተልሔም
ብለው ዘመሩለት ቤተልሔም

252.እስመ እምዘርዓ ዳዊት

እስመ እምዘርዓ ዳዊት ዘመጽአ/2/
በቤተልሔም ዘይሁዳ በቤተልሔም እንዘይ/2/

253.ሶበ ሰማዕነ

ሶበ ሰማዕነ ዜናከ መጽአነ ኀቤከ/2/
መጽአነ/4/
አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ
የምስራች ቃሉ በአንቺ ቤት ተሰማ
ወልድም ተሰጠን ሕፃን ተወለደ
አስጨናቂው ዘመን በእርሱ ተወገደ
ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ
የእግዚአብሔርን ክብር ለዓለም መሰከሩ
ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር ይሁን
ሰላም ለሰው ልጆች በምድር ላይ ይስፈን
እናትና ልጅ ፀሐይ ሳይነካቸው
የእግዚአብሔር መላእክት ከፊታቸው
ወድቀው
በከብቶች በረት አምላክ ተወለደ
የነገሥታት ንሥስ ሞትን አስወገደ
ድንቅ መካር ሀያል የሰላም አለቃ
ጌታ ሆይ በስምህ ግዛቱ አበቃ
ሰላምን የሚሰጥ አልፋና ዖሜጋ
የእስራኤል ንጉሥ ተገልጾአል በሥጋ

254.ተልኮ መቶ

ተልኮ መጥቶ /2/ ገብርኤል/2/
እንዲህ ብሎ አላት ለድንግል/4/
የማሕፀንሽ ፍሬ/2/ ኢየሱስ /2/
የተባረከ ነው ቅዱስ/4/

255.በክንፉ ጋረዷት

በክንፉ ጋረዷት/3/
ለድንግል ደስ ይበልሽ አላት/2/ ኸኸ/2/
ከጌታ ተልኮ ድንግልን ለማብሰር
ክንፋን እያማታ ምስራች ሲናገር
ድምጹን እያሰማ እስከ ሊባኖስ
በፍጥነት ወረደ መልእክት ለማድረስ
ሀሩን ከወርቅ ጋር አስማምታ ስትፈትል
ከፊቷ በመስገድ እንዲህ አላት ለድንግል
ደስታ ይገባሻል ከሰው ተለይተሽ
አምላክን ለመውለድ ስለተመረጥሽ
ድንግልም መልሳ አለችው ለገብርኤል
ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል
መሬትም ያለዘር ማፍራት እንደማትችል
እንዴትስ አምኜ የአንተን ቃል ልቀበል

መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት ለድንግል
መንፈስ ቅዱስም በአንቺ ላይ ይመጣል
የልዑል ሀይልም ይጸልልሻል
የእግዚአብሔር አብ ልጅ ከአንቺ ይወለዳል
ለእግዚአብሔር አይሳነውም
ቃሌን ተቀበይ ጽኚ በምስጋና

256.ርእይኩዋ

ርእይኩዋ ለቤተክርስቲያን አፍቀርኩዋ
ለቤተክርስቲያን/2/
ዘኢትዮጵያ/2/ ቤተክርስቲያን/2/
ትርጉም፡- አየዋት ቤተክርስቲያንን

ወደድኳት ቤተክርስቲያን /2/

የኢትዮጵያን /2/ ቤተክርስቲያን /2/

**257. በፍሥሐ ወበሰላም**

በፍሥሐ ወበሰላም /2/

ውሰተ ምጥማቃት /3/ ወረደ ወልድ

**258.ተነሱ እዘምር**

ተነሡ እንዘምር እልል እንበል/2/

በመልአኩ በገብርኤል ቃል/2/

ተወልዶልናል ተጠምቆልናል /2/

እስይ እሰይ የዓለም ቤዛ አማኑኤል /2/

**259. ሖረ ኢየሱስ**

ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ/2/

ከመ ያጥምቆ /2/ ፈለገ ዮርዳኖስ /2/

**260. በመንፈስ የሐውር**

በመንፈስ የሐውር እምኃይል ውስተ ኃይል/2/

ካህን ካህን ወነብይ/2 ዮሐንስ መጥምቅ /2/

ትርጉም፡- ካህንና ነቢይ የሆነ ዮሐንስ

መጥምቅ ከኃይል ወደ ኃይል

በመንፈስ ይሸጋገራል

**261.ኑኑ እንደሰት**

ኑ ኑ እንደሰት/2/

ጌታ ተጠመቀ/4/ ተጠመቀ በማየ ዮርዳኖስ/2/

**262.ኢየሩሳሌም**

ኢየሩሳሌም/3/ በሆን ጌታ ሲወለድ ባየን

እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሰሎሜ በሆን/2/

እንድ አረኞች ወይ ሰብአ ሰገልን በሆን/2/

**263.ዮም ፍሥሐ**

ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ/2/

እም ቅድስት ድንግል/2/ ውእቱ ኢየሱስ

ክርስቶስ/2/

**264.ተወልደ**

ተወልደ ኢየሱስ በቤተልሔም/2/ ዘይሁዳ

በቤተልሔም/2/

አዋልደ ጢሮስ አሜሃ ይሰግዳ/2/በቤተልሔም/2/

**265.ቤዛ ኩሉ**

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ/2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ/2/

**266.ወነዋ ተወልደ**

ወነዋ ተወልደ መድኃኔዓለም/2/

ፍሥሐ ለኩሉ ዘየአምን/2/

ወነዋ ተጠምወ መድኃኔዓለም/2/

ፍስሥ ለኩሉ ዘየአምን/2/

**ትርጉም-**

ዛሬ ተወለደ የዓለም መድኀኒት/2/

ደስታ ነውና ለሚያምኑት/2/

ዛሬ ተጠመቀ የዓለም መድኀኒት/2/

ደስታ ነውና ለሚያምኑት/2/

**267.ለዘ ተወልደ**

ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ምንተ ንብሎ

ናስተማስሎ ለመድኃኒነ/2/

አርዌ ገዳምነ አንበሳ ወሚመ /2/ ከራድዮን/2/

**268.ቤዛ ኩሉ**

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተጠምቀ/2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተጠምቀ/2

**269.በዛሬው ጥምቀቱ**

በዛሬው ጥምቀቱ እሰይ እሰይ

ተነግሮ አዋጅ እሰይ እሰይ

ነጻነት አገኘን እሰይ እሰይ

በእግዚአብሔር አብ ልጅ እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ ተተመቀ/2/

ከሰማየ ሰማይ ወረደ/2/

በቅዱስ ዮሐንስ ተጠመቀ

አብም መሰከረ  እሰይ እሰይ

ቃሉን አላበየም እሰይ እሰይ

የምወደው ልጄ እሰይ እሰይ

ይሄ ነው እያለ እሰይ እሰይ

አዝ------------

ጌታ በዮሐንስ እሰይ እሰይ
ሊጠመቅ ሲል ገና እሰይ እሰይ
ወደ ኋላ ሸሸ እሰይ እሰይ
ዮርዳኖስ ፈራና እሰይ እሰይ

አዝ------------

ዘለሉ ተራሮች እሰይ እሰይ
እንደ ጊደር ሁሉ እሰይ እሰይ
እፁብ ነው ድንቅ ነው እሰይ እሰይ
ምን ይገርም እያሉ እሰይ እሰይ

አዝ------------

ውኃን ወይን አረገ እሰይ እሰይ
በተጠራበት ቤት እሰይ እሰይ
የብርሃናት ጌታ እሰይ እሰይ
የዓለም መድኃኒት እሰይ እሰይ

አዝ------------

**270. በቤተልሔም ተወልደ**

በቤተልሔም ተወልደ አማኑኤል/2/
እም ዘርዓ ዳዊት/3/ ተወልደ አማኑኤል/2/

**271.ይቤላ መልአክ**

ይቤላ መልአክ ለማርያም/2/
ትወልዲ ወልደ ንጉሥ በቤተልሔም
ይቤላ መልአክ ከጌታ ተልኮ

ይቤላ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል
ይቤላ መልአክ ሰላምታ አቅርቦላት
ይቤላ መልአክ ለማርያም ድንግል
ይቤላ መልአክ ትወልጃለሽ አላት
ይቤላ መልአክ ቀዳሚውን ቃል

ይቤላ መልአክ ማኅደረ መለኮት
ይቤላ መልአክ ማርያም ውድስት
ይቤላ መልአክ የሕዝብ ሁሉ እናት
ይቤላ መልአክ እኅተ መላእክት
ይቤላ መልአክ እሙ ለብርሃን
ይቤላ መልአክ ደብተራ ፍጽምት

አዝ--------------

ይቤላ መልአክ ወገበዋቲሃኒ
ይቤላ መልአክ ሐመልማለ ወርቅ
ይቤላ መልአክ ትብርሂ እምፀሐይ
ይቤላ መልአክ ኆኀተ ምሥራቅ
ይቤላ መልአክ ሰላም ለኪ ድንግል
ይቤላ መልአክ በአልባሰ ወርቅ

አዝ--------------

ይቤላ መልአክ ወላዲተ አምላክ
ይቤላ መልአክ ማርያም ንጽሕት
ይቤላ መልአክ ወትትሌአሊ እምአድባር
ይቤላ መልአክ ስብሕት ወቡርክት
ይቤላ መልአክ ኦ ምልእተ ጸጋ
ይቤላ መልአክ እግዚአብሔር ምስሌኪ
ይቤላ መልአክ ቡርክት አንቲ እምአንስት
ይቤላ መልአክ ድንግል በኅሊናኪ

አዝ----------------

**272.ሃሌ ሃሌ ሉያ**

ሃሌ ሃሌ ሉያ /2/
በሰማይ በምድር ምሕረት ሆኗልና
ሃሌ ሃሌ ሉያ አሜን ሃሌ ሉያ

መላእክት ዘመሩ አመሰገኑት
እየተደነቁ በአምላክ ቸርነት/2/
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት አሉ
እረኞችም አብረው እሱን አከበሩ/2/

አዝ -----------

ዓለምን ለመፍጠር ከተጠበበበት
ይበልጣል ከሁሉም እኛን ያዳነበት /2/
ከዳግማዊት ሔዋን ከእመቤታችን
በረቂቅ ጥበቡ ተወልዶ አዳነን/2/

አዝ --------------

ሁላችሁም ሂዱ ከቤተልሔም

ታገኙታላችሁ በከብቶች ግርግም
ኢየሱስ ክርስቶስ ወሀቤ ሰላም
ሞታችንን ወስዶ ሕይወትን ሰጠን/2/
አዝ ----------

ወልደ እግዚአብሔር መጣ ከላይ ከሰማይ
ፍቅር አወረደው ከመንበሩ ላይ /2/
አልተጸየፈውም መሆን ከግርግም
ትኅትናው ደነቀኝ የመድኃኔዓለም /2/
አዝ ------

**273.በቤተልሔም ተወለደ**

በቤተልሔም ተወለደ /2/ አማኑኤል /2/
እምዘርዓ ዳዊት /4/ ተወልደ አማኑኤል/2/

**274.የምስራች ተወለደ**

የምስራች ተወለደ እሰይ እሰይ  /2/
የዓለም ቤዛ /2/ የዓለም መድኅን /2/
ተወለደ ከድንግል ማርያም/2/

**275.ወአንተኒ**

ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል /4/
አርኮ ለመርዓዊ ትሰመይ/2/ ነቢየ ልዑል

**276.በወንጌሉ ያመናችሁ**

በወንጌሉ ያመናችሁ/2/
እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ/4/

**277.ልዑል እግዚአብሔር**

ልዑል እግዚአብሔር /2/ ምስጋና ይገባሃል/2/
ለጥምቀት በዓል/2/ በሰላም በጤና አደረስከን/2/

**278.ኢየሱስ ክርስቶስ**

ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል ይጠብቀናል/2/
በጥምቀቱ ልጅነት ሰጥቶናል/4/

**279.እግዚኦ መርሐ**

እግዚኡ መርሐ ዮርዳኖስ አብፅሀ/2/
ወበህየ ዮሐንስ ወበህየ ፍጹመ ተፈሥሐ/2/
**ትርጉም፡-** ጌታውን መራና ዮርዳኖስ አደረሰው/2/
በዚህም  ዮሐንስ በዚህም በፍጹም ደስ አለው /2/

**280.ወነዋ ተወልደ**

ወነዋ ተወልደ መድኃኔዓለም /2/
ፍሥሐ ለኩሉ ዘየአምን /4/
**ትርጉም፡-** ዛሬ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/2/
ደስታ ነውና ለሚያምኑት/4/

**281.ውእቱ ኢየሱስ**

ውእቱ ኢየሱስ/3/ እምቅድስት ድንግል/2/
በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ ዮም ፍሥሐ ኮነ
በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ

**282.መጽዓ ወልድ**

ሃሌሉያ መጽዓ ወልድ ውስተ ዓለም ሃሌሉያ ውስተ/2/
ወለብሰ ሥጋነ ስብአ ኮነ በአርዓያ ዚአነ/2/

**283.ኸኸ ኀዲጎ**

ኸኸ ኀዲጎ ተሰአ ኸኸ ወተሰዓተ ነገድ/2/
ኸኸ ማዕከለ ባሕር ቆመ ማዕከለ ባሕር/2/

**284.ዮሐንስ አጥምቆ**

ዮሐንስ አጥምቆ ለኢየሱስ /2/
በፈለገ ዮርዳኖስ በፈለገ ፈለገ ዮርዳኖስ/2/

**285.ቤተክርስቲያን**

ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት/2/
አትመረመርም /2/ እጅግ ጥልቅ ናት/2/
በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ
የእምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመጣ
ሰው ሁሉ በስህተት/2/ ፈጣሪውን አጣ/2/
እንመስክራለን ፈጣሪያችን አለ
እንመስክራለን አማኑኤል አለ /2/
እንመነው አንካደው አማኑኤል ቸር ነው/2/
እንመስክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመስክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የአምላክ እናት ናት/2/
ኀበ ጥበባት ኀበ ልሳናት/4/
ዮሐንስ /2/ ወንጌለ ስብከት/2/

**286.መንክረ ግርማ**

መንክረ ግርማ ኃይለ ልዑል ጸላላ/2/

አማን አማን መላእክት ይኬልልዋ/2/

ሸሽ በሚያስደንቅ ግርማ

የልዑል ኃይል የጋረዳት/2/

በእውነት /2/ መላእክት አመሰገኗት/2/

**287.በቃና ዘገሊላ**

በቃና ዘገሊላ /2/

ዘገሊላ ክብካብ ኮነ /4/

**288.ዘበዳዊት**

ዘበዳዊት ተነበየ/2/

በቃና ዘገሊላ /2/ ክብካብ ኮነ /4/

**289.አንክርዎ**

አንክርዎ ለማይ አእኵትዎ ለኢየሱስ /4/

በእንተ ማይ ዘኮነ ወይን/4/

**290.ለክብረ ቅዱሳን**

ለክብረ ቅዱሳን ወለቤዛ ብዙኃን

ተወለደ ተጠመቀ እም ድንግል

በኃል ሰበከ ቤዛ ኩሉ ዓለም

**291.ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ/2/**

ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ/2/

ይኩነነ ቤዛ /4/ ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ/2/

**292.ግነዩ ለእግዚአብሔር**

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር/2/

አዝ--------------

እናመስግናሽ የአምላክ እናት በዝማሬ /2/

የዓለም ቤዛ ነውና የማኅፀንሽ ፍሬ/4/

አዝ -----------

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ /2/

መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ /4/

አዝ -----------

በድንግልና የወለድሽው ክርስቶስ/2/

የድኩማኖች ብርታት ነው የሕሙማን ፈውስ/4/

አዝ ------------

በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችንን ፋቀ/2/

በቸርነቱ ጠብቆ ከበደል አራቀን/4/

አዝ -------------

ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም የዘከረ/2/

ቅድስት ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ/2/

አዝ ----

እመቤታችን እናታችን ማርያም/2/

የተማጸነሽ ይድናል ለዘለዓለም/4/

አዝ ----

ድንልናሽ ሳይለወጥ ወልድን የወለድሽ

የጌታችን እናት ማርያም ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ

የጌታችን እናት ማርያም ንጽሕት ሆይ አንቺ ነሽ

ድንግልናሽ ሳይለወጥ ወልድን የወለድሽ /፪/

የጌታችን እናት ማርያም ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ

የጌታችን እናት ማርያም ንጽሕት ሆይ አንቺ ነሽ

**293.ተአምረ**

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ/2/

በቃና ዘገሊላ ዘገሊላ ክብካብ ኮነ/2/

**294.በኃል በኃል**

በኃል በኃል ሰብአ ሰገል /2/

በኃል ሰብአ ሰገል ሰገዱ ሎቱ/4/

ድንግል ማርያም ንጽሕት ቅድስት/2/

የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል/2/

ከሴቶች ሁሉ በአንቺ አድሮብሻል /2/

ፀሐይ/3/ ሠረቀ ፀሐይ /2/ ሠረቀ/2/

ፀሐይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠመቀ/4/

በኃል በኃል አማኑኤል /2/

እግዚአብሔር ፍቅሩን ሲገልጽልን

አንድያ ልጁን ለእኛ ሰጠን/2/

አዝ --------------

ሥጋንም ነስቶ ከእናታችን/2/

ኃጢአታችንን ሊያስወግድልን

ክርስቶስ ጌታችን ተጠመቀልን /2/
አዝ---------
እልል እልል ደስ ይበለን /2/(2)
መድኅን ተወልዶ ነጻ ወጣን
ዮሐንስ አጥምቆ ድል አገኘን/2/
አዝ -----------
አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ/2/(2)
የእግዚአብሔር መንፈስ ከለይ ወርዶብሽ
የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ /2/

**295.ዮሐንስ አጥምቆ**

ዮሐንስ አጥመቆ ለኢየሱስ /2/
በፈለገ ዮርዳኖስ በፈለገ ፈለገ ዮርዳኖስ /2/

**296.እኅትየ መራት**

እኅትየ መርዓት ቅድስት/2/
እም ዘመዶሙ ለካህናት/4/

**297.እኅትየ ይብልዋ**

እኅትየ ይብልዋ መላእክት በክብር /2/
ለማርያም ድንግል/4/

**298.እርሱ ባይወለድ**

እርሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ
ቸር አባታችን እሰይ እሰይ
እርሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ
መድኃኒታችን እሰይ እሰይ
መች ትገኝ ነበረ እሰይ እሰይ
ገነት ምድራችን እሰይ እሰይ
አዝ ------
እሰይ እሰይ ተወለደ/2/
ከሰማያት ሰማይ ወረደ/2/
ከድንግል ማርያም ተወለደ/2/
አዝ -----------
እንደጠል ወረደ እሰይ እሰይ
ከሰማይ ወደእኛ እሰይ እሰይ
ወገኖቹን ሊያድን እሰይ እሰይ
ከኃጢአት ቁራኛ እሰይ እሰይ
አዝ --------------
እሰይ እሰይ
ብርሃን ወጣላቸው እሰይ እሰይ
ለእምነት ወገኖቹ እሰይ እሰይ
በጨለማ ጉዞ እሰይ እሰይ
እንዲያ ሲሰላቹ እሰይ እሰይ
እሰይ እሰይ ------------
እግዚአብሔር አብ ላከ እሰይ እሰይ
አንድያ ልጁን እሰይ እሰይ
እርሱ ወድዷልና እሰይ እሰይ
እንዲሁ ዓለሙን እሰይ እሰይ
እሰይ እሰይ --------------

**299.የጥበብ ሰዎች መጡ**

ሰማይና ምድር የማይወስኑትን
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ
አዝ ------------
የጥበብ ሰዎች መጡ/2/ ሰምተውት በዜና /2/
እያበራላቸው ኮከብ እንደፋና /2/
አዝ -----
ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ
ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርሰን
አዝ --------------------
ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ሐዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት
አዝ --------------------
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ

የእስራኤል ንጉሥ ወደ የት አለ እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ
እጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ
አዝ ---------------------

300.አብሠራ

አብሠራ ገብርኤል ሊቀመላእክት /2/
ኸኸ ወይቤላ /5/ ትወልዲ ወልድ/2/

301.ማርያም

ማርያም/3/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ/2/
ባንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ /2/
አዝ -------------
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
አዝ --------------------
ድንግል ተቀምጣ በቤተ መቅደስ
ሐር ወር አስማምታ ስትፈትል ንግሥት
አዝ ------------------
ገብርኤል /2/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋ በመልበስ
አዝ ---------------
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርስዋ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ
አዝ --------
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

302.ከነቢያት ሀገር

ከነቢያት ሀገር ኢየሩሳሌም
ከቅድስት አውራጃ በቤተልሔም
በጎል ተወለደ/2/ መድኃኔዓለም/2/
አዝ-----
ለእኛ ቤዛ ሊሆን በበደልነው ፈንታ
ዛሬ ተወለደ ይገባል እልልታ/2/
አዝ ---------------------
የነግሥታት ንጉሥ የነዳያን ሕይወት
ተጠቅልሎ ተኛ በጎለ እንስሳ
አዝ ---------------------
ትኅትናን ሊያስተምር በሕፃንነት
በከብቶች ማደሪያ ተኛ በበረት
አዝ ---------------------
ግዑዛን የሆኑ የማይናገሩ
እስትንፋሳቸውን እንስሳት ገበሩ

303.ተወለደ

ተወለደ አምላክ ተወለደ
አዝ --------
አንዲት ብላቴና የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ
ጌታን ወለደችው በመላእክት አዋጅ
በኀቱም ድንግልና ተወለደ ጌታ
ዓለምን የሚድን የሰዎች አለኝታ
አዝ-------------
ይህ ዓለም በቃሉ ከተፈጠረበት
ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነበት
እንደምን ይገርማል ይሄ ተዋሕዶ
አየነው አምላክን ከድንግል ተወልዶ
አዝ ----------------
ፍጹም ድንግልና ክብርን የተመላሽ
እንደምን አምላክን በማሕፀን ያዝሽ
ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ጌታ
ወለደችው ድንግል የሔዋን አለኝታ
አዝ --------------------
አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም
በምድር ተፈልጎ እንደአንቺ አልተገኘም
በሐሰብ በግብር ንጹሕ ስለሆነች
ለአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች

304.እምሰማያት

እምሰማያት ወረደ ወእምማርያም ተወልደ/2/2/
ከመይኩን ቤዛ/2/ ለኩሉ ዓለም/2/ ለብሰ/2/

ሥጋ ማርያም

<u>የአስተርእዮ መዝሙር</u>

305.እንበይ ነዝ አእምሩ

እንበይ ነዝ አእምሩ በውስተ ፍትሕ

ከመ ኢያደሉ/2/

አመ ወእመ ኩሉ ጥጥዓም ሞት አዘዘ

ወልድ በርቱዕ ቃሉ/2/

ትርጉም፡- በፍርድ እንደማያዳላ እወቁ

የእርሱ እናትና የሁሉ እናት ሞትን

ያድናል ኪዳን ምሕረት/2/

306 ጊዜ እረፍታ

ጊዜ እረፍታ ለድንግል ለማርያም/2/

በልዕልና ወረደ እግዚአብሔር

በልዕልና ወረደ እግዚአብሔር /2/

ሞትሰ

ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ/2/

ሞታ ለማርያም የአጽብ ለኩሉ/4/

ትርጉም፡-ሞትማ ለሚሞተው ሰው ይገባዋል

የማርያም ሞት ግን /2/

በጣም ያስገርማል/2/

307.ተናገራ ዕዝራ

ተናገራ ዕዝራ ተናገራ ዳዊት ዘመራ/2/

ተናገራ ዕዝራ በመሠንቆ ዳዊት ዘመራ/2/

ተናገራ እያጫወታት ዳዊት ዘመራ

ተናገራ ሳታውቀው አለፈ ዳዊት ዘመራ

ተናገራ ያ መልአከ ሞት ዳዊት ዘመራ

ተናገራ ዕዝራ ተናጋራ ዳዊት ዘመራ/2/

ተናገራ ውኖች ቀለም ሆነው ዳዊት ዘመራ

ተናገራ እንጨቶች ብዕር ዳዊት ዘመራ

ተናገራ ዕዝራ ተናገራ ዳዊት ዘመራ/2/

ተናገራ ቢጽፉት አያልቅም ዳዊት ዘመራ

ተናገራ የማርያምን ክብር ዳዊት ዘመራ

308.ዘድንግል መናስግት

ዘድንግል መናስግት ኢያሪሆ/2/

ኢያሪሆ ዘኪሩቤል ኢርዕዮ

ኢያሪሆ ኢርዕዮ ዘኪሩብ/2/

309.ድንግል ወላዲተ ቃል

ድንግል /2/ ወላዲተ ቃል/2/

አሟሟትሽ በጥር ነሐሴ መቃብር ድንግል

የአንቺስ ለብቻ ነው ትንሣኤሽ ሲነገር ድንግል

ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ እንደ ፍጡር

አርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር

አዝ --------

ሥጋሽን ሲያሳርጉ መላእክት በሰማይ

ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ ድንግል

መግነዝ ተቀበለ ለሐዋርያት ሊያሳይ ድንግል

አዝ ----------

ትንሣኤሽን ሽተው ግራ ሲገባቸው ድንግል

ሐዋርያት ጾመው ተገለጥልሻላቸው ድንግል

ተቀብራ አልቀረችው በምድር ከደጇ ድንግል

ወደላይ አረገች እሷም እንደልጇ ድንግል

አዝ -------

ለማየት ሲጓጉ የድንግልን ትንሣኤ ድንግል

እርገቷን አወቁ በብዙ ሱባኤ ድንግል

እኛም እንጸልይ ደጃችን እንዝጋ ድንግል

ከወላዲተ አምላክ እንድናገኝ ዋጋ ድንግል

310.እስመ እምዘርዓ ዳዊት

እስመ እምዘርዓ ዳዊት ዘመጽአ /2/

በቤተልሔም ዘይሁዳ/4/

311.ክርስቶስ ተወለደ

ክርስቶስ ተወለደ ወተጠምቀ/2/

አስትርእዮቱ አማን አስተርእዮቱ/4/

312.አስተርዕዮ

አስተርእዮ /2/ በሰማይ ኮነ /2/

አስተርእዮ/ 2/ በሰማይ ኮነ/4/

313.ጊዜ ረፍታ

ጊዜ ዕረፍታ ለድንግል ማርያም/2/

በልዕልና ወረደ /4/እግዚአብሔር

<u>የዘመነ መርዓዊ መዝሙር</u>

<u>315. መጽአ ዘመጽአ</u>

መጽአ ዘመጽአ እምላዕሉ/2/

መርዓዊ መጽአ /2/ተቀበሎ ጻኡ ተቀበሎ/2/

316. ደስ አላት ቤ/ክ

ደስ አላት ቤ/ክ በጣም ደስ አላት /2/

ሙሽሪት ሙሽራው ልጆቿ/2/

በተክሊል በቁርባን ተዋሐዱላት /2/

<u>317. ህገ ስብእናሁ</u>

ሕገ ስብዕናሁ ዐቀበ /2/በተደንግሎ/2/

በወንጌል ዘሀሎ/2/ወፈጸመ በወንጌል ዘሀሎ/2/

<u>318. መርዓዊ ሰማያዊ</u>

መርዓዊ ሰማያዊ /2/ ለእመ ገብረ በዓለ/2/

ይኑሩ በሰላም /3/ ጸንተው ዘለዓለም/2/

ደናግል ተነሡ ያዙ መብራቱን

ሙሽሪው ደረሰ አጉል እንዳንሆን

አዝ. . . . . . .

ወንጌልን ይዘዋል ጐዳናቸው ያምራል ዓላማው

መልካም ነው እነ እርሱን እንምሰል

አዝ .. . . . . .

የድካም ዋጋቸው /2/

ብርሃኑ ያበራል ለተከታያቸው

አዝ . . . . . .

የሙሽራው ሕይወት መልካም እንዲሆን

ካህኑ ይባርኳት ቡርክት ሰው ትሁን

አዝ . . . . . .

<u>319. ይደሰት ሙሽራው</u>

ይደሰት ሙሽራው በሥርዓተ ተክሊል ሲያገባ /2/

አሸበረቀ የመቀ አጌጠ ሙሽራው አበባ/2/

በሥጋ ወደሙ ፍጹም እንዳዘዘው ወንጌሉ እኽ

በሙሽሪት ነው ያማረው /2/ሥርዓተ ተክሊሉ/2/

<u>320. ካህናት ተንሥኡ</u>

ካህናት ተንሥኡ/2/ለተናብቦ /2/

አንዘ ይብሎ ንሴብሖ/2/እንዘ ይብሎ ንሴብሖ/2/

<u>321. አድርገህልኛልና</u>

አድርገህልኛልና በቸርነትህ

አመሰግንሃለሁ እልል እልል

ለዓለመ ዓለም አማኑኤል

እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም/2/

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ

የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ

ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ

ፈጽሞ አራቅክልኝ የልቤን ትካዜ

አዝ . . . . . . .

አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ

ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ

እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ

ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ

አዝ . . . . . . .

ጥቂትዋን አብዝተህ የምትመግብ ጌታ

የምመልስልህ ባላገኝ ሥጦታ

በቀንም በሌትም ሁሌ ለሚያበራ

መንክር ለባሕርይ ዕፁብ ለአንተ ሥራ

አዝ . . . . . .

አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል

ለምስኪንዋ ጉጆ በረከት ሰጥተሃል

ድሀ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና

ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጐድል እንደገና

<u>322. ድንቅ ነው በጣም</u>

ድንቅ ነው በጣም ድንቅ ነው /2/

በሠርጋችሁ ዕለት ተገኘ መድኃኔዓለም

በሠርጋችሁ ዕለት ተገኘች ድንግል ማርያም

በቃልህ ተመርተው ለዚህ ቀን በቅተዋል
በፊትህ ጋብቻን ይኸው ፈጽመዋል
በፈሰሰው ደምህ ኅብረት መስርተዋል
በሥጋም በነፍስም /2/የአንተ ነን ብለዋል
አዝ . . . . . .
ከአዳም አንድ አጥንት ከጐኑ ወስደህ
አጋር እንድትሆነው ሔዋንን ሰጠህ
ሁለቱንም ባርከህ እንደፈጠርካቸው
ዛሬም ለሙሽሮች/2/ ሰላምን ስጣቸው
አዝ . . . . . .
ጌታ ሆይ በሕግህ በቃልህ መሠረት
አንድ ሆነዋልና በዚህ ቅዱስ ዕለት
እርሱንም እሷንም ባርከህ ቀድሳቸው
ዘለዓለማዊ ፍቅር /2/ ጽናትን ስጣቸው
አዝ . . . . . .
የዲያቢሎስ ተንኮል እንዳያስታቸው
እስከ መጨረሻው ጋሻ ሁንላቸው
ከቅድስቲቷ ቤት ሁለቱም ሳይርቁ
ጽናቱን ስጣቸው /2/ አብረው እንዲዘልቁ

323. እግዚአብሔር ፈቅዶ

እግዚአብሔር ፈቅዶ ዛሬ አንድ ሆነናል
እህቴ ሆይ ስሚ ማን ይለያየናል
ሥጋሽ ከሥጋዬ አጥንትሽ ከአጥንቴ
ተዋሕዶአልና ሆነሻል ሕይወቴ/2/
በእመብርሃን ምልጃ በጌታ ቸርነት
በቃልህ ከታመንኩ በዚህ ቅዱስ ዕለት
የአጥንትህ ክፋይ አካልህ ነኝና
ጌታዬ ልበልህ ክብሬ አንተ ነህና/2/
አንቺም ተጠበቂ ከዲያብሎስ ሴራ
ሰውነትሽ ዘወትር በጐ ምግባር ይሥራ
ቅድስና ወደሽ ከኃጢአት ራቂ
የሃይማኖትሽን ክር ማዕተብሽን አጥብቂ/2/
ከቃልህ አልወጣም ጌታዬ ሆይ ስማኝ
እስከመጨረሻው ፍጹም ታዛዥህ ነኝ
በቤተክርስቲያን ጥላ ስር በመሆን
በቃሉ እመራለሁ አንብቤ ወንጌልን/2/
እግዚአብሔር ሆይ ስማን ቃልኪዳናችንን
ጋብቻችንን ባርክ ቀድስ ጐጆአችንን
ከዲያብሎስ ሴራ ጠብቀህ እኛን
እስከመጨረሻው በቃልህ አጽናን/2/

324. ደስ ይበለን

ወንድና ሴት አድርጐ እንደፈጠራቸው
ኋላም ለኑሮአቸው ጋብቻን ሰጣቸው
አንዴ ከተጋቡ አንድ ሥጋ ናቸው
ከእንግዲህ ወደፊት ይጸናል ፍቅራቸው
ደስ ይበለን ሙሽሪት ሙሽራው/2/
አንድ አካል ሆነዋል አምላክ አጣምሮአቸው
በምንም ምክንያት ማንም አይለያቸው
በጣም ይወዳታል ባል ክብርት ሚስቱን
ስለ እርስዋ አሳልፎ ይሰጣል ነፍሱን
አዝ . . . . . .
ለአብርሃም ለሣራ እንደሰጠ ትዳር
ለእናንተም ይለግስ የዘለዓለም ፍቅር
ኣንቺም እንደሣራ አንተም እንደ አብርሃም
ተፋቅራችሁ ኑሩ እስከ ዘለዓለም
አዝ . . . . . .
ለዚህ ላበቃችሁ ለቸሩ አምላካችን
ምስጋና ይድረሰው ዛሬ ከሁላችን
በሉ ደኅና ግቡ ወደ አዲስ ጐጆአችሁ
አምላክ በጥበቡ ፍቅርን ያላብሳችሁ
አዝ . . . . . ..

325. ቃና ዘገሊላ

ቃና ዘገሊላ/2/በዚያ በሠርግ ቤት
ተገኝተሻል ድንግል ከልጅሽ ጋራ
ተገኝተሃል ጌታ ከእናትህ ጋራ
እድምተኞች ሞልተው የጋበዙት

ሲበሉ ሲጠጡ ወይኑ አልቆበት
ድንግል እናታችን ቤዛዊት ዓለም
አንቺ ደረስሽለት ሆነሽው አማላጅ
አዝ. . . . . .
አንተ እያለህስ ማፈር የለባቸው
ሁሉ ይቻልሃል ወይኑን ሙላላቸው
ማድጋው ባዶ ነው ብለሽ የተናገርሽ
ጌታን ያሳሰብሽው እመቤታችን ነሽ
አዝ . . . . .
የጌታ አምላክነት የተገለጸበት
ምንኛ ታደለ የእነዶኪማስ ቤት
ዛሬም ይኸው በዚህ በሠርገኞቹ ቤት
በረከት ፈሠሠ በአምላክ ቸርነት
አዝ . . . .. . . .
ውኃው ተለውጦ የወይን ጠጅ ሲሆን
በቃና ገሊላ ሁላችን አየን
እግዚአብሔር ከኖረ በመካከላችን
ሁሉ ይሰጠናል ይህን መሰል ወይን

326. አጅቡት በዕልልታ

አጅቡት በዕልልታ ሲመጣ ሙሽራው
ፍጹም የሚያስደስት የሠርጉ ዕለት ነው
ዘመዶቹ ሁሉ ተቀበሉት ውጡ
የሙሽራው መምጫ አሁን ነው ሰዓቱ
ዕልል /2/ እንዘምር በዕልልታ
ይህን ላደረገ ለሠራዊት ጌታ
ሁሉንም በጊዜው ይፈጽማልና
ይኸው አበቃቸው ለዚህ መልካም ዜና
ሙሽሪት ተደሰች ዝምታው ምንድነው
የዳግም ልደትሽ የሠርግሽ ዕለት ነው
አዳም ጉንሽ ቆሞ ሔዋን ሆይ ሲልሽ
መንፈሳዊ ሐሴት ይሙላ በልብሽ
አዝ . . . . .
እህት ወንድሞቿ እናትና አባቷ
ተነሡ ዘምሩ ለልጃችሁ ደስታ
መሄጃ ነውና ወደ ቤቷ ዛሬ
ወደ አዲስ ጐጆዋ ሸኙአት በዝማሬ
አዝቤተሰቦችሽን ሁሉንም ትተሽ
መሄድሽ ነውና ወደ መኖሪያሽ
ከአማኑኤል ጋራ ባልሽን ይዘሽ
ተነሽ ሙሽራዬ ደርሰዋል ሰዓትሽ
ከድንግልም ጋራ ሚስትህን ይዘህ
ተነሥ ወንድሜ ሆይ ደርስዋል ሰዓትህ
አዝ. . . . . . . .

327. ሙሽራዬ

ሙሽራዬ/3/ አበባዬ
ከጐንህ የምትሆን እህት አገኘህ
የኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለህ
የእግዚአብሔር ፈቃዱ ለዚህ ካበቃችሁ
ቤታችሁ ይመረቅ በፍቅር ያጽናችሁ
አዝ . . . . .
ወንድም አግተሻል የሚያስብልሽ
የእኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለሽ
እግዚአብሔር ይመስገን እኛም ደስ ብሎናል
በቤተክርስቲያን ሠርጋችሁ ውብ ሆኖአል
አዝ . . . . .
እንደነፍስህ አርገህ እንድትወዳት
አደራ ሰጠንህ በጌታችን ፊት
እንድታስቢለት አንቺም ለአካልሽ
አደራ ትላለች ወንጌል እናትሽ
አዝ . . . . .
በሥጋው ወደሙ ሕይወት አግኝታችሁ
ፍሬአችሁም ይብዛ ይባረክ ጎዳችሁ
አምላክ ያለበት ነው ይሄ ጋብቻችሁ
እስከ መጨረሻው ኑሩ ደስ ብሎአችሁ
አዝ . . . . . .

328. በሠርጋችን ዕለት

በሠርጋችን ዕለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንሃል በእምነት ሆነን
ከእናትህ ጋራ ከእመቤታችን
ከመላእክትህ ጋር ና በሠርጋችን
ከሐዋርያት ጋር ና በሠርጋችን
ከወዳጆችህ ጋር ና በሠርጋችን
በገሊላ መንደር እንደተገኘህ
ና በእኛ ድንኳንም ጌታ ሰንጠራህ
የጥሪ ወረቀት ልከናል እንዳትቀር
አንተነህ ክብራችን የቤታችን ፍቅር
ነይ ከልጅሽ ጋራ እመቤታችን
እንድታሟይልን የጎደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶው እንዲሞላ
በረከት የእርሱ ነው ቤታችንን ይሙላ
አዝ. . . . .
በጐደለው ሁሉ እየጨመርሽልን
ቤታችንን ሁሉ ሙይው እናታችን
ለአገልጋዬቹም ድንግል ንግሪአቸው
ጠርተን እንዳናፍር ጋኖቹን ይሙላቸው
አዝ . . . . .

## 329. ደመቀ አበራልን

ደመቀ አበራልን የአማኑኤል ሥራ/2/
ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ
በቤተክርስቲያን ጥላ ተከልለው
ተክሊል አድርገዋል ሙሽሪት ሙሽራው
ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ስለተሰጣቸው
ሙሽሪት ሙሽራው አበራ ገፃቸው
አዝ . . . . .
የተራራቀ አካል አንድ ሆነ በተክሊል
እግዚአብሔር ይመስገን እልል/2/ እንበል
አጥንትሽ ከአጥንቴ ሥጋሽ ከሥጋዬ
አዳም የሰበከው ይኸው ዛሬ ታዬ
አዝ .. . . . . . .
የተክሊሊ ብርሃኗ በእኛ መሀል በርቶ
ረቂቅ አንድነት ታየ በእርስዋ ጐልቶ
ይህን ድንቅ ነገር ለማየት ያበቃን
ምሥጢሩን የሚገልጽ እግዚአብሔር ይመስገን
አዝ . . . . . .
ነጭ መጐናጸፊያ በአንድ ተጐናጽፈው
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አረፈ በጥላው
ሙሽሪት ሙሽራው ለፍቅር ተሸነፉ
ለቁርባን መቁረቢያ ነጭ ልብስ አሰፉ
አዝ. . . . . . .

## 330. መርዓዊ ስቡህ

መርዓዊ ስቡሕ ዘለዓለም/2/
ወእስከ ለዓለም /2/ ንጉሥ ውእቱ /2/
በገሊላ አውራጃ ከሠርግ ቤት ገብቶ/2/
ጋብቻን ባርኮታል ቀድሶ አዘጋጅቶ/2/
አዳምን ብቻውን አትኑር ሲለው
ከጐኑ በመፍጠር ሔዋንን ሰጠው/2/
በግላዊ ኑሮ የትም ከመኮብለል
በአንድ አካል አንድ አምሳል ጋብቻ ይሻላል/2/

## 331. ዳዊት ይሴብሕ

ዳዊት ይሴብሕ ወይዜምር ዕዝራ/2/
እንዘይብሉ ሙሽሪት ሙሽራ/2/

## 332. መጽአ መርዓዊ

መጽአ መርዓዊ ፍሥሐ ለኩሉ/2/
በሰላም ጻኡ ተቀበሉ/2/
ትርጉም፣መጣ ሙሽራው ደስታ ለሁሉ/2/
በሰላም ውጡ ተቀበሉ/2/

## 333. ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ

ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ/2/
በእግዚአብሔር በሕያው ቃሉ
ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ /2/
አዝ ……………………

ወንድና ሴት አድርጐ እንደፈጠራቸው
በኋላም በቃሉ አንድ አደረጋቸው
እናትና አባቱን የአዳም ልጅ ይተዋል
ከሚስቱ ጋር በሰላም በአንድ ይተባበራል
አዝ . . . . .
ሁለቱም አንድ ሥጋ ሆነው ይኖራሉ
ብሎ አስተምሮናል ጌታችን በቃሉ
አንድ ሥጋ ናቸው አይደሉም ሁለት
የባልና የሚስት ሕይወት ወደፊት
አዝ. . . . . .
እንግዲህ እግዚአብሔር ካጣመራችሁ
በሆነው ባልሆነው ሰው አይለያችሁ
ለወገኖቻችሁ ምሣሌ ሆናችሁ
በክርስትና ፍቅር አምላክ ያኑራችሁ
አዝ. . . . .
ምንጣፋችሁ ብሩህ መኝታችሁ ንጹህ
ስለሆነላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ
ዓለም እንዲደነቅ ሰይጣን እንዲያፍር
በሐዘን በደስታ ይኑራችሁ ፍቅር
አዝ. . . . .

334. ደስ አለው ጌታ

ደስ አለው ጌታ በሙሽሮች ደስ አለው ጌታ/2/
በቅዱስ ቁርባን ተወስነው ደስ አለው ጌታ/2/
ደስ አላት ድንግል በሙሽሮች ደስ አላት ድንግል
/2/
በቅዱስ ቁርባን ተወስነው ደስ አላት ድንግል /2/

335. መጽዓ መርዓዊ

መጽዓ መርዓዊ ፍሥሐ ለኩሉ/2/
በሰላም ጻኡ ተቀበሉ/2/
አንድ ያደረገውን ጌታችን በቃሉ/2/
ሊለየው አየችልም የሰው ልጅ በኃይሉ/2/
ሙሽሪት ሙሽራው የሃይማኖት ፍሬ/2/
በቅዱስ ጋብቻ አንድ ሆኑ ዛሬ /2/
እህት ወንድሞቿ ክርስቲያኖች ሁሉ/2/
ሙሽሪት ሙሽራን ሁላችሁ ምሰሉ
በሥጋ ወደሙ ደግም በተክሊሉ/2/
የወንጌልን ትዕዛዝ በመፈጸማቸው/2/
የብርሃንን ተክሊሊ ደፍተው አየናቸው/2/
በመንፈሳዊ ፍቅር በመተባበር/2/
እንግዲህ ጀምሩ መልካሙን ትዳር/2/

336. የምሥራች ደስ ይበላችሁ

የምሥራች ደስ ይበላችሁ/2/
አሸብርቆ ዋለ ሙሽሮች ሠርጋችሁ/2/
ሕይወታችሁ ሰላማዊ ፍጹም ፍቅር/2/
እንደ ጽጌረዳ እንደአደይ ፈክቶ የሚኖር
አማኑኤል ያድርገው መልካም ትሥሥር
አዝ. . . . . . .
መተሳሰብ መከባበር ይሁን ግብራችሁ/2/
ሠርጐ እንዳይገባ ዲያብሎስ በትዳራችሁ
በጾም ጸሎት ይታጠር ሙሽሮች ጐጆአችሁ
አዝ. . . . .
ዓይኖቻችሁ የጐረቤት አይመልከቱ/2/
ለወሬ ለሐሜት ጆሮአችሁ አይከፈቱ
በችግር በደስታ በጾም ጸሎት በርቱ
አዝ. . . . . .
እግሮቻችሁ ይገስግሱ ወደእውነት/2/
አማናዊ ማዕድ ክርስቶስ ወዳለበት
በልባችሁ አኑሩት ታላቁን አባት
አዝ. . . . . . .
ድንግል ማርያም ቅድስት እናት ለምኚላቸው/2/
የሚፈልጉትን በሙሉ አንቺ አስጪያቸው
በሰማይ በምድርም ምልጃሽ አይራቃቸው

337. ኢያቄም ወሐና

ኢያቄም ወሐና/4/
ሙሽሮቹ ያብባሉ ገና/2/

338. ደስ አላቸው

ደስ አላቸው ሙሽራው ሙሽሪት/2/

እግዚአብሔር ስላባረካቸው/2/

ደስ አላቸው የልባቸው ምክር

.. የብቻቸው ምሥጢር

.. ዛሬ ተፈጽሟል

.. በቤተክርስቲያን

.. እርሱ በፈቀደ

.. አገናኝቷቸዋል

ደስ አላቸው ቅዳሴው ሲቀደስ

.. ዝማሬው ሲዘመር

.. ሲባረኩ በአምላክ

.. ለዚህ ክብር በቅተው

.. ተክሊል ሲቀዳጁ

.. ቁርባን ተቀብለው

ደስ አላቸው ከዝሙት ጠብቆ

.. ከዓለም ፈተና

.. ወደቤቱ ጠርቶ

.. ለቅዱስ ጋብቻ

.. ስለመረጣቸው

.. የወንጌልንም ቃል

.. በመፈጸማቸው

338. ትዌድሶ መርዓት

ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ/2/

ወልድ እንየ ቃልከ አዳም/4/

340.ሙሽሮች አበበ ፍሬያችሁ

ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ/2/

ለዚህ ቀን ይኸው ደረሳችሁ

በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ/2/

በእግዚአብሔር ቸርነት በመልካም ፈቃዱ

በቅዱስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሐዱ/2/

በሥርዓተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ

በመድኃኔዓለም ፊት ጋብቻን ፈጸሙ/2/

አዝ. . . . . . .

በቤተክርስቲያን በፈጣሪያቸው ፊት

ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚህች ቅድስት ዕለት/2/

አንድ የሚያደርጋቸው ተነቦ ወንጌሉ

በካህኑ መስቀል በረከት ታደሉ/2/

አዝ. . . . .

በወንጌል ትዕዛዝ በሐዋርያት ቃል

በእመብርሃን ፊት ጋብቻቸው ሰምሮአል/2/

በአምላክ ሥጋና ደም ሁለቱም ታተሙ

የኅብረት ቃልኪዳን በአንድ ላይ አሰሙ/2/

አዝ . . . . . . .

ጸንቶ የሚያዘልቃቸው የማይለያያቸው

ክቡር ቃል ስላለ በመካከላቸው/2/

እስከመጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል

የአማኑኤል ሥጋ አስተሳስሮአቸዋል/2/

አዝ. . . . . . .

341 የማኑ ተሐቀፈኒ

የማኑ ተሐቅፈኒ ወጸጋሙ ታኅተ ርእስየ/2/

ትብሎ መርዓት ትብሎ/4/መርዓት ለመርዓዊሃ

342 በምድራዊ ህይወት

በምድራዊ ሕይወት

በምድራዊ ሕይወት/2/በፈተና ቦታ/2/

ድንግል ትጠብቀህ እጆቿን ዘርግታ

ማርያም ትጠብቅሽ እጆቿን ዘርግታ/2/

343 በክብር ዙፋኑ

በክብር ዙፋኑ መርጦ ያስቀመጠሽ

ለእኛ ለኃጢአተኞች ተስፋችን አንቺው ነሽ

በፍጹም ንጽሕና ቤተመቅደስ ያደግሽ

የአማኑኤል የጌታዬ የፈጣሪ እናት በምን እንመስልሽ/2/

ቃና ዘገሊላ ሠርግ ደግሰው

አንቺን ከነልጅሽ በክብር ጠርተው

ሰዎች ተረብሸው በጣም ተደናግጠው

ወይኑ በማለቁ በፍርሃት ተውጠው

አዝ. . . . . .

ወይኑ በመሃል ላይ ማለቁን ሰምተሽ

ድንጋጤአቸውን እመበቴ አይተሽ

ወደ ልጅሽ ሄደሽ ብትጠይቂላቸው

ጋኑን ውኃ ሙሉት ብሎ አዘዛቸው

አዝ. . . . .

ውኃውን ወደወይን አጣፍጦ ቀይሮ

የዶኪማስንም እፍረቱን ሰውሮ

እድምተኞች ሁሉ እስከሚደነቁ

አምላክ ከእነእርሱ ጋር መሆኑን አወቁ

አዝ. . . . . .

344 በቃና ዘገሊላ ቁ.1

በቃና ዘገሊላ/2/

ዘገሊላ ከብካብ ኮነ/2/

345 በቃና ዘገሊላ ቁ.2

በቃና ዘገሊላ ማየ ወይነ ረሰየ /2/

መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ/2/

346. ኑ ተመልከቱልኝ

ኑ ተመልከቱልኝ የአማኑኤልን ሥራ/2/

ኑ ተመልከቱልኝ የእመቤቴን ሥራ

ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ/2/

ሐናና ኢያቄም በጸሎት ሲተጉ

በፈጣሪያቸው መልካሙን ቢያደርጉ

በቅዱስ ጋብቻ ጸንተው ቢራመዱ

የአምላክን እናት ድንግልን ወለዱ/2/

አዝ. . . . . .

ቀን ከሌት ሲጸልይ ዘካርያስ ካህን

ኤልሣቤጥም ተግታ ፈጣሪን ብትለምን

በእግዚአብሔር ጥበብ በስተእርጅናቸው

ቅዱስ ዩሐንስን አክብሮ ሠጣቸው/2/

አዝ. . . . . .

ጸጋ ዘአብና ቅድስት እግዚእ ኀረያ

ለመልካም ጋብቻ ሆነዋል አርዓያ

ተክለሃይማኖትን ጻድቁን ያፈሩት

ቀን ከሌት ተግተው ነው በጾምና ጸሎት/2/

አዝ. . . . . .

347. ሥላሴ ይባርኳችሁ

ሥላሴ ይባርኳችሁ /2/

በሥጋ ወደሙ ዛሬ የከበራችሁ/2/

ሥላሴ ይባርኳችሁ/2/

እመአምላክ ትከተልህ/4/

ፈተና እንዳይገጥምህ ድንግል ትከተልህ

እመአምላክ ትከተልህ

ሚካኤል በኑሮአችሁ/2/

አርምሞ ማስተዋል ትዕግስቱን ይስጣችሁ

ሚካኤል በኑሮአችሁ

ገብርኤል ከላይ ወርዶ/4/

እርሱ ይራዳችሁ በክንፎቹ ጋርዶ

ገብርኤል ከላይ ወርዶ

ዑራኤል በምልጃው/4/

የእውቀተን ጥበብ ይስጥህ/ሽ/ በጽዋው

ዑራኤል በምልጃው

ጊዮርጊስ አይለያችሁ/4/

በፈተና ጊዜ ጽናት ያሳያችሁ

ጊዮርጊስ አይለያችሁ

አዝ.. . . . .

348. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

የኢትዮጰያ ኦርቶዶከስ ተዋሕዶ

ቤተከርስቲያን ልጆች ናቸው

እንቀበላቸው ሙሽሮች ናቸው

እንቀበላቸው

አዝ... . . . . . . .

ይኸውና በድንግልና

ፈጸሙ በሥጋ ወደሙ

ለዚህ እድል ተዘጋጁ

የክብር አክሊል ተቀዳጁ

አዝ. . . . .

እልል በሉ ሚዜዎቹ

አብሮ አድጉ ጓደኞቹ

እልል በሉ ሚዜዎቿ

አብሮ አደጓ ጓደኞቿ

## 349 ያስደስታል

ያስደስታል/2/ የእኛ እምነታችን

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የጋብቻ ሥርዓታችን/2/

ተፈጸመ/2/ ዛሬ ሠርጋችሁ

ምስጋና ይግባው እንላለን /2/

ቸሩ አምላካችንን

## 350. ንፅህት ድንግል

ንጽህት ድንግል ብርክት

የአምላክ እናት እመቤት

ልጆችሽ ሙሽሮች ሁለቱም አንድ ሆነ

ተዋሀዱ ተጣመሩ በቅዱስ ቁርባኑ/2/

ፍጹም መንፈሳዊ ልዩ ፍቅር

አንቺ ያለሽበት መልካም ትዳር

መሠረቱ ዛሬ ልጆችሽ

ቅድስት ሆይ ባርኪያቸው ተገኝተሽ

አዝ. . . . .

ድንግል ጉጆአቸውን ቀድሰሽ

እውነተኛ ፍቅር መሥርተሽ

በመካከላቸው ተገኝተሽ

ሁሉን አሰጪያቸው አማልደሽ

አዝ.. . . . . .

ሙሽሮቹም አምነው በምልጃሽ

እናታችን ባርኪን ነይ ሲሉሽ

ፈጥነሽ ድረሺና በሠርጋቸው

ነይ ተመላለሽ መሀላቸው

አዝ. . . . . . .

አንቺን ለሚወዱሽ ለሚያምኑሽ

የሕይወት አጣፋጭ ቅመም ነሽ

ሙሽሮቹም ዛሬ ይጠሩሻል

የጉጆአችን ፋና ነይ ይሉሻል

አዝ. . . . . .

ቃና ዘገሊላ ተገኝተሽ

መልካሙን ጋብቻ የባረክሽ

ዛሬም ከልጆሽ ጋር በሠርጋቸው

ነይ ተመላለሽ መሃላቸው

አዝ. . . . . . . .

## 351. ወእመ አኮ

ወእመ አኮ ከመ ወሬዛ ኃየል/2/

ትዌድሶ መርዓት እንዘ ትብል/4/

## 352. ንሴብሆ

ንሴብሖ /2/ ለአምላከ ዕዝራ

እርሱን ለፈጠረ እርሷንም ለሠራ

ንሴብሖ ለአምላከ እዝራ

## 353. እልል እልል

እልል እልል ደስ ይበለን/2/

አጅበን መጣን ሙሽሮቹን/2/

እልል ብላችሁ ተቀበሉን/2/

## 354. እልል እልል

እልል እልል ደስ ይበለን/2/

አጅበን መጣን ሙሽሮቹን /2/

እልል ብላችሁ ተቀበሉን /2/

እናንተ ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ/2/

የአብርሃም የሣራ ይሁን ጋብቻችሁ/2/

መልካም መተሣሳብ ክርስቶስ ይስጣችሁ/2/

ሣራና አብርሃም ሁሉም የሚያውቋቸው/2/

ሁለቱም ቅዱሳን ናቸው/2/

ፍቅራቸውን አይቶ አምላክ ባረካቸው/2/

ለእናት ለአባት ታዛዥ ግሩም ልጅ ሠጣቸው/2/

ለጌታ መሥዋዕት እኔ ልቅረብ ያለው/2/

ይስሐቅን ለአብርሃም የሠጠው/2/

በመልካም ጋብቻ በጥሩ ትዳር ነው/2/
ቅዱስ አባታችን ፈጣሪያችን ሆይ
ጌታችን አምላካችን ሆይ
በአብርሃም ጎጆ እንደገባህበት 2
በሙሽሮቹም ቤት በረከት ሙላበት
በቃናዋ መንደር የጠራኽ ሠርገኛ/2/
አምላክ ተገኝልህ ሆነህ እድላኛ /2/
በቃናዋ መንደር የጠራሽ ሠርገኛ/2
ድንግል ጎበኘችሽ ሆነሽ እድለኛ
ማርያም .. .. ..

## 355. ይትባረክ

ይትባረክ እንደአብርሃም/2/
እኸ ዘለዓለም/4/ይትባረክ እንደአብርሃም/2/
ሙሽሪት ሙሽራው እንደአብርሃም
እንኳን ደስ አላችሁ ..
ተከበረ ዛሬ ..
ቅዱስ ጋብቻችሁ ..
አዝ. . . . .
በተክሊለ በቁርባን ..
ስለተጋባችሁ ..
እጅጉን ደስ አለው ..
ቅዱስ አባታችሁ ..
አዝ.. . . . .
በሥርዓተ ተክሊል ..
ከተጣመራችሁ ..
ደስታ ሰላም ይሙላ ..
ይመር ትዳራችሁ ..
አዝ. . . . .
እልል በሉላቸው ..
ዛሬነው ሠርጋቸው ..
የተመረጡበት ..
መልካም ጋብቻቸው ..
አዝ.. . . . .

አንቺም እንደሣራ . .
እርሱም እንደአብርሃም ..
ተፈቅራችሁ ኑሩ
እስከ ዘላዓለም
አዝ. . . . . .
በሉ ደህና ግቡ
ወደአዲስ ጐጆአችሁ ..
አምላክ በጥበቡ ..
ፍቅርን ያላብሣችሁ
አዝ. . . . . .

## 356. የሐብከ ዩም

የሀብከ ዮም የሀብከ መድኃኔዓለም
ዕድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም/2/
ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኔዓለም
ዕድሜ የማቱሳላን የአብርሃም
በቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች ተወስናችሁ
ክርስቶስ ተገኝቷል በመሃከላችሁ
የድንጋዮቹን ጋን ወይኑን/2/ሊሞላበት/2/
ከድንግል ማርያም ጋር ተገኝቷል ከዚህ ቤት
አዝ. . . . . . . .
ደስታውን አይቶ አምላክ ፍጹም ተደስቷል
ሊባርካችሁ እጆቹን ዘርግቷል/2/ በሕይወታችሁም
ፍቅር/2/ቅመም ሆኖ/2/
ትኅትናን ይስጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ/2/
አዝ. . . . .
ሠርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር የሞላበት
በሕይወታችሁ ውስጥ ክርስቶስ ይግባባት
በሕይወታችሁ ውስጥ አምላክ ይኑርበት
አዝ.. . .
የበረከት ፍሬ ጸጋው እንዲበዛላችሁ/2/
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ/2/
እራስን በመግዛት ዕውቀት/2/ተሞልታችሁ/2/
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ/2/

አዝ. . . . . . .

በሥጋ ወደሙ እግዚአብሔር

ስለመረጣችሁ/2/

የመንፈስ ቅዱስም ሕፃናቶች ናችሁ/2/

357. እፁብ ድንቅ ስራ

እጹብ ድንቅ ስራ/2/

በእውነት የታደለ የእግዚአብሔር ሙሽራ

በእውነት የታደለች የእግዚአብሔር ሙሽራ

አዝ... . . . .

ነፍሳችሁ በሰማይ ርግብ ትመስላለች

ከመላእክት ጋራ ዛሬ ዘምራለች/2/

እልል/2/ በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ

ያበራ ጀመረ ሙሽራው ፀዳሉ

ታበራ ጀመረ ሙሽሪት ፀዳሏ

ከክርስቶስ ፍቅር እንዴት ይርቃል ሰው

ሥጋና ደሙን ሳይሳሳ ለሰጠው/2/

የመንፈስ ቅዱስ ሕፃናት በመሆን

በሥጋ ወደሙ መቀደስ አለብን

በሥጋ ወደሙ መቀደስ አለብን

አዝ. . . . . .

በእግዚአብሔር ተባርኮ የመኖር ምስጢር

የዘላለም ሕይወት ይሠጣል ፍቅር/2/

ሥጋውን ፍሪዳ ደሙን መጠጥ አድርጎ

ሰጥቶናል አማኑኤል ሕይወቱን ሰውቶ/2/

358. ዘተመነያ

------እኑየ/2/ ዘተመነያ/2/

ዛቲ መራት/2/ እኅተ ነያ/2/

------ ያያት/2/ የተመኛት/2/

ይህቺ ሙሽራ/2/--------ናት

359. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር/2/

እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም/4/

እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ/2/

በሥጋ ወደሙ ልጆችሽ አንድ ሆነዋል ዛሬ/2/

በሥጋ ወደሙ በተክሊሉ የተሳሰረ/2/

በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ/4/

እመቤታችን እናታችን ማርያም/2/

ከእነርሱ አትለይ ሁልጊዜ ለዘለዓለም/4/

አዝ.. . . . . .

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመሔር/2/

እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስከለዓለም/4/

360. ደስ አላቸው

ደስ አላቸው ሙሽራው ሙሽሪት

በዝማሬ .. ..

ደምቆ ታይቷል .. ..

ጋብቻቸው .. ..

እግዚአብሔር ይመስገን ሙሽራው ሙሽሪት

ኃያሉ ጌታቸው .. ..

ለዚህ ላበቃቸው ሙሽራው ሙሽሪት

ወንድም እህታችንን .. ..

ጋብቻ ቅዱስ ነው .. ..

ብሏል አምላካችን .. ..

እንደዚህ ሲፈጸም በቤተክርስቲያን

አዝ. . . . .

መኖር የለበትም ሙሽራው ሙሽሪት

አዳም ብቻውን .. ..

ብሎ ፈጠረለት .. ..

ከጐኑ ሔዋንን .. ..

ዛሬም እንደቀድሞው .. ..

እንደ መጽሐፉ .. ..

መርጦ እህት ሰጠው ለአዳም ሙሽራው

አዝ... . . . . .

ሔዋን ጐኑ ሆና ሙሽራው ሙሽሪት

አዳም ሆይ ስትለው .. ..

በረዳትነቷ .. ..

አዳም ደስ ደስ አለው .. ..

በአምላክ መልካም ፈቃድ .. ..
በፍቅር ተሳስረው .. ..
አንድ አካል ሆነዋል ማንም አይለያቸው

361. ሙሽራዋ/4/ እጹብ ነው ደስታው ሙሽራው/2/

ሙሽራው/4/ እጹብ ነው ደስታው ሙሽራው
ሙሽራዋ/4/ እጹብነው ደስታዋ ሙሽራዋ/2/
አዝ. . . . . . .
እንደ አዳይ አበባ ሙሽሮች ፈክታችሁ
በለመለመ መስክ ያለ ፍሬ መስላችሁ
ልክ እንደ ጨረቃ እንደሰማይ ፀሐይ
መልካሙ ሥራችሁ በራ በአደባባይ
ካባዋን ደርባ በጥበቡ ላይ
የተዋሕዶ ልጅ ደምቃ ስትታይ
በቤተክርስቲያን ሥርዓት በማደን
ይኸው መሠከረ የሙሽሪት ሠርግ
መልካም ስነምግባር ፍቅር የከበበህ
የእመብርሃን ልጅ አቤት ማማርህ
ከመቼውም በላይ ዛሬ ተውበሃል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያህን ከቦሃል
መልካም ሥነምግባር ፍቅር የከበበሽ
የእመብርሃን ልጅ አቤት ማማርሽ
ከመቼውም በላይ ዛሬ ተውበሻል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያሽን ከቦሻል
የእመቤቴ ፀዳል ዙሪያሽን ከቦሻል

362. የቃናው ደስታ

የቃናው ደስታ ዛሬ ተደገመ
ጌታ ከእናቱ ጋር በሠርጉ ታዳመ
የዘላለም አምላክ ስላለ በዚህ ቤት
ሙሽራው መሽሪት አገኙ በረከት
መርዓት ተሸልማ የድንግልና አክሊል
እዩት ሥርዓቱን እጅግ ያስደስታል
አንድ አካል ሙሽሮች እዩአቸው ሲያበሩ
በወንጌሉ በተክሊሉ ሄዱ እየተመሩ
እንግዳቸው ብዙ ድንኳናቸው ሙሉ
ጌታ ከእናቱ ጋር አለ በመሃሉ
የወይን ጋኖቹ ዛሬ ሙሉ ናቸው
አማኑኤል ድንግል ማርያም ስላሉ ቤታቸው
በክብር ታጅቦ ሲመጣ መርዓዊ
እጅግ ያስደስታል አይደለም ምድራዊ
ዛሬም በዚህ ድንኳን ደስታ ተደረገ
በአማኑኤ በአምለካችን ስለተባረከ
በተክሊል በቁርባን የሆነው አንድነት
አይነጣጠልም ዳግም ወደ ሁለት
ሙሽሪት ሙሽራው ተደሰቱ ዛሬ
በሠርጋቸው ተገለጠ የእምነታችሁ ፍሬ

363. ሶበ ሠማይነ

ሶበ ሰማእነ ዜናከ መጻእነ ኀቤከ/2/
መጻእነ/4/
እንደ ሰብአ ሰገል ነገሥተ ምሥራቅ
ዝናህን ለመስማት መጣን ልንጠየቅ
አንደ ሰብአ ሰገል ነገሥተ ምሥራቅ
ዝናሽን ለመስማት መጣን ልንጣይቅሽ
ብቻህን ስላየህ ቢወድህ ፈጣሪ
ፈጠረልህ ለአንተ አጽናኝ አማካሪ
የወንጌልን ትዕዛዝ በመፈጸምህ
ለዚህ ክብር በቃህ በድንግልናህ
የወንጌልን ትዕዛዝ በመፈጸምሽ
ለዚህ ክብር በቃሽ በድንግልናሽ
አንቺ ቤተልሔም ቤተክርስቲያን
ሁለቱን አዋሐድሽ በቅዱስ ቁርባን

364. እንደ አብርሃም

እንደ አብርሃም እንደሣራ/2/
ሥላሴ ይኑሩ ከእናንተ ጋራ/2/
ቤታችሁ ይባረክ በረከት ይሙላ

ፈቅደው ይስጧችሁ ሰላምና ተድላ
ቤቱም የሥላሴ ይሁንላችሁ
ዘወትር ይኑሩ መሃከላችሁ
ጌታዬ በይው ውድሽ ነውና
እህቴ በላት ሥጋህ ናትና
ጽድቅ የተሞላ ፍሬ ይስጣችሁ
አብርሃም ሣራን ሁኑ ጸንታችሁ
ቤታችሁ ይከፈት ለእንግዳ ሰው
ከፍላችሁ ስጡ ለተራባው
መልካሙን ፍሮ አፍሩ ተግታችሁ
ስመ ሥላሴን እያሠባችሁ

365. ተፈሥሒ ቤተክርስቲያን

ተፈሥሒ ቤተክርስቲያን ተፈሥሒ ቤተ ሥላሴ
ያሳደግሻቸው ልጆችሽ አብርሃም ሣራን ሲሆኑልሽ
ያሳደግሻቸው ሙሽሮችሽ አብርሃም ሣራን
ሲሆኑልሽ
አዝ. . . . . . .
ትምህርትሽ ገብቶአቸው የወንጌሉ ቃል
በኑሮ ሊያበሩ ይኸው ወጥተዋል
በክርስቶስ ትምህርት በቃሉ ተመርተው
ለዓለም መሠከሩ ተራራ ላይ ቆመው
ተፈሥሒ
አዝ. . . . . . .
ከእንቅቡ በታች አይደለም መብራቱ
በራ እንጂ ለሁሉ ከእነበረከቱ
ጢስ የሌለው ሻማ ደምቀው የከበሩ
ልጆችሽ ሙሽሮች እንደጧፍ አበሩ። ተፈሰሒ
አዝ. . . . . .
ሰላም ላንቺ ይሁን ደስ ይበልሽ በጣም
የዘራሽው ማሳ ፍሬውን ሲሸከም
ካባ ደረብሽለት ለወንዱ ሙሽራ
አክሊል ደፋሽለት ከምርቃት ጋራ
ተፈሰሒ
አዝ. . . . . .
ቃልሽ ይለውጣል ግሩም ነው ኃያል
አመንዝራዎቹን ድንግል ያደርጋል
ተገለጠ ክብርሽ በሙሽሮች ዛሬ
መከር ሆኖልሻል ባፈራሽው ፍሬ ተፈሥሒ
አዝ. . . . . .
ሰላም ላንቺ ይሁን ደስ ይበልሽ በጣም
የዘራሽው ማሳ ፍሬውን ሲሸከም
ካባ ደረብሽለት ለወንዱ ሙሽራ
አክሊል ደፋሽለት ከምርቃት ጋር ተፈሥሒ
አዝ. . . . . .

366. አምሮ ሲያበራ

አምሮ ሲያበራ ኑ ተመልከቱ/2/
በእግዚአብሔር ክብር ሲሞላ ቤቱ/2/
ማነው የገባው በዚህ ጣሪያ ስር
ለሙሽሮቹ ደስታ ሊያበስር
ቤቱ ተሞላ ሰላም ፍስሐ
እናቅርብለት ምስጋና አምኃ
በአብርሃም ቤት የተገለጠው
በአላዘር ቤት እራት የበላው
ከእናቱ ጋራ ገባ ከእቤቱ
ቤተዘመዱ ኑ ተደሰቱ
የእኛ ሙሽራ ደስ ይበልህ
ታላቅ እንግዳ ገብቷል ከቤትህ
ሙሽራችን ሆይ ደስ ይበልሽ
የሰማይ ንግስት ጎባኝችሽ
ለእድምተኞቹ መልካም ወይን አለን
የቃናው ጌታ የጠመቀልን
አናፍርም እኛ እንግዳ ጠርተን
አምላክ ከኛ ጋር ስለሆነልን

367. እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ እሰይ/2/
በተዋሕዶ ምሥጢር ሠናይ

እሰይ እሰይ በአዳም ተጀምሮ
.. .. የአንድ አካል ምስጢር
.. .. በገነት ሲኖሩ
.. .. በጽድቅ ምድር
አካሌ ናት አላት ሔዋንን በፍቅር
እሰይ እሰይ መካን ሆነው ሣለ
.. .. ሐናና እያቄም
.. .. የጸናው አንድነት
.. .. አልተነጣጠለም
.. .. በእምነት ቢቆሙ
.. .. በጾም በጸሎት
ድንግል ተወለደች ልትሆን መድኃኒት
እሰይ እሰይ ዛሬም በሙሽሮች
.. .. ይህንን አይተናል
.. .. በቅዱስ ጋብቻ
.. .. በማይነጣጠል
ምሥጢር ተፈጸመ በሥርዓተ ተክሊል
አዝ. . . .
እሰይ እሰይ የተዋሕዶ ምስጢር
.. እጅግ የጠለቀ
.. በአመኑት ልቦና
.. ፈጽሞ ታወቀ
ዛሬም በሙሽሮች ክብር ተደነቀ

368. አሐዱ አካል

አሐዱ አካል----------/2/
ወመርዓቱ------------/2/
ዘአስተጻመረ /2/ እግዚአብሔር/2/

369. አዳም ሆይ

አዳም ሆይ እህት አገኘህ/2/
በሐሴት ይሙላ ልቡናህ ደስ ይበልህ
ሔዋን ሆይ ወንድም አገኘሽ/2/
በሐሴት ይሙላ ልቦናሽ ደስ ይበልሽ
ብቻህን መሆንህን እግዚአብሔር አይቶ
የከበደ እንቅልፍን በአንተ ላይ አምጥቶ
አጥንት ወሰደና አንዷን ከጎንህ
እህት እንድትሆንህ ሔዋንን ሰጠህ
ሄዋን ሆይ ……
ከጎኑ ተፈጥረሽ በሥላሴ ጥበብ
አክብሪው ባልሽን ተዋደዱ ከልብ
አዳም ከጎንሽ ነው የሚያስብልሽ
የአምላክን ስጦታ ውሰጅው ፈቅደሽ
አዳም ሆይ----------
አካልህ ሔዋን ናት የአንተ እጣ ፈንታ
አምላክ ባረካችሁ በብዙ ደስታ
የኑሮ ተካፋይ አምላክ ከሰጠህ
ሕይወቴ ነች ብለህ ሂድ ወደ ሚስትህ

370. ሙሽራው ደስ ይበልህ

ሙሽራው ደስ ይበልህ/2/
ፈቃዱ ሆኖ ጌታህ
እጹብ በረከት ሰጠህ
ሙሽሪት ደስ ይበልሽ/2/
ፈቃዱ ሆኖ ጌታሽ
እጹብ በረከት ሰጠሽ
ሁለት አይደለም ቃላቸው
ዘወትር አንድ ነው ድምጻቸው
የኑሮን ሕይወት እንዲገፉ
በአንድነት ሆነው ተሰለፉ
ምድራዊ አይደል ሰማያዊ
የማይመረመር ምሥጢራዊ
በሥጋ ወደሙ አንድ ሆነው
ሙሽሪትና ሙሽራው
ሁለት አይደለም ኑሮአቸው
ከእንግዲህ አንድ ነው ጎጆአቸው
መሠረት ጣሪያ ግድግዳው
እግዚአብሔር ነው ምሰሶው

371. ንሴብሖ ለሥላሴ

ንሴብሖ ለሥላሴ/2/
ክበር ተመስገን አምላከ ሙሴ/2/
የእኛ አማላጅ እናታችን/2/
ነይ ነይ ወደኛ እመቤታችን/2/
ፈጥነሽ ተገኚ በመሃላችን
ና ወደኛ ሚካኤል/2/
መልአከ ምክሩ ለልዑል
ከእግራችን ይውደቅ ሳጥናኤል
ና ወደኛ ገብርኤል/2/
ከእሳቱ አውጣን ከነበልባል
በክንፍህ ጥላ እንከለል
ና ወደኛ ዑራኤል/2/
እንደ ቅዱስ እዝራ ሱቱኤል
ጥበብን ስጠን ማስተዋል
ና ወደኛ በፈረስ/2/
የልደው ፀሐይ ጊዮርጊስ ገድልህን ሰምተን
እንፈወስ/2/
ና ወደኛ ተክለሃይማኖት/2/
ይጠብቀን ያንተ ጸሎት ጸንተን እንድንቆም
በሃይማኖት/2/

372. የቤታችን ራስ

የቤታችን ራስ ልጅሽ ነው
አማላጅነትሽ የሚያድነን ነው/2
እመብርሃን/2/ሰላም አንቺ እኮ ነሽ ለቤታችን/2/
ምን አለንና እኛ በጓዳችን
የጎደለ ነው ይኸው ማድጋችን
ነይ ከልጅሽ ጋር እንድትሞይልን
ድንግል እመቤታችን/2/
ያለን ውኃ ነው ከባዶ ጋን ጋራ
የጓሮውም ወይን ብዙም አላፈራ
የደሃ ጎጆአችን እንዲባረክልን
ድንግል አሳስቢልን/2/
በሠራኽታ ምድር ታምራት ያደረገ
በኤልያስ አድሮ ሕዝቡን የባረከ
ዛሬም እርሱ ነው የቤቱ ሰላም
አምላክ መድኃኔዓለም/2/
ጭንቀትን አይተሽ የልብን ሐዘን
ታሳስቢያለሽ እንዲኀበኝን
እኛም አንቺን ጠርተን ከእፍረት ድነናል
ድንግል ክብር ይገባሻል/2/

373. ቤታችን ይቀደስ

ቤታችን ይቀደስ በረከት ይሙላ/2/
ፍቅር አንድነትን አድለን ጌታ
ቤታችን ይቀደስ የማያልቅበት
.. .. ለሥጋ አምላክነህ
.. .. ገበናችንን
.. .. የምትሰውረው
.. .. በጎጆአችን ውስጥ
.. .. ሁሌ የምትኖረው
ቤታችን ይቀደስ ለጾም ለጸሎት
.. እንድንተጋ
.. ለሠናይ ምግባር
.. እንድንነሣ
.. ዘወትር ጧት ማታ
.. እንድናስብህ
.. በትዳራችን
.. ከእኛ አትለየን
ቤታችን ይቀደስ የምናመልከው
.. አንተን ብቻ ነው
.. ተስፋችን በአንተ
.. እጅግ ጽኑ ነው
.. ማን ይመስልሃል
.. በምድር በሰማይ
.. ወረት የሌለህ

..          ቅዱስ አምላክ ነህ

374. ደስይበለን

ደስይበለን ደስይበለን
አምላክ አለ መሀላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
እልልታ ነው በሰማያት
በሙሽሮች ብሩህ መብራት
በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክካችሁ
የክብር አክሊሊ ስለሰጣችሁ
የፍቅር ሕይወት ይሁንላችሁ
ምሣሌ ነው ዛሬ ሠርጋችሁ
የዓለም ደስታ ሳይማርካችሁ
በእግዚአብሔር ቤት ሆነ ሠርጋችሁ
ለዚህች ዕለት አደረሳችሁ
በአምላክ እቅፍ ሆነ ነፍሳችሁ
የዘለዓለም ሙሽሮች ናችሁ
ለመዳን ቀን የተጠራችሁ

375. በበጎ ፈቃዱ

በበጎ ፈቃዱ ሁሉ በእርሱ ሆነ/2/
ነገር ሁሉ በእርሱ ተከናወነ/2/
ሰማይና ምድር ክብሩን ተናገሩ
ፈጥሮአቸዋልና እንዲገለጥ ክብሩ
በፈጠረው ፍጥረት የሚታወቅ እርሱ
እግዚአብሔር ይመስገን ስሙን አወድሱ
አልሆነም ያለእርሱ ፍጹም አንዳች ነገር
ብንመረምረው በሰማይ በምድር
ፈቃዱ ነውና መልካምና በጎ
ፈጥሮ አሳይቶናል ሁሉን ውብ አድርጎ
ክረምትና በጋ ሌሊትና ቀን
ሁሉን አሳይቶ ጌታ አስተማረን
ያደረገው ሁሉ እንከን የሌለው
ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምሳሌም የለው
ያዘነውን ያውቃል ደስም ያለውን
ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ስለሚከወን
ችግርና ደስታ ለበጎ ነውና
ይህን ያስተማረን ይድረሰው ምስጋና

376. እልል በይ

እልል በይ/4/ ቤተክርስቲያን ሆይ እልል ባይ
እልል ባይ ቅድስት ቤተክርስቲያን
..          እጅግ ደስ ይበልሽ
..          ልጆችሽ ለተክሊል
..          ስለደረሱልሽ
..          በስርሽ ተምረው
..          በቃልሽ ታንጸው
..          ለዚህ ክብር በቁ
..          አበሩ ደመቁ
እልል በይ መልካሙን ቃልሽን
..          ሕይወት የሆነውን
..          አንድ ሰው ለአንድ ነው
..          ብለሽ ያዘዝሽውን
..          እነዚህ ሙሽሮች
..          በቤትሽ የኖሩ
..          የሃይማኖት ፍሬዎች
እልል በይ ከክፉ ጠብቀሽ
እልል በይ ሠላምን ስጪቸው
..          በትዳራቸው
..          ከህግ እንዳይወጡ
..          በዓለም ተስበው
..          ቤተክርስቲያን ሆይ
..          እንግዲህ ባርኪያቸው

377. ሙሽራው ከሙሽሪት ጋር

ሙሽራው ከሙሽሪት ጋር
በአደባባይ ደምቀው ታይተዋል
እልል በሉ ሚዜዎቹ /ሚዜዎቿ/
የደስታ ተካፋዩቹ/ተካፋዩቿ/

እስቲ ዘምሩለት ለሙሽራው .. ከወንድ የመራቂ
በአንድነት ሆናችሁ .. ተክሊል ተጭኖባት
ወደ አዲሱ ቤት ለሙሽራው .. የድንግልናዋ
መግባቱን አይታችሁ .. ኮራን በልጃችን
እስቲ ዘምሩላት ለሙሽሪት .. በአዲሷ ሙሽራ
በአንድነት ሆናችሁ
ረዳት አገኘች የእኛ ሙሽራ
ጥሩ ወንድምን
አዝ. . . . .
ሥነምግባር ላለው ለሙሽራው
የቀና ሃይማኖት
ደስታው ደስታችን ነው የሙሽራው
ክብሩም ክብራችን ነው
ሥነምግባር ላላት ለሙሽሪት
የቀና ሃይማኖት
አጅቧት በደስታ ሙሽሪትን
በሆታ በእልልታ
አዝ. . . . .
ስትበቁ ለክብር ለሙሽሮቹ
ለመልካም ትዳር
ጎጆ ስትቀልሱ ለሙሽሮቹ
በእግዚአብሔር ፈቃድ
አብነት ለመሆን የእኛ ሙሽሮች
ለጓደኞቻችሁ
ወልዳችሁ ለመክበድ የእኛ ሙሽሮች
እግዚአብሔር ይርዳችሁ

378. <u>የክብሯ መግለጫ</u>

የክብሯ መግለጫ የድንግልናዋ/2/
ይኸው ዛሬ ታየ በተክሊሉ ደምቃ
ይኸው ዛሬ ታየ ካባዋን ደርባ
የክብሯ መግለጫ ከሆኑት ነገሮች
.. ቅዱስ ጋብቻ ነው
የክብሯ መግለጫ ክብሯን መጠበቋ

የክብሯ መግለጫ ከእናት ከአባቷ ቤት
.. አሸብርቃ ወጣች
.. ረዳት ልትሆነው
.. ወደ ባሏ ሄደች
.. ዛሬስ በዓይናችን
.. ሁላችን አየነው
.. ቀድሞም ኩራታችን
.. ይህንን አውቀን ነው
አዝ. . . . . . .
.. በሥርዓት ማደጓን
.. ዓለም መሰከረ
.. አለል ዘለል ሳትል
.. መኖሯ ታወቀ
.. እንግዲህ ሙሽራው
.. ኩራ ደስ ይበልህ
.. ደግ ጨዋ መርጦ
.. እግዚአብሔር አደለህ

379. <u>ተነሥ ሙሽራዬ</u>

ተነሥ ሙሽራዬ አለብህ እንግዳ
እንደ ዶኪማስ ቤት ቤትህን አሠናዳ
ቸር አምላካችን ነው የዚህ ቤት እንግዳ
እመቤታችን ናት የዚህ ቤት እንግዳ
አምላክ አያዳላም ሁሉንም ይሰማል
ጥሪህን አክብሮ በቤትህ ይገባል
ምንም አትጨነቅ ሰላም ይሁን ልብህ
በእምነት አስተናግደው ይሙላና ሐሣብህ
የዓለም ፈጣሪ ጌታችን በቤትህ
ከእናቱ ጋር መገኘቱን አይተህ

በልብህ አኑረው ታላቅ ቸርነቱን
የፍቅሩን በረከት ድንቅ ተአምራቱን
በቤትህ የገባው አንተ የጠራኸው
አልፋና ያሜጋ ሁሉን አድራጊ ነው
ተአምራት ያደርጋል በእጆቹ ሥራ
መድኅን ክርስቶስ ከእናቱ ጋራ

380. ከመፅጌ
ከመ ጽጌ ሮማን ከመ ጽጌ/2/
ሙሽራዬ/2/-----------------
ሲሳዬ/2/

381. አንሶሰወ
አንሶሰወ ከመ ሰብእ እሙነ ኮነ/2/
ተቀበሉ መርዓዊ መድኃኒነ ወረደ/2/

382. የኢትዬጵያ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ልጆች ናቸው እንቀበላቸው ሙሽሮች ናቸው
እንዘምርላቸው
ይኸውና በድንግልና ፈጸሙ በሥጋ ወደሙ
ለዚህ እድል ተዘጋጁ
የክብር አክሊል ተቀዳጁ
አዝ. . . . . .
እልል በሉ ሚዜዎቹ አብሮ አደጉ ጓደኞቹ
እልል በሉ ሚዜዎቿ አብር አደጓ ጓደኞቿ

383. ትብሎ መርዓት
ትብሎ መርዓት ለመርዓዊሃ
አፈቅሮ /2 /እስከ አመፈቀደ
ትርጉም፡-
ሙሽሪት ሙሽራው እስከፈቀደ
ድረስ እወድሃለሁ ትለዋለች

384.አብርሂ
አብርሂ /2/ ወለተማርያም/2/
እንቁ ዘጳዝዮን ዘኀረየኪ ገብረሥላሴ/2/

385. አማእኩኪ
አማእኩኪ ቅድስት ቤተክርስቲያን
ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ/2/
ድምጸ እንዚራ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር/2/

386. ወአንቲኒ
ወአንቲኒ መርዓት እም ኀበኒ መጻእኪ
ወኀበኒ ተሐውሪ መድኃኒተ ኩኒ/2/
መርዓተ ሕጉ ለመርዓዊ ዐቢይ/4/

**የኪዳነምሕረት መዝሙር**

**387. አምላክ ለእኛ ብሎ**
አምላክ ለእኛ ብሎ ቃል ኪዳን የሰጣት /2/
የኃጥአን አማላጅ ድንግል ማርያም ናት /4/
እንደ አማለድሽው በላዔ ሰብእን /2/
እኛንም እባክሽ አደራ አማልጅን /4/
ምሕረት እንድናገኝ ከአምላካችን /2/
አማላጅ ሁኚልን እመቤታችን /4/
ከአንቺ በተገኘው በመልካሙ ፍሬ /2/
ዓለም ተቀድሷል ነጻ ወጥቷል ዛሬ /4/
ስምሽ ግርማ ያለው ኪዳነምሕረት /2/
የሰዎች አማላጅ የጌታዬ እናት /4/
ካህናት በክብሮ ሲያመሰግኑሽ /2/
እኛም በእልልታ እንዘምርልሽ /4/

**388.ኪዳንኪ ኮነ**
ኪዳንኪ ኮነ /3/ ኪዳነ ምሕረት /2/
ለኃጥአን ቤዛነ /2/ ኪዳንኪ ኮነ /4/
**ትርጉም፡-**

**389.ክነፈ ርግብ**
ሃሌ ሃሌ ሉያ ክነፈርግብ በብሩር ዘግቡር /2/
ወገበዋቲሃኒ ሐመልማለ ወርቅ በሐመልማለ ወርቅ /2/
**ትርጉም :-**

**390.አንቲ ምሥራቅ**
ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ወገበዋቲሃኒ ሐመልማለ
ወርቅ /2/
አንቲ ምሥራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ <u>አማን በአማን</u>
<u>(3) አ ይኃልቅ ኪዳንኪ ወላዲተ አምላክ /2/</u>

እንደ ርግብ ክንፍ በብርም እንደተሠራ ጎኖችሽም
የወርቅ ሐመልማል /2/
አንቺ ምሥራቅ ልጅሽም የጽድቅ ፀሐይ ነው
እውነት በእውነት (3) አያልቅም ቃል ኪዳንሽ
የአምላክ እናት /2/

**391.ሶበሰ ኪዳንኪ**

ሶበሰ ኪዳንኪ ምክንያተ ድኂን ኢሀሎ /2/
ፈለገ እሳት ወደይን እም አስጠመ ኵሎ
ፈለገ እሳት ወደይን ወደይን እም አስጠመ ኵሎ
/2/
**ትርጉም** :- የመዳን ምክንያት የሆነው ቃል
ኪዳንሽ ባይኖር ኖሮ የእሳት ማዕበል ሁሉን
ባሰጠመ ነበር

**392.አንቺ ነሽ ተስፋው**

አንቺ ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነምሕረት/2/
በተሰደደ ጊዜ ከገነት /2/

**393.መርሕ ዘገነት**

መርሕ ዘገነት መርሕ ዘገነት /2/
አንቺ ነሽ /2/ ኪዳነምሕረት
ቅድስት እመቤቴ የጌታዬ እናት
ሆነሽ የተገኘሽ ንጽሕት ቅድስት
አንቺ ነሽ . . .
የሲና ሐመልማል የሰው ልጅ ሕይወት
አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት
አንቺ ነሽ . . .
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት
በደኅና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት
አንቺ ነሽ . . .

**394.ተናዘዘብኪ**

ተናዘዘ ብኪ አኮኑ ኀሊና ቀዳማይ አብ /2/
ኪዳነምሕረት ማርያም ኪዳነምሕረት
ኪዳነምሕረት ማርያም ኪዳነአምላክ
**ትርጉም** :-

**395.ሰላም ለኪ**

ሰላም ሰላም ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ /2/
የሕይወት መሠረት ሰላም ለኪ
የፍጥረት አለኝታ ሰላም ለኪ
ድንግል አደራሽን ሰላም ለኪ
ሁኝልን መከታ ሰላም ለኪ
አዝ . . .
በላዔ ሰብእ ዳነ ሰላም ለኪ
ብዙ ነፍስ አጥፍቶ ሰላም ለኪ
የአንቺን ስም ለጠራ ሰላም ለኪ
ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ ሰላም ለኪ
አዝ . . .
ተማጽነንብሻል ሰላ ለኪ
በአማላጅነትሽ ሰላም ለኪ
ድንግል ሆይ አደራ ሰላም ለኪ
አማልጅን ከልጅሽ ሰላም ለኪ
አዝ . . .
እኛ ብንከተል ሰላም ለኪ
በጎ ምግባርን ሰላም ለኪ
በሰላም በጤና ሰላም ለኪ
እንኖራለን ሰላም ለኪ
አዝ . . .
የልቦናቸው በር ሰላም ለኪ
ለተዘጋባቸው ሰላምለኪ
እንዲያመሰግኑሽ ሰላምለኪ
ድንግል ሆይ እርጃቸው ሰላምለኪ

**396.አማን በአማን**

አማን በአማን (2) ኪዳንኪ /2/
ኪዳንኪ ኢየሐልቅ /4/
**ትርጉም**:-እውነት በእውነት/4/
አያልቅም ቃልኪዳንሽ/4/

**397. አማልጂን ከልጅሽ**

ማርያም /2/ ድንግል ማርያም /2/
አማልጅን ከልጅሽ /2/ ከመድኃኒዓለም /2/
ኃጢአተኞች ከኃጢአት እንፈውስ
በማርያም ድንግል /2/ ክብርን አገኘን
በማርያም ድንግል /2/ አክሊል አገኘን

398.አዳም ንባብኪ

አዳም ንባብኪ ርግብ ሠናይት/2/
በልባስ ወርቅ/2/ ንኢ/2/ ኪዳነምሕረት /2/
ትርጉም:- ነገርሽ (አነጋገርሽ) በጣም ጥሩ ነው።

ወርቅ ለብስሽ ነይ

399. እንበለ ምግባር

እንበለ በምግባር ባሕቱ እመ ኢይጸድቅ አነ/2/

ቦኑ ለከንቱ ኪዳኒኪ ኮነ ቦኑ ለከንቱ ኪዳነኪ ኮነ /2/

**ትርጉም፡-** *ያለበጎ ሥራ የምንጸድቅ መንግሥተ ሰማያትን የምንወርስ ካልሆነ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ቃል ኪዳን ኪዳንሽ ለከንቱ ነበርን*

400. ኪዳንኪ ኮነ

ኪዳነኪ ኮነ/4/

ለኃጥአን ተስፋነ/2/ ኪዳንኪ ኮነ/4/

**ትርጉም፡-** የምሕረት ኪዳን ያለሽ እመቤታችን ለኃጥአን ተስፋቸው ነሽ፡፡

401. አመ ወርኃ ነጊድ

አመ ወርኃ ነጊድ የኀልቅ ወይፀራህ ሴጥ/2/

በገጸ ፈጣሪ ቤዛ ይኩነኒ ኪዳንኪ

በገጸ ፈጣሪ ቤዛ ይኩነኒ ኪዳን/4/

**ትርጉም፡-** በእለተ ምፅአት ጊዜ ኪዳንሽ በፈጣሪ ፊት ቤዛ ይሁን፡፡

402. ነይ ነይ ማርያም

ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ የጻድቃን

እመቤት የመላእክት እህት/2/

ሁላችሁ እመኗት ከልብ አማላጅ ናትና በእውነት እናመስግናት እናወድሳት አማላጅ ኪዳነምሕረት/2/

403.ልቤን አነሳስቶ

ልቤን አነሣሥቶ ያመለክተኛል

የአምላክን እናት እመናት ይለኛል/2/

እመን /4/ የአምላክ እናት አዛኝቷን /2/

404. ዕርገታ

ዕርገታ ለማርያም ዕርገታ ውስተ ሰማያት

ወበዓታ ወበዓታ ውስተ ገነት /4/

ገነዝዋ ሐዋርያት/4/

ገነዝዋ /2/ በስብሐት/4/

405. ተበሃሉ

ተበሃሉ በሰማያት/2/ እለ ኪያኪ አፍለሱ/2/

ማርያምሰ እንተ በምድር ታንሶሱ

406. ዐረገች

ዐረገች በስብሐት ዐረገች በልልታ

በስብሐት በልልታ <u>ዐረገች</u>/2/ በዕልልታ/2/

ከሙታን ተነሥታ ዐረገች በዕልልታ/2/

<u>ዐረገች</u>/2/ በዕልልታ/2/

407. ማርያም ዐረገች

ማርያም ዐረገች /2/ ወደ ገነት

የሰማይ መላእክት በደስታ እያጀቧት

ዐረገች ወደ ገነት/2/

408. ጴጥሮስ

ጴጥሮስ ወጳውሎስ አጠኑ ሥጋሃ/2/

ለማርያም/2/ በማዕጠንተ ወርቅ

409. አእረግዋ

አእረግዋ መላእክት ውስተ ሰማያት/2/

አእረግዋ መላእክት ውስተ ሰማያት/4/

አሳረጓት መላእክት ወደ ሰማያት/2/

አሳረጓት መላእክት ወደ ሰማያት/4/

410. እኸ ማርያምሰ

እኸ ማርያምሰ እኸ እንተ በምድር/2/

እኸ በሰማያት ታንሶሶ በሰማያት/2/

411. ኦ ምርአግ

ኦ ምርአግ እምድር ውስተ ሰማይ /2/

ወብኪ ተሐደሰ ጊዮርጊስ ሰማዕት

412. ኦ ርኅርኂተ

ኦ ርኅርኂተ ሕሊና አፍቅሮተ ሰብእ ልማዳ

ለእለ ጌሰሙ/4/ <u>ትመስል</u>/2/ እንግዳ

<u>ኪዳነምህረት እመቤት</u>

ኪዳነምሕረት እመቤት

የዓለም ሁሉ መድኃኒት

ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕት
አንቺ ነሽ የአምላካችን እናት
ጌታ አንቺን መረጠሽ ልዩ አድርጎ
በሚያስደንቅ ምስጢሩ ተዋሕዶ
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ
ያለሕማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ
እናትነት ድንግልና አስተባብረሽ ይዘሻልና/2/
ድንግልም እናትም እመብርሃን ቅድስተ ቅዱሳን
እኛን አማልጅን /2/

413. **በጌቴ ሰማኔ**

በጌቴ ሰማኔ በአትክልቱ ቦታ /2/
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ/2/
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት /2/
በእኛ ላይ ደረሰ የዘለዓለም ሞት/2/
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ/2
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ (2)
ተጠማሁ/3/ ሲላቸው/2/
ኦምጣጤ አመጡለት በሃሞት ቀላቅለው/2/
ድንግል አልቻለችም ዕንባዋን ልትገታ/2/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ/2/
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው /2/
እንዲህ ሲል ጸለየ አባት ሆይ ማራቸው/2/
በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ (2)
በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ/2/

414. **የአብርሃም አማላክ**

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ /2/
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ/2/
የሐስት ምስክር አቁመው ከሰሱት /2/
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት/2/
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ/2/
ከሮማዊው መንግሥት እንዲኖር ተፋቅሮ/2/
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ /2/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ /2/
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ /2/
በችንካር ላይ ቆሙ ምንም ሳይሰለቹ /2/
የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ/2/
የሾክ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ /2/

415. **መስክረ ቀራንዮ (1)**

መስክረ ቀራንዮ መስክረ ጎልጎታ
›› ›› ›› ሊቶስጥራ
የተቀበለውን የአምላክን መከራ/2/
ሊሰቅሉት ሲወስዱት መስቀል አሸክመው
ስምዖን ቀሬናዊ ከመንገድ አገኘው(2)
ከድካሙ ብዛት ሳይሰሉት እንዳይሞት
ለቀሬናዊ ሰው ስሞዖን መስቀል አሸከሙት/2/
የአምላክን ትዕግሥት በማየት ተደንቆ
ጲላጦስ ጠየቀው እንዲፈታው አውቆ /2/
ጌታም መለሰለት ከላይ ካልተሰጠ
በእኔ ላይ ልትፈርድ አንዳች ኃይል የለህ/2/
ስቀለው እያሉ ባንድ ላይ ሲጮሁ
ጲላጦስ ጨነቀው የሚያደርገው ጠፋው/2/
ከደሙ ንጽሕ ነኝ በማለት ታጠበ
የጌታን ንግግር ቃሉንም አሰበ/2/
መከራ መስቀልህ ሲነገር ይጨንቃል ነፍስም
ትርዳለች ሥጋንም ይዳከማል/2/
ድካምህን ሁሉ ከንቱ እንዳላደርገው
በንስሓ እንባ ኃጢአቴን እጠበው /

416. **መስክረ ቀራንዮ /2/**

መስክረ ቀራንዮ ንገሪን ጎልጎታ
ካሳ እንደሆነልን እንዳዳነን ጌታ/2/
በአምላክነቱ ፈጥሮ ዓለማትን
ሥጋን መዋሐዱን ሰዎችን ለማዳን
ክብሩን ዝቅ አደርጎ በታላቅ ትኅትና
ለፍርድ ሲወስዱት ሊቀበል መከራ
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ
አይሁድ በየተራ ሲገርፉት ሲያዳፉት

እንዲታገሳቸው በፍጽም ቸርነት
ምንም  ሳያጠፋ በደል ሳይኖርበት
በመስቀል እንዲሞት ቅጣት ተፈርዶበት
ወደኋላ ታስሮ ተገርፎ ተመቶ
ያየውን መከራ የሾህ አክሊል ደፍቶ
የሞቱ ሙታንን ከመቃብር ጠርቶ
በራሱ ውርደት ክብሩን ለሰው ልጆች ሰጥቶ
በሕይወት እንድንኖር ዳግም እንዳንሞት
ትንሣኤን በመስበኩን በከበረች ሰንበት

## 417.አዘነች

አዘነች /2/ እናቱም ጨነቃት
እያየችው ልጇን በመስቀል ላይ ሰቅለውት
እዩት ተመልከቱት የአምላክን ሥራ
በመሰቀል ላይ ሆኖ ለዓለም ሲያበራ
አይሁድ ወንበዴዎች ይዘው አሰቃዩት
የሾህ አክሊል ሠርተው በላዩ ደፉበት
የድንግልን ሐዘን እጽዋት አይተው
ያለቅሱ ጀመረ ከመሬት ተደፍተው
መች እነሱ ብቻ ፀሐይም ጨለመች
የጌታዬን እርቃን እኔ አላይም አለች
የሰማይ ከዋክብት የአምላክን ሞት አይተው
ወየው/2/ አሉ ከመሬት ተደፍተው
በይበልጥ ጨረቃ እርር ክስል አለች
ይህንን ስትሰማ መልኳን አጠቆረች
ምድርም አዝና ነበር በጣም ተቸግራ
ሲገርፉት እያየች ጀርባወን በወይራ
ወየው መጨከኑ የሰው ልጅ ተፈጥሮ
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ
ማርና ወተትን የሚመግብ ጌታ
አጥቶ ተቸገረ የውኃ ጠብታ
ያን ሁሉ በትዕግሥት ችሎ አሳለፈና
ይመግበን ጀመር ሰማያዊ መና

## 418. ሞተሃልና ስለእኔ

ሞተሃልና ስለእኔ ምንም ሳይኖርብህ ጥፋት
ተከሰህ ተወቅሰህ በጲላጦስ ፊት
ኢየሱስ አማለከ ምሕረት ስብሐት ለከ/2/
የአንተ መንገላታት ሁልጊዜ ያሳዝነኛል ሲወራ
በመስቀል ላይ ሆነህ ያየኸው መከራ
ኢየሱስ የህይወት እጀራ ስብሐት ለከ.2/
ከልዑል ቦታ ዝቅ ብለህ ፈጣሪ ፍጡራን አምላክ
በሰው ፊት ተዋርደህ ስለሰው የሞትክ
በመስቀል ላይ ተጠማሁ እያልክ ስብሐት ለከ/2
መሐሪ ጌታ ሆይ አሁንም እንደ ቸርነትህ ብዛት
የእኛን በደል ሁሉ ሳትመለከት
አድነን ከዳግመኛ ሞት ስብሐት ለከ/2/

## 419. ዘጠኝ ሠዓት ሲሆን

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አባት ሆይ
በመስቀል ሆነህ ››  ››
ድምፅህን በማሰማት ›› ››
ነፍስህን ሠጥተህ  ››  ››
ክዋክብት ከሰማይ በሙሉ እረገፉ
ጨረቀና ፀሐይ ደም አጎረፉ
ብርሃናት ጨለሙ ከሠው ተለያዩ
ሥጋ በመስቀል ላይ ተጋልጦ ስላዩ
ጌታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ
አሰምቶ ጮኸ ተጠማው እያለ
ማርና ወተትን ለሚመግበው
ሀሞት አመጡለት ይቅመሰው ብለው
አካሉ ሲውጋ ውኃ ደም ፈሰሰ
በምድር ተረጭቶ ዓለምን ቀደሰ
የእስራኤል ሴቶች ዋይ ዋይ ሲሉልህ
ለእነርሱ አሰብክ እንጂ ለአንተስ አላሰብክ
እናቱ ስታለቅስ በመስቀል ስር ሆና
ዮሐንስን ሰጠ ጠብቆ እንዲያጽናና
መላእክትም ታዩ አጋንንትም ሸሹ
የአይሁድ ሠራዊት ፈርተው ተረበሹ

## 420. ኪርያላይሶን

ኪራያላይሶን (3)
በሰማይ በምድር ሥልጣኑ ያለህ ኪያላይሶን
በፍርድ አደባባይ አንተን አቆሙህ
እኛን አድን ብለህ መራቅ ተፋብህ
በአክሊል እሾህ ላይ በመቃ መቱህ
የተንኮልን ነገር አንዳች ቢያጡብህ
ይህስ ይሳደባል ብለው ከሰሱህ
እሳተ መለኮት ዓለምን የፈጠርክ
ሥጋ በመልበስህ በሰይፍ ተመታህ
በእኛ አመጽ ግርፋት የተገረፍክል ኪርያላይሶን
በሸንጎ እንዳንቀርብ የተሰቀልክልን
ኤሎሄ (2) የሲቃ ድምጽ
ዛሬም ይሰማናል ይህ ጥሪ ቃልህ
ስቃይህን አስታውስን እናነባለን ኪያላይሶን
የምሕረት እጆችህ እንዲዳብሱን
ስለእኛ መከራ ስለተቀበልህ
አሁንም ደግፈን እንዳንጠፋብህ
በእጆችህ ቀድሰህ አንዳልሰጠሃቸው
እስቲ በእሳት እጅህ ተከላከላቸው
አንተ በባሕርይህ ሁሉን ቻይ ሆነህ
በመስቀል ቸንክረው ቀራንዮ አዋሉህ

## 421. ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ አይሁድ አማጽያን ሰቀሉህ ወይ
የዓለም መድኃኒት የዓለም ሲሳይ ሰቀሉህ ወይ /2/
የአዳም በደል አደረሰህ አንተን ለመሰቀል
የሔዋን ስህተት አበቃህ ለሞት ቸሩ
አባት/2/
ንጹሕ ክርስቶስ ሆነ ወንጀለኛ ብለህኛ ስለእኛ
መሰቀል አሸክመው አስረው ገፈፉህ እያዳፉህ/2/
እጅና እግርህን በብረት ተመታ የዓለም ጌታ
የሾህ አክሊል ደፍተህ ጎንህን ተወጋህ አልፋ
ኦሜጋ/2/
ግብዞች እንደራሳቸው መስሏቸው
ምራቅ እየተፉ በፊትህ ቀለዱ አንተን ሊጎዱ/2/
በመስቀል ላይ ተጠማሁ ስትል ታላቅ በደል
ሀሞትና ከርቤ ሰጡህ ቀላቅለው ጠጣ ብለው/2/
ይቅር ባይ ግልጽ በደላችንን ሁሉ ሳታይ
አንተ ቅር በለን በእኛ ሳትከፋ እንዳንጠፋ /2/

## 422. በዕጸ መስቀል ላይ

በዕጸ መስቀል ላይ በዚያ አደባባይ
አምላክ ሆይ ጌታ ሆይ ተንገላታ ወይ
መከራ አየህ ወይ
መስቀል አስይዘው ኪራያላይሶን
ወደ ጎልጎታ
ሲገራፉ ሲዳፉ
ስትንገላታ
ያንን አቀበት ኪርያላይሶን
ያንን ዳገት
ጀርባህ ተገርፎ
ስትቃትት
አንተን እያዩ ኪርያላይሶን
ሴቶች ሲያለቅሱ
እናቶች ቀርበው
ላብህን ዳበሱ
መስቀል አስይዘው ኪያላይሶን
እንዲያ ሲያዳፉህ
የቀሬናው ሰው
ስምኦን አገዘው

## 423. ለእኛ ብሎ ተንገላታ

ለእኛ ብሎ ተንገላታ የሁላችን ጌታ
አዳም ቅጠል በልቶ ባመጣው በሽታ/2/
አምላክ ዋለ ቀራንዩ ለብሶ ከለሜዳ
አዳም ሕግ አፍርሶ በጎተተው ዕዳ/2/
ለመስቀሉ ተሰለፈ እየተገረፈ
በዕጽ ሊፈውሰው በዕጽ ላይ አረፈ/2/

ምንም በደል ሳይኖርበት የዓለም መድኃኒት
ፍዳን ተቀበለ ለሰው ልጆች ድኅነት/2/
በመሬት ላይ ተንገላታ ሩኅሩኅ ጌታ
አዳም ቅጠል በልቶ ባመጣው በሽታ/2/

424. ኦ የማይሞተው ሞተ

ኦ የሞይሞተው ሞተ/2/
ሄደ ቀራንዮ እየተጎተተ
ወድቆ እየተነሣ እንዲያ እየቃተተ
ሞትን ይሽረው ዘንድ የማይሞት ሞተ/2/

እጅና እግሩን ታስሮ ሄደ አደባባይ
እየተገረፈ ታግሶ ስቃይ
አለቀሰች ቆማ ድንግል ማርያም
አለቀሰች ቆማ ድንግል ማርያም
ተሰቅሎባት ልጇ መድኃኔዓለም

በአሁይድ አደባባይ ፍርድ ተንጋደደ
ወንበዴ ተለቆ ንጹሕ ሰው ታረደ
የማይሞተው ሞተ ለሰው ፍቅር ብሎ
ዋለ ቀራንዮ በእረንጨት ላይ ተሰቅሎ
ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ሥጋውን ለመኑ
እንዲፈቅዱላቸው ሄደው መቃብር
ገንዘው ቀበሩት በአዲስ መቃብር
ቅዱስ ቅዱስ ኃያል በክብር

425. በትዕግሥቱ ብዛት

በትዕግሥቱ ብዛት ባይገለጥ ኃይሉ
ስቀለው ስቀለው አይሁድ ተባባሉ/2/

የኃያላን አምላክ አልፋና ኦሜጋ
እንድኛ ታመመ በለበሰው ሥጋ
ኅብስት አበርክቶ የሚመግብ ጌታ
ታሰሮ ተገረፈ እንደክፉ ሽፍታ

እጅና እሮቹ ታሰረው ብታይ
ድንግል አለቀሰች እለች ዋይ ዋይ
የሚንቀጠቀጡለት መላዕእክት በፊቱ
እንደምን በችንካር ተወጋ ደረቱ

የንጹሐን አምላክ ወንጀለኛ ተብሎ
ዋለ ቀረንዮ እርቃኑን ተሰቅሎ
በደል ሳይኖርበት ተሰቀለልን
ሞታችንን ሞቶ ሕይወትን ሰጠን

426. በእለተ አርብ

በእለተ ዓርብ ሥላሴ ሰውን ፈጠሩ ልክብራቸው
የተፈጠሩትም አዳም ሔዋን ናቸው
ለጠቅላላው ዓለም ኃይል እንዲሰጣቸው
አፍርሰው ወደቁ በሰይጣን ተሳስተው
ወይ በደል ወይ ጉዳት
የሁላችን አባት  አዳም ያን ግዜ
ጀመረ ልቅሶውን
ተሳስተቶ በመብለት እጸ-በለስን
ሊወርስ ፈልጎ አምላክነትን
ባልሆነ መካሪ በክፉ ሰይጣን
ወይ በደል ወይ ጉዳት

ይህችን እፀ በለስ ባትቆርጫት
ከሰይጣን ጋር ተማክረሽ
የምድሩ ሳይበቃሽ የሰማይ ሽተሽ
እኔን አዋረድሽኝ አንቺም ተዋረድሽ
ከእንግዲህ ይጥቀምሽ ከንቱ ምኞትሽ
ወይ በደል ወይ ጉዳት

አትውቀሰኝ እንጂ አዳም
ምን ላድርግ ብለህ ነው ጌታዬ
ሰይጣን አስቶኝ ነው አዬ መከራዬ
ከእንግዲህ ወዲህ እሳት ነው ኑሮዬ
ስለተጣላሁኝ ከቸር ፈጣሪዬ
ወይ  በደል ወይ ጉዳት
ከጎኔ ተፈጥረሽ ሔዋን
እንኳን ልትረጂኝ ጎዳሽኝ
አንቺን ሳስተሽ እኔን አሳትሽኝ
በማስመሰል ነገርሽ ስላበላሽበኝ
እስከመቼ ድርስ ሞቼ ቀረሁኝ

ወይ ጉዳት ወይ ጉዳት

ንጊዜ ከገነት ሲወጡ በጥፋት

ሲገፈፍ ክብራቸው

መጣላት ጀመሩ እርስ በራሳቸው

አንቺ ነሽ  አንተ ነህ ሆነ ነገራቸው

ነገር ግን አይጠቅምም መነዛነዛቸው

ወይ በደል ወይ ጉዳት

## 427. ድንግል የዚያን ጊዜ

ድንግል የዛን ጊዜ /2/ ሐዘንሽ በረታ

በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ/2/

የግፍ ግፍ ደርሶበት የዛን ጊዜ

ተጠማሁ ሲለሽ

ለውሻ ያጠጣሽ በወርቅ ጫማሽ/2/

አዝ----------

ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ

ራርቶ ሆድሽ

ለፍጡር በማዘን ወኃ ያጠጣሽ/2/

አዝ----------

ተጠማሁ እያለ የዚያን ጊዜ

ሲናገር ልጅሽ

ታዲያ እንደምንቻለው ወላድ እጀትሽ/2/

አዝ----------

እንደዚያ ስታለቅሽ የዚያን ጊዜ

ሐዘን ሲውጥሽ

እነማን ነበሩ ያስተዛዘኑሽ /2/

አዝ----------

ስታለቅሽ በማየት የዚያን ግዜ ራርቶ ልጅሽ

ዮሐንስን አጽናኝ እንደልጅ ሠጠሽ /2/

## 428. አለምን ለማዳን

አምን ለማዳን የተሰቀለው

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው

ጌታችን ተሰቅሎ ቢያዩት መላእክት

በዝማሬ ፋንታ አለቀሱለት

ሚካኤል ዝም አለ ገብርኤል ገረመው

አምላኩ እርቃኑን ተሰቅሎ ስላየው/2/

ነፍሱን ለወዳጁ የሚሰጥ ቢገኝም

ለጠላት የሚሞት በጭራሽ አይኖርም

ጠላቶቹ ስንሆን ለኛ ሞተው

ክርስቶስ ልዩ ነው ወደርም የለው/2/

ውራን ቢያበራ የሞተን ቢያስነሣ

በመመስገን ፈንታ ሆነበት አበሳ

ሰማያዊው ዳኛ ሊፈረድበት

ተኮስ ቀረበ በጲላጦስ ፊት /2/

በጸሎተ ሐሙስ ዕለተ እራት የሆነው 2/

አርብ በመስቀል ላይ የተሰቀለው

ፍቀር አስገድዶት ለኛ የሞተው

መልካሙ እርኛችን መድሃኒዓለም ነው/2/

## 429. ምደረ ቀራንዮ

ምደረ ቀረንዮ ምደረ ጎልጎታ

መድኃኒት ክርስቶስ በአንቺ ተንገላታ/2/

መስክሪ አንቺ ምድር ግዑዚቷ ሥፍራ

መድኃኒት ክርስቶስ ያየብሽን መከራ/2/

ደሙ እንደውኃ ሲፈስ መስቀሉ2/

በቀራንዮ ቦታ መከራውን ሲያይ/2/

ፀሐይ ከለከለች ደማቅ ብርሃኗን /2/

ለመሸፈን ብላ የአምላክን እርቃን/2/

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ገለጸው /2/

በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ እያለ /2/

የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ /2/

እጆቹን እግሮቹን በችንካር ተመተው/2/

ቸሩ መድኃኔዓም እባክህ ማረን/2//

ደካሞች ነንና እንዳንቀር ጠፍተን/2/

በቆረስከው ስጋ ባፈሰስከው ደም/2/

አቤቱ ተራዳ እስከ ዘላለም/2/

## 450.አምላክ ለእኛ ብሎ

አምላክ ለእኛ ብሎ ቢያፈሰው ደሙን

ፀሐይ ከለከለች ደማቅ ብርሃኗን
በመስቀል ላይ ዋለ በኢየሩሳሌም
እዩት ተመልከቱት መስቀሉ ማማሩ
ለተመራመረው ብዙ ነው ምሥጢሩ
ቢገርፉት ቢሰቅሉት በያላግጡበት
ምንም አላገኙም በእርሱ ላይ ስህተት
ፈጣሪ መኖኑ ምሥጥሩ ገብቷት
ጌታን አልይዝ አለች ግዑዟ መሬት
ይህ ታላቅ ንጉሥ ሲገለጥ በሰማይ
የናቁት ሁሉ ይሉለታል ዋይ ዋይ
ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሲሸሹ የት ልግባ ይላል
ትልቁ ትንሹ
ወደላይ  ያረገው የከበረ ሥጋ
ዳግመኛ ይምጣል ሁላችን አንዘንጋ

451.አልፋና ኦሜጋ

አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንክ
በከሀዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ/2/
ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡ ክርስቶስ ሆይ አሉህ
ጽድቅን ስለሠራህ በወንጀል ከሰሱህ
ለአደም ቤዛ ልትሆን ብዙ ተንገላታህ
አዝ---------
ቅዱሳን እጆችህ የፊጥኝ ታስረው
እደበግ ጎተቱህ ልትምራቸው
የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ
ፊትህን ሸፈኑህ ለመመጻደቅ
አዝ---------
በዚያ አደባባይ በጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሐና ቀያፋ ከካህናቱ ደጅ
ከእነሄሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአወጅ
ግርፋት ሕማሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ
ዕደርና አላደር ጸናትና አደራ
ተፈልገው መጡ ለችንካር መከራ
አምስቱ ችክካሮች ቅንዋት መስቀል
አይሁዶች አመጡ ገላህን ለማቁሰል
ሊያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ
የሰላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ
ግፈኞቹ አይሁድ በአንተ ላይ ቀለዱ
ምራቅ ተፉብህ አንተኑ ሊጎዱ
ለእኛ ወገኖች ሀጢያት ሳደከመን
የመስቀልህ ጥላ ማረፊያ ይሁነን

452. ቅዱስ (3) እግዚአብሔር

ቅዱስ (3) እግዚአብሔር
ለአማልክት አምላክ እናቀርብ ምስጋና
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
ለነገሥታት ንጉሥ እናቀርብ ምስጋና
የእስራኤል አምላክ ቅዱስ/2/
ቅዱስ /2/ በጠራንህ ጊዜ ፈጥነህ ድረስ/3/
ተገዙ ለእግዚአብሔር ስሙንም ጥሩ
ድንቅ ሥራውንም ለአሕዛብ ንገሩ
ቅዱስ/2/ በጠራንህ ጊዜ ፈጥነህ ድረስ/3/
አትወድምና በእውነት የሰው ልጆችን ጥፋት
የእስራኤል አምላክ ቅዱስ
ቅዱስ (2) በጠራንህ ጊዜ ፈጥነህ ድረስ/
አቤቱ ጸሎቴን ስማ በያሬድዊ ዜማ
የእስራኤል አምላክ ቅዱስ
ቅዱስ /2/ በጠራንህ ጊዜ ፈጥነህ ድረስ
የእስራኤል አምላክ ቅዱስ
ቅዱስ/2/ በጠራንህ ጊዜ ፈጥነህ ድረስ/3/
የእስራኤል አምላክ ቅዱስ

453. አቤቱ በመንግሥትህ አቤቱ

በመንግሥትህ አስበኝ/2/
በበደሌ ብዛት /2/ አይተህ አትጣለኝ/2/
ሳስበው በደሌ ብዙ ነው/2/
በጨለማ ነፍሴን በላት ውድማ/2/

ሆዴ ባባ አፈሳለሁ እንባ/2/
እርቃኔን ቀረሁኝ ተገፈፈ ልብሴ
መድረሻው ጠፋብኝ ተጨነቀች ነፍሴ
የብርሃን ጸዳሌ ከዓይኔ ተገፈፈ
ከፊትህ ለመቆም ጉልበቴ ታጠፈ
አልቻልኩም ደግፈኝ እንድቆም/2/
ለገነት የበቃ ያቀማኛ ሽፍታ
እኔንም ደግፈኝ አውጣኝ የዚያን ለታ/2/

454.አባታችን ሆይ

አባታችን ሆይ የሁላችን ጌታ /2/
ቅዱስ መንፈስን ስጠን በተርታ /2/
ወደአንተ መልስ የሰውን ልቡና/2/
ባላወቀው መንገድ እርሱ ሄዷልና/2/
እዝነ ልቡናችንን ወደአንተ አዘንብለን/2/
ይቅርታን ልንጠይቅ ከፊትህ የቆምነው/2/
መሐሪ መሆንህን ስለምናውቅ ነው /2/
አይተህ እንዳላየ ታልፈዋለህ ሁሉንም/2/
መዓቱም ምሕረቱም ሁሉም የአንተ ሲሆን /2/
ሥልጣንህ ረቂቅ ነው አይመረመርም/2/
ዘመንና ወራት ሊሺሩት አይችሉም/2/
የፍቅር ባለቤት ቸሩ አምላካችን /2/
እድሜ ለንስሓ ስጠን ለሁላችን/2/
እንማልድሃለን በልቅሶ በሐዘን/2/
የይቀርታ ብዛት ከእኛ ጋር እንዲሆን/2/
የሰማይ መላዕክት የምድር ሰራዊት /2
ያመሰግኑሃል በቀንና ሌሊት /2/

455. ወንበዴ ነበርኩኝ

ወንበዴ ነበርኩኝ ሀገር ያስለቸው
በመስቀል ላይ ሆኖ ታሪኬን ለወጠው
አስበኝ ስላልኩት በኋላ ስትመጣ
ገነትን ለማየት የመጀመሪያው ሰው ሆነኩኝ ባለዕጣ
አዳም ሕግ አፍርሶ ባመጣው በሽታ/2/
አቤት ፍቅሩ የእግዚአሔር/2/
ግሩም ፍቅሩ ›› ››
ኃያል ፍቅሩ ›› ››
ግሩም ፍቅሩ ››››
አስበኝ ስላልኩት አሰበኝ ጌታዬ
ወንበዴ ነበርኩኝ ስርቆት ነው ሙያዬ
በመስቀል ላይ ሆኖ ሕዝቡን ያስብ ነበር
እኔስ አላየሁም /2/ እንዲህ ያለ ፍቅር
አልታይም ብዬ ኃጢአትን ስሠራ
ተመለስ ይለኛል ስሜን እየጠራ
እንዳልሞትበት ነው በኃጢአት ታስሬ
ፍቀሩን አልዘልቀውም/2/ እንደዚህ ዘርዝሬ
መከራ ሲከበኝ መጥቶ ያጽናናኛል
በሐዘኔ ጊዜ እግዚአብሔርም ያዝናል
ዓይኑ ከእኔ አይርቅም ጥበቃው አይጠፋም
ስሙን እጠራለሁ/2/ በጌታዬ አላፍርም

456. በኢየሩሳሌም

በኢየሩሳሌም በበጎች በር በቤተ ሳይዳ እኖር ነበር
ማን ያድነኛል እያልኩኝ አልጋህን ይዘህ ሂድ አለኝ
‹‹ ‹‹ እምነትህ አዳንህ አለኝ
‹‹ ‹‹ አምላኬ መጥቶ ፈወሰኝ
በአልጋ ላይ ከዋልኩ ስንብቻለሁ
ሰውነቴ አልቆ መንምኛለሁ
ውኃውን ሳያማታ ቅዳሜ
ቀደመው የዳኑ እኔ ቆሜ
አይዞህ የሚለኝ የሚያጽናናበኝ
ደገፊም የለኝ ብቸኛ ነኝ
ሠላሳ ስምንት ዓመት እያሉ
ተሳለቁብኝ መፃጉዕ እያሉ
እዘንልኝና አድነኝ
ሙሉ ጤነኛ አድርገኝ
ልትድን ትወዳለህ ሲለኝ

እውነትም እውነት አልመሰለለኝ
አዎ እወዳለሁ ስለው ጌታ
ፈወሰኝ አምላክ የእኔ አለኝታ
ስማኝ አምላኬ እጮሃለሁ
ኃጢአቱ በዝቶ አለቅሳለሁ
በመብል ጠፍቶ ልጅነቱ
ባሪያህ አድረገኝ ውድ አባቴ
እንደእኔ ታማሚ የሆናችሁ
አምናችሁ ጌታ ያድናችሁ
እነደእኔ ድውይ የሆናችሁ
የጌታ እናት ታመልዳችሁ

457. <u>የዳዊት ሀዘኑ</u>

የዳዊት ሐዘኑ የጴጥሮስ ንስሓ/2/
እኛን ያነጻናል እንደ ንጹሕ ውኃ/2/
ይቅር ባይ ነህና የሰውን በደል
የእኔን አበሳዬን አሁን ይቅር በል
የዳዊት ሐዘን የጴጥሮስ ለቅሶ/2/
የተቀበለ አምላክ ተበድሎ ክሶ
የዛሬም ይቅር በል የሕዝቡን አበሳ/2/
አንተ የከፈልክልን የእኛ ሁሉ አበሳ
በደለኛው እኔ የአንተን ሕግ ጥሼ /2/
ንጹሀ ስጋዬን በጭቃ ለውሼ /
በንስሓ ውሃ አጥቤና ስድሼ/2/
አሁን ይቅር በለኝ መጣሁ ተመልሼ

458. <u>ልቤ አቤት በል</u>

ልቤ አቤት በል እንጂ አምላክህ ሲጣሪ
በሐዘን በልቅሶ ትካዜህን አውራ
በደሌን አውቄ ይቅርታ ልጠይቅ
ሁን ቻይ ነህና ፍጥረትህን የማትንቅ
አለቅሳለሁ ዘወትር አነባለሁ
አውቃለሁ አምላኬን ብዙ በድለሁ
ልቅሶና ጩኸቴን ተቀበለኝ
ጎስቋላ ሆኛለሁ ኃጢአት ያደከመኝ/2/
መንገድ ተላልፌ ፈጣሪ አስቀየምኩህ
በሚጠፋ ንብረት አምላኬን ለወጥኩህ
አሁን ግን አምኜ ብዙ እንደበደልኩህ
በረከሰ አንደበት ይቅርታን ለመንኩህ
የኃጢአት ጉዞ እኔን ሰልችቶኛል
ኃጢአቴ በዝቶብኝ መቆም ተስኖኛል
ነሽና በፊቱ ክብር ሞገስ ያለሽ
ድንግል ልመናዬን አድርሺ ከልጅሽ

459. አቤቱ አቤት ኃጢአቴ

አቤቱ አቤት ኃጢአቴ ብዛቱ/2/
መስፈሪያም የለውም እርስ ካልተወኝ በቸርነቱ
ከእኔ ኃጢአት ይልቅ ይበዛል ምሕረትህ
አደራ እንድትምረኝ ጌታ በቸርነትህ/2/
እስከ አንገቴ ደርሶ የኃጢአቴ ብዛት
ሊውጠኝ ነውና አውጣኝ የእኔ አባት/2/
ለእግሬ መቆሚያ ከሌለው ባሕር
ድረስልኝ ጌታዬ ወድቄ እንዳልቀር/2/
ወደአንተ ስጣራ በጩኸት ደክሜ
ተስፋ ሊያስቆርጠኝ የኃጢአት ሸክሜ/2/
ወደ ኃላ ልቤ እንዳይመልስኝ
መልካም እረኛዬ አንተ ጠብቀኝ/2/
የሠራሁት ሁሉ ከአንተ አይሰወርም
ይቅር ትለኛለህ አልጠራጠርም/2/
መመለሴን እንጂ መሞቴን አትወድም
በዚህ እጽናናለሁ ከፍቅርህ አልርቅም/2/
አንተን ስበድልህ ይቅር እንዳልከኝ
የሚበድሉኝን ይቅር በልልኝ /2/
ይቅርታ ለማድረግ እኔን ቢከብደኝ
አንተ አይቸግርህም ይቅርታ ስጠኝ /2/

460.<u>አደባባይ ቆሜ</u>

አደባበይ ቆሜ ስምህን ከመሰበክ
መጀመሪያ ልቤ ከፊትህ ይንበርከክ
ከአገልግሎት በፊት አንተን ልወቅህ

መሥዋእት ከማቅረብ ልታዘዝልህ/2/

አሐዱ አብ ብዬ ስምህን ብቀድስ

ለድሆች ብሰጥ ቤትህ ብገሰግስ

በመላእክት ልሳን ብዘምር በእልልታ

ምን እጠቅማሃለሁ ካልፈራሁ ጌታ/2/

ተራራ እስካፈልስ እምነት ቢኖረኝ

ሥራ ከሌለበት ምንም አይጠቀመኝም

ልቤን ስትመረምር ከሆንኩኝ ቀላል

ክርስቲያን መባሉ ምን ይጠቅመኛ/2/

ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል

ከውጭ ተጥሎ በእግር ይረጋገጣል

አንተን ለሚከተል እንዳልሆን እንቅፋት

አምልኮቴ ይሁን በፍቅር በፍርሃት/2/

የእውቀት ሰው መሆን አይጠቅመኝ

እኔስ መስቀልህ ነው ፍቅርህ ያሸነፈኝ

ከእምነቴ የተነሳ መታዘዝ ይሁነኝ

ስምህን መፍራት ነው በእምነት የሚያኖረኝ/2/

<u>461. በከሃሊነቱ</u>

በከሃሊነቱ በአምላክነቱ /2/

ይቅር ይለናል ይታደገናል/2/ በቸርነቱ

ምን ይከፈለዋል ምን ይሆን ዋጋው

ለፈጠረን ጌታ ለይቅር ባዩ

የድኅነትን መንገድ ንስሓን የሠራ

እንዳንጠፋበት ነው ዳግም በመከራ

ይቅር ይለናል ይታደገናል/2/ በቸርነቱ

የሰው ልጅ ከኃጢአት እስኪመለስ ድረስ

አይቸኩልም እርሱ መዓትን ለማድረስ

ትእግሥቱ ሰፊ ነው ሥራው እረቂቅ

ቸርነት ገንዘቡ ቢሰጠው አልያቅ

ይቅር ይለናል ይታደገናል/2/ በቸርነቱ

<u>462. ወደ ሕይወት መንገድ</u>

ወደ ሕይወት መንገድ ይመራኛል ጌታ/2/

በጨለማ ሕይወት እንዳልንገላታ/2/

ፈጣሪ ብቻ ነው ሕይወቴና ክብሬ /2/

በእርሱ ደስ ይለናል ሳቀርብ ዝማሬ/2/

ጉልበት ሁሉ ለአንገተ በፍርሃት ይስግዳል/2/

ምሕረትን አድለን ፈጣሪ ቸል አትበል/2/

ለኃያሉ ጌታ በአንተ ይረካል/2/

በምሕረትህ ማረን አቤቱ ፈጣሪን/2/

ሰላምን አድላት ለኢትዮጵያ /2/

እጆችዋን ዘርግታ ስትል ሃሌ ሉያ/2/

<u>463. ለእኛ ብሎ</u>

ለእኛ ብሎ ተንገላታ የሁላችን ጌታ/2/

አዳም ቅጠል በልቶ ባመጣው በሽታ /2/

አምላክ ዋለ ቀራንዮ ለብሶ ከለሜዳ/2/

አዳም ሕግ አፍርሶ በገተተው እዳ/2/

ለመስቀሉ ተሰለፈ እየተገረፈ/2/

በእጽ ሊፈውሰው በእጽ ላይ አረፈ/2/

በመስቀል ላይ የዋለውን እናመስግን/2/

በእጽ የሞተው በእጽ አዳነው

ምንም በደል ሳይኖርነት አልም መድኃኒት/2/

ፍዳን ተቀበለ ለሰው ልጆች ድኅነት/2/

በመሬት ላይ ተንገላታ እሩህሩሁ ጌታ /2/

አዳም ሕግ አፍርሶ ባመጣው በሽታ/2/

›› ›› ›› በገተተው እዳ

<u>464. ነነዌን ሊያቃጥል</u>

ነነዌን ሊያቃጥል የወረደው እሳት/2/

ተመልሶ አረገ/2/ በጾምና ጸሎት/2/

ስለሆነ ከልብ የሐዘናቸው ምንጩ

ነበር እንደ ራሄል/2/ ዕንባ እየረጩ

ለነነዌ ሰዎች ደስታን ያበሰረ

ጋሻና ጦራቸው/2/ ጾም ፀሎት ነበረ

እንኳን የሰው ልጆች እንስሳት ሳይቀሩ

በዮናስ ስብከት/2/ ጾም ፀሎት ተማሩ

465. እስራኤል ሠለቸው

እስራኤል ሰለቸው የሰማዩ መና/2/

ዓለም አምሮት ሄደ ጸጋውን ተወና/2/
የእግዚአብሔር ስጦታ ኀብስቱ ስልችቶት/2/
ዓለም አምሮት ሄደ ከተወው ባርነት/2/
የፈርዖን ጅራፍ አልታየው አለ
የእህል አምሮቱን ውርደቱን ከለለ/2/
ግብፅ ልሄድ ብሎ አመጸ በእግዚአብሔር
መድርሱ አልገባውም ከከነዓን ሀገር/2/
የኪዳኑ ታቦት የሙሴ ገጽታ
ዓለም ስላማረው አደረገው ተርታ /2/
የአምላክን ካህነት የአሮን ሥርዓት
በዓለም ለወጠው ትልቁን አምኃ/2/
የኀብረቱን ጉዞ በፍቅር የሄደው
የማኀሌት ደስታ እስራኤል ታከተው/2/
የእግዚአብሔርን ድንኳን ደመና ያጀባት
የኪዳኑን አርማ በበረሃ ተዋት/2/
ዛሬም ይህ ትውልድ እስራኤልን ሆኗል
ቤክርስቲያኑን አምላኩን እረስቷል/2/
ግብጽና ባቢሎን አጓጉተው ወስደውት
ወርቁን ከእጁ ጣለ መዳብ አስጎምጅቶት/2/

466. አዝናለሁ አለቅሳለሁ

አዝናለሁ አለቅሳለሁ
ስለ በደሌ ሁልጊዜ አለቅሳለሁ
አዝናለሁ አለቅሳለሁ
ስለጥፋቴ ሁለጊዜ አለቅሳለሁ
ነገር ግን መሐሪ ነህና እንደምታድነኝ
አምናለሁ/2/
ሥጋዬ ለራሱ እያታለለኝ/2/
ሁለን በመፈለግ ወሰደና ለጥፋት ሰጠኝ
ከመሬት ተገኝታ እመሬት ልትገባ/2/
ከንቱ አስቀረችኝ ያሳሳች ሥጋ ስገብጋባ /2/
ትቻት ልመጣ ነው አፈር ሥጋዬን
›› ›› ›› መሬት ሥጋዬን
እንድትቀበላት አምላኬ ሆይ አደራ ነፍሴን/2/

467. ሞቼ ስለማልቀር

ሞቼ ስለማልቀር ትንሣኤ ስላለኝ
በተስፋ ቤታችን ስለምንገኘኝ
ወዳጅ ዘመዶቼ አታልቅሱ በቃኝ/2/
አቀናለሁና ገና አዲስ ኑሮ
አምላክን አስቡት ይብቃችሁ እሮሮ/2/
ይልቅ ጸልዮላት ለነፍሴ እረፍት
ዓለም አታላይ ናት ዘላቂ አይደለች
ለሥጋ ነው እንጂ ለነፍስ አትመች/2/
ግን ከሥጋ ጋር ስንኖር ትእዛዙን ከጠበቅን
ለተዘጋጀው ቤት ወራሾች እኛው ነን/2/
መቼም ከማያልቀው በረከት ያደልከን
ዘላለማዊ ሕይወት ለሰጠኸኝ
ምስጋናችን ይድረስህ ጸጋህ አይለየን
እኛ በድለን ትህዛዝህን ጥሰን
አንተ በመስቀል ላይ ደምህ ፈሰሰልን
ፍቅርህን ስናስብ እጅግ ይደንቀናል
ለዚህ ሁሉ ውለታህ ምን እንከፍላለን

468.የጥበብ ሃገሯ

የጥበብ ሃገሯ ወዴት ነው
ማደሪያዋስ ወዴት ነው/2/
በውኑ ጎዳናዋ ከወዴት ተቃኘ
ዝናና ወሬዋ ከወዴት ተገኘ
ፈልጎ የገዛት ማነው በቀይ ወርቅ
ባሕሩን ታሻግሮ ስሟን በማወቅ
ማነው ያወረዳት ከደመና በላይ
ድምጿንስ የሰማ ከላይ ከሰማይ
እርሷን የሚጠሉ ናቸውና ከንቱ
አይቀርላቸውም ኃላ የሞት ሞቱ/2/
ሁሉን የሚያውቅ እርሱ ያውቃታል
የእውቀት ጎዳናዋ ያስተምርላታል
በክርስቶስ ፈቃድ ምድር ላይ ታየች

እነሆ ቤት ሠራች ሰባ አምድ አቆመች/2/
ጥበብ ግን እርሱ ነው መድኃኒታችን
በሥጋ ተገልጦ እኛን አዳነን
በደሙ ፈወሶ ተወዳጅን
ለእርሱ የመረጠን ይክበር ይመስገን /2/

469. አማኑኤል ሆይ

አማኑኤል ሆይ መድኃኒቴ ሆይ
አትተወኝ አንተ ሞትን እንዳላይ/2/
የግብፅ ከተማ ደምቃ ስትታየኝ
ተስሎንቄ አድጋ ለዓይኔ ስትስብኝ
ኤልሻዳይ ኢየሱስ ልቤን መልስልኝ/2/
መታመን በሰው ላይ ምንም አይጠቅምም
መከታነት በሰው ለእኔ አይሆንም
አትተወኝ አንተ አምላክ ዘለዓለም/2/
የሚያጽናናኝ የለም እኔ እንዲህ ስከፋ
ህምልምም ሆነብኛል የሰው ሁሉ ተስፋ
ቃልህን የሚታጥፈው አንተ ከእኔ
አትጥፋ/2/

470. ዋ ለነፍሴ

ዋ ለነፍሴ ምንም ስንቅ አልያዝኩኝ /2/
አዬ ለእኔስ ወዮልኝ ዋ ለነፍሴ
ምንም ስንቅ አልያዝኩ
ነፍሴን እየጎዳሁ ሳስብ ስለሥጋ
ዓለም ስትሰበኝ እዳላገኝ ዋጋ
መንፈስህን ስጠኝ ከበደል እንጻኝ
ቃልህን እሰማለሁ ማስተዋል የለኝም
ፍጹም ሆኖ መቆም ጌታ ሆይ አቃተኝ
ታዲያ እንደፈቀድህ እንዴት ብዬ ልገኝ
ድካሜን ታውቃለህ አምላክ ሆይ አበርታኝ
አለቅሳለሁ ጌታ ከእግርህ ስር ወድቄ
ሕይወቴ ተዛብቶ በኃጢአት ማቅቄ
ዘመኔን ጨረስኩኝ መልካምን ሳልሠራ
ቸርነትህ ይርዳኝ ልኑር ከአንተ ጋራ
ፈተናው ከበደኝ ለነፍሴ ፈራሁኝ
ደስታ ከእኔ አርቆ ቢበዛ ሃዘኔ
አትተወኝ አንተ ሁንልኝ ከጎኔ

471. ተይ ተመከሪ

ተይ ተመከሪ ነፍሴ ሆይ ተይ ተመከሪ/2/
በዓለም መድኃኒት ነፍሴ ሆይ በእግዚአብሔር ታመኚ/2/
አዝ ----------
ለሥጋ መገዛት ነፍሴ ሆይ ምነው ቢቀርብሽ
ውረደት ነው ፍጻሜ ነፍሴ ሆይ የሚከያናንብሽ
መልካም የሆነወን ነፍሴ ሆይ
ጽድቁን ተከተይ
ክርስቶስን መስለሽ ነፍሴ ሆይ
ቸርነትን ሥሪ
ሞትን ማን ይመርጣል ነፍሴ ሆይ ሕይወትን
በመጥላት
ከእንግዲህ መራቅ ነው ነፍሴ ሆይ
ከስርቆት ከዝሙት
ጸጋህ እንዲበዛልሽ ነፍሴ ሆይ
የቃሉ በረከት
ከቤቱ አትጥፊ ነፍሴ ሆይ ፍቅር ከሞላበት/2/
ለአንቺ ነበር ጌታ ነፍሴ ሆይ
ደሙን ያፈሰሰው
ተሰቅሎ ሞቶ ነው ነፍሴ ሆይ
ፍቅርን የገለጸው
በፍቅሩ ሳሰበኝ ነፍሴ ሆይ
ላፈቀረኝ ጌታ
ምስጋና አቀርባለሁ ነፍሴ ሆይ ዘወትር ጠዋት ማታ /2/
ብወድቅ ምርኩዝ ድጋፍ ነፍሴ ሆይ ጋሻ ይሆነኛል
ለፍርድ አይቸኩልም ነፍሴ ሆይ
በፍቅሩ ያየኛል
ማን እንደርሱ አለ ነፍሴ ሆይ
ውለታው የበዛ
መሐሪ ይቅር ባይ ነው ነፍሴ ሆይ የሕይወቴ ቤዛ/2/

472. ዓለም ወረተኛ

ዓለም ወረተኛ ከዳተኛ ነች/2/
ዛሬ ከአንተ ጋር ናት ነገ ከሌሎች /2/
አምላክ ለመኖሩ እኛ ማስረጃ ነን/2/
እልፍኝ ያለ ሠሪው በምንም አላየን/3/
አለም ኃላፊ ናት እናስተውል ሰዎች/2/
እንደ ጠዋት ጤዛ እንደጥላችን ነች/3/
አስተውል ወንድሜ በተሰጠህ ተስፋ/2/
ለሥጋህ አድልተህ ነፍስህ እንዳትጠፋ /3/
ሰዎች አንታለል ለሚቀረው ዓለም/2/
እኛስ እናልፋለን ቃሉ ግን አያልፍም /3/
አምላክ የለም ቢሉ የተሳሳቱት/2/
የህልም እሩጫ ነው ከንቱ መዋተት/3/
መራቀቅ ቢበዛ በሆነው ባልሆነው
በቁመቱ ስንዝር የሚጨምር ማነው/3/

473.ለውለታህማ

ለውለታህማ ጌታ ምን እንከፍልሃለን./2/
ለማይነገር ስጦታህ ተመስገን እንልሃለን/2/
ማቃችንን ቀይረህ አዲስ ላለበስከን
ቁስላችንን አጥበህ ዘይት ለቀባኸን
ጠላት ሲያዋርደን አንተ ላከበርከን
ለዚህ ሁሉ ውለታህ ምን እንከፍልሃለን
እኛ በበደልን ትእዛዝህን ጥሰን
አንተ በመስቀል ላይ ደምህ ፈሰሰልን
ፍቅርህን ስናስብ እጅግ ይድነቀናል
ለዚህ ሁሌ ውለታህ ምን ይከፈልሃል
የእኛ ፍቅር ስቦህ ከሰማይ ወርደህ
ደካማ ሥጋችንን ተዋርደህ አክብረህ
እግራችንን አጥብህ ፍቅር ላስተማርከን
ውለታህ ከብዶናል ምን እንከፍልሃለን/2/
ባሮች እንዳልነበርን ልጆች አደረከን
መቼም ከማያልቀው በረከት አደልከን
ዘለአለማዊ ሕይወት ለሰጠኸን
ምስጋናችን ይድረስኽጸጋህ አይለየን

474 . እርዳኝ ዝም አትበል

እርዳኝ ዝም አትብል የሠራዊት ጌታ
ተስፋ እንደሌለው ሰው ልቤ አያመንታ
አንተን ለማገልገል የነበረኝ ብርታት
ዛሬ ተስኖኛል አቅቶኛል መትጋት
ጨንቆኝ እጣራለሁ ጸጋ አጣ ሕይወቴ
እባክህ አርመኝ እርዳኝ መድኃኒቴ
ልቤ ድንጋይ ሆኖ ቃልህ አልሰበረው
የእጅህን ሥራ ጌታዬ አስተካክለው
የክርስታና ኑሮ ሥርዓቱን አፍርሼ
አለቅሳለሁ ጌታ በኃጢአት ተከስሼ
ሰላምና ፍቅር ነበር ክርስትና እኔ ግን ተናወጽኩ
አልጸናሁምና
ሥራዬና ቃልህ አልገናኝ አሉኝ
በጠማማው ልቤ አንተን አሳዘንኩኝ
ጽኑ መሠረት ነህ የሕይወት አለት
እየተናወጽኩኝ አቃተተኝ መትጋት
በእረፍት ውኃ ዘንድ በለመለመ ሳር
በጎችህን ሁሉ በፍቅር የምታኖር
በሕይወቴ እንዲታይ የቸርነትህ ክብር
ከደጅህ ተጥዬ ለስምህ ልዘምር

475. በመከራ ፅና

በመከራ ጽና በፈተና ጽና
ለጊዜው ነው እንጂ ሁሉም ያልፋልና
ኢዮብ ተጨንቀ በጣም ተማረረ
በመከራው ብዛት ትዕግሥትን ተማረ
ልጅ የሌለው ሆነ አጣ ንብረቱን
በመከራ ጸና አልካደም አምላኩን
መፈተን መልካም ነው ያነጻል እንደወርቅ
በመጨረሻው ቀን በክብረ እንድትደምቅ
አንዱን ሳትሻገር ሌላው ቢተካብህ
በሕይወትህ ዘመን ፈተና ቢያጠቃህ
ከአምላክህ ተስማማ ራስህን አዋርድ

በቃሉ ተመራ እንድፈቃዱ ሂድ
ዋጋህ ከአምላክህ ዘንድ በሰማይ አለና
በርታ ክርስቲያን ሆይ በፈተና ጽና

## 476. የሰው ልጅ

የሰው ልጅ በኃይልህ ፈጽሞ አትመካ/2/
አንድ አምላክ አለና በኃይሉ ኃይልን የሚለካ/2/
አዝ -----------

ኃይል አንደ ሶምሶን ከአምላክ ሲሰጥ
እንጻ/2/

በጉልበት መመካት ለማንም አይበከጂ/2/
ሰናክሬም ቢነሳ በሕዝቅያስ ላይ/2/
የደረሰበትን አልሰማህም ወይ/2/

አዝ ------------
ጎልያድ በኃይሉ ዳዊትን ቢንቀው/2/
አዋረደው እንጂ ኃይሉ ምን ጠቀመው /2/
እንደ ዳታንና እንደአቤሮን አይሆንም በግድ/2/
ተመርጦ ነው እንጂ ለክብር በአምላክ ፈቃድ/2/
ክህነትን ለአሮን ሕግንም ለሙሴ/4/
ከሰው ሁሉ መርጠው ሰጧቸው ሥላሴ

## 477. የሰማዩ አባት

የሰማዩ አባት ደግ ነህ መልካም እረኛ ነህ
ለሁሉም ጊዜ አለህ በጊዜው ሁሉን ታደርጋለህ/2/
አዝ -----------

ማን ያበድርሃል እግዚአብሔር ለአንተ
ብድራትን

ሁሉን ታደርግለህ በኃይልህ ችሎታህ
አንችልም እግዚአብሔር እኛ በአንተ ፊት
አዝ ------------

ከታናሽነቱ ጀምረህ እኔን ያስተማርከኝ
የቃልህን ወተት በቤትህ ለእኔ የመገብከኝ
ለአንተ የምከፍልህ አግዚአብሔር አንዳችም የለኝ
አዝ ------------

ለማልቀስ ጊዜ አለው አምላኬ ደርሶ ለመሳቅ
ከራሣችን ፀጉር አንዷቷን ጥቂቱን ሣናውቅ
የእኛስ ተግባር ሆኗል ለሁሉም ደርሶ
መጨነቅ/2/

## 478. አቤቱ ልንበርከክ

አቤቱ ልንበርከክ ልማር
ህግን አስተምረኝ ወድቄ እንዳቀር/2/

አቤቱ ለመማር ስፈልግ ደጅህን ስጠና
ተመለስ ይለኛል የሥጋ ፈተና
አቤቱ በልቤ እርሻ ላይ የዘራኸውን ቃል
ዲያብሎስ ወፍ ሆኖ ከልቤ ይለቅማል

አቤቱ ይህንንም ያንን ሁሉን ነገር ስመኝ
ከቤትህ እንዳልርቅ ቃልህ ይመልሰኝ
አቤቱ አባት ላንድ ልጁ እንደሚራራለት

በቁጣህ አትቅሰፈኝ በደሌን በማየት

አቤቱ ውለታህ ምን ያህል ጌታ የአንተ ፍቅር
ምን ይከፈለዋል ሲያጠፋ ለሚምር
አቤቱ ቁስሌን አጥበህልኝ ማቄን ለቀየርከው
ተአምርህን እኔ ዘርዝሬም አልዘልቀው

አቤቱ ኃያል ነህ ገናና አማካሪም የለህ
ፍርድህ ሚዛናዊ የእውነት አባት ነህ
አቤቱ የተዋረደውን አንተ ታከብራለህ
መልክና ቁመና መች ትመዝናለህ

## 479. ላይቀር መሞት

ላይቀር መሞት አፈር መልበስ መግባት ከመቃብር
መስሎኝ ቋሚ ይህ ሥጋዬ ለእርሱ ብቻ ስጥር
ዘመን መቁጠር እለት ወራት ክረምት በጋ
ሌሊትና ቀን ሲፈራረቅ ሲጨልም ሲነጋ
በማየቴ ሆነ መደሰቴ/2/
ኸረ ወዲያ ወዲልኝ ዋይ ብለሽ ለነፍሴ
አድርጎኛል የኃጢአት ምንጭ ደካማው መንፈስ
መሐሪ አምላክ ለጋስ ጌታ ቸሩ ፈጣሪዬ
አንተ እኮ ነህ ለዘላለም ለእኔ መመኪያዬ

ይቅር በለኝ ምሕረትህ አይራቀኝ/2/

480. በኢያሪኮ መንገድ

በኢያሪኮ መንገድ ጌታ አንተ ስታልፍ
ግፊያ ሆኖ ስደነቃቀፍ
የዳዊት ልጅ ማረኝ ብዬ ተማጸንኩህ
ዓይኔንም ፈወስከኝ ዛሬ ማየት ቻልኩኝ/2/
አንተን እንዳላይ ቁመቴ አጠረብኝ
ከፊት እየሮጥኩ ከዛፍ ላይ ወጣሁኝ
ጌታ ሆይ ጠረኸኝ ዘኬዎስ ሆይ አልከኝ
ቤቴ እንድትገባ ፍቃድህ ሆነልኝ/2/
ሐሴትም ሆነልኝ በጣምም ደስ አለኝ
አንተን በእንግድነት በቤቴ ተቀበልኩኝ
ኃጢአቴን ሁሉ በአንተ ፊት ጥያለሁ
ሀብቴን አካፍል ዘንድ እንዲገባ አውቃለሁ/2/

የክፋትን ገንዘብ መስብሰቤን ትቼ
አንተን ልክተልህ ሁሉን ረስቼ
ኑሮዬንም ባርከው የሕይወት ዘመኔን
መርጫለሁ አንተን በቤትህ መኖሬን/2/

481. ማረን አባታችን

ማረን አባታችን ማረን
ማረን  እግዚአብሔር
ከዘመኑ መቅሰፍት
ከልለህ አውጣን ሰውረህ
እግዚአብሔር ሆይ ይብዛ ምሕረትህ
ሕፃናት ሲያለቅሱ እናት አባት አጥተው
ተስፋቸው ሲጨልም አዛውንት ጧሪ አተው
አትጨክን አምላክ ቁጣህን መልሰው
የዘመኑን ንዳድ እሳቱን አብርደው
አዝ------------
ያለ እድሜው ሲቀጠፍ ወጣሩ አንደ አበባ
ወላጅ አንጀቱ ሲያር ሲታጠብ በእንባ
እዘንልን አምላክ ምሕረትህን አብዛ
ከመድኃኒት አንተ ነህ ለሕይወታችን ቤዛ
አዝ------------
እንኳን የታመመው የቆመው ሲሰጋ
የሥጋዊ ጥበብ መላም አጥቷል ዋጋ
ከሰው ወገን የለም አንዳች ቅንጣት ተስፋ
ምሕረትህ ይብዛልን በሞት እንዳንጠፋ
አዝ------------
ሕግህ ከለላ ነው ከጥፋት መዳኛ
አንድ ለአንድ እንጽና እንዳናዝን እኛ
ሌላ መላም የለ ቃልህ ያድነኛል
ከዘመኑ ስጋት ነጻ ያወጣናል

482. በሥራዬ የት ይሆን

በሥራዬ የት ይሆን መግቢያዬ/2/
ጨነቀኝ ጠበበኝ ነፍሴ ወዲያልኝ/2/
ተሸክሜ የኃጥያት ክምር/2/
ይመሻል ይነጋል በከንቱ ስዞር/2/
ገሰገሰ ቀኑ ጨለመብኝ /2
በድያለሁ ወደ አንተ እጮሃለሁ/2/
ይቅር በለኝ እማጸንሃለሁ
ችላ አትበለኝ ከፊትህ ቆሜአለሁ/2/
አለፈብኝ በከንቱ ጊዜዬ/2/
እየንጎሁ ለዚች ለሥጋዬ /2/
በንስሓ ሳላጥበው እድፌን /2/
ልትደርሰ ነው ያች የፈተና ቀን /2/

483. ልመናዬን ስማኝ

ልመናዬን ስማኝ ቃሌን አድምጠኝ/2/
እውነተኛ አምላክ ሰላምህን ስጠኝ/2/
ክርስቲያኖች ሁሉ ትዕዛዙን አክብሩ
ምስጋናን አቅርቡ ስገዱ ዘምሩ
የጌታን አመጣጥ ለዓለም ንገሩ
ደቀመዛሙርቱ ወንጌል አስተምሩ
አዝ-----------
በመልካም የሚሄድ ጽድቅን የሚሰራ

የፈጣሪውን ስም በከንቱ የማይጠራ
ይጎበኛል በምድር ከሰማዩ ስፍራ
በቀኝ ይቀመጣል ከቅዱሳን ጋራ
አዝ------------

ስለጠላቶቼ በጽድቅ ምራኝ
በጦር ቃል ከበቡኝ ተሳለቁብኝ
መሐሪ ይቅር ባይ መጠጊያ ሁነኝ
አንተ በቸርነትህ ይቅርታ ስጠኝ

484. ሁላችን እንጸልይ

ሁላችን እንጸልይ የሃይማኖት ጸሎት/2/
እንድናወቅ ምሥጢሩን /2/ የተዋሕዶን እምነት
የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ከገባን
ከቶ ምንም አይኖር/2/ የሚያደናግረን
የአምላክ ሰው መሆን ምሥጢረ ሥጋዌ
ያስረዳናል በእውነት/2/ የአንድነት ህላዌ
የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ይረቃል/2/
በሃይማኖት ጸሎት በሃይማኖት
ትምህርት ጎልቶ ይታወቃል

485. ሰው ለሰው

ሰው ለሰው /2/ ቢፋቀር ምነው /2/
ለሰው ይመስለዋል ብዙ የሚቆይ
ግን በድንገት ያልፋል ሁሉንም/2/ ሳያይ
ሀብትን ከማቻል ቀኑን ሳውቀው
በድንገት ይጠራል/2/ አይከተለውም
የሰው ልጅ በተራ መጠራቱ ላይቀር
ምነው አንዱ ለአንዱ መቃብር/2/ ባይቆፍር
አይጠቅምም መጨነቅ እንዲያው ለውበት
ይረግፋል ይጠፋል ሁሉም/2/ ከመሬት
ዋ ቁንጅና ከንቱ ማማርም ብላሽ
አፈር ትቢያ ሲሆን ሲጨለም/2/ሲመሽ
ደሀ ባለጸጋ አንድ ነው መንገዱ
በጨርቅ ተገንዞ በሳጥን/2/ መሄዱ
ሰው ዙሪያውን ቢያጥር መዝጊውን ቢሠራ
በሕንፃ ላይ ሕንፃ ቢያስመስል ተራራ
አይቀርም መሄዱ ሁሉም/2/ በየተራ

486. መፅሐፍ ቅዱስን

መጽሐፍቅዱስን ሁሉም ያነበዋል
ምእራፍና ቁጥሩን ሁሉም ይጠቅሰዋል
በዚህ ብቻ አይበቃም ተርጓሚ ያሻዋል/2/
እንደፈቃዳችን ብንተረጉመው/2/
በውጥን የሚልቀው ስህተቱ ብዙ ነው/2/
ከቶ በሰው ፈቃድ ትንቢት እንዳልመጣ /2/
ይነግረናል መጽሐፍ ከሕግ እንዳንወጣ
ይመክረናል መጽሐፍ ከሕግ እንዳንወጣ
እንጠይቅ መምህራን ያሉት በደረጃ /2/
እናንብብ መጽሐፍት ይሁኑን ማስረጃ/2/

487. ኑ እንቅረብ

ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ/2/
ሥጋውን እንብላ /2/ ደሙንም እንጠጣ
የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፋን ኃጢአታችን በንስሓ አንጽተን
እንቀበልው አምነን በልጅነታችን
አዝ------------
መቅረብ ወደጌታ በእውነት የሚገባው
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው
ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱት
ከዋክብት በሰማይ የተነጠፉት
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት/2/
አዝ------------
ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትመግበናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይኸው ተዘጋጀ
ለግብዣ ተጠራን አዋጁ ታወጀ
አዝ------------
መጥቁ ተወለደ እንቅረብ በእልልታ

በኋላ አይረባም ዋይታና ጫጫታ
ይህንን እድል ፈጥነን እንጠቀምበት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይበት
አዝ------------

አሁኑ ቅረቡ ታውጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን እንኩ

488. ነፍሴ ሆይ

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ/2/
የተቀበለው በቀራንዮ
ያን ሁሉ መከራ በመስቀሉ ላይ
ለአንቺ ሲል ነውና ነፍሴ ሆይ
ተዘጋጅተሽ ኑሪ ሁልጊዜ
በነገ በዛሬ እንዳትታለዪ/2/ ነፍሴ ሆይ
በንስሓ ጥምቀት ታጠቢና
ክቡር ደሙን ጠጪ ሥጋውንም ብይ/2/
ነፍሴ ሆይ
ዘላለም በደስታ እንድትኖሪ
ከዘላለም ቤትሽ መንግሥተ ሰማይ/2/
ነፍሴ ሆይ

489. ወደአንተ እስግዳለሁ

ወደአንተ እሰግዳለሁ ሳለሁ በሕይወቴ
ላንተም እገዛለሁ እስከ እለተ ሞቴ
አንተ ነህና መድኃኒቴ የዘላለም ቤቴ /2/
ሳይመሽብኝ ቀኑ ሳይጨልም ድንገት
በጽድቅ ጎዳና ልጓዝ ወደፊት
ምራኝ መንገዱን አሳየኝ እንዳልሳሳት
የነፍስ የሥጋዬ የሕይወቴ ቤዛ
አትበለኝ ችላ በደሌ ቢበዛ
አንተን አምኜ እኖራለሁ ወዴት እሄዳለሁ/2/

490. አንድ ጊዜ

አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሆኛለሁ/2/
በፍቅሩ ተስቤ በደሙ ድኛለሁ
ዓለም ተይኝ ንቂ ትቼሻለሁ
ጥበበኛው ሰይጣን በመጣው ቢመጣ
ዳግም ተመልሼ ከእቅፍህ ላልወጣ
በመስቀሉ ግርጌ አርፌ እኖራለሁ
ዓለም ተይኝ የእግዚአብሔር ሆኛለው
አዝ------------

ቢያሙኝ ቢያጥላሉኝ ቢሳለቁብኝ
ውርደትን ተንኮልን ቢሸርቡብኝ
ለእኔ እንደው ደስታ ነው ሐዘንም የለኝ
ሰይጣን እፈር የክርስቶስ ነኝ
አዝ------------

ጓደኞቼ ጠሉኝ ተለውጬባቸው
የጥንቱን ፀባዬን ስለነፈግኋአቸው
ብቻዬን የሆንኩኝ ቢመስለኝም ለእኔ
ጌታ እንደሆን አለልኝ ከጎኔ
አዝ------------

491. መቼ ነው ጌታ

መቼ ነው ጌታ ኸረ መቼ ነው
መቼ ነው ጌታዬ እንደቃልህ የሚሆን ጉዞዬ/2/
አልተማርኩም አልል አስተምረኸኛል/2/
ቃልህን እንደ ወተት አጠጥተኸኛል/2/
አዝ------------

የታል አኗኗሬ አንተን የሚመስለው/2/
በልማድ ሕይወት ነው የምመላለሰው/2/
አዝ------------

ይህ አንደበቴማ በቃልህ ሠልጥኗል/2/
ልቦናዬ ካንተ ከፊትህ ኮብልሏል/2/
አዝ------------

አንተን እንደማውቅህ አብዝቼ ባወራ/2/
የተዘራው ሁሉ ፍሬ አላፈራ/2/
አዝ------------

እዘንልኝና መንገዴን አቅናልኝ/2/

የአመጸ ሥራዬን በደሌን ተውልኝ/2/

አዝ------------

## 492. እስከመቼነው

እስከ መቼ ነው የማልለወጠው
ባልተሰበረ ልብ የምመላለሰው/2/

በሰጠኸኝ ጸጋ ድካሜ ተከድኖ
ዓለም ይክበኛል አልቆና አግኖ
ይህን ከንቱ ወጥመድ ጣለው ከኋላዬ
ትንሽ ሰው መሆኔን ይወቅ ህሊናዬ /2/

አዝ------------

ፀሐይ ስትቀላ ከዋክብት ሲረግፉ
ለገናናው ክብርህ ወድቀው ሲሸነፉ
ለሁለት ሲከፈል ድንጋያማው አለት
የእኔ ልብ መቼ ይሆን የሚሸነፍለት/2/
ቃልህን ስሰማ ልቤን ይነካኛል
ጽታቅን አስባለሁ ሐዘን ይሰማኛል
ወዲያው ተመልሼ ሁሉን እረሳለሁ
ለዚህ ዓለም ስብከት ልቤን እከፍታለሁ/2/

## 493. ከወገኔ ጋራ

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ
በደስታ በሐሴት ስሙን እጠራለሁኝ
ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና
ዘወትር አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና/2/

አዝ------------

ሕዝቡ ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያን
ሲዘምር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን
በረከት የሞላው ዝማሬ ይገርማል
ከአጣኑ ጋር ወደ ላይ ይወጣል/2/

አዝ------------

ቀሳውስቱ ሌሊት ማኅሌት ሲያቀርቡ
ከመላእክት ጋራ ወርብ ሲወርቡ
ብርሃን ለብሰዩ በድሰታ ስንዘምር
ትዝታው ልዩ ነው ህሊና ሲሰውር

አዝ------------

እራዕይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደመላእክቱ
የፅጌው ዝማሬ የትንሣኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እዳንዳይመስለን ተርታ

አዝ------------

## 494. እያለፈ ነው ዘመኔ

እያለፈ ነው ዘመኔ ትእዛዙን ሳልፈጽም ወየው ለእኔ/2/
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለሁ ና ብሎ ወደእኔ/2/
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለው ነይ ብሎ ወደ እኔ

በወጣትነቴ ሳልሠራ እያየሁ አለፈኝ ብዙ አዝመራ/2/
ከእንግዲህ በመሥራት ጌታ ሆይ ልኑር ከአንተ ጋራ/2/
የማስብበት በየለዕቱ ንጹሕ ልብን ስጠኝ አቤቱ /2/
ከትእዛዝህ ወጪ በመሆን እዳልቀር በከንቱ /2/
እንደየሥራው ለመስጠት በግርማ መንግሥቱ ሲመጣ/2/
ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፊተናን የወጣ/2/
እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ እየተማራችሁ ከቃሉ/2/
ይመጣሉና በእርሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ/2/
ትዕግሥትን በመያዝ ሁላችሁ እስከመጨረሻው ጠንክሩ/2/
ያን ጊዜ ይሆናል በእርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ/2/

## 495. አማኑኤል ሆይ

አማኑኤል ሆይ መድኃኒቴ ሆይ
አትተወኝ አንተ ሞትን እንዳላይ /2/

የግብፅ ከተማ ደምቃ ስትታየ
ተሰሎንቁ አደጋ ላይኔ ስትሰበኝ
ኤልሻዳይ ኢየሱስ ልቤን መልስልኝ/2/
መታምን በሰው ላይ ምንም አይጠቀምም
መከታነት በሰው ለእኔ  አይሆንም
አትተወኝ አንተ አምላክ ዘለዓለም/2/
የማ የጽናናኝ የለም እኔ እንዳ ህ ስከፋ

ህልምም ሆኖብኛል የሰው ሁሉ ተስፋ
ቃልህን የማታጥፍ አንተ ከእኔ አትጥፋ /2/

496. እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው/2/
ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሶብን ሳለ በእኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሲያድነው
በመከራ ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው/2/
አዝ------------
አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነአን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎልበት
እንደ ምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት/2/
አዝ------------
በሐዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቀቴን የሚያርቅ ነው የፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ሐዘኔን
አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ቢነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ሐዘኔን አስረሳኝ

497. አታውኪኝ ነፍሴ

አታውኪኝ ነፍሴ አታስጨንቂኝ /2/
በዓለም መድኃኒት በእግዚአብሔር ታመኚ/2/
ዋልያ እንደሚናፍቅ ወደ ውኃ ምንጮች/2/
ጌታዬን ለማየት ነፍሴ ናፈቀች/2/
የሕይወትን ውኃ እያስታወሰችኝ /2/
ወደሕያው አምላክ ነፍሴ ተጠማች/2/
አዝ------------
መቼ ተነሥቼ መቼ እደርሳለሁ/2/
የጌታዬን ፊቱን መቼ አየዋለሁ/2/
የአምላኬን ውኃ እያስታወሰች/2/
የሕይወትን ውኃ እያስታወሰች/2/
ወደሕያው አምላክ ነፍሴ ተጠማች/2/
አዝ------------

498. ነብዩ ዳንኤል (የአብርሃም አምላክ በሚለው ዜማ)

ነብዩ ደንኤል በጾም ስላመነ /2/
ከአንበሶች ጉድጓድ ሕይወቱን አዳነ2/
ኤልያስ የወጣው በእሳት ሰረገላ/2/
በጾም በጸሎት ነው አይደለም በሌላ/2/
የነፍስንም ቁስል ጾም ታድናለች/2/
የሥጋን ፍላጎት እያደከመች/2/
እስቲ ልብ እናድርግ እናስተውል ደግሞ /2/
ጌታ ለሐዋርያት ያላቸውን ቀድሞ/2/
ይህ ርኩስ መንፈስ ሊወጣ የሚችል/2/
በጾም በጸሎት ነው እንደ ወንጌሉ ቃል/2/

499. የነፍሳችን ቤዛ(አማን በአማን በሚለው ዜማ)

የነፍሳችን ቤዛ የቅዱሳን ሀብት/2/
ጸጋን የሚያሰጠን ጾም ነው መድኃኒት/2/
የእስራኤል ልጆች በሙሴ ሲመሩ/2/
በጾም በጸሎት ነው ባሕር የተሻገሩ/2/
ቅዱሳን አባቶች ጾም ነው ጋሻቸው /2/›
ወደሕይወት መንገድ የሚመራቸው/2/
ክፍላችን እንዲሆን ከቅዱሳን ጋራ/2/
ፍቅር ቤታችንን በጸሎት እንሥራ /2/
ልባችንም ይሁን የጸሎት ጎዳና/2/
የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድንወርስ በጤና/2/

500.ፍቅርና ሰላምን

ፍቅርና ሰላምን ታፈራለች ጾም /2/
ፍጻሜ የሌለው እስከ ዘለዓለም/2/
የጾምንም ፍሬ ሁላችን እውቀን/2/
በጸሎት እንትጋ ፍሬው አይለፈን/2/
አምላክ ተፈተነ በክፉ ጠላት/2/
ጾምን ሊመሠርት ስለእኛ ሕይወት /2/
አምላክ ተሸክመ ሕመማችንን

የሕይወትን ውኃ ከጎኑ ሰጠን/2/
ሕዝቦችህን ጠብቅ ከክፉ ፈተና/2/
ቅዱስ አምላካችን ኃይላችን ነህና/2/

501. አሐዱስ

አሐዱስ ሶበ እም ማርያም ተወልደ/2/
ኮነነ ዘመደ/2/ ኮነነ ዘመደ/2/
በአምላክ ኅሊና የታሰበች
ከዓለም በፊት የታወቀች
በእርሷ ለማደር ቃል ተላከ
በነቢያትም ተሰበከ
አዝ------------
ከፍጥረቱ አስበልጦ
ከሴቶች ሁሉ እርሷን መርጦ
ዙፋኑን ትቶ መጣ ወረደ
ሥጋዋን ለብሶ ተዋሐደ
አዝ------------
በተዋህዶ አከበረን
ከእኛ ተወልዶ ዘመድ ሆነን
በማህፀኗ ለማደሩ
የገጠመ ነው ያ ምስጢሩ

502. ኦ. ድንግል ደስ ይበልሽ

ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ
ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
ገብርኤል በቃሉ ደስታን ያሰማሽ
ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
የዘለዓለም አምላክ እናት ስለሆንሽ
ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
ከፍጡራን ሁሉ  በላይ ስለሆንሽ
ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ

የነገስታት ንጉስ ዙፋን ስለሆንሽ
ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
የድኅነቴ ዓርማ ልዩ ምልክቴ
ለእኔም ነሽ እናቴ እመቤቴ
የድኅነቴ ዓርማ ልዩ ምልክቴ
ልዩ ነሽ እናቴ እመቤቴ
የምታማልጅን ከቸሩ አባታችን
ለእኛም እናታችን እመቤታችን/2/
የምታማልጅን ከቸሩ አምላካችን
ለእኛም እናታችን አስታራቂያችን
ስለ ውድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጵያ
ለልጆችሽ አሳሳቢ ብለሽ ሃሌ ሉያ
ድንግል ሆይ አሳሳቢ ብለሽ ሃሌ ሉያ/2/
ስለ ውድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጵያ
ለልጇሽ አሳሳቢ ብለሽ ሃሌ ሉያ

503. እኔስ በምግባሬ

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ
እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ /2/
ያንን የእሳት ባሕር እንዳላይ አደራ
ድረሽልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ /2/
የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መጽኃኒት ነይ በደመና/2/
አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ ረዳት ምርኩዜ /2/
አፈሳለሁ እንባ በጣም ተጨንቄ
እማጸንሻለሁ በደሌን አውቄ/2/

504. የእመቤታችን አማላጅነቷን

የእመቤታችን አማላጅነቷን ክብሯን
የቀነሰ ያዋረደ
እዳ አለብን /2/ ከፈጣሪያችን/2/
የተሰጣት ሙሉ ሥልጣን
ክብር ያገኘች በቃል ኪዳን
ስሟን የጠራ እንደሚድን
በመጽሐፍ ሲነገር
እዳ አለብን/2/ ከፈጣሪያችን/2/
ዻዊተ ኵሉ የተባለች
በነቅዱስ ኤፍሬም የተመሰገነች
በእነ አባ ጊዮርጊስ ምስጋናን ያገኘች
በመናፍቃን ዘንድ ምነው ተዘነጋች
እዳ አለብን/2/ ከፈጣሪያችን /2/

ከሴቶች ሁሉ ልዩ ናት እያልን
በሁለቱም ወገን በፍጹም ድንግል
የብርሃን እናቱ ማርያም ስትባል
በደካሞች ዘንድ ምነው ተዘነጋች
እዳ አለብን/2/ ከፈጣሪያችን/2/
ቃና ዘገሊላ ከልጅዋ ጋር ሳለች
ከሠርግ ቤት ገብታ ድንግል አማልዳለች
እንኳንስ እመአምላክ ቤዛዊተ ኩሉ
ጻድቃን ሰማዕታት በእውነት ያማልዳሉ
እዳ አለብን/2/ ከፈጣሪያችን/2/

505. ከፈጣሪ በታች

ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ/2/
ማን አለ እንዳንቺ ድንግል ንፁህ በአለም ላይ /2/
ኦ ድንግል ማርያም ዘላለም/2/
መኩሪያ ነሽ መመኪያ
አምላክ ለማደሪያ መርጦ ያዘጋጀሽ/2/
ጽዮን የተባለች ሀገር ድንግል ሆይ አንቺው ነሽ/2/
በሐሳብሽ ድንግል ድንግል በስጋሽ/2/
ከፍጥረታት ሁሉ ላንቺ ምሣሌም የለሽ/2/
ፍቅሩ ለዘላለም የማይጠገበው/2/
ከስም ሁሉ በላይ ጣፋጭ ድንግል የአንቺ ስም ነው/2/
በእዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና/2/
ይገባሻል ላንቺ ድንግል ሁልጊዜ ምስጋና
አዝ- - - - -
እስኪ ልያዝና ደጋፊ ምርኩዜን
እስኪ ልያዝና የረሃብ መድኃኒቴን
ወደ አምላኬ ቤት ልሄድ ልቀጥል ጉዞዬን/2/
አዝ - - - - - -
ለፍርድ ስጠራ በደለኛው እኔ/2/
የእኔ መማጸኛ ድንግል ቁሚልኝ ከጎኔ/2/

506. ድንግል ሆይ ስላንቺ

ድንግል ሆይ ስላንቺ ነውና መሐሪ
አማልጅን ከአንዱ ልጅሽ ከፈጣሪ
ስሙን እንዳልጠራው አንደበትም የለኝ
እንዳልጠራው ሥራዬ አሳፈረኝ
ታወቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ
አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሣሪ
አማልደኝ ከአምላክ ከፈጣሪ
በፊቱ እንዳላፍር የተጠራው ለታ
ጻድቃን ሰማዕታት እናንተም ሁላችሁ
አማልዱኝ ከአምላኬ ከአምላካችሁ

507. እናት አለኝ

እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ የምታጽናናኝ
እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ
የተቀኘላት እዝራ በመሰንቆ
እናትነቷን ንጽሕናዋን አውቆ
ያመሰገናት ዳዊት በበገና
አትለየኝም እናቴ ናትና /2/
ለቅስ ስተክዝ ወድቄ ከፊቷ
አቅፋ አጽናናችኝ እኔን ከደረቷ
ታስታርቃለች ሁሌ ለኃጥአን
ትማጸናለች በዕንባ ዝክር ልጇን/2/
የአዳም ተስፋ ናት ድንግል እናታችን
መርጦ ያደረባት ክርስቶስ ጌታችን
ታማልዳለች ዛሬም ለዘላለም
የአምላክ እናት የፍጥረታት ሰላም/2/

508. አድኝኝ እናቴ

አድኝኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
ሥጋዬ ከኃጠአት ከቶ አልራቀምና
ሸክሜ የከበደኝ ብቸኛ ሆኛለሁ
አትለይኝ ድንግል አደራ እልሻለሁ/2/
አዝ......
የአማኑኤል እናት የተዋሕዶ አክሊል
አትጥፊ ከመሀል እንድትሆኝን ኃይል
ምንም ቢበዛብሽ የእኛ ጉስቁልና
ከእኛ ጋር ከሆንሽ አለን ቅድስና/2/
አዝ.......
ተስፋዬ ነሽና እመካብሻለሁ
ግራ ቀኝም አልል ምርኮኛሽ ሆኛለሁ
ስቅበዘበዝ አይቶኝ ተስፋ የሰጠኝ
እግዚአብሔር ይመስገን ካንቺ ያስጠጋኝ/2/

አዝ......

በሥጋ ደክሜ በነፍስ እንዳልጠፋ
እማጸንሻለሁ ድንግል የእኔ ተስፋ
የመንግሥቱ ወራሽ እንድሆን አድርጊኝ
መልካም ሥራ መሥራት እኔን አስተምሪኝ/2/
አዝ......

አንቺ የሌለሽበት ጉባኤው ባዶ ነው
በቁም የደረቀ ሕይወት የተለየው
በመካከል ገብተሽ ሙዱው የጐደለውን
ሠርጉ ተደግሷል ጐብኝልን ጓዳውን/2/

509. <u>ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም</u>

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም
ድንግል ማርያም/2/
ንጽሕተ ንጹሐን ማርያም
ድንግል ማርያም /2/
ታማልዳለች ከልጇ ከመድኃኔዓለም /2/
ታማልዳለች ከልጇ /2/ ከመድኃኔዓለም
ታማልዳለች/4/ ልጄ ሆይ ይቅር በል እያለች
አባቶቻችን ነቢያት ወሐዋርያት/2/
ጻድቃን ወሰማዕታት
ያማልዳሉ በእውነት ያማልዳሉ /2/
የማልዳሉ በእውነት /2/ ያማልዳሉ
ያማልዳሉ /4/ አምላክ ሆይ ይቅር በል እያሉ
ሰባቱ ሊቃነ መላእክት ሚካኤል ወገብርኤል
ሩፋኤልና ፋኑኤል
ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ
ሰባቱ ሊቃናት መላዕክት አፍኒን ራጉኤልና
ሳቁኤል
ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ
ያማልዳሉ ከክፉም ይጠብቃሉ /2/
ያማልዳሉ ከክፉም /2/ ይጠብቃሉ
ያማልዳሉ /4/ ከክፉም ይጠብቃሉ
በዱር በገደል በበረሀ በዋሻም ያሉ /2/
ያማልዳሉ በእውነት ያማልዳሉ /2/
ያማልዳሉ በእውነት /2/ ያማልዳሉ
ያማልዳሉ /4/ አምላክ ሆይ ይቅር በል እያሉ

**510. ሀጢያቴ በዛ**

ኃጢአቴ በዛ እመቤቴ
ምሕረት ላኪልኝ ለሕይወቴ
የፈጣሪ እናት አዛኝት
በአንቺ ነው ማግኘት የጽድቅ ሕይወት/2/
ከሲዖል አውጪኝ አዛኝት
የጻድቃን እናት እመቤት
ሰላማዊት ናት ሀገረ እግዚአብሔር
በአንቺ ነው መወጣት ከኃጢአት ቀንበር/2/
የሚሰግዱልሽ ጻድቃን ሰማዕታት
የሚላኩልሽ ቅዱሳን መላዕክት
ከእነርሱ ጋር ነይ እመቤቴ
እንዲታረቀኝ ሰማያዊው አባቴ/2/
አስታርቂኝ እኔን ከልጅሽ
እማልዳለው ከፊትሽ
ስምሽን ጠርቶ ያፈረ ማነው
የአዳም ተሰፋ ስራሽ ድንቅ ነው/2/
የፍቅር እናት እመቤታችን
አስታርቂን እኛን ከጌታችን
ዘወትር ነይልን እናቴ ማርያም
ላንቺ ቅርብ ነው መድኃኔዓለም

511. <u>ነፍሴ ሆይ</u>

ነፍሴ ሆይ /2/ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ /2/
ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ
እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ
በምሕረቱና በቸርነቱ የሚጠብቅሽ የሚከልልሽ
ምኞትሽን በበረከቱ የሚያጠግባት
ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ
ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚልሽ ደዌሽንም ሁሉ
የሚፈውስ
ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት
ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ
ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ
እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ
ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ

512. <u>ዓይኑ ዘርግብ</u>

ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ /2/

ሐመልማለ ወርቅ /2/

ልብሱ ዘመብረቅ /2/

ነፍስና ሥጋዬ በምግብ ተጣልተው

መልአኩ ዑራኤል ቆሞ አስታረቃቸው

ለሰዎች ደኅንነት ጽድቅን የሚሰብከው

ነውና ዑራኤል የሰላም መልአክ

እጅና እግሬ ታስሮ ሽባ የነበርኩኝ

ይኸው ተጠምቄ በጠበሉ ዳንኩኝ

ስእለቴ ሰምሮልኝ ሁሉን አግኝቻለሁ

ለአምላክ ዑራኤል እመሰክራለሁ

አልፈልግም ሐኪም ምን ያደርግልኛል

አምላከ ዑራኤል ፈጥኖ ያድነኛል

ሕሙማን ለምኑ ስንፍና አይያዛችሁ

ኑና ተጠመቁ ጠበሉ አለላችሁ

ያመናችሁ ሰዎች ኑና ተጠመቁ

አማላጅነቱን በግልጽ አሳውቁ

አምላከ ዑራኤል አንተ ችላ አትበለኝ

መጥቻለሁና በችሎታህ እረዳኝ

513. <u>ምድር ጸዳች</u>

ምድር ጸዳች ሐሴት አደረገች

ምድር ጸዳች ከእድፍም ነጻች

በክርስቶስ ደም በእውነት ታጠበች/2/

ሴቶች ትንሣኤውን ሲያወሩ በደስታ/2/

ጮሐ ስትመሰክር ምድር አፍዋን ከፍታ/2/

የተዘጋው ዓለም ሲገለባበጥ/2/

ምን ተናገሩ አይሁድ ከፍርድ ለማምለጥ/2/

አያልቅባቸውም የእነርሱ ፈሊጥ/2/

መግነዙ ተገኘ ከመቃብር ወድቆ/2/

ምልክት እንዲሆን ተወላቸው አውቆ/2/

እሑድ በማለዳ መቃብሩን ሲያዩ

ሁሉም ተለውጦ ልቅሶው ደስታ ሆነ/2/

ሁለቱ መላእክት ብርሃን የለበሱ/2/

ተነሥቷል አሏቸው ሴቶቹ ሲደርሱ/2/

ሐዋርያት ሰምተው ዜና ትንሣኤውን/2/ አላቸው

በድንገት ሰላም ለእናንተ ይሁን/2/

514. እንደተቆጣኝ አልቀረም

እንደተቆጣኝ አልቀረም በርኅራኄው ማረኝ

ቁጣውን መልሶ ለነፍሴ ለልቤ መጽናኛ ሰጠኝ

ምን ልክፈለው ለአምላክ ለወደደኝ

ልስገድለት ላመስግነው ኃይል ይስጠኝ/2/

ዳገት ቁልቁለት በዛብኝ ለጽድቅ ወደአንተ ስጓዝ

ጠላት ተጠምጥሞ ከአንገቴ ጎንጎኔን ነደፈኝ በመርዝ

መፍትሔው ጠፋብኝ ስቃይ በዛብኝ

አምላኬ ሆይ በጥበብህ አላቀኝ /2/

ብቻኛ ነኝ ጭንቅ የያዘኝ የጠበበኝ

የዓለም ነፋስ ማእበሉ ያንገላታኝ

መላም የለኝ እኔ ተክዤ ቆሜአለሁ

ኃይሌ ጉልበቴ መድኃኒቴ በለኝ አለሁ/2/

ቆሜ ሳየው ፊት ኋላዬን ቀኝ ግራዬን

ረዳት የለኝ ምርኩዝ የለኝ ነኝ ብቻዬን

የውስጥ የውጭውን ዘርዝሬ የምነግረው

እንደነፍሴ የምቆጥረው የማዋየው/2/

አይተህ ይህን መጨነቄን መገፋቴን

ላክልኝ ለኔ ድንግልን እመቤቴን

ቅዱሳን ሰማእታት ጻድቃን መላዕክትን

ፍጥረትህ ነኝ እንዳልጠፋ አትጨክን /2/

የነበርክ ያለክ ለዘለዓለም የምትኖር

ከሥራዬ ባሳዝንህ ዘወትር

ያለረዳት አጽናኝ ብቻዬን ያልተውከኝ

ተስፋ አልቆርጥም ላመሰግንህ ፍቀድልኝ/2/

515. <u>ስለ እኔ የሞተው</u>

ቤዛ የሆነልኝ ስለእኔ የሞተው

በፍቅሩ ማረከኝ ጠራኝ በይቅርታው

ሰዎች ሲጸየፉኝ ሊወግሩኝ ሲያስቡ

እርሱ ተቀበለኝ በሚራራ ልቡ

ቀረብኩኝ ወደ እርሱ ሽክሜን ተሸክሜ

ጭነቴ ተራግፎ እንዲቀየር ስሜ

ከእግሩ ሥር ተደፋሁኝ አምኜ በደሌን

በዕንባዬ አጠብኩት ንጽሕ ቅዱስ

ኃጢአተኛ ሳለሁ እርሱ ግን ወደደኝ

ሰው ቢፈርድብኝ አምላኬ ነጻ አወጣኝ
እንደሰው ፍርድማ ተወግሬ ነበር
እርሱ ግን ታደገኝ አነጻኝ በፍቅር
ሽቱውን ቀባሁት ሰጠሁት መባዬን
እርሱም ተቀበለኝ ለወጠው ታሪኬን
የኃጢአት ኑሮ ጨለማ ሕይወቴን
ብርሃን ሆነልኝ ቃሉን በመስማቴ
እንደሰው አይደለም ጥፋቴን አይወድም
ይምረኛል እንጂ በሰው ላይ አይፈርድም
እኔን ከፍ ያደረከኝ ከወዳቂነቴ
ምስጋና ይድረስህ የሰማዩ አባቴ

516. <u>የጌታዬ እናት ጸለየች</u>

የጌታዬ እናት ጸለየች
ማርያምም እንዲህ እያለች /2/
ነፍሴ ጌታዬን ታከብረዋለች
መንፈሴም በአምላኬ ሐሴት ታደርጋለች
<u>የእኔን የባርያይቱን ትኅትና</u>
<u>የእስራኤል አምላክ ተመልክቷልና /2/</u>
ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል
እርሱ ታላቅ ሥራ አድርጐልኛል
<u>ስሙም ቅዱስ ነው ምሕረቱም</u>
<u>ለትውልድ ትውልድ ለዘላለም /2/</u>
ኃይል አድርጓል ጌታ በክንዱ
ትዕቢተኞች ተዋረዱ
<u>ገዢዎች ከዙፋን ስለተጣሉ</u>
<u>ትሁታን ደግሞ ከፍ ከፍ አሉ /2/</u>
ባለጠጐች ሲጠሙ ሲራቡ
ድሆች በምሕረት ጥቂት ጠገቡ
<u>ለአባቶቻችን እንደማለ</u>
<u>ምሕረቱን አስቦ እኛን ተቀበለ /2/</u>

517. <u>እግዚአብሔር አለኝታችን</u>

እግዚአብሔር አለኝታችን ግሩም ነው
እግዚአብሔር ግሩም ነው ኃያል ነው
ለጠላት ክንዱ ብርቱ ኃያል ነው
ሕዝቡን ሲመግብ እጁ ሰፊ ነው
የማያልቅበት ቸር እረኛ ነው
ሰማይና ምድርን የፈጠረ
<u>ክዋክብትን በሕዋ ያኖረ</u>
በቃሉ ብቻ ምድርን ያጸና
ማን ያክለዋል እርሱን በዝና
በሞት ጥላ ውስጥ አምላክ ታደገን
በሐዘን ጊዜ ጌታ ጐበኘን
ፍቅሩ ኃያል ነው ሩኅሩኅ ጌታ
ምን ወሰን አለው ለአንተ ውለታ

518. <u>ከዳዊት አብራክ</u>

ከዳዊት አብራክ ዘርን ባያስቀርልን ኑሮ
አዳም በሲዖል በቀረ በውርደት አንገቱን ቀብሮ
ዝምታ በወረረን በወደቅን ማቅለብሰን
ቸርነቱ በዝቶ ግን እመቤታችንን ሰጠን
ፀሐይ ክርስቶስ ወጣ ከቤተልሔም ሀገር
የእንጀራ ቤት ነችና የእኛ የፍቅር ባሕር
ተበልቶ አይጠግብም የማኅፀንሽ ፍሬ
ሕይወት ሆኖን በላነው የማኅፀንሽን ፍሬ
ግርማዋ የሚያስፈራ የሙሴ ቤተመቅደስ
ተገናኙብሽ በሰላም ሰውና ሥሉስ ቅዱስ
የወርቅ መንበር ነሽና ደመና የከበበሽ
የሥላሴ ሙሽራ <u>ዕፁብ</u>/2/ ድንቅ ነሽ

519. <u>ስሜ ተለውጦ</u>

ስሜ ተለውጦ ዘማዊ ብባልም
ራራልኝ ጌታ ነውሬን አልቆጠረም
ፈሪሳዊያኑ አካልበው ቢወስዱኝ
ኢየሱስ ግን በፍቅር ፊት አየኝ በርኅራኄ አየኝ
.. በፍቅር ፊት አየኝ በርኅራኄ አየኝ
የተደበደበው አካሌን ስላየ
ስለእኔ መዋረድ አምላክ ተሰቃየ
አወጣኝ ከድንጋይ ከቀያፋ በትር
ለእኔ ያደረገውን <u>ኧረ እንዴት ልዘርዝር /4/</u>
ከዘማዊት ሴት ጋር አወራ ተብሎ
መስቀል አደረገ ስሜን ተቀብሎ
ቀራጭና ዘማን ያድናል ይባላል
ትከሻው ሰፊ ነው <u>እኛን ተሸክሟል</u> /4/
ከኃጢአት ስወድቅ በሕይወት ዘመኔ
ቸርነቱ በዝቷል በረከቱ ለእኔ
መሐሪ መሆኑን ጌታ ሲገልጽላት
በልዩ ቸርነት <u>ዘማዊቷን ጠራት</u> /4/

ነውር ያለባችሁ ተሰብሰቡ በእርሱ
ከውርደት ያድናል መሐሪ ነው እርሱ
ለበሽተኞች ነው የመጣሁት ብሏል
ነፍስና ቁስልህን ደዌህን የድናል /4/

520. ተሰቀልክ ወይ

ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ወይ /2/
ምድር አለቀሰች እያለች ዋይ ዋይ
ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ወይ
ኮረብቶች ደንግጠው መድረሻ ጠፋታቸው
ከዋክብትም ፈርተው ጨለማ ዋጣቸው
እጅግ አይደንቅም ወይ ጌታ መሰቀሉ
የጌቶቹ ጌታ ችንካር ላይ መዋሉ
ሰማይና ምድርን በፈጠረበት
ጨለማና ብርሃን ባደረገበት
ችንካር ተከሉበት መትተው በብረት /2/
ድንግል አለቀሰች ዕንባዋ ፈሰሰ
ስደተኛ ልጅዋ መከራን ቀመሰ
ሕማሙን ሳስበው አለቅሳለሁኝ
የስቃዩን ነገር አስባለሁኝ
ዕንባዬን ጠራርጐ ርሃቤን ተካፍሎ
ሞተልኝ ጌታዬ ስለ ሞቴ ብሎ
እኔ ልሙትልህ ሲለኝ ሰማሁት
እንዲህ የወደደኝ ምን አደረኩለት

521. ዛሬ ተይዣለሁ

ዛሬ ተይዣለሁ በፍቅሩ ስጦታ
ውለታህ ማርኮኛል የሠራዊት ጌታ
ከአመድ ያነሣኸኝ ከትቢያ ተጥዬ
ውለታህ ከበደኝ ማረከኝ ጌታዬ /2/
ያልሰጠኸኝ ነገር በዚህ ምድር የለም
ፍቅርህ ወሰን የለው ድንቅ ነው ዘላለም
እኔነቴን ሳስብ ምንድን ነኝ እላለሁ
ፍቅርህን ሳስተውል ሁል ጊዜ አለቅሳለሁ
/2/
ለብቻዬ ሆኜ አምላኬን ሳስበው
ከኀሊና በላይ ውለታህ ብዙ ነው
የተጣለውን ሰው ማንሳት ያውቅበታል
ምስኪኑን ሲያጽናና ከሁሉ ይበልጣል/2/
ሰው ነህ ተብያለሁ አንተ ሰው ስላልከኝ
ማን ያስታውሰኛል አንተ ባታከብረኝ
አትጣለኝ አንተ ሁሉም ያከብሩኛል
ኃጢአቴን ባትቆጥር ለእኔ ይበቃኛል

522. ስምህ በሁሉ ተመሰገነ

ስምህ በሁሎ ተመሰገነ
ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ
አንተን ማወደስ ያስደስተናል
ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል
አምላክ ተመስገን በሰማያት
ስምህ ይወደስ በፍጥረታት
ከሕፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ
አንተን ማመስገን ይሁን የእኛ እጣ /2/
በምግብ እጦት ብንሰቃይም
ማኀሌትህን አናቋርጥም
የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም
እንዘምራለን ለአምላካችን ስም /2/
ሰማዩ ዝናብ ደመና ሲያጣ
ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም
ቸርነትህን እንጠብቃለን
ከአንተ ደጅ ጌታ የት እንሄዳለን /2/

523. ማን ነው እርሱ

ማን ነው እርሱ ማን ነው እርሱ/2/
ምድርን የሠራ በኃያል ቃሉ ማን ነው እርሱ
ሕይወትን የሰጠ ለፍጥረት ሁሉ ማን ነው እርሱ
የባሕርን ሞገድ የሚገስጸው ማን ነው እርሱ
የኃይላት ጌታ ጌታችን ማን ነው ማን ነው እርሱ ማን ነው እርሱ /2/
ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ
ማነው ጌታችን ሁሉንም የሚያይ
ማን ነው እርሱ ማን ነው እርሱ
ከፈሳሾች ውስጥ ወንዙን የሚያፈስ
ማን ነው እርሱ
ምድርን ልምላሜ ፍጹም የሚያለብስ
ማን ነው እርሱ
ጥቃቅን ነፍሳት የሚመግበው
ማን ነው እርሱ

የሚመሰገን ጌታችን ማን ነው
ማን ነው እርሱ
አዝ-------------
የሰማይ መብረቅ የሚያንጐዳጉድ
ማን ነው እርሱ
በፍትሕ በእውነት ለጽድቅ የሚፈርድ
ማን ነው እርሱ
አምሳያ ለእርሱ የሌለው ጌታ
ማን ነው እርሱ
እግዚአብሔር ስሙ የሁሉ አለኝታ
ማን ነው እርሱ
አዝ-----------
ስብራትህን የሚጠግነው ማን ነው እርሱ
ትንሽነትህን የማይጸየፍ ማን ነው እርሱ
አድሎን የማያውቅ ለሰዎች ፊት " "
ለሁሉ የሚሰጥ የጽድቅ ሕይወት " "
አዝ----------------
እውነትና ምሕረት የከበቡት
ማን ነው እርሱ
ለሕዝብ የሚሰጥ ልዩ ሕይወት
ማን ነው እርሱ
የሚፈሩትን የሚያከብራቸው
ማን ነው እርሱ
የአማልክት አምላክ ስሙ ቅዱስ ነው " "
አዝ-------------

524. ስምሽ ማርያም

የተወደደ ስምሽ ማርያም
እንዳንቺ ንጹሕ በዓለም የለም
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
በንጽሕናሽ በመመረጥሽ
ድንግል በእውነት እጹብ ድንቅ ነሽ
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
ፍጥረታት አንቺን ይማጸኑሻል
ከሲዖል ዓለም አውጪን ይሉሻል
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
አስራትሽን ኢትዮጵያን
ጠቢቅልን ድንግል ሕዝቧን
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም

525. በዘር አንድ የሆነው

በዘር አንድ የሆነው ሌዋዊው ትቶኛል
ባዕዱ ሳምራዊ ከሞት አድኖኛል
በቁስሌ ላይ ዘይት የሚያስ ፍቅረኛ
የሰላም ሰው ስጠኝ ሁነኛ ጓደኛ /2/
ከማይጠፋው ትውልድ ስለተወለድን
አይቀርም እመኑ በምድር ዘራችን
ከእግዚአብሔር ተወልደን ልጆች ተብለናል
ባሮች አይደለንም ነጻነት ወጥተናል /2/
አንተን የሚመስል ቀናና የዋኅ ሰው
ወንጌልኽን ነገረኝ ሕይወቴን ለወጠው
ዓለም የሰጠችን ሞት ነበረ ድሮ
ክርስቲያን አዳነኝ ወንጌልን አስተምሮ /2/
በሥጋና በደም የማልዛመደው
በክርስቶስ ጥምቀት ዘሩ ከእኔ ጋር ነው
ጓደኛዬ እርሱ ነው ሕይወት የሚሰጠኝ
በቃሉ በፍቅሩ ተመስጫለሁኝ /2/
ልቡ ቅን የሆነ ጓደኛ መርጬ
ሰላሜ ልዩ ነው ዛሬ ተለውጬ
ክርስቲያን በሙሉ በዚህ ያስታውቃል
ፍቅሩ ይለውጣል ሥራው ይማርካል/2/
ከዓለም ጉድጓድ ውስጥ መስዬ ወድቄ
ይኸው ሰላም ሆንኩኝ ከአምላከ ታርቄ
እውነተኛ ፍቅር አስተማረኝና
አዲስ አደረገኝ እኔን ክርስትና /2/

526. ተስፋ አለኝ

ተስፋ አለኝ በአምላኬ
ተስፋ አለኝ በእግዚአብሔር
ምናምንቴ ሆኜ በዚህች ምድር ብኖር
ተስፋ አለኝ በእግዚአብሔር
ጥበብ የተሞሉ ታላላቅ ኃይለኞች
ሥልጣን የጨበጡ የምድር ብርቱዎች
ስላልተመረጡ በሀብታቸው ብዛት
ተስፋ አለኝ ለጽድቁ ለሰማያዊ ቤት/2/
የአምላክ ዓይን ልዩ ነው አያዳላም ለሰው
ፍቅሩ ለፍጥረቱ ምንጊዜም እኩል ነው

ፀሐይን ለፍጥረት ያወጣል በእኩል
ጻድቅና ኃጥእ ክፉ ሰው ነው ሳይል/2/
በኃጢአት ብወድቅም ሕይወቴ ቢጉድፍ
በንስሓ ዳንኩኝ እኔ ሳልቀሰፍ
አምላክ ቸርነቱ ምሕረቱ አድኖኝ
አዲሲቷን ምድር እናፍቃለሁኝ /2/
ያለፈው በደሌ ተደምስሷልና
ወደፊት ለፍቅሩ ለጽድቅ ሥራ ልቅና
በዓለም ከሚኖሩ ባለተስፋ ሁነውሰላም ያገኛል
ክርስቶስን መርጠው /2/

### 527. አልፈርድም እኔ

አልፈርድም እኔ በማንም በደል በማንም ኃጢአት
በፈረድኩበት እንዳልመዘን ጌታ ሲመጣ በኃይል
በሥልጣን
በቸርነቱ አምላክ ባይተወው በደሌን ሁሉ
ውስጤ ቢፈተሽ በተሰጠኝ ሕግ በቅዱስ ቃሉ
በምን ምግባሬ በሰው ፈርዳለሁ ዓይኔን አቅንቼ
በደል በዝቶ ለራሴ ሳላውቅ በኃጢአት ሞቼ

ይልቅ የአንዱን ሸክም ሌላው ሰው አዝሎ መጓዝ
ይሻላል
መፍረድ ከመጣ አንድም ሰው አይድን ሁሉም
በድሏል
ወንድም ወንድሙን እየከሰሰ ለፍርድ አቁሞ
አሕዛብ ያያል በንትርኩ እጅግ ተገርሞ

ክርስቲያን ሆኖ ከወንድሙ ጋር እየተጣላ
ዓለም ዳኝችን በጸብ ፍርድ ቤት ታረቁ ብላ
ክርስቲያን ሆነን በአሕዛብ መሃል እየተካሰስን
አምላክ አዘነ የመስቀሉን ዓላማ ትተን

መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል እንጂ ለጠላቶቹ ምሕረት ሲለምን
ለጽድቅ ሥራ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማን ነው የሾመን በወንድሞች ላይ አርጐ ፈራጅ

መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል እንጂ ለጠላቶቹ ምሕረት ሲለምን
በጽድቅ ሥራ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማነው የሾመን በወንድሞች ላይ አድርጐ ፈራጅ

### 528. ምስጋና ጀመረ

ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ማኅሌታይ ያሬድ ዘኢትዮጵያ
ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ

ይበል /2/ ይበል ሃሌ ሉያ
ጥዑመ ልሳን ያሬድ ዘኢትዮጵያ

ብሉይን ከሐዲስ ሐዲስን ከብሉይ
አስተባብሮ ቃኘው ያሬድ ማኅሌታይ
ምሥጢር ተገልጾለት ከምድር እስከ ሰማይ

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሥጢር እያስማማ
ምስጋና ጀመረ በጽዮን ከተማ
ለቅድስት ሥላሴ በሦስት ዓይነት ዜማ

በወርቅ ጽናጽል በብር ከበሮ
ዜማው ሲንቆረቆር በሰው ልጆች ጆሮ
የያሬድ ዝማሬ ያድሳል አእምሮ

ተዋሕዶ አቅርቢ ለአምላክ ምስጋና
በፅዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና
ዜማውን ከያሬድ ተምረሻልና

### 529. ዮሐንስ ሔደ ዮርዳኖስ

ዮሐንስ /2/ ሔደ ዮርዳኖስ
የበደለውን ሕዝብ ጠረቶ ለንስሓ
ያስተምር ጀመረ ገብቶ ከበረሐ
አባጣ ጎባጣ ጠማማ ኮረብታ
ይስተካከል አለ ሁሉም በየቦታ

በዮርዳኖስ ማዶ በሔኖን ከተማ

የንስሓ ጥሪ በሩቁ ተሰማ
ግመል ጸጉር ለብሶ ወገቡን ታጠቀ
ዮሐንስ ተመርጦ ጌታን አጠመቀ

ባሕር ተጨነቀች ሸሸችም በፍርሃት
እሳተ መለኮት እንዳያቃጥላት
መንፈስቅዱስ መጣ ሲሆነው ምስክር
ከአብ መወለዱን ልጅነቱን ሲያከብር

530. <u>ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ</u>
ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ /2/
ተንገላታህ ላብህ እስኪፈስ
አመላለሱህ አስረው ገረፉህ
ፊትህን ሸፍነው በብትር መቱህ

እንደ ተራ ሰው እንደ ቀጣፊ
እጅህን አስረው መቱህ በጥፊ

ከመሳፍንቱ ከመኳንንቱ
አደባባይ ዋልክ ደርሶ ትንቢቱ

መስፍኑ ቆሞ ምን ላድርገው ቢል
ሁሉም በጩኸት አሉት ይሰቀል

ሁሉም ከሰሱቱ ሁሉም ጮኩበት
የነገሥታት ንጉሥ ተፈረደበት

531. <u>እንዲህ አለው ጴጥሮስ</u>
እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስን
ምሥጢር ገሃድ ሲሆን በዚያ በተራራ
ባንድ ላይ እንኑር ሦስት ዳስ እንስራ
አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱን
ለኤልያስ

ተለወጠ ገጹ ከመ ጽጌሬዳ
ወርዶ ከለላቸው ደመና ጸዓዳ

ከሰማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ሲል

ኤልያስም ሄደ በሰረገላው
ሙሴም ከመቃብር ወደ መኖሪያው

ስለአስደነቃቸው ግሩም ተአምራቱ
ይህን ምሥጢር አይተው ተሰነባበቱ

532. <u>አምላካችን ቅዱስ ነው</u>
አምላካችን ቅዱስ ነህ
ፈጣሪያችን ቡሩክ ነህ
የዘለዓለም አምላክ ነህ/2/

የአዳም ልጅ ከትቢያ/2/ ወደ ነበረበት
መልሶም ከአፈር እንዲሆን ከመሬት
በተናገርከው ቃል ባዘዝከው መሠረት
እንደ ጒርፍ መጥተህ ትወስዳለህ ድንገት

ከሕልም የረዘመ/2/ ሕይወት የለንም
ማለዳ እንደሚበቅል እንደ ጠዋት አረም
ጠውልጒ እንደሚቀር እንደ ጠዋት አረም

ሕይወትህ ናትና እንደ ጠዋት ጤዛ
ረግፎ ለሚቀር ውበትና ለዛ
እባክህ የሰው ልጅ ኃጢአትን አታብዛ

ዕድሜያችን ሰባ ዓመት ቢበዛ ሰማንያ
በመከራ ያልቃል እርሱም በዓለም ዙሪያ
እኛም እናልፋለን በጭራሽ ሳንሠራ
በራስ ተሸክመን የኃጢአት አዝመራ

የመከራ ዓመታት አሳልፈናል
ፍርድህን በመፍራት ተሸብረናል

እባክህ ጌታ ሆይ በቸሮታህ ሥራ
ለአገልጋዮችህ አምላክ ሆይ ራራ

533. <u>አስተርአየ ገብርኤል ግብተ</u>

አስተርአየ ገብርኤል ግብተ
ወእንዘ ትፈትል /4/ ወርቀ ወሜላት

ከአዳም ልጅ መካከል ከእነዳዊት ዘር
መርጦ ተወለደ ከድንግል በክብር
ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ
አዳምን ሊያድነው ስላየው ተራቁቶ
ሐር እየፈተለች ቤተመቅደስ ሆኖ
ገብርኤል ነገራት ሰማያዊ ዜና
ትፀንሲ ብሎ በድንቅ ሰላምታ
ከማኅፀኗ አደረ ቃሉ ሳይፈታ
ከልዑል ዙፋኑ ከመንበሩ ወርዶ
አዳነን ከፍዳ ከማርያም ተወልዶ
የነገሥታት ንጉሥ ቤዛ ኩሉ ዓለም
ሥጋዋን ለበሰ መድኃኔዓለም
ንጉሥ መወለዱን ሰብአሰገል ሰምተው
አምኃ አቀረቡ ከሩቅ ምሥራቅ መጥተው
የዳዊት መዝሙሩ ተፈጸመለት
የሳባ ነገሥታት ወርቅ አመጡለት

534. <u>ነፍሴ ሆይ</u>

ነፍሴ ሆይ /2/ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ/2/
የተቀበለው በቀራንዮ ያን ሁሉ መከራ በመስቀሉ ላይ
ለአንቺ ሲል ነውና ነፍሴ ሆይ
ተዘጋጅተሽ ኑሪ ሁል ጊዜ በነገ በዛሬ
እንዳትታለይ /2/ ነፍሴ ሆይ
በንስሓ ጥምቀት ታጠቢና ክቡር ደሙን ጠጪ
ሥጋውንም ብይ /2/ ነፍሴ ሆይ
ዘለዓለም በደስታ እንድትኖሪ ከዘለዓለም ቤትሽ
መንግሥተ ሰማይ መንግሥተ ሰማይ ነፍሴ ሆይ

535. <u>እግዚአብሔርን ጥራው</u>

እግዚአብሔርን ጥራው በመከራ ጊዜ
ያድንሃልና ከሐዘን ከትካዜ
ጋሻና ጦሬ ብለህ ምርኩዜ
አመስግንህ ዘንድ እነሣለሁ በእኩለ ሌሊት
እንዳመሰገነህ ነብዩ ዳዊት
በንጹሕ ልቡና እንደ መላእክት
እግዚአብሔርን ጥራው
በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ
እርስ በርሳችሁም ተዋደዱ
ጸብና ክርክር እንዲወገዱ
እግዚአብሔርን ጥራው
እምነትን ከሥራ አስተባብረህ ከልብ
በወጣትነህ ፈጣሪህን አስብ
ሥራህም በሰው ፊት ይብራ
እንደ ፀሐይ ይብራ እንደ ኮከብ
እግዚአብሔርን ጥራው
በቤተ ክርስቲያን ጸሎት በድንግል ኪዳን
አቤቱ ጠብቃት ኢትዮጵያን
ለሕዝቧም ስጣቸው ፍቅር አንድነትን
እግዚአብሔርን ጥራው
እለምንሃለሁ አምላኬ ሆይ አንዲት ነገር
ከቤትህ ገብቼ በደስታ እንድኖር
ከባለሟሎችህ ከአብርሃም ከይስሐቅ
ከያዕቆብ ጋር
እግዚአብሔርን ጥራው
ደርሶልኛልና በመከራ ቀን
አከብረዋለሁኝ ቅዱስ አምላኬን
እጆቼንም ይዞ የሚመራኝን
እግዚአብሔርን ጥራው
ኑሮዬ ሲጨልም ግራ ሲገባኝ
ያለ ፈጣሪዬ ዘመድም የለኝ
ብወድቅ የሚያነሳኝ የሚደግፈኝ

536. <u>አምላክ ሆይ</u>

አምላክ ሆይ አደራ ያን ጊዜ እንድትራራ
አምላክ ሆይ አደራ ስለእኛ እንድትራሪ

ወደ አፈርነት ፈጥነህ ሳትመለስ
የሰው ልጅ ተዘጋጅ በንስሓ ታጥበህ
ነውና ዕድሜያችን እንደ አደይ አበባ
ነገ ሳይሆን ዛሬ ንስሓ እንግባ
ሰው በአፉ ቢያምን በልቦናው ክዶ
ምንም ጥቅም የለው ያለ ተዋሕዶ
ፈራሹ ሥጋዬ ለማትፈርሰው ነፍሴ
እባክህ ተገዛ ለቅድስት ሥላሴ
ምንም ብበድልህ ቢበዛ ኃጢአቴ
አቤቱ አትቅሰፈኝ በወጣትነቴ
ለፍርድ ስትመጣ በእለተ ምጽዓት
ምን እመልስ ይሆን አምላክ ከአንተ ፊት

537. <u>ሞትን ድል አድርጐ</u>

ሞትን ድል አድርጐ ተነሣ ክርስቶስ ተነሣ
እሰይ/2/
እኛንም ከሞት ሊያስነሣ
ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ
ሰላም ሰላም ለሰው ልጆች በምድር ሆነ ሰላም
ነፍሳትን ነጻ አወጣ ከጨለማ ጓሮ እሰይ /2/
የሲኦልን በር ሰብሮ
ኃይሉንም በኃይሉ ሽሮ
ሞት በትንሣኤ ተሻረ የሰው ልጅ ከበረ
እሰይ/2/
ጠላት ዲያብሎስ አፈረ
እጅና እግሩንም ታሰረ
እንዳይኖር ለዘለዓለም ሞት በአዳም ላይ ነግሶ
እሰይ/2/
ክርስቶስ ተነሣ ሞትን ደምስሶ
ግርማ መለኮቱን ለብሶ

538. <u>አንጻኝ</u>

አንጻኝ እጠበኝ ከኃጢአቴ /2/
አንተ ነህና መድኃኒቴ
አንተ ነህና ረዳቴ አንጻኝ እጠበኝ ከኃጢአቴ /2/
ላንተ ይገዛ ሰውነቴ
ይቅር ከእንግዲህ መዋተቴ
ፊትህን መልስ ራራልኝ
<u>ልኑር ከአንተ ጋር እዘንልኝ/2/</u>
እንዳልመለስ ወደኋላ
የኃጢአትን ፍሬ እንዳልበላ
ጠብቀኝ እንጂ በኃይልህ
እንዳልወድቅብህ ልጅህ
ኃጢአቴን አጥበህ አሣርፈኝ
አምላኬ አንተነህ ሌላም የለኝ
እኔነቴን ሳስብ አሳዘነኝ
ልኑር ከአንተ ጋር እዘንልኝ

539. <u>ተይ ተመከሪ</u>

ተይ ተመከሪ ነፍሴ ሆይ ተይ ተመከሪ /2/
በዓለም መድኃኒት ነፍሴ ሆይ
በእግዚአብሔር ታመኚ
ለሥጋ መገዛት ነፍሴ ሆይ
ምንው ቢቀርብሽ
ውርደት ነው ፍጻሜው " "
የሚያከናንብሽ
መልካም የሆነውን " "
ጽድቁን ተከተይ
<u>ክርስቶስን መስለሽ</u> " "
<u>ቸርነትን ሥሪ</u> /2/
ሞትን ማን ይመርጣል ነፍሴ ሆይ
ሕይወትን በመጥላት
ከእንግዲህ መራቅ ነው " "
ከስርቆት ከዝሙት
ጸጋ እንዲበዛልሽ " "
የቃሉ በረከት
<u>ከቤቱ አትጥፊ</u> " "
<u>ፍቅር ከሞላበት</u> /2/
ለአንቺ ነበር ጌታ ነፍሴ ሆይ
ደሙን ያፈሰሰው
ተሰቅሎ ሞቶ ነው " "
ፍቅሩን የገለጸው
በፍቅሩ ለሳበኝ " "
ዘወትር ጠዋት ማታ
<u>ምስጋና አቀርባለሁ</u> " "
<u>ዘወትር ጠዋት ማታ</u> /2/
ብወድቅ ምርኩዝ ድጋፍ ነፍሴ ሆይ

ጋሻ ይሆነኛል
ለፍርድ አይቸኩልም " "
በፍቅሩ ያየኛል
<u>ማን እንደ እርሱ አለ</u> " "
<u>የሕይወቴ ቤዛ</u> /2/

**540. <u>ነይ ነይ</u>**

ነይ ነይ እመቤቴ ነይ ነይ
ነይ ነይ ድንግል ማርያም ነይ ነይ
ነይ ነይ የእኛ አማላጅ ነይ ነይ
ነይ ነይ የእኛ ተስፋ ነይልኝ
<u>ከአንቺ በስተቀር ማንም የለኝ</u>
<u>ድንግል ማርያም ሆይ ድረሽልኝ</u> /2/
በዚያች በጠባብ በር ነይ ነይ
ማንስ ይወስደኛል " "
ይህ ደካማ ሥጋ " "
ሰፊውን ይለኛል ነይ ነይ
በሰፊውም ሄጄ " "
አሁን ወድቂያለሁ " "
እመአምላክ ከዚህ አውጪኝ ነይ ነይ
ተማጽኜሻለሁ " "
ምሪኝ ተከተይኝ " " አላውቅም
መንገዱን " "
ወደ ሕይወት ጐዳና " "
የሚያሻግረውን " "
ኃጢአትና በደል ነይ ነይ
በላዬ ላይ ሰፍሮ " "
ጽድቅን እንዳልሠራ " "
ይዞኛል ቀስፎ " "
ዓለማዊ ነገር " "
የጠቀመኝ መስሎኝ " "
በዲያብሎስ ታንቄ ቀረሁ " "
ከዲያብሎስ ገመድ " "
ኸረ አንቺው አውጪኝ " "
አዛኚት ነሽና " "
አትጨክኚብኝ " "
የዳዊት መሰንቆ ነይ ነይ
የኤልያስ መና " "
እናቴ ልበልሽ " "
አዛኝት ነሽና " "
አንቺንም ተማጽኖ " "
ያጣ የለምና " "
አንቺው አርቂልኝ " "
ያን ሰይጣን መሰሪ " "
ከእኔ ሳትለይ " "
ከእኛው ጋር ኑሪ " "

**541. <u>ስምሽ ጣዕም አለው</u>**

ስምሽ ጣዕም አለው ኪዳነምሕረት /2/
በላኤሰብእም ይህን አሰበ
ከጥርኝ ውኃ አንጠባጠበ
ልቤ በልጅሽ ላይ ሲያምጽ በጭካኔ
ይህን ዓለም አይቶ ሲንከራተት ዓይኔ
በልቤ ጽላት ተሣይብኝ
ጣዕምሽ ከዓለም እንዲለየኝ/2/
ጠላት ሲፈትነኝ ሊጥለኝ በሥጋ
በክፉ ምኞቴ ነፍሴ ስትወጋ
እንደ አባቶቼ ልጥራሽ እኔም
ማን አለኝና በዚህ ዓለም/2/
በስምሽ ተማጽነው ነፍሳት ተምረዋል
ከቅዱሳን ዓለም ምሕረት አግኝተዋል
ወደብ ነሽ አንቺ ማረፊያ ቦታ
እየወደድኩሽ ልኑር በደስታ

**542. <u>እመቤቴ ስልሽ</u>**

እመቤቴ ስልሽ ፊትሽ ተንበርክኬ/2/
አማልጅኝ ከልጅሽ ከቸሩ አምላኬ
ሳለቅስ ስተክዝ ስወድቅ ከደጅሽ /2/
አይዞህ አለሁ በይኝ ድንግል ስለምንሽ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲርድ ሰውነቴ
ባዶነት ሲሰማኝ ጠፍቶኝ እኔነቴ
ድረሽልኝ ድንግል መጽናኛ እናቴ
የዓለም ስደተኛ ሆኜ ቀርቻለሁ
የዓለም መጻተኛ ሆኜ ቀርቻለሁ
ድንግል በስደትሽ አማልጅኝ እላለሁ

ዓለሙ ዘርግቶ ጥላውን በእኔ ላይ
አልቻልኩትምና ይኸን ሁሉ ስቃይ
ሰላማዊት እናት ድንግል ሆይ
ሰላምን ሕይወትን ከሚሰጠው አምላክ
ፍቅርን ቸርነትን ከሚያድለው አምላክ
በአንቺ አማላጅነት ሕይወቴ ትባረክ

543. መልእእተ ወንጌል

መልእክተ ወንጌል በደሙ የጻፈ
ስቃዩን ታግሶ ችሎ ያሣለፈ
በርሀብ በግርፋት በግዞት አብዝቶ
በገድል በትሩፋት ጠላትን ድል ነሰቶ
ንዋየ ኅሩይ ነው ለዓለም ያበራ
ሐዋርያው ጳውሎስ ለጽድቅ የተጠራ /2/
እንቅልፋን እያጣ ሌት ተቀን ሳይታክት
የኂላውን ትቶ ተጓዘ ወደፊት
በድካም ተጠምዶ በገድል እያረሠ
ከደማስቆ እስከ ሮም ቃሉን አዳረሠ
እውነትን መናገር ከቶ ያላፈረ
ሕዝብን ከአሕዛብ በአንድ ያስተባበረ
አምላኩ እንዳይናቅ ከልቡ የተጋ
ጸንቶ የተጓዘ ለምትበልጠው ጸጋ

በሮም አደባባይ ሰማዕት የሆነ
የተዋሕዶ አርበኛ ለአምላክ የታመነ
በጣዕመ ስብከቱ ዓለሙን አጣፋጦ
አክሊል ተቀዳጀ ሳይታክት ሮጦ

544. አባታችን ሆይ

አባታችን ሆይ የሁላችን ጌታ /2/
ቅዱስ መንፈስህን ስጠን በተርታ/2/
ወደአንተ መልሰው የሰውን ልቦና /2/
ባላወቀው መንገድ እርሱ ሄዷልና
እዝነ ምሕረትህን ወደኛ አዘንብል /2/
ይቅርታን ልንጠይቅ ከፊትህ ቆመናል
ይቅርታን ልንጠይቅ ከፊትህ የቆምነው /2/
ምሐሪ መሆንክን ስለምናውቅ ነው
ትዕግሥትህ ሰፊ ነው አያልቅም ምሕረትህ /2/
የፍቅር ባለቤት ይቅር ባይ አንተ ነህ
አይቶ እንዳላየ ታልፈዋለህ ሁሉን /2/
መዓቱም ምሕረቱም ሁሉም ያንተ ሲሆን
ሥልጣንህ ረቂቅ ነው አይመረመርም /2/
ዘመንና ወራት ሊሽሩት አይችሉም
የፍቅር ባቤት ቸሩ አምላካችን /2/
እድሜን ለንስሓ ስጠን ለሁላችን/2/
እንማልድሃለን በለቅሶ በሐዘን /2/
የይቅርታህ ብዛት ከእኛ ጋር እንዲሆን
የሰማይ መላእክት የምድር ሠራዊት /2/
ያመሰግኑሃል በቀንና ሌሊት።

545. የሰው ልጅ ሁል ጊዜ

የሰው ልጅ ሁል ጊዜ በጣም ደስ ቢለው /2/
ደግሞ የጭንቁን ቀን ማሰብ ተገቢ ነው /2/
ምንም ቢደሰቱ ቢበዛ ምቾች /2/
ድኻም ሆነ ሀብታም እኩል ነው በሞት /2/
ሰው ሆይ አትጨነቅ ለዓለም ጕዳና /2/
ዓለሙም ንብረቱም ኃላፊ ነውና /2/
ሀብት አገኘሁ ብለህ በጣም ደስ አይበልህ /2/
ድኸየሁም ብለህ አይዘን ልቦናህ /2/
ይፈራረቃሉ አይኖሩም አብረውህ /2/

ኸረ ሰው ሆይ ልብህ ለምን ቸላ አለ /2/
ከባድ የሞት እዳ በራስህ እያለ /2/
ያ የጨለማ ቀን ትዝ ትዝ እያለኝ /2/
እንባዬ ከመውረድ አላቆምም አለኝ /2/

546. ዕዳ አለብን

የእመቤታችን አማላጅነቷን
ክብሯን የቀነስን ያዋረድን
ዕዳ አለብን /2/ ከፈጣሪያችን /2/
የተሰጣት ሙሉ ሥልጣን
ክብርን ያገኘች በቃልኪዳን
ስሟን የጠራ እንደሚድን
በመጽሐፍ ሲነገረን።
አዝ . . . . .

ቤዛዊተ ኩሉ የተባች
በእነ ቅዱስ ኤፍሬም የተመሰገነች
በእነ አባ ጊዮርጊስ ውዳሴን ያገኘች
በመናፍቃን ዘንድ ምነው ተዘነጋች።

አዝ . . . .

ከሴቶቹ ሁሉ ልዩ ልዩ ነች እያልን
በሁለቱም ወገን ብፊጹም ድንግል
የብርሃን እናቱ ማርያም ስትባል
በደካማዎች ዘንድ እንዴት ትቃለል።

አዝ . . . .

ቃና ዘገሊላ ከነልጇ ጋር ሳለች
ከሠርግ ቤት ገብታ ድንግል አማልዳለች
እንኳንስ እመአምላክ ቤዛዊተ ኩሉ
ጻድቃን ሰማዕቃት በእውነት ያማልዳሉ።

አዝ . . . .

547. **አቤት የዚያን ጊዜ**

አቤት የዚያን ገዜ ክርስቶስ ሲመጣ /2/
ትንሹም ትልቁም /3/ መድረሻውን ሲያጣ
ከምሥራቅ ከምዕራብ ከሰሜን ከደቡብ /2/
ነፋሳት ሲላኩ /3/ መዓትህን ለማዝነብ
ሰማይና ምድር በአንድ ሲዋሐዱ /2/
የት ይሆን መድረሻው /3/ የት ይሆን መንገዱ

አዝ . . . .

ጻድቃን በቀኝ በኩል ኃጥአን በግራ /2/
ሲነፋ መለከት /3/ ሲደለቅ እንዚራ
ምድር ቀውጢ ስትሆን አጽም ሲሰበሰብ /2/
ኃፍረት ይይዘዋል /3/ ሰው ለፍርድ ሲቀርብ

አዝ . . . .

ጨኸት ሲበረታ የማይጠቅም ልቅሶ /2/
እንደ ቁራ ጠቁሮ /3/ ጽልመት ተላብሶ
ገነትን ሰያገኙ ጻድቃን በሥራቸው /2/
ኃጥአን ወደ ሲኦል /3/ ተፈረደባቸው።

አዝ . . . .

548. **በአምሳሉ ፈጥሮናል**

በአምሳሉ ፈጥሮናል እናመስግነው
በአርዓያው ፈጥሮናል ሁሉ በእጁ ነው።
ከእኛ የሚፈለገው ማመን
ከእኛ የሚጠበቀው መታመን
አፍም ይጹም ከማውራት ይከልከል
ጆሮም ይጹም ከመስማት ይከልከል
ዓይን ይከልከል ከማየት ይቆጠብ
ልሳን ይጹም ከመናገር በአርምሞ
እጅ እግር ይጹም ከመዳፈር በተደምሞ

አዝ . . . . .

መምጫው ደርሷል ቀርቧል ቀኑ
እንመላለስ በብርሃኑ

አዝ . . . . .

549. **ጊዜዬ እስኪደርስ**

ጊዜዬ እስኪደርስ ወደአንተ መምጫዬ ለለ
ለንስሓ አብቃኝ አቤቱ ጌታዬ አቤቱ ጌታዬ
ብርሃኔ መድኃኒቴ ተስፋህ ይመልሰኝ
ጥፋቴን ደምስሰህ ይቅርታ አድርግልኝ
ተስፋዬ እረዳቴ አንተ አትጣለኝ
አምላኬ አታጥፋኝ ከሲኦል አድነኝ

አዝ . . . . .

መሐሪ ይቅር ባይ ምሕረትህ ይጎብኘኝ
ከኃጢአት ፍላጻ ጸጋህ ይታደገኝ
አዳኜ መድኃኒቴ ሰላምን ላክልኝ
ይደኅነት ደጆችህን በፍቅር ክፈትልኝ

አዝ . . . . .

አቤቱ ምሕረትህ በእኔ ላይ ይሁን
ተጨነኩ ጌታዬ ስጠኝ ሰላምን
ከክፉ እንድሸሽ አድነኝ እኔን
በጎ እንድሠራ ምራኝ መንገዱን

አዝ . . . . .

ሕይወት ሞት ድኅነት መኖራቸውን ባምንም
ኃጢአት ውድቀት ጥፋት አያዘናጋኝም
ሥርየት እንደማገኝ ተስፋ ቢኖረኝም
ትምክህቴ አንተ ነህ በሌላ አልመካም

አዝ . . . . .

የበደሌ ብዛት የማ የስከፋም በሆን

በሥጋ በደምህ እጠብ ኃጢአቴን
ወደንተ እመጣለሁ አደራ ነፍሴን
በሰማያዊ ቤት አኑር ሕይወቴን
አዝ . . . . .

560. **ጌታ ያለው**

ጌታ ያለው ሁሉም አለው
የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት ነው
እመኑ በጌታ ይህ ብቻ ይበቃል
የቀረውን እርሱ በፍቅሩ ይሰጣል
አዝ . . . . .
ሰላም ላጡ ሰላም ፍቅርን ላጡ ፍቅርን
ለታረዙት ልብስን ለተራቡት እንጀራን
ለተጠሙት ውኃን ለታመሙት ፈውስን
ተስፋ ላጡ ተስፋን ለደካሞች ኃይልን፡፡
አዝ . . . .

561. **ከእምነት አደባባይ**

ከእምነት አደባባይ አሻግሬ አይቼሽ
እስካነጋግርሽ በውኔ አግቃቼሽ
አነጋግሪኝ ማርያም ጆሮዬ እንዲነቃ
ኃጢአቴን እጠቢው አድርጊው ጥሩ እቃ
ኦ! ድንግል ሆይ እጅግ ግሩም ነሽ
የልቤ እንዲደርስ እንዴት ልበልሽ
ኪሩቤል ሱራፌል አእላፍ መላዕክት
ክብርት ናት አሉ የጌታ እናት
መልአክ የሚያጽናናሽ በቀኝም በግራ
የሲና ሐመልማል የተቦር ተራራ
አዝ . . . . . .
የልጅሽ ትሕትና ያንቺ ደግነት
የክርስተያን ምርኩዝ የሆንሽ እመቤት
እንዴት ላመስግንሽ የልቤ እንዲደርስ
የትሕትና እናት የፍቅር ውቅያኖስ
አዝ . . . . . .
መዓዛሽ ያማረ ግሩም ጽጌረዳ
እኔ አንቺን አምነኜ ፍጹም አልጎዳ
ትሕትናን ልጫማ ፍቅርን ልልበስ
ባንቺ አማላጅነት በመንፈስ ቅዱስ
አዝ . . . . . .
ኸረ እንዴነት ቢሆነው የምስተካከለው
ዓይንሽን በዓይኖቼ እመቤት የማየው
አንቺን የማይበት ምንም ዓይን የለኝ
እንቅልፍ ሲወስደኝ በህልሜ ጥሪኝ
አዝ . . . . .
ኃይልና ብርታቴ አንቺ ሁኚልኝ
ከጠላት ስዋጋ ጋሻ ሆነሽኝ
ማልቀስ አስተምሪኝ መሳቁ ይብቃኝ
የሲያል እሳቱ እንዳያቃጥለኝ
አዝ . . . . . .
ላስብሽ በአርምሞ ወደ ላይ መጥቄ /2/
የምድሩን ሳሳድድ እንዳልቀር ወድቄ /2/
አዝ . . . . . .

562. **ንሴብሖ**

ንሴብሖ /2/ ለአምላክ ዕዝራ /2/
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ስለፍቅርህ ልጀምር ማኅሌት
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
ስመለከት ወደሰማይ በጨረቃ ብርሃን
ግርማ ለብሴ አስገረመኝ የአምላኬ ዙፋን
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ እንዘምር
እልል እንበል በምስጋና ጺጋውን እንጨምር
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
አዕዋፍ በማለዳ መዝሙር ሲዘምሩ
በቋንቋቸው የአንተን ክብር በምሥጢር ሲያወሩ
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
ክበሮ ሆይ ጸናጽል ሆይ ለምስጋና ተነሥ
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሆ ለአምላክ ዕዝራ

563. **የአብ ቃል አክብሮሽ**

የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ

እግዚአብሔር በቃል ፍጹም ያከበረሽ
የምንመካብሽ መሰላል አንቺ ነሽ /2/
ቅድስና ላንቺ ጽድቅም ላንቺ ሆኖ
ዓለምን የፈጠረ በአንቺ ተወስኖ
የገነት ፍሬ ነሽ ሕይወትን ያፈራሽ
አንቺን ለመረጠ አንቺን ላነጻሽ
ምስጋና ይድረሰው ለቸሩ አምላክሽ /2/
አዳም የኖረብሽ የኤዶም ገነት ነሽ
የኤፌሶን ወንዝ ወርቅ የሚፈልቅብሽ
የግዮን ማዕበል ኢትዮጵያን የከበብሽ
ዮርዳኖስን ሆነሽ አሕዛብን ፈወስሽ
በልጁ ቃልነት አብም አከበረሽ /2/
መዓዛሽን ወዶ ወልድ ዋሕድ ዋጀሽ
አብም በሰማያት በጎሊናው ጻፈሽ
መንፈስቅዱስ መጥቶ አንቺን አከበረሽ
እመካብሻለሁ እመቤቴ ስልሽ /2/
ወልድ በመውደዱ ከአንቺ መወለዱን
ንጹሕ ሆኖ አግኝቶት ቅዱሱ ሥጋሽን
ለቃሉ ማደሪያው ጽላትና ታቦት
በብሩህ ደመና ተመስለሽለት
ከሥጋሽ ተከፍሎ ከደምሽ ደም ወስዶ
ከነፍስሽም ነፍስ ፍጹም ተዋሕዶ /4/

564. **ማነው የሚያድነኝ**

ለዚህ ለኃጢአት ሕግ ከተሰጠ
ከሕይወት መርገምን ከመረጠ
ልሞት ከተሰጠ ከንቱ ኑሮ
ማነው የሚያድነኝ ሞትን ሰብሮ
ሥጋ በሥጋ ሕግ ይስበኛል
መንፈስ በመንፈስ ሕግ ይጠራኛል
ለየትኛው ጌታ ተገዝቼ
የቱን እመርጣለሁ አንዱን ትቼ
ኃጢአት እሰራና ይጨንቀኛል
አምላኬ ሲለየኝ ይሰማኛል
ጌታዬ ሲለየኝ ይሰማኛል
አምላኬ ሲለየኝ ይሰማኛል
አዝ . . . . . .
በኃጢአት በመኖር በዚህ ዓለም
የአምላክን ትዕዛዝ በማጣመም
በስርቆት በዝሙት በሰካር
በዲያብሎስ ፈቃድ ስንኖር
የኋላ የኋላ ውድቀት ነው
አምላክ በክንዶቹ ያልያዘው
የጨለማ ጉዞ ምን ይጥማል
ዓይን እያሳወረ ያዋርዳል
አዝ . . . . . .
መላእክት በሰማይ ያለቅሳሉ
የእግዚአብሔር ቅዱሳን ያነባሉ
በኃጢአት ተማርከን ስንወሰድ
ሰይጣን ድል አግኝቶ ስንዋረድ
አዝ . . . . . .

565. **ቅያሜው ይቅርና**

ቅያሜው ይቅርና አምላክ ሆይ ታረቀን
አንተ ስለራቅኸን ሞት ነው የከበበን
እስከመቼ ድረስ ሕዝብህ ተጐሳቁሎ
በረከሰ መንፈስ ለርኩሰት ተጥሎ
ምድር እያለቀሰች ደም እየሸተታት
እባክህ አምላኬ ኢትዮጵያን ታረቃት
እባክህ አምላኬ አገሬን ተረቃት
አዝ . . . . .
የዘመኑ ጣዖት ገንዘብ እያሳተን
ይህ ደካማ ሥጋ አምላክን አስተወን
ግብዝነት ሞልቶት ፈራሹ አካል
በነፍስ በሽታ ሕዝባችን ታሟል/2/
አዝ . . . . . .
ክንፋችን ተመትቶ መብረር አቅቶናል
በመንፈስ በሽታ ሕዝባችን ታውኳል
ምግባር የጐደለን ተራ ሰው ስለሆን
እባክህ ጌታችን በፍጥነት ታረቀን /2/
አዝ . . . . . .
ጸጋህ የተለየን ባዶነት የመላን
እርቅ የተነፈገን ሰላም የጐደለን
ሆነን ስለቀረን እግዚአብሔር ታረቀን

ጽድቅህን አድለን ጽድቅን ለተመኘን

አዝ . . . . . .

566. **የሀብከ ዮም**

የሀብከ ዮም የሀብከ መድኃኔዓለም /2/

ዕድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም /2/

ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኔዓለም /2/

ዕድሜ ማቱሳላ የአብርሃም/2/

በቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች የተወሰናችሁ /2/

ክርስቶስ ተገኝቷል በመካከላችሁ /2/

የድንጋዮቹን ጋን ወይኑን ወይን ሊሞላበት /2/

ከድንግል ማርያም ጋር ተገኝቷል ከዚህ ቤት /2/

ደስታውን አይቶ አምላክም ፍጹም ተደስቷል /2/

ሊባርካችሁም እጆቹን ዘርግቷል /2/

በሕይወታችሁም ፍቅር ፍቅር ቅመም ሆኖ /2/

ትሕትናን ይሰጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ /2/

አዝ . . . . . .

ሥርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር
የተሞላበት /2/

በሕይወታችሁ ውስጥ ክርስቶስ ይግባበት

በሕይወታችሁ ውስጥ አምላክ ይኑርበት

አዝ . . . . . .

የበረከት ፍሬ በጸጋው እንዲበዛላችሁ /2/

ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /2/

እራስን በማገዛት ዕውቀት /2/ ለመላችሁ /2/

ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /2/

በሥጋ ወደሙ እግዚአብሔር ስለመረጣችሁ /2/

የመንፈስቅዱስም ሕፃናቶች ናችሁ /2/

አዝ . . . . . .

567. **ኢትዮጵያ ሆይ**

ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ /2/

ከሕዝብሽ ጋር እልል በይ /3/

እጆችሽን በበረከት ስለመላ /2/

ስላዳነሽ በጭንቅ ቀን ከሞት ጥላ /2/

እግዚአብሔር ብርሃንሽ ስለሆነ /2/

ከአስፈሪው ቀን ልጆችሽን ስላዳነ /2/

ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ /2/

በሽብሸባ እልል በይ /3/

በሽብሸባ ለአምላክሽ ዘምሪለት /2/

ስብራትሽን ይጠግናል በምሕረት /2/

ለሕዝብሽ እግዚአብሔር ኃይላቸው ነው /2/

በስቃይ የጐበኘ መመኪያቸው /2/

አዝ . . . . . .

ሕዝብህን ባርክ ለዘላለም ጠብቃቸው /2/

በፍቅርህም ከፍ አድርጋቸው /3/

የምስጋና ነጐድጓድ ከአፍሽ ይውጣ /2/

ድሮም ቢሆን እግዚአብሔር ነው የአንቺ ዕጣ /2/

አዝ . . . . . . .

እግዚአብሔር ልዩ ነው

እግዚአብሔር ልዩ ነው ኃያል አምላካችን ልዩ ነው /3/

ሞትን ድል የነሳው ልዩ ነው /2/

ከክብርና ሞገስ ሞልቶ የተረፈው ልዩ ነው

ብርሃንን እንደ ልብስ የተጐናፀፈው ልዩ ነው

በትዕዛዝ ብቻ ዓለምን ያቆመው ልዩ ነው

እኛን የተቤዠ በእውነት ልዩ ነው /2/

አዝ . . . . . . .

በበረከት ክንዱ አጥብቆ የያዘን ልዩ ነው

እራሱን የሠዋው የዓለም ብርሃን ልዩ ነው

አካሉን መድኃኒት አድርጎ የሰጠን ልዩ ነው

የፈውሳችን ፀሐይ የጽድቃችን ጮራ ልዩ ነው

አዝ . . . . . . .

568. **እሰይ እሰይ**

እስቲ እሰይ እሰይ እሰይ እሰይ

አምላክ ከእኔ ጋር ነው እሰይ እሰይ

ያጣ ሰው ብመስል እሰይ እሰይ ንብረት ባይኖረኝ እሰይ
እሰይ

የአምላኬ ፊትህ እሰይ እሰይ ትቶቃስ አያውቅ እሰይ
እሰይ

ደኻ ሰው መስዬ እሰይ እሰይ የሰው ዓይን ሲጠላኝ
እሰይ እሰይ

እተማመናለሁ እሰይ እሰይ አፍቃሪ አምላክ አለኝ እሰይ
እሰይ

በድህነት ስኖር እሰይ እሰይ አካሌ ተራቁቶ እሰይ
እሰይ
ደስ ብሎኝ እኖራለሁ እሰይ እሰይ ጎሊናዬ ረክቶ
እሰይ እሰይ
አምላክ ስለጠራኝ እሰይ እሰይ በታላቅ ደስታ
እሰይ እሰይ
ከፊቴ አይለይም እሰይ እሰይ ዘወትር በቦታ እሰይ
እሰይ

አዝ . . . . . .

አለ በፊቱ ነው እሰይ እሰይ የሚናገርልኝ
እሰይ እሰይ
አምላክ ያውቅልኛል እሰይ እሰይ እኔ ምን
አለብኝ እሰይ እሰይ
ሰርቼ በረከት እሰይ እሰይ ዘወትር አላጣም
እሰይ እሰይ
እግዚአብሔር ይመስገን እሰይ እሰይ
አላሳፈረኝም እሰይ እሰይ

አዝ . . . . . .

እንደ አእዋፍ እሰይ እሰይ አፎን ይከፍትና እሰይ
እሰይ
ስመገብ እኖራለሁ እሰይ እሰይ የአምላክን መና
እሰይ እሰይ
ድንቢጦችን እንኳን እሰይ እሰይ ያልዙዋቸው ጌታ
እሰይ እሰይ
ይመስገን ዘወትር እሰይ እሰይ በእውነት ጠዋት
ማታ እሰይ እሰይ

አዝ . . . . . .

## 569. የእኛ ጌታ

ይእኛ ጌታ የኛ መድኅን
በቸርነትህ ታደገን እኛ እንደሆን ኃይል የለን /2/
ጠዋት ለምልማ ታማ ጠፋች
የሰው ኅሊና እያባባች
ዓለም ምኗ ነው የጣፈጠን
እያሳሳቀ የወሰደን

አዝ . . . . .

ዛሬ አለሽ ሲሏት ትጠፋለች
ከነተንኮሏ ዓለም ሟች ነች
እሾህ በቅሎባት እሾህ ሆና
በመተላለፍ ሰው ሊያልቅ ነዋ

አዝ . . . . . .

ከእኛ ጋር ያለው ኃይል ነው
በሥጋዊው ዓይን ባናየው
የጠሩ ብዛት መቼ ያድናል
የዓለም ጥንስስ ተዋሕዷል

አዝ . . . . . . .

እንደሰው ጥበብ ጥበበኛ
እንደሰው ወደር ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በአምላክ ፊት ሲታይ ሕመምተኛ

አዝ . . . . . .

## 570. ለእኔስ ልዩ ናት

ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም
ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን
ፈልጌ /4/ ለአንቺ ምስጋና አላገኘሁም /2/
ልቤ ሲያበቅል የኃጢአት አረም
ውስጤ ሲሸፍት አልተወችኝም
ከቤተመቅደስ እጄን ዘርግታ
ትጠራኛለች የእኔ መከታ

አዝ . . . . . .

የሆዴን ሐዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለሁ አንድም ሳይቀር
የምትሸሽጊ የሕዝብን ኃጢአት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኚት

አዝ . . . . . .

ጣዕሙ ልዩ ነው ከአንቺ ጋር መኖር
ድንግልን ይገፍ መቼም አላፍር
ወደ ጽድቅ ሕይወት ትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴ እኮ ነች

አዝ . . . . .

በሐዘን ስሰበር ማንን እጠራለሁ
ውስጤ ሲደማ ለማን እነግራለሁ

ከኃጢአት እድፍ ንጹሕ መሆኛዬ
አንቺ ነሽ ለእኔ የኔስ መጽናኛዬ
አዝ . . . . .
የኃጢአት ቁስል ያለአንቺ አይጠግም
ልቤ ሳይፈቅድ በሕይወት አልኖርም
ከልጅሽ ሌላ ምደኅን የለኝም
ከጸሎት በቀር ፍጹም አልድንም
አዝ . . . . . .

571. **እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ**

እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ
ስለ ስምህ እቃጠላለሁ
ፍቅርህ እኔን ይመስጠኛል
እንደ እግዚአብሔር ከየት ይገኛል
ዓለም ሁሉ በጠራኝ ጊዜ
ስንገላታ ይዞኝ ትካዜ
አንተ ከኔ አልተለየህም
እግዚአብሔር ሆይ ወደር የለህም
አዝ . . . . .
ሳኦል እኔን ሲያሳድደኝ
ጐልያድም ሲዝተብቃኝ
ግርማ ሆነህ ከፊት የቆምክ
እግዚአብሔር ሆይ ስምህ ይባረክ /2/
አዝ . . . . .
ሞቷል ብለው ቀብረውኝ ሰዎች
ምስኪን ሆኜ ሳይኖረኝ አንዳች
ከመቃብር ቆፋሮ አወጣኝ
አይዞህ ብሎ አምላኬ አጽናናኝ
አዝ . . . . .
ሐሳብህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል
ለዘለዓለም ያበራልሃል
ታማኝ አባትህ እርሱ ነውና
ሰላም በረከት የእርሱ ነውና
አዝ . . . . . .

572. **የመስቀሉ ፍቅር**

የመስቀሉ ፍቅር /ነገር/ ቢገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን
የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው /4/
እመቤታችን አለች ከጎናቸው
አባ ሕርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ነገር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋራ ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር
አዝ . . . . . .
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው
ተዋሐደ ስትል አማኑኤል አለችው
ሕሙማን ሲፈውስ ኢየሱስ አለችው
ንጉሥ ነውም ብላ ክርስቶስ አለችው
ተሰቅለ ስታየው መደኅኑ አለችው
ለመናኜው ጸሎት ልዩ ዕጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እመብርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን /ከጽዮን/
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኝማለሽ ምን ልሁን
ድንግል እመቤቴ የእኔ እረዳት
ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሀገር የሚሉሽ
እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ /2/
ቤተልሔም ስሄድ አይሻለሁ
ቀራንዮ ስሔድ አይሻለሁ
ፍጹም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ /2/
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ እምዬ ማርያም

573. **ኑ ተመልከቱልኝ**

ኑ ተመልከቱልኝ የአምላክን ቸርነት
አንደበት የለኝም ሥራውን ለማውራት
ሰላምና ፍቅሩ በልቤ ተሞልቷል

በምን ቋንቋ ላውራው ቃላቶች ያጥሩኛል /2/
ሰማይ ጉም ቢመስል ቀላያት ቢናጉ
የጥፋት አጋንንት እጅጉን ቢተጉ
እኔን የሚጠብቅ ኃይሉን አይሰውርም
እረኛዬ ከእኔ ዘወትር አይርቅም

አዝ . . . . .

ፍርሃት ከእኔ ላይ ጨለማም ተወገድ
በጌታዬ ትምክህት እንደልቤ ልሂድ
የሞት አበጋዞች ተስፋችሁ ጨልሟል
እግዚአብሔር ሊያድነኝ አጠገቤ ቆሟል

አዝ . . . . .

ቅዱሳን በሙሉ ለእኔ ዘብ ቆመዋል
ውደእነርሱ ኅብረት ሊስቡኝ ጓጉተዋል
ዘወትር በመዓልት ድንግል ትመጣለች
በብርሃን እጆቿ ትባርከኛለች

አዝ . . . . . .

574. ኪዳነ ምሕረት

ኪዳነምሕረት እናቴ አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር /የሰላም/ እናት ነሽና /2/
የተገለጠው ብርሃን በምሥራቅ የተወለደው
በፍቅር ሰንሰለት አስሮ ዓለምን ሁሉ አዳነው
/2/

አዝ . . . . .

በረሃውን ባሰብኩት ጊዜ የግብፅን የአሸዋ ግለት
አንቺ ትንሽ ብላቴና ኧረ እንዴት ቻልሽው
በእውነት /2/

አዝ . . . . . .

ዝም ብዬ ይደንቀኛል የአምላክን ሥራ
ሳስበው
ምክንያት አንቺን አድርጎ ይህንን ዓለም
አዳነው/2/

575. ከወገኔ ጋራ

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ
በደስታ በሐሴት ስሙን እጠራለሁኝ
ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና
ዘወትር አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና /2/

ሕዝቡ ተሰብስቦ በቤተክርስቲያን
ሲዘምር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን
በረከት ይሞላል ዝማሬው ይገርማል
ከእጣኑ ጋራ ወደላይ ይወጣል

አዝ . . . . . . .

ቀሳውስቱ ሌሊት ማኅሌት ሲያቀርቡ
ከመላእክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ
ብርሃኑን ለብሰን በደስታ ስንዘምር
ትዝታው ልዩ ነው ሕሊና ሲሰውር /2/

አዝ . . . . . . .

ራእይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደመላእክቱ
የጽጌው ማኅሌት የትንሣኤው ደስታ /2/
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ /2/

576. ከካራን ውጡ

ከጣራን ውጡ ከነዓን ግቡ
ወደ ጽድቅ ሕይወት ዛሬ ቅረቡ
ካራን ጣዖት ነው የሚመለከው
የአሕዛብ ሀገር የሙት መንደር ነው /2/
እንደአባታችን እንደ አብርሃም
ወገኖች ውጡ ከካራን ዓለም
የግፍ እንጀራ ይብቃችሁና
ከካራን ውጡ በአምላክ ጐዳና

አዝ . . . . .

የጣዖት ምስል ከሚሸጥበት
ዓለም በዝሙት ከሚነድበት
ከሰዶም መንደር ከካራ ውጡ
የኃጢአትን ሰንሰል ዛሬ ቁረጡ

አዝ . . . . . . .

የኃጢአት ዓለም ዛሬ ይብቃና
የፍቅር ሕይወት እንልበስና
ከካራን መንደር በፍጥነት ወጥተን
ከነዓን ገብተን ማደር አለብን

አዝ . . . . . . .

ማርና ወተት ከሚፈልቅበት
ሰዎች በፍቅር ከሚኖሩበት

ከሰማያዊት ኢየሩሳሌም

ዛሬ ብንገባ እናገኛለን የአምላክን ሰላም

577. ኪዳነ ምሕረት ሩኅሩኅ

ኪዳነምሕረት ርኅሩኅ ተይ አታቁሚኝ ከበሩ

የሲዖል አለንጋ መራራ ነው አሉ

አንቺ አማልጅኝ እግዝእትነ ኩሉ ሰጊድ ሰላም /2/

ኃያል እንዲህ ነው ኃያል ቅዱስ ሚካኤል ኃያል

የለበሰው ልብሱ የወርቅ ሐመልማል

የታጠቀው ሰይፉ የእሳት ነበልባል

ይህም ተጽፏል በቅዱስ ቃል ሰጊድ ሰላም/2/

ኃያል እንዲህ ነው ኃያል ቅዱስ ገብርኤል ኃያል

ሠለስቱ ደቂቅን ከእቶን ያዳናቸው

ቂርቆስ ኢየሉጣን ከእሳት ያወጣቸው

የሚረዳን ፈጥኖ ደራሽ ቅዱስ ገብርኤል ነው /2/

ሰማዕት እንዲህ ነው ሰማዕት

ቅዱሰ ጊዮርጊስ ሰማዕት

ለወዳጆቹ ፈጥኖ ሲደርስ

ጣላቶቹንም ሲደመስስ

ጊዮርጊስ ዘልዳው ንጉሥ

ጻድቅ እንዲህ ነው ጻድቅ ተክለ ሃይማኖት ጻድቅ

በአንድ እግራቸው ቆመው ለሰባት ዓመት

ጠላትን ድል ነሱ በጾምና በጸሎት /2/

578. የአርያም ንግሥት

የሰማይ የምድር የአርያም ንግሥት

አንቺ ነሽ እመቤት የአምላክ እናት

ኧኸ ድንግል አማላጅን ኧኸ ቅድስት ተራጂን

ለሔዋን ተስፋዋ ለአዳም ዘር ሕይወት

ለደኅነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ በእውነት

የኦሪት መጽናኛ ለሐዲስ ኪዳን በር

የወንጌል መሠረት የአምላክ ማኅደር

አዝ . . . . . .

የአብርሃም እርሻ የምሥጢር ዋሻው

እናትና ድንግል ሁለቱን ሆንሽው

የኤፍሬም ውዳሴ የያሬድ ውብ ዜማ

የማትጠልቂ ፀሐይ የሃይማኖት ሻማ

579. ለንስሐ ሞት አብቃኝ

ለንስሓ ሞት አብቃኝ /2/

በሂሶፕ እርጨኝ እጠበኝ

እንደ በረዶ አንጻኝ /2/

አመፃዬ በዛ ኃጢአትን ጨመርኩኝ

ልቤ ደነደነ ክፋትን ፈጸምኩኝ

እንደ ፈርዖን ልቤ እንዳይጸናብኝ

አድነኝ እንደ ኖኅ አምላክ ራራልኝ

አድነኝ /3/ ስለ ድንግል ብለህ አድነኝ

አድነኝ /2/ ስለ ጻድቃን ብለህ አድነኝ

አዝ . . . . . .

ኃጢአቴም በረታ ሰለጠነብኝ

ከቃልህ አስወጣኝ ሕግህን ጣስኩኝ

እንደነነዌ ሕዝብ ንስሓን ስጠኝ

ምሕረትህን ልከህ ልቤን ስበርልኝ

አድነኝ /3/ እንደ ቸርነትህ አድነኝ

አድነኝ /2/ እንደ ምሕረትህ አድነኝ

አዝ . . . . . .

ያደፈው ገላዬን አንተ አጥራልኝ

ከሰዶም ገሞራ እንዳይብስብኝ

መንገድና ሕይወት አንተ ነህ ምራኝ

የቅዱስ ጴጥሮስን ንስሓ ስጠኝ

አድነኝ /3/ እንደ ቸርነትህ አድነኝ

አድነኝ /3/ ስለ እናትህ ብለህ አድነኝ

አድነኝ /2/ ስለ ጻድቃን ብለህ አድነኝ

580. ጊዮርጊስ በዚያች ቀን

ጊዮርጊስ በዚያች ቀን ከፈተናው አንጻር

ሰለሃይማኖቱ የታየው ምን ነበር

ያመነው አምላክ አላውቀውም እንዲል

በሥልጣን በገንዘብ እርሱን ለመሸንገል

ነገር ሲሸርቡበት የዱዲያኖስ ጭፍሮች

ለመሥዋዕት ሲቀርብ መንፈሱ ምን አለች

አዝ . . . . .

ስገድ ባሉት ጊዜ ሰው ለሠራው ምስል

ትዝ አለው ጊዮርጊስ የአምላኩ ሕያው ቃል

ከሠለስቱ ደቂቅ ከዳንኤል ጋራ
በእሳቱ ነበልባል ውስጥ ተአምር ሲሰራ

አዝ . . . . .

ቂርቆስ ኢየሉጣን ከመቃጠል ዋጅቶ
ያቀዘቀዘውን ፍሉ ን ውኃ አጥፍቶ
አስታውሷል ጊዮርጊስ ያንን ኃይል ጌታ
መስቀል መሸከሙን በዚያች በጎልጎታ

አዝ . . . . . .

ጴጥሮስና ጳውሎስ አባቶቹን መስለ
ሞትን አሸነፈ በእምነቱ ተጋድለ
እንድንጸና በእምነት ይህችን ዓለም ንቀን
በሰማዕቱ ምልጃ አምላክ ይጠብቀን።

581. **<u>አልተወኝም ጌታ</u>**

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል /2/
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ ይለኛል
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነሽ ይለኛል

አዝ . . . . . .

በበደል ጉራንጉር በኃጢአት ጫካ
ብጠፋበት እንኳን አልተወኝም ለካ
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል

አዝ . . . . . .

ለሥልጣን ለክብር ብዬ ስክደው
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው
ለእኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም

አዝ . . . . . .

ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን
ከጭንጫ መቃብር ላወጣኝ እኔን
በሕይወቴ ሁሉ ፍጹም ለመራኝ
ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ

582. **<u>አምላካችን ተመስገን</u>**

አምላካችን ተመስገን /2/ ለዛሬ ያደረስከን
አምላካችን ተመስገን /2/ ለዚህ ቀን ያደረስከን
በኃጢአት ስንማቅቅ በምሕረትህ ጠራኸን
በዓለም ስንባዝን ነበር በቃልህ መራኸን

አምላክ ሆይ ተመስገን
ትእግሥትህ ብዙ ነው አያልቅም ርኅራኄህ
የምንከፍልህ ምን ይሆን ብዙ ነው ውለታህ
አምላክ ሆይ ተመስገን

አዝ . . . . . .

ከቶ የማትፈልግ ከሰው ልጆች ወረታ
ቸር ፈጣሪ ነህና ሥራህ ድንቅ ነው ጌታ
አምላክ ሆይ ተመስገን
ይቅር ባይ አምላካችን ሆይ አንተን እናመልካለን
ከመዓትህ ታግሰህ ሁሉንም ይቅር አልከን
አምላክ ሆይ ተመስገን

አዝ . . . . . .

ኃጢአታችን ጨለማ ቢያደርገው ኑሮአችንን
በአንተ ተጎናጽፈናል የማዳንን ብርሃን
አምላክ ሆይ ተመስገን
ስለአደረክልን ሁሉ ስለ ግሩም ሥራህ
የራስህን እንስጥህ ተመስገን እንበልህ

583. **<u>ባርከን</u>**

ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን /2/
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሐሳብ አድርገን /4/
ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን /2/
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሐሳብ አድርጊን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን

ጥሪህን ስንሰማ ወደአንተ እንድንመጣ
በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ሳንወጣ
በሕይወት ስንደክም እንዳንጠፋ በዓለም
እርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኔዓለም

ከተፈረደብን የባርነት ሕይወት
ከመጣብን መርገም በመብል ምክንያት
ከሲዖል እስራት እኛ የዳንብሽ
ድንግል ሆይ ሁል ጊዜ አይለየን ምልጃሽ።

አንድነት ስናጣ ፍቅር ስትመነምን
በምግባር ስንደክም ሲጐድል እምነታችን
በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ
በምሕረትህ ጐብኘን አንተ ሁነን ተስፋ

ርኅርኅተ ኅሊና ቅድስት እናታችን
አሳስቢ ሁል ጊዜ ስለ ኃጢአታችን
ሊያድነን ነውና ክርስቶስ መሞቱ
አሳስቢ እመአምላክ ድንግል ወላዲቱ

584. **የቅዱሳን አምላክ**

አብርሃምን ከካራን የጠራኸው ጌታ
ለሙሴ በሲና የሆንከው መከታ
ልጠፋ ነውና በሥጋ ፍላጎት
የይስሐቅም ጌታ ሕይወቴን ታደጋት /2/
የኤርትራን ባሕር በኃይልህ የከፈልክ
በሲና በረሃ ሕዝብህን የመገብክ
ኖኅ ከጥፋት ውኃ የዳነብህ አምላክ
ሎጥን እንዳዳንከው ፍጹም ምሕረትን ላክ /2/
የተነበዩልህ ነቢያት በሙሉ
አምላክ ሰው ይሆናል ይወለዳል ሲሉ
ከዓሣ አንበሪ ሆድ ዮናስን ያወጣህ
ዓለም ልትውጠኝ ነው አይለየኝ ጸጋህ /2/
ሥጋን ተዋሕደህ በወሰንከው ሰዓት
የሞትክልኝ አምላክ ያዳንከኝ ከሞት ሞት
እንደወንጌልህ ሕግ የምኖር አድርገኝ
በመጨረሻው ቀን በቀኝህ አድርገኝ /2/
አልቻልኩኝምና ልፈጽም ሕግህን
የሐዋርያት አጽናኝ ስጠኝ ብርታትህን
ምግባረ ጎደሎ ሆኛለሁኝና
የቅዱሳን አምላክ እርዳኝ እንድጸና /2/

585. **ድንግል ሆይ**

ወላዲተ አምላክ የሁሉ እመቤት
ለምኝልን ለእኛ ከልጅሽ ምሕረት
በአንቺ አማላጅነት በእርሱ ቸርነት
እንዲያወጣን ነጻ ከፍርድ ቅጣት
ድንግል ሆይ ለምኝልን /2/
በበደል ተዳክሞ ፈቃደ ነፍሳችን
በምድራዊ ምኞት ናውዞ ልቦናችን
ፍቅርና ትሕትና ጠፍቶ ከፊታችን
ለሞት እንዳይሰጠን ይህ ክፉ ሥራችን
አዝ . . . . . .
የምስኪኖች ተስፋ የደካሞች ኃይል
ጠውልገናልና ጥላ ሁኚን ድንግል
እምነት ጨምሪልን ልቦናችን ይጽና
እመአምላክ አብሪልን የመዳንን ፋና
አዝ .. . . . . .
ፍጹም እንዳናዝን እንዳናፍር ኋላ
ተነጥቀን እንዳንቀር ከዘለዓለም ተድላ
በፍቅርሽ መልሺን ከሲኦል ጎዳና
ድንግል መመኪያችን ተስፋችን ነሽና

586. **ስለድንግል ብሎ**

ስለድንግል ብሎ ኢትዮጵያን ይጎበኛት
ድሮስ ከአምላክ በቀር ይህች ሀገር ማን አላት
በሠራዊት ብዛት መች ትጠበቃለች
በቅዱሳን ጸሎት እሳት ካልታጠረች
ዓለም ሽምቀባት አሕዛብ ይስቃል
በልጆችሽ እንባ አውሬው ይቀልዳል
ታላቅ ሕዝብ መሆኑን ማን በነገራቸው
ከዘመናት በፊት አምላክ የጎበኘው /2/
እውነተኛ እንባ ፈለቀ ከምድር
በፍጡራን ዋይታ ፍጹም ብታማርር
እንባና ደማችን ተደባልቆ ፈሷል
አምላክ ቅጣት ይብቃ አቤቱ ይቅር በለን /2/
ቅዱሳንን መንቀፍ ወገኔ ተውና
ይልቅ ስለእነርሱ የጽድቅ ጎዳና
በረድኤታቸው በክብራቸው ጥላ
እንከተላቸው ከፍቅራቸው ኋላ /2/

587. **አምላክ አለ መሃላችን**

ደስ ይበለን ደስ ይበለን
አምላክ አለ መሃላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምሕረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን እድሜ የጨመረልን
ለንስሓ ጊዜ የሰጠን

ኃጢአትን ይታገስሃል
በቸርነት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥእ የጽድቅ ሕይወት
አዝ . . . . . .
እልል በሉ የጎበኛችሁ
በምሕረቱ አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ አመስግኑ ዝምም
አትበሉ
ድንግል ማርያም ትጸልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አንዴ እንዲያድነን

**588.ዴማስ ሆይ ተመለስ**

የይሁዳ ጉዞ አያዋጣምና
ዴማስ ወደ ሕይወት እባክህ ቶሎ ና /2/
ከወንጌል ገበታ መመገብ ጀምረህ
ወንድሜ ተመለስ ወዴት ትሄዳለህ
ይጠራሃልና መስቀሉን ተመልከት
የወንጌል ቡቃያ እውነተኛ ሕይወት /2/
አዝ . . .
ብዙ ክርስቲያኖች መንገዱን ጀምረው
የዓለም አሸንክታብ ድምቀት ሲጠራቸው
ፈተና ሲመጣ ወንጌሉን ወርውረው
ሞትን ይመርጣሉ ሕይወትን ሰርዘው /2/
አዝ . . .
የመስቀሉ ሕይወት ከልብህ ሳይጠፋ
በእግዚአብሔር ጉባኤ መስክረህ በይፋ
ልጁ የተባልከው በጥምቀት ቀለበት
እንዴት ትሄዳለህ ተነድተህ ወደሞት /2/
አዝ . . .
የክብር አክሊሉ ተዘጋጅቶልሃል
አምላክ ለሽልማት ዴማስ ሆይ ይልሃል
ወዴት ትሄዳለህ እባክህ ተመቀስ

**589. <u>ባሰማት ጊዜ</u>**

ስሙ ገብርኤል የተባለ ለድንግል ነገራት መልካም
ዜና
<u>እንደምትወልደው ወልድን በድንግልና /2/</u>
ባሰማት ጊዜ ቃሉን ቅዱስ ገብርኤል በለዛ
ድንግል ቀረበች ወደ እርሱ ፍጹም ትኅትናን ይዛ
ትፀንሻለሽ ሲላት መልአኩ ፍጹም በልቧ ሳትመካ
እንደ ቃልህ ይን አለችው በቃሉ ተማርካ /2/
አዝ . . .
ዓለም መድኃኒት ነውና ከአንቺ የሚወለደው መንፈስ
ቅዱስ
ትሰይሚዋለሽ ስሙንም ብለሽ ኢየሱስ /2/
አዝ . . .
እጹብ ድንቅ ነው ሁልጊዜ ለድንግል ማርያም የተሰጣት
እድል
የአምላክ እናት ሆኖ መመረጥ ከሴቶች መካከል /2/
አዝ . . .
ጸጋን የተመላሽ ሆይ ይገባሻል ለአንቺ ክብርና
ምስጋና
የክብር ባለቤት ሁል ጊዜም ከአንቺ ጋር ነውና /2/
አዝ . . .

**590. አባታችን**

አባታችን ሆይ የምትኖር በሰማይ
መንግሥትህ ትምጣልን <u>ክብርህን እንድናይ/2/</u>
ፈቃድህ በሰማይ ሕይወት እንደሆነ
እንዲሁም በምድር <u>ሰላምን ስጠን</u>/2/
ስጠን ለዛሬ የዕለት ምግባችንን
በደላችንንም ይቅር <u>እንድትለን</u>/2/
ጌታ ሆይ አታግባን ከክፉ ፈተና
አንተ ካልረዳኸን <u>ኃይል የለንምና</u>/2/
ኃይልና ምስጋና መንግሥትም የአንተው ናት
አሜን ለዘለዓለም <u>ይሁንልን ዕረፍት</u> /2/

**591.ሰላም ላንቺ ይሁን**

ሰላም ላንቺ ይሁን (3) ማርያም ድንግል (2)
የሴቶች መመኪያ የሴቶች አክሊል (2)
ሰላም ላንቺ ይሁን (3) የሁሉ እመቤት /2/
የኃጥአን ተስፋ የጻድቃን(2) ሕይወት /2/
ሰላም ላንቺ ይሁን/3/ የሁሉ ወዳጅ/2/
የጽድቅ መሰላል የዓለም /2/ አማላጅ/2/

ሰላም ለወለድሽው/3/ አምላካችንን /2/
ሰማይና ምድር የማይችሉትን/2/
ሰላም እመቤት /3/ አምላክን የወለድሽ/2/
የሰማይ መላእክት የሚያመሰግኑሽ /2/
ሰላም ለመቤቴ /3/ አምላክ የመረጠሽ/2/
ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ /2/ ነሽ/2/

**592.የዓለም ንግሥት የሆንሽው**

የዓለም ንግሥት የሆነሽው ድንግል ማርያም
እናቴ
ታመሰግንሽ አንቺን ሁልጊዜ ሕይወቴ
ማርያም ባርኪኝ እመቤቴ እሰግድ ለኪ፡፡
እንዳልንገላታ ጠብቂኝ በኃጢአት ዓለም ጎዳና
ደግሞም እንድመገብ ሰማያዊ መና
ማርያም የአዳም ጤና እሰግድ ለኪ፡፡
ተሸጨ ስኖር ልጅሽ በኃጢአት ከተማ ዓለም
የሚያወጣኝ ጠፍቶ የእናት ልጅ ወንድም
ወጣሹኝ በልጅሽ ደም እሰግድ ለኪ፡፡
ከቅድስት ቦታ ሀገር ከቤተልሔም ተነሥተሽ
ምድረ ግብፅ አውራጃ ፈጥነሽ ስትደርሺ
ማርያም መከራን አየሽ እስግድ ለኪ
ያ ምቀኛ ሰይጣን ንጉሥ ተንኮል የተመላው
ልጅሽን ሊገለው ደሙንም ለማፍሰስ
ተሯሯጠ በእግር በፈረስ እስግድ ለኪ፡፡
ያንቺ መንገላታት ሁልጊዜ ያሳዝነኛል ሲወራ
በምድረ ግብፅ ሁሉ ያየሽው መከራ
ማርያም ነፍሴን አደራ እሰግድ ለኪ፡፡ /2/

**593.እመቤታችን ላንቺ**

እመቤታችን ላንቺ ስላምታ ይገባሻል/2/
ከሴቶች ሁሉ /3/ ተመርጠሻል
ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል /2/
ተዘጋጀላት/3/ የመመረጥ ዕድል
እመቤታችን ------------
እያረጓጓት የሰማይ መላእክት /2/
ቤተ መቅደስ ኖረች/3/ አሥራ ሁለት ዓመት
እመቤታችን ላንቺ-------
መንፈስ ቅዱስ እንደቀረባት አውቆ
ሰገደላት /3/ ዘካርያስ ታጥቆ
እመቤታችን ላንቺ -------------
መንፈስ ቅዱስ እንደቀረባት አውቃ
ተሳለመቻት /3/ ኤልሣቤጥም ታጥቃ
እመቤታችን ላንቺ ---------------
አያስደንቅም ወይ የማርያም ትኅትና
ውኃ ስትቀዳ/3/ የአምላክ እናት ሁና
እመቤታችን ላንቺ -----------
የምንጭ ውኃ ምሥጢር የሚያመለክተው/2/
የአምላክ መገኛ ምንጭ /3/ እርሷ መሆንዋን ነው
እመቤታችን ላንቺ --------

**594.ማርያም እመቤቴ**

ማርያም እመቤቴ የአምላክ እናት
ማደሪያ የሆንሽው ዙፋን ለመለኮት
ከሴቶች ሁሉ አንቺ ነሽ የተባረክሽ የነጻሽ በእውነት
ከቶ እንደምን ቻልሽው መድኃኔዓለምን
ሰማይና ምድር የማይችሉትን
ለዚህ የተመረጥሽ ታላቋ እድለኛ
ምሕረትን ከልጅሽ ለምኝልን ለኛ
ማርያም እመቤቴ --------------
ምንኛ ድንቅ ነው ምሕረቱ የወልድ፣
ያንቺን ሥጋ ለብሶ ሲሆነን ዘመድ፡፡
ከዙፋኑ ወርዶ ያገለገለሽ
የሕይወት ሙሽራ ማርያም አንቺ ነሽ
ማርያም እመቤቴ --------------
የነቢያት ሞገስ የሐዋርያት
የሰማዕታት አክሊል የጻድቀን እናት
የእኛ መመኪያችን የኃጥአን ተስፋ
ወልድን በመውለድሽ ኃዘናችን ጠፋ
ማርያም እመቤቴ ----------------

ቅዱሳን በገነት ሲያመሰግኑሽ
መላእክት በሰማይ ሲያገለግሉሽ
እኛም የአዳም ልጆች ከመሬት ሆነን
ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን
ማርያም እመቤቴ ------------

**595.የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ**

የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተልሔም የተቀደስሽ ነሽ
የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ በበረት
የዓለም መድኃኒት ----------------
አዋቂዎች ሁሉ በቅን አሳባቸው
ወደአንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው/2/
የዓለም መድኃኒት --------------
ለተከታይ ትውልድ ምሣሌ ለመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤን /2/
የዓለም መድኃኒት -----------------
የሚያድለው ጌታ እውቀት ለሕፃናት
የሚመሰገን ነው በአፈ መላእክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ በበረት
የዓለም መድኃኒት ---------------
ሥጋ ለብሶ ቢታይ ረቂቅ መለኮት
በአንድ ላይ ዘመሩ ሰውና መላእክት /2/
የዓለም መድኃኒት --------------------

**597.ክርስቶስ በስምህ**

ክርስቶስ በስምህ ይዘናል ቀኖና
ስቅለት ትንሣኤህን እናያለንና
ጾም ማለት እንግዲህ ይኸው ነው ሥርዓቱ
ሐዋርያት ጾመው ለእኛ አበረከቱ
ነፍስና ሥጋችን በመብል ተጣልተው
ሽማግሌ ሆኖ ጾም አስታረቃቸው
አብርው እያደሩ አብረው እይዋሉ
አያምርም አይመስልም በመብል ሲጣሉ
ነፍስም ከስጋዋ መለየቷን አውቃ
የዓለም ተድላዋን ደስታዋን ንቃ
በጾም በሱባኤ ትኖራለች ታጥቃ።
ነፍስም ለሥጋዋ ትመክረው ጀመረች
በብዙ ምሳሌ እያመሳሰለች
ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትውደድ
ከአዳም ጀምሮ ከመጀመሪያው ሰው
መብል ሲጎዳ እንጂ ሲጠቅም መቼ አየኸው /2/

**598.አቤቱ ማረን**

አቤቱ ማረን ይቅር በለን /2/
ያለአንተ መድኃኒት የለን/2/
ሥጋዬን ብሉና ደሜን ጠጥታችሁ
ዘለዓለማዊ ሕይወት ይኑራችሁ
አቤቱ ----------------
ብሎ ነበር እርሱ የሚሰማው ጠፋ
ሁሉም በየድርሻው ምኞቱን ሲያስፋፋ
አቤቱ ------------
በሕይወት ለመኖር ትዕዛዙን ጠብቀን
ምኞት ሳነበዛ እናስብ ስሙን
አቤቱ -----------
በሥጋው ቀድሶ ሲያድነን በደሙ
ምን ውለታ ሠራን ለአምላክ በስሙ
አቤቱ -------------------
ይህን ቅዱስ ሥጋ ይህን ክቡር ደም
እንዴት ልጆች ብቻ በልተውት ይፈጸም
አቤቱ -----------------
ብዙ ሰው ለግብዣ ተጠርቶ ነበረ
ጊዜን በማሳለፍ ከዚያው ከደጅ ቀረ
አቤቱ ----------------
ሌሎቹ በጥበብ ለመዳን ሲደክሙ
ሕይወት የተገኘው በሥጋ ወደሙ
አቤቱ -------------

**600.እስመ ለዓለም ምሕረቱ**

እስመ ለዓለም ምሕረቱ /2/

አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ/2/

አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት/2/

መሐሪ ነውና ለሰው ልጆች ሕይወት/2/

እስመ ለዓለም ምሕረቱ /2/

የምይሞተው ሞቶ የተቀበረው/2/

ከገሀነም እሳት እኛን ሊያድን ነው/2/

እስመ ለዓለም ---------------

ከማርያም የነሣው ያ ቅዱስ ሥጋው/2/

ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው

እስመ ለዓለም ---------

በፈጠርው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ/2/

ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ጎትቶ/2/

እስመ ለዓለም ------------

**601.ተገርፎ ተሰቅሎ**

ተገርፎ ተሰቅሎ የሞተው አንበሳ

ተገንዞ በጨርቅ ተቀብሮ እንደሬሳ

በሞት እጅ ተይዞ አልቀረም ተነሣ/2/

እናምለን ትንሣኤህን

በሥልጣንህ መነሣትህን

አርዓያ ነውና ለሁላችን

አፈር ቢረበረብ ሣጥን ቢደረደር

ድንጋይ በድንጋይ ላይ ደግሞም ቢነባበር

ምድር አልቻለችም አምላክን ለመቅበር /2/

እናምናለን ----------

አምላክ ስትነሣ ፈርሶ መቃብሩ

ሰቶች ትንሣኤህን ደፍረው ተናገሩ

እንሞታለን ብለው ማንንም ሳይፈሩ/2/

እናምናለን -------------

እንግዲህ አልፈራም ሞትና ኩነኔ

አምላክ ከሞተልኝ ተሰቅሎ ስለኔ

ተደምስሷልና የሞት ልጣኔ /2/

እናምናለን ------------------

**602.ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል**

ሰላም ሰላም /2/ ማርያም ድንግል

ልመናሽ ለሚያምኑት ድኅነት ያስጣል /2/

ደቀ መዛሙርቱ በሐሣብ ሲዋኙ

ይኸው በቅርብ ቀን ምልክት አገኙ

ሰላም ሰላም -----------

ለእኛ ለልጆችሽ ኃጢአት ላደከመን

ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን

ሰላም ሰላም -----------

በሐና በኢያቄም እመቤታችን

በዚህች ቀን ባርኪልን ስብሰባችንን

ሰላም ሰላም ---------

603. <u>ስብሐት ለአብ</u>

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ

ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም

ምስጋና ከማቅረብ <u>ከቶ አንወሰንም</u> /2/

ዛሬም ወደፊትም ደግሞሞ ለዘለዓለም

ስብሐት ለአብ ----------

ከዚህ ከማራኪ ከኃላፊው ዓለም

የጠራ ይድናል <u>የፈጣሪውን ስም</u> /2/

ሊኖረን ይገባል ፍቅርና ሰላም

ስብሐት ለአብ ---------------

ያልከውን አስበህ እናንተ ሁላችሁ

ስሜን ከጠራችሁ <u>ሁለት ሦስት ሁናችሁ</u>

እኔም እገኛለሁ በመካከላችሁ

ስብሐት ለአብ ---------

አቤቱ አምላክ ሆይ እንለምንሃለን

እንድትገኝልን በመካከላችን /2/

ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦስት ሆነን

ስብሐት ለአብ ------

**604.በሞት ጥላ ወድቀን**

በሞት ጥላ ወድቀን ስንከራተት/2/
በረቀቀው ፍቅሩ ዋጀን ከጥፋት /2/
በጎልጎታ የታይ ፍጹም መድኃኒት
ሃሌ ሃሌ ሉያ ለአንድ ለኃያሉ ጌታ /2/
ስለእኛ ተዋረድክ በጎልጎታ
የሞት ሸክም ከብዶን በጣር ስንባዝን /2/
ወረደ ከሰማይ መጣ ሊያድነን /2/
ከባርነት ቀንበር ነጻ ሊያወጣን
አዝ-----------
ምንም ባልበደለ ምንም ባላጠፋው /2/
ሁሉን ማድረግ ሲቻል ደካማ የሆነው/2/
ሕይወትን ሊድለን ስለወደደን ነው
አዝ ---------------
እስቲ አስትውሉ የፍቅሩን ብዛት/2/
ለመስቀሉ ሞት ታዝዞ እኛን ያዳነበት/2/
ምንም አቻ የለው የጌታ ቸርነት
አዝ --------------

**605.በዓለም ጥላ ማረፍ**

በዓለም ጥላ ማረፍ አይምስልህ ጤና
ዓለም ከንቱ ጥላ ትሄዳለችና
ዓለም ጥላ ስትሄድ ፀሐይ ስትበረታ
ደግሞ ወድቆ ቀረ የሰው ልጅ አውታታ
ተነሡ እንከተል እኛም ከሄዱት
አፈር ከሽተተን ከያዘን በሽታ
ብንቆርብ አንቀርም ይህን ጊዜ እንበርታ
መቆረብ በሕይወት ነው ንስሓ መግባት
ይህ ሁሉ አይገኝም ከገቡ መሬት
ሰዎች ተጠንቀቁ እወቁ ሁላችሁ
ዓለም አታላይ ናት እንዳታስቀራችሁ

**606.ኑ እንቅረብ**

ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ /2/
ሥጋውን እንብላ/3/ ደሙንም እንጠጣ
የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፋን ኃጢአታችን በንስሓ አንጽተን
እቀበል አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደጌታ (እግዚአብሔር) በእውነት የሚገባው
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው
እንቅረብ -----------
ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት
ከዋክብት ሰማይ የተነጠፋለት
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት
እንቅረብ --------------
ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይኸው ተዘጋጀ
ከግብዣው ተጠራን አዋጁ ታወጀ
መጥቁ ተደወለ እንቅረብ በዕልልታ
በኂላ አይረባንም ዋይታና ጫጫታ
ኑ እንቅረብ ----------------
ይህችን ዕድል ፈጥነን እንጠቀምበት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይበት
ከአሁኑ ቅረቡ ታውጇል አዋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን እንኩ
ኑ እንቅረብ ---------------

**607.የሰው ልጆች ሁላችን እንማር**

የሰው ልጆች ሁላችን እንማር
አስተባብረን ሃይማኖት ከምግባር
የሰው ልጆች ሁላችን እንማር
መልካም ሥራን በመሥራት እንኑር
የሰይጣን ድል መንሻ የክብር መውረሻ
ሃይማኖት ናትና እውነተኛ ጋሻ
አዝማች ------------------
ለእውነተኛ ሥራ ሁላችን እንበርታ

ጻድቃን ሰማዕታትን አድርገን መከታ
አዝማች -------------
ፍዳ ዓለምን አልፈን እንድንሄድ ሁላችን
ጸንተን መገኘት ነው በሃይማኖታችን
አዝማች -----------
የሰይጣን ድል መንሻ የክብር መውረሻ
ሃይማኖት ናትና እውነተኛ ጋሻ
አዝማች ----------------
እምነታችን ሁሉ ይሁን በፈጠሪ
ይቅር ባይ ነውና ሲቻለው መሀሪ

**608.ላይቀር መሞት**

ላይቀር መሞት አፈር መልበስ መግባት ከመቃብር
መስሎኝ ቋሚ ይህ ሥጋዬ ለእርሱ ብቻ ስጥር
ግን ለነፍሴ ቀረ ማስታወሴ/2/
ዘመን መቁጠር ዕለት ወራት ክረምትና በጋ
ሌትና ቀን ሲፈራረቅ ሲጨልም ሲነጋ
በማየቴ ይሆን መደሰቴ/2/
ኸረ ወዲያ ወዲያልኝ ዋይ ይብላኝ ለነፍሴ
አድርጎኛል የኃጢአት ምንጭ ደካማው መንፈሴ
ላልኖር በዓለም ቆሜ ለዘለዓለም
መሐሪ አምላክ ለጋስ ጌታ ቸሩ ፈጣሪዬ
አንተ እኮ ነህ ለዘለዓለም ለእኔ መመኪያዬ
ይቅር በለኝ ምሕረትህ አይራቀኝ/2/

**609.መመኪያዬ አንተ ነህ**

መመኪያዬ አንተ ነህ የነፍሴ መዳኛ
ተመለከት ወደእኔ አትስጠኝ ለዳኛ
ሕይወቴን ለአንተ /2/ ብያለው
አምላክ የእኔ ጌታ የት አገኝሀለሁ፡፡
ከበደሌም አንጻኝ ደግሞሞ ከኃጢአት
በመንፈስ ይታደስ መላ ሰውነቴ
ሕይወቴን ላንተ ---------
አቀበቱ ልቤ በጭንጫ ላይ ትዕቢት
አሸብርቆ ነበር አልፈርስም መስሎት
ሕይወቴ ለአንተ ------------
የጾም ንጉሥ መምጣት ስለተነገረ
መደልደል አለበት እየተሰበረ
ሕይወቴን ለአንተ ---------------
ሶስናን ያደንካት ከሐሰት ምስክር
እኔንም አድነኝ ካልታሰበ ነገር
ሕይወቴን ለአንተ -------------

**610.አምላክ ሆይ ወደእኛ**

አምላክ ሆይ ወደ እኛ ባትመጣ ለብሰህ የማርያምን ሥጋ
ባክኖ የነበር የአዳም ዘር ውጤቱ ነበር የሚያሰጋ
በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን ድኅነትን ለሰው ልጅ ስትሰጥ
ምን የበዛ ነበር ትኅትና ትዕግሥትህ የማይለወጥ
የሾክ አክሊል ደፍተው በራስህ ጎንህን ሲወጉ በጦር
አንተ ግን ለእነርሱ ከአባትህ ምሕረትን ትለመን ነበር
ግን መቼ ዐወቁ እነርሱ በኃጢአት ደንድኖ ልባቸው
መድኃኒታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም ሞትክላቸው
ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍጻሜ በኋላ
ኸረ እንዴት ዕድለኞች ናቸው በፊትህ የሚያገኙ ተድላ
በዚያች በደብረ ዘይት ቦታ ደስታና ልቅሶ ሲፈልቅ
ከቶ ከየት ይሆን እጣዬ ያን ጊዜ የእኔ አወዳደቅ
የፀፀት እሮሮ በፊህ እንዲያቃጥለኝ እኔን
እርዳኝ ፈጣሪዬ ከአሁኑ አድሰው የዛገው ልቤን

**611.የብርሃን መውጫ**

የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል
የተነበየላት ነቢዩ ሕዝቅኤል /2/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር /2/
የዳዊት መሰንቆ የጊዴዎን ፀምር
በገነት መካከል ያለች ለምለም ሳር
አፍርታለችና ያለወንድ ዘር
እስቲ እናመስግናት እንዲህ በማለት

ቅድስት እናታችን ስብሐት ወቡርክት
አንቀጸ ብርሃን ማዕርገ ሕይወት
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በዕውነት
በደኅና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት /2/
እንደመቤታችን አርምሞ ትዕግሥት
ያድለን ፈጣሪ ፍጹም መደኃኒት

**612.ድንግል ሆይ ስላንቺ**

ድንግል ሆይ ስለአንቺ ነውና መሐሪ
አማልጅን ከአንድ ልጅሽ ከፈጣሪ
ስሙን እንዳልጠራ አንደበትም የለኝ
ፊቱንም እንዳላይ ሥራዬ አሣፈረኝ
ድንግል ሆይ ----------------
ታውቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ
ትዕዛዙን እንደሻርኩ ሕጉን እንደጣስኩኝ
አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሣሪ
አማልደን ከጌታዬ ከፈጣሪ
ድንግል ----------------
በፊቱ እንዳላፍር የተጠራሁ ለታ
እለምነዋለሁ ከአሁኑ ይቅርታ
ጻድቃን ሰማዕታት እናንተ ሁላችሁ
አማልዱኝ ከአምላኬ ከአምላካችሁ
ድንግል ሆይ ------------------

**613.ድንግል ማርያም እናታችን**

ድንግል ማርያም እናታችን /2/
የጌታችን እናት ለምኚልን /2/
ክብርህን አትተው ከጫፉ ስትደርስ /2/

**የሆሣዕና መዝሙራት**

614.**የሆሣህና መዝሙር**

ሆሣዕና እምርት እንተ አቡነ ዳዊት /2/
ቡርክት እንተ ትምጽእ መንግሥት /4/
ትርጉም፡- የታወቀች የድኅነት ቀን የምትመጣይቱ
የአባታችን ዳዊት መንግሥት ቡርክት ናት

**615.ሰላምሽ ዛሬነው ኢየሩሳሌም /2/**

ወደአንች መጥቷልና አምላክ ዘለአለም/2/
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕፃናት በኢየሩሳሌም
አንቺ ቤተልሄም የዳዊት ከተማ/2/
የሕዝቦችሽ ብርሃን መጣልሽ በግርማ/2
አዝ --------------
ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙለት/2/
መስቀል ተሸከመ ሊሆነን መድኃኒት /2
አዝ -----------
የኢየሱስን ሕማም ደናግልም አይተው/2/
እያለቀሱለት ሄዱ ተከትለው/2/
አዝ ---------------

**616. እመአፈ ደቂቅ ወሕፃናት**

እመአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ /2/
በእንተ ጸላዒ /4/ ከመትንስቶ ለጸላዒ ወለገፋኢ /2/
ትርጉም፡-ከሕፃናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጅህ የጠላት ዲያብሎስ ምክሩን ታፈርስ ዘንድ

**617.ሆሣእና /2/ በአርያም**

ሆሣዕና በአርያም
ቅድስት ሀገር ሆይ ኢያሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም
አዝ ------
በአህያ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ የመጣው
ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው
አዝ --------
ኃይልና ሥልጣኑ በአንድ ላይ ስላለው ጠላቶች አፈሩ ሕዝብሽም ደስ አለው
አዝ ……….
ሠውማ ቢዘምር ምን ያስደንቃል
ሆሣዕና ሰው ቀርቶ ድንጋይ ያናግራል
አዝ ……..

**618.ሆሣዕና በአርያም**

ድኅነት ሆነ ለሁላችን ዛሬ በዓለም
አክብሮናል ፈጣሪያችን በኢየሩሳሌም

**619. ደቂቅኒ ይጸርሁ**

ደቂቅኒ ይጸርሁ ወሕዝብኒ ኪያሁ ይሴብሕ /2/

ወይብሉ ሆሣዕና በአርያም ብሩክ አንተ

መድኃኔዓለም/2/

**620.አብርሃም ነስዐ /4/**

አእፀቀ በቀልት አብርሃም ነስአ/4/

**621.በትፍሥሕት ወበሐሴት**

በትፍሥሕት ወበሐሴት /2/

ይሁቦሙ ኃይለ ወሥልጣን /4/

**622.ይባዕ ንጉሠ ስብሐት**

ይባዕ ንጉሠ ስብሐት /2/

ይባዕ ንጉሠ ስብሐት /4/

**623.አርዉ ኆኅተ መኳንንት**

አርዉ ኆኅተ መኳንንት /2/

ይባዕ አምላከ ምሕረት

**624.ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና**

ሆሣዕና ብለን እናቅርብ ምስጋና

ሆሣዕና በሉ ሆሣዕና

ለወልደ አምላክ ሆሣዕና

ትኅትናን ላሳየን ››

ስሙ ይባረክ ››

አዝ ……….

ሆሣዕና በሉ ››

ለሰማይ ንጉሥ ››

ግርማን ለብሶ መጣ ››

እኛን ሊቀድስ ››

አዝ ………

ሆሣዕና በሉ ሆሣዕና

ለወልደ ዳዊት ››

ነቢያት በትንቢት ››

የተናገሩለት ››

ሐዋርያት በወንጌል ››

የሰበኩለት ››

አዝ………..

ሆሣዕና በሉ ››

ለአምላከ ምሕረት ››

ተወልዶ ከድንግል ››

እንደ ሕጻናት ››

እረኞች በዋሻ ››

የሰገዱለት ››

የአዳም ልጆች ሁሉ ››

ደግሞም መላእክት ››

አዝ ………

<u>**የትንሣኤ መዝሙር**</u>

**625..ትንሣኤከ ለእለ አመነ**

ትንሣኤከ ለእለ አመነ /2/

ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ /4

**626. አማን በአማን**

አማን በአማን /4/

ተንሥአ እምነ ሙታን/4/

**627. ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ**

ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ/2/

ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ /4/

ምደር ጸዳች ሐሴት አደረገች /2/

በክርስቶስ ደም በእውነት ታጠበች/4/

**628. እም እቶነ**

እም እቶነ እሳት ዘይነድድ አንገፈነ /2/

ብርሃናተ ዘይትአጸፈ ተንሥአ ለነ/4/

ትርጉም፡-ከሚነደው እሳት ከነበልባሉ አወጣን/2/

ብርሃናትን ተጎናጽፎ ተነሣልን/4/

**629. ጌታ ተነሥቶአል እልል በሉ**

አምላክ ተነሥቶአል የምስራች በሉ

ሙስና መቃበር በኃይሉ አጥፍቶ

ሁላችን አየነው ክርስቶስ ተነሥቶ

አዳምን ለማዳን ቃል ኪዳን ገባለት

ዘመኑን ጠብቆ ካሣ ሊከፍላት

ከሰማያት ወርዶ የተሰቀለው
ሞትን በሞት ሽሮ ይኸው አየነው
ደቀመዛሙርቱ እጅጉን ተጨንቀው
በጌታችን መሞት በሐዘን ተሞልተው
በተዘጋ ደጃፍ ተሰብስበው ሳለ
እጆቹን ዘርዓቶ ሰላም ለእናንተ አለ
ማርያም መግደላዊት እየገሠገሠች
በሌሊት ተነሥታ ወደ አምላኳ ሄደች
አይሁድ አንገላተው የሰቀሉት ጌታን
ተነሥቶ አግኝታ ተመላች በደስታ
አዝ -------------

630. **ተስፋ ሕይወት ተሠርዓ**

ተስፋ ሕይወት ተሠርዓ /4/
በሰማያት ተሰፋ ሕይወት ተሠርዓ /4/
ኃይለ ጽልመት ተሠደ /4/
በሰንበት ኃይለ ጽልመት ተሠደ /2/

631. **ሠርአሊነ ሠንበተ ሠንበተ ለእረፍተ ዚአነ**

ሠርዓ ለነ ሰንበተ ሰንበተ ለእረፍተ ዚአነ /2/
ሠርዓ ለነ ሰንበተ ለእረፍተ ዚአነ /2/
ሠራልን ሰንበትን ለእረፍት /2/
ሠራልን ሰንበትን ለእረፍት /2/

632.**ፈኑ ዲቤነ ብርሃነከ**

ፈኑ ዲቤነ ብርሃነከ /4/
ትንሣኤ ትንሣኤከ ለእለ አመነ/2
ትርጉም፡- ትንሣኤህን ለምናምን ለእኛ ብርሃንን ላክልን

633. **መድኃኒተ ኮነ**

መድኃኒተ ኮነ /8
ለአሕዛብ መድኃኒተ ኮነ /4
ትርጉም፡- ክርስቶስ ለእኛ ለኃጥአን መድኃኒታችን ነው፡፡

634.**ክርስቶስ ተንሥአ**

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን /2
አሠሮ ለሰይጣን አግዓዞ ለአዳም ሰላም ሰላም እምይእዜሰ ይኩን ሰላም/2/
ትርጉም፡- ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን በታላቅ ኃይል በታላቅ ሥልጣን ሰይጣን አስሮ አዳምን ነጻ አወጣው ከእንግዲህ ይሁን ሰላም

635.**ንሴብሖ**

ንሴብሖ /2 ለእግዚአብሔር /2/
ስቡሐ ዘተሰብሐ /4
እናመስግነው /2/ እግዚአብሔርን /2/
ምስጉን ነው የተመሰገነ /4/

635. **እሰይ ተነሣ እሰይ እሰይ ተነሣ**

እሰይ ተነሣ እሰይ እሰይ ተነሣ /2/
ተደመሠሠ በአምላክ የዓለም አበሣ
ክብርና ምስጋና እሠይ እሠይ ተነሣ
ይግባው ፈጣሪያችን እሠይ እሠይ
ሞትን አሸንፎ እሠይ እሠይ
አርዓያ የሆነን እሠይ እሠይ
አዝ.......
በክርሰ መቃብር ››
ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ››
ተቀብሮ አልቀረም ››
ተነስቷል በሰንበት ››
አዝ.......
ለሐዋርያቱ ››
የምሥራች ያለች ››
ማርያም መግደላዊት ››
ምንኛ ታደለች ››
አዝ.......
ዘበኞች ቢያቆሙ ››
አይሁድ ተሞኝተው ››
አልቻሉም ሊያስቀሩት ››

ሞትን ድል አደረገው ››
አዝ.....

**637.ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንፀባርቅ**

የአምላክና የሰው ልጆች እውነተኛ እርቅ
ደስ ይበለን በትንሣኤው ብርሃን
እልል እንበል በአንድነት ሆነን
ተነሣልን መድሃኒታችን
ከፊት ለፊት በመሣሉ የመስቀሉ ነገር
የሚወደው ሐዋርያ የወንጌል መምህር
ዮሐንስም ስቅለቱን በማየቱ
ሲያዝን ኖረ በምድራዊ ሕይወቱ
ቢያሠቅቀው ሞቱ ግርፋሩ
ሞኝነት ነው ለሚጠፋት መሠናከያቸው
በዓለም ጥበብ ለሚኖሩት እውነት ተስኗቸው
ለጠቢብ ሰው በመንፈስ ለሚኖረው
እውነተኛ የመዳን ቀን ዓርማ ነው
ከገሃነም እሳት የሚያደን ነው
እስከመሞት ላስተለየው ቅዱስ ሐዋርያ
ለዮሐንስ የወንጌል ሰው ለፅድቅ ባለሙያ
ምስጋናችን በምድር ይድረሰው
እንላለን በሰጠን ምሣሌው
ሰዎች ሁሉ እንከተለው

**638.የሕያዋን አመላክ ሙታንን ሊያስነሳ**

በእኩለ ሌሊት ክርስቶስ ተነሣ /2/
ሙታን ይደለንም ክርስቶስ ተነሣ
ሕያዋን ነን እኛ ክርስቶስ ተነሣ
በመስቀሉ የዳንን ››
ከኃጢአት ቁራኛ ››
የተዋረደውን ››
ሊያከብር ዳግመኛ ››
ሞትን አሸንፎ ››
ተነሣልን ለእኛ ››
አዝ ------------
እናንተስ አትፍሩ ክርስቶስ ተነሣ
እነግራችኋላው ››
የተሠቀለውን ››
እንድትሽ አውቃለው ››
ሕያዉን ከሙታን ››
ለምን ፈለጋችሁ ››
እንደተናገረው ››
ተነሥቷል ጌታችሁ ››
አዝ --------
ክርስቶስ ሲነሣ ክርስቶስ ተነሣ
በሰንበት ሌሊት ››
አስቀድሞ ታየ ››
ለመግደላዊት ››
እርሷም ትንሣኤውን ››
ለዓለም አበሠረች ››
ጌታዬን አየሁት ››
ተንስቶአል እያለች ››
አዝ ---------

**639. እልል አማኑኤል ተነሣልነም**

እልል /6 አማኑኤል ተነሣልን
ደስ ይበልን ሁላችንን
የሲዖል ደጆች ተከፈቱ እልል
የሰይጣንም ሠራዊቶች አፈሩ እልል
በጨለማው ዓለም ተወጠን ሳለን
ጌታ በትንሣኤው ዛሬ አበራልን
አዝ ------
መቃብራት ሁሉ ተከፈቱ እልል
የታሠሩ ነፍሳት ከግዞት ተፈቱ እልል
መግደላዊት ማርያም ትንሣኤውን አይታ
ነገረች ለሐዋርያት በደስታ ተሞልታ
አዝ -------
ሁለቱ መላእክት ብርሃን የለበሱ እልል
ተነሥቷል አሏቸው ሴቶቹ ሲደርሱ እልል

ሐዋርያት አይተው ዜና ትንሣኤውን
አሏአቸው ለድኅነት ሰላም ለእናንተ ይሁን
አዝ ----------

640. **ክርስቶስ ተነሣ**

ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን በታላቅ ኃይል በታላቅ ስልጣን /2/
ሰይጣንን አስሮ /2/ ነፃ አወጣን አዳምን /2

641.**እንዘምር ሁላችን ለቸሩ ፈጣሪ /2**

በትንሣኤው ኃይሉ ሞትን አሣፋሪ /4
እሰይ አገኘነው ሕይወታቸንን /2 ደስ ይበለን /2
ትጉህ የማይተኛ ጊዜውን አክብሮ /2
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል በርብሮ/2/
አዝ -------
ሞት ሆይ ወዴት አለህ ከቶ ማሸነፍህ /2
ኃይልክ ተዋረደ አንተም ድል ተመታህ /2/2
አዝ -----
አረገ በስብሐት አገረ በእልልታ /2
ሞትን ድል አድርጎ የሠራዊት ጌታ /2/2
አዝ ------

642.**ገበረ ሰላመ በመስቀሉ**

ገበረ ሰላመ በመስቀሉ /2
ትንሣኤሁ አገሀደ ሰላም ገብረ/4

643.**ሠላም ሠላም**

ሠላም ሠላም /2
እምይእዜስ ይኩን ሰላም /4

644.**ኑ እናምስግን በዝማሬ በእልልታ**

ጠላት ድያብሎስን በሞቱ የረታ
ከእኛ ጋራ ነውና የሠራዊት ጌታ
ጨለማውን ኑሮ የሰደት ሕይወት
በእግዚአብሔር ፍቅር ብርሃን በራበት
ባርነት ቀርቶ ነጻነት ወጣን
ልመናችንን እግዚአብሔር ሰማን
አዝ -----
መሠናክሉን ክፉውን ፈተና
አልፈነው ወጣን በአምላክ ጎዳና
አምላክ ከኛ ጋር ስለነበር
ዲያብሎስ አፍሮ ተዋርዶ ቀረ
አዝ -----
የሚያስጨንቅ ዛሬ ተፈታ
የሕዝቡን እንባ አበሰ ጌታ
በምሕረቱ ስለጎበኘን
አምላካችን ኑ እናመስግን
አዝ ----

645.**ፋሲካ/6**

ተዝካረ ትንሳኤሁ ለመድኃኒነ/4/

646.**ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታን**

ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታን/2/
ተንሥአ ወፈትሆሙ ለሙቁሐን

**ጵራቅሊጦስ መዝሙር**

647.**አንትሙስ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም/**

አንትሙስ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም/2
እስከትለብሱ ኃይለ እምአርያም /4/
እናንተ ግን ቆዩ በኢየሩሳሌም ሀገር /2
እስክምታገኙ ኃይል ከሰማይ /2

648.**አምላካችን ዐረገ**

648.አምላካችን ዐረገ /2/ ወደ ሠማያት /2
የሠማይ መላእክት በደስታ እያጀቡት ዐረገ ወደሰማያት /2/

649.**ኃበ አቡሁ ዐርገ ሠማያት ዐርገ ሠማያት**

ኀበ አቡሁ ዐርገ ሰማያት ዐርገ ሰማያት /2
ጰራቅሊጦስሃ መንፈስጽድቅ አውረደ /4
ትርጉም፡- ወደ አባቱ አረገ መንፈስቅዱስንም ላከልን

650.**ዐረገ በስብሐት**

ዐረገ በስብሐት /2 ውስተ ሠማያት /2
ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግም ይመጽእ በስብሐት

ትርጉም በምስጋና ወደ ሰማይ አረገ በአባቱም ቀኝ
ተቀመጠ ዳግመኛም በምስጋና ይመጣል

**651.ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ዕርገቱ ለክርስቶስ**

እምድኅረ ተንሥአ እሙታን በአርብዓ ዕለት
በይባቤ ወበቃለ ቀርን አማን መንክር ስብሐተ
ዕርገቱ
አማን በአማን /4
መንክር ስብሐተ እርገቱ /4

**652.ዐቢያ ዜማ ተሰማ** /2

እንዘ የአርግ ወልድ ዲበ መንበሩ
ሚካኤል ወገብርኤል ትንሣኤሁ ዘመኑ/2/

**653.ዐርገ እግዚእነ** /4

በይባቤ /4/ ወበቃለ ቀርን /2
ጌታችን ዐረገ /4
በእልልታ/4/ በመለከት ድምጽ

**654.ዐረገ በስብሐት ዐረገ በእልልታ በስብሐት** /2

በእልልታ ዐረገ ዐረገ በእልልታ
ሞትን ድል አድረጎ የሠራዊት ጌታ /2
ዐረገ ዐረገ በእልልታ

**655.ዘመሩ ለአምላካችን ዘምሩ**/2

ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ /4
ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ /2
ይክበር ይመስገን መድኃኔዓለም የዓለም
ቤዛ/4

**656.ወይቤሎሙ ሑሩ ወመሀሩ ለዘየአምን** /2

ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት /4/
በሕይወታችሁ ስበኩ በኑሮአችሁ
ከጽንፍ እስከ ጽንፍ
በዓለም ዙሪያ አዳርሱ ሳትሰለቹ
ደመና ጠቅሳችሁ እንደወፏ
አዝ -----
በኃጢአት ገመድ ተይዞ ለታሰረው
በዓለም ጽልመት ለተዋጠው
የእውነት መንገድ ብርሃን ለጠፋበት
በሁለንተናው ፈንጥቁበት
አዝ -------
የጽድቅ እንጀራ በማጣት ለተራበው
የሕይወታችን ውኃ ለተጠማው
ቀቢፀ ተስፋ በልቡ ላደረባት
የወንጌልን ማዕድ አቅርቡለት
አዝ----------
አርድአተ ወንጌል ካህናት ሊቃውንት
ለተልዕኮ የጠራችሁ
ከእውነተኛው ምንጭ ከጌታ ከባሕሩ
ከሕይወትን ውኃ የጠጣችሁ
አዝ -----
ወይበሎሙ ሑሩ ወመሐሩ ለዘየአምን /2
ወንጌል መንግሥተ ሰማያት /4

657.መንፈስ ቅዱስ ወረደ ላዕለ ሐዋርያት /2

ተመሲሎ /5 በነደ እሳት /2
መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በእሳት
አምሣል ወረደ

658.እየባረካቸው ወደ ላይ አቀና/2

መድኃኔዓለም /2 አረገ በክብር ደመና /2/
ተሰብስበው ሳሉ ሁሉም በአንድነት
በመካከል ሆኖ ሥግው መለኮት
ባረካቸው ቀደሳቸው አረገ በዓይን እየታያቸው /2
አዝ ----
እንዲልክላቸው አጽናኙን መንፈስ
ከላይ ከአርያም ከአባቱ ሲደርስ
ኃይል ሆናቸው አጸናቸው /2
በቃሉ አንድ አደርጋቸው
አዝ -----
በአንድነት ሆነው ኢየሩሳሌም
ተስፋ ሲጠብቁ ከላይ ከአርያም

መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሣል /2
ወረደ በምሕረት ወሣህል
አዝ ----
መላእክት በሰማይ እልል እልል አሉ
እርገቱን አጅበው ምስጉን ነህ እያሉ
የሰማይ ደጅ ተከፈቱ ዘመሩ ሊቀመላእክቱ /2
አዝ ---------
659.

670.

<u>የግንቦት ልደታ</u>

671.**ዮም ኮነ ፍሥሐ**
ዮም ኮነ ፍስሐ በእንተ ልደታ ለማርያም /2/
አማን አማን በአማን ተወልደት /2 እመብርሃን/2/
672. **እስመ እበውእ ውስተ**
እስመ እበውእ ውስተ መካን ማኅደረ ስብሐት ቤተ እግዚአብሔር
በቃለ አሚን ወበትፍሥሕት ደምጹ
እለ ይገብሩ በዓለ ልደታ ለማርያም
ትርጉም፡- እገባለሁና ወደቦታዋ ማኅደረ ስብሐት ቤተ እግዚአብሔር በእምነትም ቃል በደስታም ዘምሩ የማርያም ቅድስት ልደቷን የሚያከብሩ
673.**እምሐና ወኢያቄም** /4/
አላ በሩካቤ ዘበሕግ /2
674.**ዓምደ እሳት ጾርኪ** /4/
ኦ ማርያም /3/ መንክር ልደትኪ
675.**አማን በአማን** /4/
ተወልደት እመብርሃን /4/
676.**የምስራች ተወለደች እሰይ እሰይ**
የአምላክ እናት /2/ የመድኃኔዓለም /2/2
ተወለደች ድንግል ማርያም
677.**ኦ ማርያም መንክር ልደትኪ ወእጹብ ግብርኪ /2/**
ጾርኪ /3/ዓምደ እሳት መደኃኔዓለም/2/
678.**ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መድኃኒት /2/**
እናመስግናት እናወድሳት እንውደዳት /2/2
እንውደዳት የአዳም ሕይወት
አዳም ሲሠደድ ከጥንቱ ርስቱ
ፊቱን ሸፈነው ጭንቁት ፍርሃቱ
እያለቀሰ ገነትን ሲያጣ
ተስፋ አንቺ ሆነሽው የመደን እጣ
ሊባኖስ ተራራ ተሰማ ዜና
ምሥራቅ ወለዱ ኢያቄም ወሐና
ዳግማዊት ሔዋን ምክንያተ ድኅነት
ልደቷን ሰማን በቅድስት ዕለት
የልደትሽ ቀን ልደታችን ነው
በአንቺ ነውና ልጅ የተባልነው
ፋራን የተባልሽ ቅድስት ተራራ
በአንቺ መወለድ አለሙ በራ
679. **አዕይንታ ዘርግብ/ 2/ኢያቄም ወለዳ**
ኢያቄም ቀለዳ /6 ዘርግብ ኢያቄም ወለዳ/2/
ትርጉም ፡- አይኖቿ የርግብ ዓይን የመሠለ ማርያም ኢያቄም ወለዳት
680.**አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ በላዕሌኪ** /2
ጻኢ እም ሊባኖስ እኅትየ መርዓት 4/
ትርጉም፡- የለብሽም ነውር ምንም በላይሽ ላይ/2
ውጪ ከሊባኖስ እኅትየ መርዓት /4
681.**ከሊባኖስ**
ከሊባኖስ ከሊባኖስ ከልጅሽ ጋር ነይ
እመ አዶናይ ከሊባኖስ ወደእኛ ነይ
ጥበቃሽ ዘወትር ከሊባኖስ
እንዳይለየኝ ››
በሔድኩበት ሁሉ ››

ማረፊያ ሁኚኝ ››
አዝ .........
እኔ ባሪያሽን››
ድንግል አትርሺኝ ››
በጽድቅ ሠሌዳ ››
ስሜን ጻፊልኝ ››
አዝ ........
ነፍስና ስጋዬ ››
አደራ እልሻለሁ ››
በልጅሽ ጽኑ ፍቅር ››
ተማጽኜሻለሁ ››
በልጅሽ ጽኑ ፍቅር ››
ተማጽኜሻለሁ ››
አዝ ..........
ከመሞት በፊት
ለንስሓ አብቂኝ
ለነፍሴ ማረፊያ
አዘጋጂልኝ
አዝ .....................
ከአንበሶች መኖሪያ
ከነብሮች ተራራ
መጥተሽ አስደስቺኝ
እናቴ ሙሽራ
አዝ ........................
የልብስሽ መዓዛ
የሊባኖስ ሽታ
ሮማን ናርዶስ ነው
እናቱ ለጌታ
አዝ .......................
እመቤቴ ስልሽ
ስምሽን ስጠራ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ
ከቅዱሳን ጋራ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ
ከሚካኤል ጋራ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ
ከገብርኤል ጋራ
ፈጥነሽ ደረሺልኝ
ከዑራኤል ጋራ

682. **አማን በአማን /4/**
እምብርሃን ተወለደት /4/

683. **እኅትየ መርዓት ማርያም ቅድስት /2/**
እምዘመዶሙ ለካህናት /4
እኸ እኅትየ ይብልዋ መላእክት በክብር /2/
ለማርያም ድንግል /4/

684.. **ኢያቄም ወለዳ ኢያቄም /2**
ዳዊት ዘመዳ ኢያቄም ወለዳ /4
ትርጉም፡- የኢያቄም ልጅ የዳዊት ዘመድ ናት

685.**ሐመልማላዊት /6**
ሙሴ ዘርእያ/2 በደብረ ሲና /2 ማኅደረ ስብሐት /2

686.. **ኢያቄም ወኸና እናት አባትሽ ቤተ እግዚአብሔር**
ወስደው ስእለት የሰጡሽ መና ከደመና
የወረደልሽ ፍጹም ድንግል የሆነሽ
ማርያም አንቺ ነሽ
ኦ እመ ክርስቶስ ማርያም አንቺ ነሽ
ኦ የክርስቶስ እናት ማርያም አንቺ ነሽ

687. **ማኅደረ መለኮት /2/**
ማርያም እመብዙኃን /4

688.**ኢያቄም ወሐና /4**
ድንግል ማርያም ወልደዋቷልና
ይድረሳቸው ክብርና ምስጋና

689. **ኦ ድንግል አምሣል ወትንቢት /2 የሐዋርያት**
ሞገሶሙ ለሐዋርያት /4
ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢት የሐዋርያት
ሞገሣቸው አንቺ ነሽ

690.**የሐና ልጅ ነሽ የኢያቄም በረከት /2/**

ድንግል ድንግል ወለዲተ ቃል
የሐና ልጅ ነሽ የፀሐይ እናቱ
የሐና ልጅ ነሽ ድንግል የምሥራቅ ደጅ
ቅድስት ቅዱሳን
የፍጥረት አማላጅ
ለእናቷ አንዲት ናት
ለወለደቻት
የኢያቄም ስጦታ
ምሣሌም የላት
አዝ….
የጾም ጸሎት ፍሬ
የቅድስና ሀብት
ከአምላክ የተሰጠች
ንጽሕት እመቤት
ደመና በመሆን
ሕዝብን የጋረደች
የኢያቄም በረከት
ድንግል ማርያም ነች
አዝ……
በሊባኖስ አድባር
ዛሬ ደስታ ሆነ
መላእክት ዘመሩ
እርቅም ተወጠነ
እኛም ደስ ይበለን
መዳናችን ቀርቧል
ከሐና ከኢያቄም
ንጹሕ ዘር ተገንቷል
አዝ…..
የሰላም ብሥራት ነሽ
የፍጥረታት ተስፋ
በአንቺ ቅድስና
ሐዘናችን ጠፋ
ምክንያት አንቺ ሆንሽን
ዓለም ሁሉ ዳነ
እግዚአብሔር ታረቀን
ሁሉ በአንቺ ሆነ

691.**ማርያምስ ተሐቱ እም ትካት ውስተ ከርሱ**
ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ /2
እሰመ በእንቲአሃ ወበእንተ አዝማዲሃ
ተሰቀልኩ ዲበ እፅ ይቤ መድኃኔዓለም /2
ትርጉም፡- ማርያምማ ታበራለች በአዳም ባሕርይ ውስጥ እነደ ነጭ እንቁ በአዳም ባሕርይ ውስጥ /2
እርሷን ደስ ይበላት ብሎ ስለወገኖቿ
ተሰቀልኩ አለ በእንጨት መስቀል ላይ መድኃኔ ዓለም /2

692. **ማርያም ድንግል ምክሆን ደናግል ይእቲኬ**
ቤተ ምስአል ዘአሰሀጸቡ ታቀልል /2
ለኩሉ ፍጥረት ትተነብል በአክናፈ መላእክት ትኬለል
ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል
ትርጉም፡- ማርያም ድንግል መመኪያቸው ለደናግል እርሷም እኮ የምልጃ ቤት ናት የሚያስጨንቀውን የምታቃልል /2
ለፍጥረት ሁሉ ትማልዳለች በመላእክት ክንፎችም ትጋረዳለች እርሷ ትበልጣለች ከኩሩቤል
ደግሞም ትልቃለች ከሱራፌል

693. **እስመ እም ዘርዓ ዳዊት ዘመጽአ** /2
በቤተልሔም ዘይሁዳ /4
ትርጉም፡- የእመቤታችን ትውልዷ ከዳዊት ወገን ነው
ከዳዊት ዘር የመጣው የይሁዳ ክፍል
ለምትሆን በቤተልሔም ተወለደ

694. **ማርያም ንጽሕት ድንግል ማእመንት**
ወላዲተ አምላክ ሰአሊተ ምሕረት ለውሉደሰብእ /2
ሰአሊ ለነ ኀበ ክርስቶስ ወልድኪ ይሥረይ
ኃጢአተነ ሰአሊ ለነ ቅድስት

ትርጉም፡- ማርያም ንጽሕት ድንግል ታማኝ
አምላክን የወለድሽ የምሕረት አማላጅ ነሽ
ለሰው ልጅ ሁሉ /2/
ለምኝልን ከልጅሽ ከክርስቶስ ይቅር እንዲለን
ቅድስት ሆይ ለምኝልን /2

**695. ንጽሕተ ንጹሐን ከዊና ከመታቦት ዘዶር**
ዘሲና ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግልና
ነበረት /2
ሲሳያ ኅብስተ መና ወስቴሃኒ ስቴ ጽሙና/2

**696. ዮም ፍሥሐ ኮነ** 2/ **በእንተ ልደታ ለማርያም** /2/ በባርነት ሳለን
ኃጢአት በዓለም ነግሣ
በድንግል መወለድ
ቀረልን አበሣ
እግዚአብሔር መረጠሽ
ልትሆኚ እናቱ
ይኸው ተፈጸመ
የዳዊት ትንቢቱ
አዝ…………
የሔዋን ተስፋዋ
የአዳም ሕይወት
የኢያቄም የሐና
ፍሬ በረከት
ምክንያተ ድኅነት
ኪዳነምሕረት
ድንግል ተወለደች
የአምላክ እናት
አዝ……..
በሔዋን ምክንያት
ያጣነውን ሰላም
ዛሬ አገኘነው
በድንግል ማርያም
የምሥራች እንበል
ሐዘናችን ይጥፋ
ተወልዳለችና
የዓለም ሁሉ ተስፋ
አዝ…………

**697. እንተ በምድር ሥረዊሃ/**
ወበሰማይ አእጹቂሃ/
ሐረገወይን ሐረገወይን
ድንግል ሐረገወይን

**698. አማን በአማን/4/**
እመብርሃን ተወልደት/4/

**699. ሰአሊ ለነ ማርያም ሰአሊ ለነ 2/**
አክሊለ ንጹሐን/2/ ሰአሊ ለነ 4/
ትርጉም፡- ለምኝልን ማርያም ለምኝልን/2/
የንጹሐን አክሊል/2/ ለምኝልን/2/

**700.ሰላም እለኪ/6**
ሰላማዊት ማኅደረ ስብሐት
ሰላማዊት ደብረመድኃኒት

**701. ኮነ ዮም/2/ በእንተ ልደታ ለማርያም/2/**
ከመ ትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃን ነቢያተ ከመ ትቤዙ/2/

**702. ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደታ ለማርያም**
እምሐና ወኢያቄም ከመ ትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃነ አማን
ተወልደት እመብርሃን

702 **-ሀ-. ሰአሉለነ** <u>**ሐና ወኢያቄም**</u>/2/
ዘወለድክምዋ ለድንግል ማርያም/4/
ለምኑልን <u>ሐና ወኢያቄም</u>/2/
እናትና አባቷ የድንግል ማርያም

**702-ለ-.እሰይ ተወለደች በዛሬዋ ዕለት ድንግል ማርያም**
የአምላክ እናት /2/
የምስራች እልል በሉ የአዳም ልጆች ሁሉ
የምስራች እልል በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ

702 **-ሐ- ሐናና ኢያቄም በስለት ያገኙሽ/2/**
ድንግል እናታችን <u>በጣም ደስ ይበልሽ</u> /2/
ለመዳን ምክንያት የሆነችው እናት /2/

ንጽሕት ቅድስት እያልን <u>እናመስግናት</u>/2/
በቤተመቅደስ ኖርሽ በቅድስና/2/
እየተመገብሽ <u>ሰማያዊ መና</u>/2/
እጹብ ነው ድንቅ ነው የአምላካችን ሥራ/2/
የሰጠን ድንግልን <u>እንዳናይ መከራ</u>/2

<u>**የቅዱሳን መላዕክት መዝሙራት**</u>

**703. እንደአናንያ**

እንደ አናንያ እንደአዛርያ እንደ ሚሳኤል
አጽናን እኛን/2/
አጽናን እኛን/3/ በእምነታችን/2/

**704.ሚካኤል**

ሚካኤል ገብርኤል ዑራኤል ሱርያል ወፋኑኤል/2/
ሚካኤል ሊቀ መላእክት አማልደን በምሕረትህ
ልመናችን ቀርቧል ፊትህ/2/
ገብርኤል ሊቀ መላእክት ሠለስቱ ዲቂቅን ከእሳት
ያወጣህ በእውነት/2/
በሐዘናችን በመከራችን ቁምልን ከፊታችን
ዑራኤል ነህ አለኝታችን/2/
ወላጆችን ሲጨንቃቸው እንዲፈታ ማኅፀናቸው
ሩፋኤል ነህ ረዳታቸው

**705.ገብርኤል**

ገብርኤል አብሠራ ለድንግል ወይቤላ/2/
ትወለዲ ንጉሥ ገብርኤል ይቤላ/2/
**ትርጉም፡-** ለእመቤታችን ገብርኤል
አበሠራት
እንዲህም አላት ንጉሥ ትወልጃለሽ

**706.ውእቱ ሩፋኤል**

ውእቱ ሩፋኤል ውእቱ መልአከ ኃይል
ልዑል ውእቱ ልዑል መንበር
ይስአል ለነ ይስአል ለኢትዮጵያ
**ትርጉም፡-** የኃይል መልአክ ሩፋኤል ነው
እኛን ይጠብቀን ሀገራችንን ኢትዮጵያ
ይርዳልን

**707.አማልደን ስንልህ**

አማልደን ስንልህ ስማን እዘንልን/2/
አጽናን አረጋጋን/2/ ገብርኤል
የእኛ መመኪያ አባታችን
እግዚአብሔር ራሱ ክብርን አቀዳጅቶህ
ለተልዕኮ እንድትፈጥን አድርጎ የሾመህ
እንደ ሦስቱ ሕፃናት አንተን እንደጠሩ
ዛሬም አውጣን ገብርኤል ሆይ ከነፍሳችን ጠላት
እምነት አለን እያልን የቀና ምግባር
እባክህን ሊቀመላእክት እንድስት ርዳን
መላእክትን ሁሉ ያረጋጋሀቸው
እንተኮ ነህ ኃያል መልአክ ጽኑ ቁሙ ያልካቸው
እኛስ እናምናለን በአማላጅነትህ
በተሠጠህ በአምላክ ጸጋ ኃይላችን አንተ ነህ
የምሥራች መልአክ ተብለሃልና
ደስ አሰኝን ደስታ ስጠን ተጨንቀናልና
ኢትዮጵያንም ታደግ ተዋሕዶንም ጠብቅ
ሊቀመልአክት በል ቁምልን ሰይፍህንም ታጠቅ
ሠራዊትህ ከበው እነርሱ ያጽናኑን
ዘወትር ሳትርቀን ሰላምን ለግሠን
አዝ----

**708.ኦ ገብርኤል**

ኦ ገብርኤል መልአክ ናዝዘኒ ወአጽምአኒ ቃልከ/2/
አይመርየ /2/ በእንተሰ አሰስኩ ኪያከ/2/
**ትርጉም፡-** ቃልህ አረጋጋኝ አጸናኝ ስለዚህ አውቄ
አንተን ፈለኩህ

**709.ሩህሩህ**

ሩኅሩኅ መልአክ ነህና ለሁሉ የምትራራ/2/
ገብርኤል አዛኙ እንተ አውጣን ከመከራ/4/
የሚያሳድዱኝ ገብርኤል ሲቆሙ ከፊቴ
ጋሻ ይሆነኛል ገብርኤል ›› ጠባቂው አባቴ
እሳተ ነበልባል ገብርኤል›› ኃያል መልአክ ነህ
ስምህን ሲጠሩ ›ገብርኤል› ፈጥነህ ትደርሳለህ

አዝ ------
በራማ የምትኖር ገብርኤል የመላእክት አለቃ
አብሣሪ መልአክ ነህ ›ገብርኤል› የእኛ ዋስ
ጠበቃ
ቂርቆስ እናቱን ገብርኤል›› አንተ አዳንካቸው
ከእግዚአብሔር ተልከህ ›› ከሞት ሠወርካቸው
አዝ ---------ገብርኤል
ለእነ ሚሳኤል ገብርኤል ለእነ አናንያ
ረዳት ሆንካቸው ገብርኤል›› ለእነ
አዛርያ
ለኛም መድኃኒት ነህ ገብርኤል››
በእምነት ለለመንህ
ሁሌ ትደርሳለህ ›ገብርኤል›
በአማላጅነትህ

**710.የራማው ልዑል**

የራማው ልዑል ገብርኤል /4/
ተመላለስ መሀለችን ስምህን ጠርተን ና
ስንልህ/2/
ትርጉም፡- ገብርኤል ለመናገር ትሩ ልሣን
ስጠኝ /እንደበት ስጠኝ/ መንፈስ
ቅዱስን አሳድርብኝ የብርሃን
መጎናፀፊያ እድንጎናፀፍ በመልጃህ
ተራዳን

**711.ገብርኤል**

ገብርኤል አማልደን ከአምላካችን /2/
እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን
አደራህን ቁምልን ከጎናችን /2/

**712.የብርሃናት አለቃ**

የብርሃናት አለቃ የጌታ ባለሟል ሊቀ
መላእክት /2/
ንዓ ራጉኤል /4/ ራጉኤል መጋቤ
ብርሃናት/2/ ኸኸ/2/
ከዋክብትን ልትመግብ ፀሐይን ልትመራ
ሥልጣን የተሠጠህ
ሥራህ የደመቀ ራጉኤል አንተ ነህ /2/
ራጉኤል መጋቢ ብርሃን/2/ ኸኸ
አዝርእት አብበው ፈክተው
የሚታዩት እጅጉን ለምልምው/ኸኸ/ 2/
በፀሐይ ብርሃን በአንተ አጋዥነት ነው /2/
ራጉኤል መጋቤ ብርሃን /2/ ኸኸ

**713.ቅዱስ ገብርኤል ርዳን**

ቅዱስ ገብርኤል ርዳን ሊቀ መላእክት /2/
ልጆችህን አውጣን ከሚነድ እሳት
ልጆችህን አውጣን ከዓለም እሳት
ከማይጠፋው እሳት ከዚያ ነበልባል
ከጨለማው ሥርዓት ከክፉ ሲኦል
ነፍሳችንን ነጥቆ ሰይጣን እንዳይጎዳን
ዋስ ጠበቃ ሁነን ቅዱስ ገብርኤል ርዳን/2/
ረድኤት በረከትን ጸጋህ አይለየን
እንለምንሃለን አደራ እንዳትርቀን
የቀደመው ጠላት ዙሪያችን ከቦናል
ቅዱስ ገብርኤል ድረስ የእግዚአብሔር
ባለሟል/2/
ናቡከደነጾር ገደል ሲከታች
እሳቱን አንድዶ ከእሳት ቢጥላቸው
ከራሳቸው ፀጉር አንድ እንኳን ሳይጠፋ
ቅዱስ ገብርኤል ደርሶ ሆነላቸው
ተስፋ/2/
ብቸኝነት ከብዶን ሐዘን ሲያስጨንቀን
እኛ እንጠራሃለን ቅዱስ ገብርኤል ብለን
በፈጣሪያችን ፊት ስለእኛ ቆመህል
የነደደብንን እሳት አብርደሃል/2/
ሥልጣንህ ግሩም ነው በአምላክህ ፊት
እንሠግድልሀለን የጸጋ ስግደት
ፈጥነህ የምትሰማን ወዳንተ ስንጮህ

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል
ነህ/2/
አዝ ----

#### 714.ገብርኤል መጽአ

ገብርኤል መጽአ ይርድአነ ወያድኅነነ/2/
ተፈኒዎ/2/ እም አርያም /2/ ከመ
ያድኅነነ/2/
ገብርኤል መጣ ሊረዳን ሊያድነን /2/
ተልኮ /2/ ከሰማይ /2/ እኛን ሊያድነን

#### 715.ገብርኤል ነው

ገብርኤል ነው በእውነት አስደሣች
መልአክ/2/
ትርጓሜ ሰው ሆነ አምላክ/2/
ቂርቆስና እናቱ ከእሳት ሲጣሉ/2/
ውኃ ሆነ ጠፋ ነበልባሉ/4/
ቤተ መቅሰስ ስትኖር ድንግል እመቤት
/2/
አበሠራት የአምላክን ልደት/4/
ሠለስቱ ደቂቅ ከእሳት ሲጣሉ/2/
ውኃ ሆነ ጠፋ ነበልባሉ/4/
ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያዳነ/2/
ገብርኤል ዛሬም ያድነን/4/

#### 716.ቀዋምያን

ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት
ዑራኤል ወሩፋኤል /2/
ይትፌነዉ ለሣህል /2/ እምነበ ልዑል/2/
ለነፍሳት የቆሙ እነዚህ መላእክት
ዑራኤልና ሩፋኤል /2/
ከልዑል ዘንድ ለይቅርታ /2/ ይላካሉ
ከልዑል/2/

#### 717.ይቀልል

ይቀልል ሩጸቶሙ/2/
እም ነፍሳት ሑረቶሙ/2/
ትርጉም፡- ሩጫቸው ከነፋስ ይፈጥናል

#### 718.ገብርኤል ምልአኒ

ገብርኤል ምልአኒ መንፈሰ ልሣን
ለተናብቦ መንፈሰ ልሣን /2/
ሞጣዕተ ብርሃን /2/ ዘይት ገለብቦ ሞጣዕተ
ብርሃን/2/

#### 719.ራጉኤል ከሰማያት

ራጉኤል ከሰማያት እኸ
በልዕልና ወረዳ በልዕልና /2/
ፈጣሪያችን አማኑኤል እኸ
ልመናችንን ተቀበል በራጉኤል
ልመናችን ተቀበል በሩፋኤል
ልመናችን ተቀበል በሚካኤል
ልመናችን ተቀበል በገብርኤል
ሚካኤል ከሰማያት እኸ
በልዕልና ወረደ በልዕልና
ፈጣሪያችን አማኑኤል እኸ
ልመናችን ተቀበል በሚካኤል
ልመናችን ተቀበል በገብርኤል
ልመናችን ተቀበል በዑራኤል
ልመናችን ተቀበል በሳቁኤል
ፈጣሪያችን አማኑኤል እኸ
ልመናችን ተቀበል በራጉኤል
ልመናችን ተቀበል በፋኑኤል
ልመናችን ተቀበል በሚካኤል
ልመናችን ተቀበል በገብርኤል
ገብርኤል ከሰማያት
በልእልና ወረደ በልእልና/2/
ምልጃውን ሰምተህ የራጉኤልን/2/
አድነን ጌታ ልጆችህ እንዳንባዝን/2/
ተስፋ ስናደርግ ምሕረትህን/2/
ስለ ወዳጅህ ሕዝብህን አድንልን
ስለ ወዳጅህ ኢትዮጵያን ጠብቅልን/2/

720.ጸሊ ኀበ አምላክ

ጸሊ ኀበ አምላክ ራጉኤል መልአክ /2/
ዓውደ ዓመት ከመ ይትባረክ /4/
**ትርጉም፡-** ዓውደ ዐመቱ ይባረክ ዘንድ ራጉኤል
መልአክ ወደ አምላክ ጸልየ /ለምን/

721.ንቁም በበህላዌነ

ንቁም በበህላዌነ /2/ እስከ ንረክቦ
ለአምላክነ /2/
ጌታችንን እስክናውቀው በልዕልና
ባለንበት እንጽና
ይህን ብለህ መላእክትን እንዳረጋጋህ
ቅዱስ ገብርኤል አጽናን በምልጃህ
አዝ . . .
አጠንክረን በሃይማኖት በምግባርም
ከክህደት ከጥርጥር አውጣን
አዝ . . .
ቅዱስ ገብርኤል አረጋጊ አጽናኝ መልአክ
መላእክትን በሰማያት እንጽና ያልክ
ከሃይማኖት ልንወጣ ስንባዝን
ና ና ባርከን ቅዱስ ገብርኤል ሆይ አጽናን
አዝ . . .

722..ናና ገብርኤል

ና ና ገብርኤል መልአከ ራማ
ዘውገ ማርያም አሐቲ ድንግል /2/
ዘዳግመ በሉ እሰይ ዘዳግመ ጽጌ ይበል
አምሳለ ኪያሁ ዘይመስል አልቦ ካህን ጥዑመ
ልሳን /2/
**ትርጉም :-**

723.ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ

ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ /2/ ልብሱ ዘመብረቅ
/2/
ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ የወርቅ ልምላሜ /2/
ና /3/ ስለምንህ ቆሜ
ገብርኤል ሊቀ መላእክት /2/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣ ከእሳት
በሠልስቱ ደቂቅ ናቡከደነጾር ተቆጣ
እሳቱ ነደደ ነበልባሉ ወጣ
ግን ኃያል ገብርኤል ሊያድናቸው መጣ
ገብርኤል ሊቀመላእክት /2/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣ ከእሳት
ሠለስቱ ደቂቅ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ብለው
ምስጋና አቀረቡ ከእሳቱ ላይ ሆነው
ገብርኤል ሊቀ መላእክት /2/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣ ከእሳት
ራጉኤል ሊቀ መላእክት /2/
እመ ኀበ ልዑል ወረደ /2/
መጋቤ ብርሃናት አንሶሳዊ ፋና
ራጉኤል ና /5/ አማላጅ ነህና
ራጉኤል ሊቀ መላእክት /2/
እመ ኀበ ላዕለ ወረደ /2/
ዑራኤል ሊቀ መላእክት /2/
ለዕዝራ ያጠጣህ ፅዋዐ ሕይወት
በዓለም ፈተና በስቃይ ኩነኔ
ስባዝን ስጨነቅ ስጠበብ ወይ እኔ
ዑራኤል የእኔ ኃይል ቁምልኝ ከጎኔ
ዑራኤል ሊቀ መላእክት /2/
ለዕዝራ ያጠጣህ ፅዋዐ ሕይወት

724.አዕርግ ጸሎተነ

አዕርግ ጸሎተነ ውስተ ኑኃ ሰማይ /2/
ከመ መዓዛ ፀሐይ /4/ ሊቀ መላእክት /2/
**ትርጉም :-**

725.መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ዑራኤል /2/
ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኒዓለም
**ትርጉም :-** የሰላም መልአክ ቅዱስ ዑራኤል ስለ እኛ
ለምንልን ጸሎታችንነም በመድኃኒዓለም ፊት አሳርግልን

24.ዑራኤል ወሩፋኤል

ዑራኤል ወሩፋኤል /4/

አስተምህሩ ለነ በሰያል ወበትሕትና ኀበ ውእቱ
ነበልባል/2/ እግዚአብሔር
**ትርጉም፡-** ዑራኤል ወሩፋኤል ሆይ በትሕትናና
በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ለምኑልን

**የቅዱሳን ጻድቃን መዝሙራት**

726.ሐዋርያው

ሐዋርያው መነኩሴ የመረጡት ሥላሴ/2/
ተክለሃይማኖት ሆኗል ጠበቃ ለነፍሴ /2/
አዝ----------------
ዳሞት ይናገረው ያንተን ሐዋርያነት
የወንጌል ገበሬ የጣዖታት ጠላት
ጸሎተኛው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ክንፍን የተሸለምክ እንደ ሰማይ መላእክት
/2/
አዝ ------------------
ብራናው ሲገለጽ ገድለ ተክለሃይናኖት
ከሰው ልጅ ልቡና ይወጣል አጋንንት
የቅዳሴው እጣን ሲወጣ ከዋሻው
ምድርን ይባርካል ጸሎቱ ምህላው/2/
አዝ --------------
ከሱራፌል ተርታ ቆመህ በማጠንህ
ሥሉስ ቅዱስ እያልህ ስታመሰግን
ጸሎት ትሩፋትህ ትኅትና ስግደትህ
ጾምህ ከፍ አድርጎ ሰማይ አደረሠህ/2/
አዝ -----------------
ዛፉ ሲመነገል አምላክ የተባለው
ሞቶሎሚ ሲያፍር ትልቅ ሰው ነኝ ያለው
የጻድቁ ጸሎት ብዙ ነው ምስጢሩ
ስድስት ክንፉ አወጣ ቢቆረጥ አንድ እግሩ
/2/
አዝ ---------
የኢትዮጵያን ምድር አረስከው በመስቀል
ጭንጫው ፈራረሰ ተዘራበት ወንጌል
ትናንት የዘራኸው ዛሬም ለእኛ ሆንዋል
አምላክ ተክለ አብ ብለን ተምረናል

727.ገድሉ ተአምራቱ

ገድሉ ተአምራቱ እጅግ ብዙ ነው
ጣዖትን አዋርዶ የተሸለመው
የተዋሕዶ ኮከብ ተክለሐዋርያ
አባ ተክለ ሃይማኖት ዘኢትዮጵያ
አዝ ------------------
ዳግማዊ ዮሐንስ ጠፈር የታጠቀ
ንጹሕ ባህታዊ ጠላት ያስጨነቀ
የጸጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ
በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስከተለ
አዝ ---------------------
ደካማ መስሏቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት
ባላስድስት ክንፉ ጻድቁ የእኔ አባት
እርሱስ አንበሳ ነው ትናገር ደብረ አስቦ
ሌጌዎን ሲዋረድ እፍረት ተከናንቦ
አዝ -----------
ከካህናት መካከል ኅሩይ ነው አቡዬ
መጣው ከገዳምህ ልሳለለምህ ብዬ
ኢትዮጵያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ወልድ ዋሕድ ብለህ ምድሪቱን ቀደስካት
አዝ -----------------
የባረከው ውኃ የረገጥከው መሬት
ጥላህ ያረፈበት ሆንዋል ጸበል እምነት
ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ
ይሰብካል ተክለአብ ዛሬም እንደጥንቱ
አዝ ------------------

728.ንዌጥን ዜማሁ

ንዌጥን ዜማ /2/
ሊያሬድ ጥዑመ ልሳን /4/
እንጀምር ዜማውን/4/
የያሬድን /2/ ጥዑመ ልሳን/4/

729.ተነግሮ የሚያልቅ

ተነግሮ የማያልቅ ነው ጸጋህ /2/
በጸሎት የተጋህ የሃይማኖት ፍሬ
ተክለ ሃይማኖት የወንጌል ገበሬ
አዝ -----------------------
በወንጌል ብርሃን ሕዝቡን የመራኸው
የኃጢአቱን ባሕር ከፍለህ ያሻገርከው
ኢትዮጲያዊው ሙሴ በመስቀልህ ባርከን
ፍሬ እንድናፈራ ንጹሕ አድርገን/2/
አዝ --------------------
ሐዲስ ሐዋርያ አባ ተክለሃይማኖት
ወንጌል ያስተማርከው ለክርስቶስ መንግሥት
ጠበልህ እንድምረን ውረድ አባታችን
በእጣንህ መኣዛ ይፈወስ ደዌአችን /2/
አዝ --------------
ለማጠን የበቃህ የሥላሴን መንበር
ሰይጣን ከቶም አይደርስ በሄድክበት ሀገር
ለህሙማን ሁሉ የሆነካቸው ፈውስ
ጠብቀን አቡዬ በሥጋም በነፍስ
አዝ---------------
በጣሙን የበዛ ትሩፋት ምግባርህ
ጸሎትህን ያልተውክ ቢቆረጥ አንድ እግርህ
ምዕራፈ ቅዱሳን የወንጌል ገበሬ
እኛንም አድነን ከዘህ ኣለም አውሬ
አዝ ---------------------

730.አባ አቡነ

አባ አቡነ/2/ መምህርነ አባ ተክለሃይማኖት/2/
እምአእላፍ ኅሩይ/2/ አባ /6/
አቡነ ተክለሃይማኖት /2/

731.ለሳዉል ወኬፋ

ለሳዉል ወኬፋ/2/
አክሊሎሙ ትኩነነ ተስፋ/4/

732.የአምላክን በረከት

የአምላክን በረከት ጸጋውንም ሽተው
በመከራ ጸኑ ከዲያብሎስ ታግለው
በእምነታቸው ጽናት በእግዚአብሔር ጸጋ
ቅዱሳን አባቶች አግኝታዋል ዋጋ
የእምነቱ ገበሬ ተክለሃይማኖት
በአምላክህ ታምነህ ድል አደረግኽ ጠላትን
ፈጣሪ የሰጠኽን ረድኤት በረከት
ለእኛም እንዲሠጠን ለምንልን ከአምላክ
የአምላክ ባለሟል ገብረመንፈስቅዱስ
ኢትዮጵያን አስማርካት በጾምና ጸሎት
ታማኝ አገልጋይ ነህ ለኀብረተሰብህ
ልጆችህን አስተምረን እንንዝ በአንተ እግር
ጻድቁ አባታችን ታማኝ አገልጋይ
አቡነ አረገዊ ደስ ያሰኛል ሥራህ
እንደ አምላክህ ፈቃድ በሕጉ ተመርተህ
በዘንዶ ጀርባ ላይ ደብረ ዳሞ አየንህ
ቅዱስ የሦስት ዓመት ሕፃኑ ቂርቆስ
ገድልህ አስደናቂ የህሙማን ፈውስ
እናትህ ኢየሉጣን በርቺ አይዞሽ እንዳልክ
ልጆችህን ጠብቀን ከዲያብሎስ ተውሣክ
አዝ -----------------

733.የጸጋ ምስጋና

የጸጋ ምስጋና ለሰው አለውና
ለገብረሕይወትም ይገባል ምስጋና
ገብረመንፈስቅዱስ የኣለም ብርሃን/2/
እኛንም አንደአንተ አምላክ ይባርከን/2/
ጊዜአችን እንደሳር መሆኑን አንርሳ/2/
እንደ ገብረሕይወት ለጽድቅ እንነሣ /2/
ማግኘት ከፈለግን የዘለዓለም ሕይወት
ለጽድቅ እንነሣ እንደ ገብረሕይወት

734.ማርቆስ ዘአንበሳ

ማርቆስ ዘአንበሳ የወንጌል ገበሬ

በዓለም ላይ ዞረህ የዘራኸው ፍሬ
መጽደቁን ስላየ ጠላት ገብቷልና /2/
ፍሬ እንደያፈራ መስቀሉን ይዘህና/2/
ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኖኅ
ሰማይ/2/
ማርቆስ /2/ ሰባኬ ወንጌል
የምታመልኩትን ኑ ዛሬ ምረጡ
የምስጋናን መሥዋዕት ወደ ኢያሱ አምጡ
የቀለጠውን ወርቅ ጥጃውን ትታችሁ/2/
እግዚአብሔርን ያዙ ይሁን አምላካችሁ/2/

<u>735.ተክለሃይማኖት</u>

ተክለሃይማኖት ተክለ አብ ተክለ ወልድ
ተክለ መንፈስቅዱስ
አባታችን አማልደን አስታርቀን
ከፈጣሪ ጋር ከአምላካችን/2/
በሦስት ቀን ሥላሴን ያመስገንህ
ከጭንጫ ድንጋይ ውኃ ያፈለቅህ
አባታችን ተክለሃይማኖት
አማልደን በኃጢአት
እንዳንሞት/2/
እንደ መላእከት ክንፍ የተሠጠህ
ሰማዕት ነቢይ አንድም ካህን ነህ
መምህራችን ሐዲስ ሐዋርያ /2/
አስተምረን የጽድቅ ባለሞያ/2/
አዝ---------------
እንደ ሱራፌል በሰማይ ሲያጥን
በምድር ላይ ረድእ ሆኖ ማገልገሉን
በተሠጠው ጸጋ ሲያስነሣ ሙታን
ክህነቱ ከአንተ ዘንድ ናት
አባታችን ፍታን ከኃጢአት /2/
አዝ ------------------

**736.ዘከመ ጸለየ**

ዘከመ ጸለየ አቡነ ተክለሃይማኖት /2/
በደብር/3/ ሊባኖስ ገዳም
ዘከመ ጸለየ አቡነ ገብረመንፈስቅዱስ/2/
በደብር/3/ ዝቋላ ገዳም/2/

**737.ማርቆስ ሐዋርያ**

ማርቆስ ሐዋርያ ወንጌላዊ ሰማእት/2/
ሰበከ በግብፅ በመላው ዓለም
ሰበከ በእስክንደርያ በመላው ግብፅ /2/

**738.ባርከን አባታችን**

ባርከን አባታችን ጻድቅ መነኩሴ
/2/ተክለሃያማኖት
ባርከን አባታችን ጻድቁ መነኩሴ ገብረመንፈስ
ቅዱስ
ባርከን አባታችን ጻድቁ መነኩሴ አቡነ አረጋዊ
ተወከፍ/3/ ስምዐነ ጸሎታችንን /2/

<u>739.ታማልደናለች</u>

ታማልደናለች /2/
ማርያም/2/ ቤዛዊት ዓለም/4/
ሚካኤል መልአክ ሊቀመላእክት/2
ዘአወረድከ/2/ መና ከደመና/4/
ገብርኤል መልአክ አብሣሬ ትስብእት /2/
ዘአብሠራ/2/ ለማርያም ንጽሕት/4/
ሩፋኤል መልአክ ሊቀመላእክት/2/
ዘአብርሃ/2/ አይኑ ለጦቢት/4/
ዑራኤል መልአክ ለእዝራ ነቢይ /2/
ዘአስተዮ/2/ ጽዋዓ ልቡና/4/
ሰሎሞን ይቤላ/4/
ርግብየ ሠናይትየ ሰሎሞን ይቤላ/4/
ገብረመንፈስቅዱስ /4/
ሐዋርያ /2/ ዘእስክንድርያ/4/
ተክለሃይማኖት /4/
ሐዋርያ/2/ ዘኢትዮጵያ /4/
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ/2/
አእማደ /2/ ቤተክርስቲያን

## 740.ፊልጶስ

ፊልጶስ አባታችን ፊልጶስ መምህራችን
የተባረከ ነው ስምህ/2/
እኛ ልጆችህ/2/ ጠብቀን በጸሎትህ/2/
የኢትዮጵያ ባለውለታዋ
ቅዱስ ፊልጶስ ነህ አድማቂዋ
አዝ --------
ከእግዚአብሔር ተልከህ
ወደ ጋዛ ምድረ በዳ ወረድህ
ትንቢተ ወንጌልን የሠጠህ አንተ ነህ
አዝ-------------
ቤተክርስቲያን ሠርታ በስምህ አንጻ
ስለ መታሠቢያህ ፅላት አስቀርጻ
እንድትጠብቃት ከሰይጣን ፍላጻ
አዝ ----------------
በስምያን ጥንቆላ ሕዝብ ያምን ነበር
በወንጌል ስብከትህ
ሕዝብ ወደ አምላክህ ዞረ
አዝ ------
በከተማ ሁሉ ዞረህ ያስተማርክ
ስለ አዳኝ ጌታ ብለህ የሠበክ
ድውያንን ፈወስህ ጸጋ ተሠጥቶህ
አዝ -----------------

## 741.አምላክ ባከብራት

አምላክ በከበራት በተክለሃይማኖት ደጅ/2/
በረከት ይገኛል ከጻድቁ እጅ/2/
በመከራ ጊዜ ተክለ ሃይማኖት
በችግሯ ቀን ተክለ ሃይማኖት
እንደ ደረስክላት ተክለ ሃይማኖት
እግዚእ ኀረያንን ተክለ
ሃይማኖት
እኛን ታድነን ዘንድ ተክለ ሃይማኖት
አንተ ደግ አባት ተክለ ሃይማኖት
መጥተናል ከቤትህ ተክለ ሃይማኖት
ከያለንበት ተክለ ሃይማኖት
አዝ------------
ከአምላክ በተሠጠህ ተክለሃይማኖት
በቃል ኪዳንህ ተክለ ሃይማኖት
ህሙማን የሚያድን ተክለ ሃይማኖት
የንፈሮ ውኃህ ተክለ ሃይማኖት
ድውይ የሚፈውስ ተክለ ሃይማኖት
ግሩም ጸበልህ ተክለ ሃይማኖት
ዘለዓለም ይኖራል ተክለ ሃይማኖት
በዓለም ሲያስጠራህ ተክለ ሃይማኖት
አዝ ----------
ለ29 አመት ተክለ ሃይማኖት
ተክሎ ጦሮችን ተክለ ሃይማኖት
ለእኛ ለልጆቹ ተክለ ሃይማኖት
ተስፋ ለቆረጥን ተክለ ሃይማኖት
ደከመኝ አላለም ተክለ ሃይማኖት
ቆሞ ሲጸልይ ተክለ ሃይማኖት
አዝ ---------
የቅዱሳን ሀገር ደብረ ሊባኖስ
ደብረ ሊባኖስ ደብረ ሊባኖስ
ታጥራ ትኖራለች ደብረ ሊባኖስ
በመንፈስቅዱስ ደብረ ሊባኖስ
በቅዱሳን ጸሎት ደብረ ሊባኖስ
ስለተቀደሠች ደብረ ሊባኖስ
ለአድባራት ሁሉ ደብረ ሊባኖስ
በክብር ትበልጣለች ደብረ ሊባኖስ
አዝ -------------

## 742.እቀቡኒ

እቀቡኒ አበዊየ እምአፈ አንበሳ ወተኩላ/2/
ነአኩቶ ለአብ ይምርሃነ ገብረ ማርያም/2/
ወላሊበላ/2/

ትርጉም፡- አባቶቼ ነአኩቶ ለአብ
ይምርሃነ ክርስቶስ
ቅዱስ ላሊበላ ከነጣቂ አንበሳና ተኩላ
ጠብቁኝ

743. **የቅዱሳን በዓት**

ልቡና የሚመስጥ መዓዛ እጣኗ
ኅሊናን ይገዛል ዝማሬ ድንዋ

የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው
ቤ/ክ ናት አምባ መጠጊያቸው

የመላእከት ዜማ የአእዋፍ ዝማሬ
የሚለቀምባት የትሩፋት ፍሬ
አዝ -------------
ይዘምሩበታል በአንድነት ተባብረው
የሌዋዊው በትር ጸናጽል ከበሮው
አዝ -------------
ወራዳዋን ዓለም የናቋት በቅድሚያ
የእምነት አርበኞች ያገኟዋት በፍልሚያ
አዝ -----------------
መውደቂያዬ ይሁን ከመቃብራቸው
ይፈውሳልና ተረፈ አጽማቸው
አዝ ----------------------
ከኃጥአን ድንኳን መውጣቴ ነው ዛሬ
የቅዱሳን በዓት ልትሆነኝ ሀገሬ

744. **በድፍረትና**

በድፋረትና በትዕቢትም በመናቅም/2/
በጻድቃን ላይ የሚናገሩ /2/ ክንፈሮች ዲዳ
ይሁኑ /2/

745. **ይትፌስሁ**

ይትፌሥሑ ጻድቃን የዋሃን ውሉደ
ብርሃን/2/
በትፍስዶት የሀሎ ውስተ አድባር

ትርጉም፡- በምድር የዋሃን የሆኑ የብርሃን
ልጆች

746. **ተክለሃይማኖት**

ተክለሃይማኖት ፀሐይ የኢትዮጵያ ሲሣይ
ምዕራፈ ቅዱሳን /2/ በነፍስም በስጋ አትለየኝ
የቅዱሳን አርእስት የዋሻው ብርሃን
የጸሎት ባለቤት የነዳያን መድኅን
ገና ስትወለድ አምላክ የመረጠህ
የድውያን እምነት ፈዋሹ አንተነህ/2/
አዝ ------------------
ገና በሦስት ቀን በሕፃንነትህ
ጌታን አወደሰው ቅዱስ አንደበትህ
ደግሞም እግዚአብሔር አስቦሃልና
በወጣትነትህ ወጣህ ለምነና/2/
አዝ------------
ሌትና ቀን ሳትመርጥ ክረምትና በጋ
ስትጸልይ ውለህ ስትጸልይ ነጋ
በመቆምህ ብዛት አንድ እግርህ ሲነሣ
ጸሎትህን ፈጸምክ ለሥጋ ሳትሣሣ/2/
አዝ----------
ምንኛ ድንቅ ነው ቅዱስ የአንተ ብርታት
7 ዓመት ሙሉ በአንድ እግርህ ጸሎት
የዓለም ግሣንግሷ ሀብቷ ሣይስብህ
ለኢትዮጵያ ጸለይክ ቆመህ በአንድ እግርህ/2/ ›
አዝ ---------
የሃይማኖት ተክል የኢትዮጵያ አባት
ምሕረት ከአምላክ ለሀገርህ አሠጣት
እኛንም አግዘን ጽድቅን እንድንሠራ
በተሠጠህ ሥልጣን ጠብቀን አደራ/2/
አዝ --------------

747. **ተክለአብ**

ተክለአብ ሐዲስ ሐዋርያ /4/
ሐዲስ ሐዋርያ /2/ ዘኢትዮጵያ /2/

748.ዜና ወዳሴከ

ዜና ውዳሴከ ፈጸምኩ/2/ ተክለሃይማኖት /2/

በሊኒ አባ ወልድየ በለኒ አባ /2/

ወልድየ ተክለሃይማኖት/2/

749.ቅዱሳን አባቶች

ቅዱሳን አባቶች በገዳም ያላችሁ

ሰላምን አሠጡኝ ከፈጣሪ አስታርቃችሁ

በሀገራችን ላይ ይደር በረከት ጸጋችሁ

አምላክ በበደላችን በእኛ እዳይከፋ

ምልጃችሁ አይለየን በኃጢአት እንዳንጠፋ

ሰላም ለእናንተ ይሁን ቅዱሳን አባቶች

ከዓለም ርቃችሁ በጾም ጸሎት የጸናችሁ

በገድል በትሩፋት ዲያብሎስን የረታችሁ

ቅዱሳን አባቶች በእኛ ላይ ይደር ጸጋችሁ

ውርጭ ሀሩሩን ሣትሰለቹ በጸሎት የጸናችሁ

በረከታችሁ በእኛም ይደር በልጆቻችሁ

ጸጋችሁ ብዙ ነው ጸሎታችሁ ኃይል ያደርጋል

ከጥፋት ጠብቆ አጋንንትንም ይዋጋል

የእናንተን ጽናት አይቶ እኛንም ታግሶናል

በኃጢአት ስንረታ በምሕረት ጎብኝቶናል

750.ትዌድሶ

ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ መጠነ ብዝኃ ህማሙ/2/

ትዌድሶ ደብረ ሊባኖሰ ገዳሙ /4/

እስመ በውስቴታ ተገብረ ፍልሠተ ሥጋሁ ወአጽሙ

ትዌድሶ----------

እምነ አድባራት ኩሎን ዘተለአለት በስሙ ትዌድሶ

ኢየሱስ ክርስቶሰ እንተ ቀደሰ በደሙ

ትዌድሶ---------

ትርጉም፡ ጻድቁ ተክለሃይማኖት ብዙ ህማም የተቀበለባት ቅዱስ አጽሙ ያረፈባት በስሙ ከታነጹት አድባራት ሁሉ ከፍያለች ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የቀደሳት ደብረ ሊባኖስ ታመስግነዋለች

751.ጼና አልባሲሁ

ጼና አልባሲሁ /2/

ለገብረመንፈስቅዱስ ከመጼና ስሂን /2/

አልባሲሁ ዘሜላት /2/

ዘወረደ  ውስተ ገነት /2/

ትርጉም፡- የገብረ መንፈስ ቅዱስ ልብሳቸው እንደ ሽቱ ያማረ ነው ደግሞም ልብሳቸው እንደነጭ ሐር ነው እርሱም ወደ ገነት የወረደ ነው

752. ያሬድ ማኅሌታይ

ያሬድ ማኅሌታይ ለእግዚአብሔር ካህኑ ስብሐተ ትንሣኤ ዘይእዜኑ  ኦሪት ቶታህኑ ወወንጌል አሳዕኑ (2)

ትርድአነ ነአ በህየ መካኑ ከመ ፀበል ግዑዛነ ፀርነ ይኩኑ (2)

ትርጉም፡- የጫማህ ማዘቢያ /ማሰሪያ /ኦሪት የእግርህ መጫሚያ ወንጌል የሆነና የትንሣኤን ክብር የምታስተምር የእግዚአብሔር አገልጋይ ማኅሌታዊ ያሬድ በዚህ ቦታ ትረዳን ዘንድ ና

753.ሰማየ በአብ

ሰማየ በአብ ወበወልድ አርያመ ወበመንፈስ ቅዱስ ኀበ ዓረጉ አነ (2)

ሰማዕኩ እመላእክት ዝማሬ በአድንኖ ወበአትሕቶ ቦ ዘያጽሕሱ ወቦ ዘይዜምሩ (2)

ትርጉም :- በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ቸርነት ሰማይ ወጥቼ ጽርሐ አርያም ደርሼ ከመላእክት ዝማሬ  (ምስጋና) ሰማሁ ከእነርሱም በዝቅታና በትኅትና የሚያሸበሽቡ አሉ ዙሪያውንም ቆመው የሚዘምሩ አሉ

754.በኢትዮጵያ ምድር

በኢትዮጵያ ምድር የዞርክ የዜማን ትምህርት

ያስተማርክ (2)

የክህነትን ሥራ በክብር የፈጸምክ ብጹዕ ነህ /2/

ቅዱስ ያሬድ ብጹዕ ነህ (2)

**755 የጻድቃን ከተማ**

የጻድቃን ከተማ ሆነች መንግሥትህ

አምላክ የፈጠርካት ለወገኖችህ /2/

የአራዊት ድምጽ የሌሊቱ ግርማ

በትዕግሥት አለፈ ያን ሁሉ ጨለማ /2/

ሀብት ንብረትን ተድላን ሁሉ ናቁ

መንግሥትን ብቻ ለማየት ናፈቁ /2/

ቅዱሳን እጆችህ ሰውን የፈጠሩ

ለሰው ልጆች ሲሉ በሐብል ታሠሩ /2/

ይህንን ሁሉ ነፍስ ቅዱሳንም አይተው

በኀዘን አለፈ መላ ሕይወታቸው /2/

ምሕረትህ የበዛ ቸሩ አምላካችን

በምህረትህ ጎብኛት ኢትዮጵያን /2/

**756.ጻድቃንስ ኢሞቱ**

**757.ቅዱሳን በሙሉ**

ቅዱሳን በሙሉ ከአምላክ አማልዱን /2/

ልንጠፋ ነውና በዝቶ በደላችን /4/

ድድቃን ሰማዕታት ንጹሐን ሁላችሁ /2/

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዓለምን ንቃችሁ /2/

ለሰማያዊው ክብር ለአክሊል የበቃችሁ /2/

ወደ አምላክ አቅርቡም በጽኑ ምልጃችሁ /4/

ድንግል እናታችን ከዳነ ምሕረት /2/

ቅድስተ ቅዱሳን የጻድቃን እናት /4/

ርኅርኅተ ኅሊና አሳስቢ ከልጅሽ /2/

ይቅርታ እንድናገኝ በፍጹም ልመናሽ /4/

**758.ቅዱሣን መስክሩ**

ታምሩን ያያችሁ ቅዱሳን መስክሩ

ፍቅሩን ቸርነቱን ለዓለም ንገሩ /2/

በየዋህ ልቡና ንጹሕ መሥዋዕት

አቤል ግለጽልን ለጽድቅ መሞትን

ኖኅም ተናገረው ለአንተ የታየህን

ዛሬን ብቻ ትተህ ነገን ማሰብህን

አዝ . . .

ተናገር አብርሐም የአምላክን ሥራ

እንዴት እንደነበር ያኔ ስጥጠራ

ልጅህን ያሰጠህ ፍቅሩን ግለጽልን

በእምነት መታዘዝን ለእኛም አስተምረን

አዝ . . .

ግለጽልን ዮሴፍ እንዴት እንደነበር

ፍትወትን ድል ነስቶ ለሃይማኖት ማደር

ከራስ ደስታ ይልቅ ለወገን መሞትን

አስተምረን ሙሴ ፍቅርና ጽናትን

አዝ . . .

**759.ምስጋና ጀመረ**

ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ

ማኅሌታይ ያሬድ ዘኢትዮጵያ

ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ

ይበል /3/ ሃሌ ሉያ

ጥዑመ ልሳን ያሬድ /3/ ዘኢትዮጵያ

ብሉይን ከሐዲስ ሐዲስን ከብሉይ

አስተባብሮ ይዞ ያሬድ ማኅሌታይ

ምሥጢር ተገልጦለት ከምድር እስከ ሰማይ

አዝ . . .

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሥጢር እያስማማ

ምስጋና ጀመረ በእነዚህ ከተማ

ለቅድስት ሥላሴ በሦስት ዓይነት ዜማ

አዝ . . .

በገና ጸናጽል ሲመታ ከበሮ

ዜማው ሲንቆሮቆር በሰው ልጆች ጆሮ

የያሬድ ዝማሬ ያድሳል አዕምሮ

አዝ . . .

ምእመናን እናቅርብ ለአምላክ ምስጋና

በእዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና

ዜማውን ከያሬድ ተምረናልና

**760.መዓርዒረ ቃል**

ኦ መዓርዒረ ቃል /2/

አበ ኢትዮጵያ ዘውገ ሱራፌል

የይስሐቅ አበባ መዓርዒረ ቃል የታውክልያ ፍሬ

መዓርዒረ ቃል

በኢትዮጵያ ፈካ ደምቆ ሲታይ ዛሬ

ከካህናተ ሰማይ መዓርዒረ ቃል ከሱራፌል ጋራ

መዓርዒረ ቃል

ስውር ምሥጢር አየህ በምድር ልታፈራ /2/

አዝ . . .

የሰላም መምህር መዓርዒረ ቃል የቅኔ ባለቤት

መዓርዒረ ቃል

ከሰማይ ገባህ በትዕግስትህ ብዛት

ሱራፌል ኪሩቤል መዓርዒረ ቃል የሰማይ

መላእክት መዓርዒረ ቃል

በአንተ ተደነቁ ቢያዩህ በሰማያት/2/

አዝ . . .

የብርሃን ፀዳል መዓርዒረ ቃል የዓለም ሽልማት

መዓርዒረ ቃል

ለምድር ሰገነት ነህ ለኢትዮጵያም አባት

የመላእክት አምሳል መዓርዒረ ቃል የዓለም

ማኅቶት መዓርዒረ ቃል

ልዩ ነህ ቅዱስ ነህ ያሬድ የእኛ አባት /2/

አዝ . . .

ባሕር ምስጋናህ መዓርዒረ ቃል ምሥጢር

ማዕበል መዓርዒረ ቃል

እንደ ግዮን ሞልቶ ሁሌ ይታያል

እንዴትስ ይደንቃል መዓርዒረ ቃል የአንተ

ስጦታህ መዓርዒረ ቃል

ዕጹብ ነው ! ድንቅ ነው ! ምስጋና ይድረስህ /2/

አዝ . . .

መዓዛ ቅዱሳን መዓርዒረ ቃል ሞገሰ ምዕመናን

መዓርዒረ ቃል

በኢትዮጵያ አበራ የዜማህ ወጋገን

የሕያዋን ሕያው መዓርዒረ ቃል የቅዱሳን

መኩሪያ መዓርዒረ ቃል

ትኮራብሀለች እናት ኢትዮጵያ /2/

**761.ጻድቅ ተክለ አልፋ**

ጻድቅ ተክለ አልፋ

ጻድቅ ወከመ ወናህ ሴሊተ

ሽሽ ይበል ሽሽ/2/

ወገድሉ ጸዳል እንደ ኮከብ እንደጨረቃ/2/

እንደ ቀን ፀሐይ ተክለ አልፋ እንቁባሕርይ

ሽሽ ይበል ሽሽ/2/

ጻድቅ ተ/ሃይማኖት ዘደብሩ ሲና

ወኢቲሣ ግሩም መዋኢ አንበሳ

ሽሽ ይበል ሽሽ /2/

ጻድቅ ገብረመንፈስቅዱስ በምድረ ዝቋላ

ወዘምድረ ከብድ መለኮት መንፈሣዊ/2/

ነበልባላዊ ባሕረ ገዳማዊ

**762.ግሩማን መላዕክት**

ግሩማን መላእክት /2/ ሱራፊል ወኪሩቤል/2/

ወረዱ ዮም ይትቀበሉከ በብሔር አማን/2/

ገብረመንፈስቅዱስ ገባሬ ኃይል /2/

ትርጉም፡- ኃይልን ተአምርን የምታደርግ ገብረ

መንፈስቅዱስ

ቅዱስ ሆይ ክንፋቸው በነበልባል የሆነ

የሚያስፈሩ

መላእክት ሱራፌልና ኪሩቤል እውነት በማለት

ይቀበለህ ዘንድ ዛሬ ወረዱ

**የሰማዕታት መዝሙር**

**763.አማን በአማን**

አማን በአማን/4/

መርቆሬዎስ ትሩፈ ገድል

**764. ሰማዕታት የዚህችን**

ሰማዕታት የዚህችን ዓለም ጣዕም በእውነት

ናቁ/2/

ደማቸውን ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ/2/

ስለ መንግሥተ ሰማያት መራራ ሞትን

ታገሱ/4/

**765.ዮሐንስ**

ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት/2/

በረከትህ ይደር በኛ ሕይወት/4/

766.ቅዱስ ጊዮርጊስ/1/

ቅዱስ ጊዮርጊስ አማለደን/2/

ከመድኃኔዓለም አስታረቀን/2/

ፈጣሪ አምላካችን ማረን /4/

በእውነት ይቅር አለን /4/

767.ሕፃን መእሙ

ሕፃን ወእሙ /4/

ክልዔሆሙ ፈጸሙ ገድሎሙ/4/›

768.በእምነታቸው

በእምነታቸው ዳኑ ከዚያ ነበልባል/2/

አናንያ አዛርያ ሚሳኤል/2/

ናቡከደነፆር ጨካኙ ንጉሥ

በባቢሎን ሀገር ጣዖት የሚነግሥ

እያለ ስገዱ አማኙን ሲያምጽ

ወጣቶች ተነሡ በቅናት መንፈስ

አናንያ አዛርያ ሚሳኤል/2/

አዝ --------

ለሠራኸው ጣዖት አንሰግድም እያሉ

በመንፍስ ቅዱስ ኃይል ልባቸው ሞሉ

የፈጠረን አምላክ ያድናል ሲሉ

ዘናንያን አዛርያ ሚሳኤል /2/

አዘ ------------

ነበልባል ነዲዱ እያቃጠላቸው

በጭካኔ መንፈስ አስወረወራቸው

ገብተው ሲፀልዩ ፍህሙ ሳይነካቸው

መልአኩን ልኮ አበረደላቸው

ገብርኤል /2/ በመስቀል /2/

አዝ -----------

እንደ ሶስቱ ሕፃናት በእምነት ለሚቆም

መልአኩን ይልካል እገዚአብሔር ሊረዳው

እሣቱም ይበርዳል መልዐኩን ሲልከው

ገብርኤል 12 በመሰቀል

አዝ -----------

769.ጊዮርጊስ ብርሃኑን

ጊዮርጊስ ብርሃኑን አበራ/2/

ዱድያኖስ አፈረ ከጣዖቱ ጋራ

ጊዮርጊስ ብርሃኑን አበራ /2/

ለዲያብሎስ ያልሠገደ ጀግናው ጊዮርጊስ

ደግሞ በዓይን ታየ ክብሩ ሲወደስ

ከሞት አፍ ያወጣት ቤሩታይትን

በሰማእቱ ገድል ድል ሆነ ሠይጣን

ቅዱሱ ሰማዕት ጊዮርጊስ አባታችን

አሳየ ሥልጣኑን ከሞት እንደሚያድን

መድኃኒት ክርስቶስ የገለጠው ብርሃን

እኛም እንድንድን ከዘመኑ አውሬ

እስቲ እንግለጽለት ክብሩን በዝማሬ

ተዋሕዶ አበራ ደግሞ እንደገና

ደራጎን ድል ሆኖ ሞቶ ቀርቷልና

ለአሸናፊ ጌታ ለእግዚአብሔር ልዑል

ምስጋና እናቅርብ እንበል እልል

ጊዮርጊስ አበራ ብርሃን/2/

ሰው በላውም አውሬ ሞተ ደራጎን/2/

ጊዮርጊስ አበራ ብርሃን

770.ምስክረነቱን ገለፀ

ምስክርነቱን ገለጸ ቂርቆስ ሕፃን/2/

በእሳት ተፈተኖ አለፈኸኸ ፈተና ደስ ይበለን/2/

ቂርቆስ ኢየሉጣን ሁለቱም በአንድ ልብ ምን ጨከኑ/2/

ተቃቅፈው ሲገቡ ወደ እሳት ጋኑ/2/

ሕፃኑ እና እናቱ በእሳት ውስጥ ሲወኙ

ያለ ምንም ፍርሀት/2/

ገብርኤል ተላከ እነርሱን ለማውጣት /2/

በርዶና ቀዝቅዞ የእሳቱ ነበልባል

በጌታችን መስቀል /2/

ሁለቱም ሰማዕታት ተጎናጸፉ ድል/2/

አዝ --------

771. **መጥመቀ መለኮት**

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ /2/

መንገድ ጠረገ ለኢየሱስ መምጫው

ሊደርስ

ተክለሃይማኖት በጸሎት/2/

ተክለሃይማኖት በጸሎት የእኛ አባት

ገብረመንፈስቅዱስ ሐዋርያ /2/

ከንሒሳ መጥተው ጸለዩላት ለኢትዮጵያ

ዜና ማርቆስ በጽኑ እምነት/2/

ፀሐይ አቆሙ እንደ ኢያሱ በደብረ

ብስራት/2/

እመቤታችን ድንግል ማርያም /2/

ምሕረት አሰጭን ከመለኮት

ከመድኃኔዓለም

መሰቀሉን ይዞ በፈረስ/2/

ከዘንዶ አስጣላት ቤሩታዊትን ቅዱስ

ጊዮርጊስ

772.**አርሴማ**

አርሴማ አርሴማ ቅድስት ሰማዕት /2/

ምሕረት ለምኝልኝ ከዓለም መድኃኒት

የዓለም አሸንክታብ ሳይስብሽ ጽድቅን

የመረጥሽ  የጌታ አገልጋይ አርሴማ

ቅድስት አንቺ ነሽ

መስቀል ተመርኩዘሽ በዓላማሽ የጸናሽ

አርሴማ ቅድስት

ተቀዳጅተሽ አክሊል ሙሽራ ሆነሽ ሰማዕት

የዚህ ዓለም ደስታ ርስት ጉልት ንብረት

ሣይሰብሽ

ዘላለማዊ ሕይወት ክብር ጸጋ ስለመረጥሽ

የዓለም መድኅን አማኑኤል በእውነት አከበረሽ

በእግዚአብሔር ዘንድ በፍቅር/2/ አድገሽ

የሰማእታት አክሊል በረከት ሆነሽ ተሸላሚ

አዝ --------------

773.**መጽሐፈ ዜናሁ ለቂርቆስ**

መጽሐፈ ዜናሁ ለቂርቆስ መንፈሳዊ ወዘመንክሮ

ሰላም/2/

ጸሐፍ ውስተ ልብየ/2/ እንዘ ትገብር ከለመ

ደመከ አምላካዊ በመስቀል ዘዘነበ/2/

አንተ ቅዱስ ቂርቆስ ሕፃን ለአምላክ ሆንክ

ምስክር/2/

በእኛም ልብ ጻፍልን /2/ የአምላክን ፍቅር/2/

በእስክንድሮስ ዘመን ነበርክ ታላቅ

አስተዋይ ሕፃን

አምላክህም ሰጠህ /2/ የክብር አክሊልን/2/

ያ ሁሉ መሣሪያ ሣይስፈራህ የመሠከርክ

የአምላክን ክብር

ድንቅ ነው የአምላክ ሥራ/2/ ለዚህ ሕፃን

ሰጠው እንዲኖር ሣይፈራ/2/

አትፍሪ እዳልካት እናትህን እኛንም አድነን

ከመከራ/2/

እንድንድን ርዳን ከዲያብሎስ ጭፍራ

በጽድቅህ አድለን እንኑር በሥራ/2/

**774.ፀሐይ ዘልዳ**

ፀሐይ ዘልዳ ኮከብ ዘልዳ/2/

አድነኒ /2/ ጊዮርጊስ እሞተ እዳ/2/

ከሰው ወገን ያለ አድነኒ

ልክ እንደአንተ ያለ ››

ሰባት ዓመት ሙሉ ››

መከራን የቻለ አድነኒ/2/ ጊዮርጊስ እሞተ

እዳ

አዝ ------------

በምግባር በሃይማኖት አድነኒ

በማገበ ተጋድለህ ››

ሰባት አክሊላትን ››
ጌታ የሸለመህ አድነኒ /2/ ጊዮርጊስ እሞተ
እዳ
አዝ --------
ሲበሉ ሲጠጡ አድነኒ
ነገሥታት ከበው ››
በጸሎትህ ጠፋ ››
ወርዶ እሳት በላቸው አድነኒ/2/
ጊዮርጊስ እሞተ እዳ
አዝ -----
ፍጡነ ረድኤት አድነኒ
ጊዮርጊስ ፈጣኑ ››
እኛንም አድነን ››
ከክፉ ሰይጣን አድነኒ/2/
ጊዮርጊስ እሞተ እዳ
አዝ----
በሞተር ቢፈጩህ አድነኒ
ዱድያኖስ ተስፋቶ ››
አሳፈረው እርሱ ››
ከሞት አስነሥቶ አድነኒ/2/
ጊዮርጊስ እሞተእዳ
አዝ -----------------

**775.ስብሐት አብ ወወልድ**

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ/2/
ዘአንበሩ ብየ አክሊለ ሞገሰ/2/
መዘምረ እኩን ለጊዮርጊስ /6/

**776.ከመ ፀብል**

ከመ ፀበል ዘነፋስ ዘራውሂ ደብረ
ይድረስ/2/
አማን በአማን ቅዱስ ጊዮርጊስ /4/
ትርጉም፡- እውነት በእውነት ጊዮርጊስ
ቅዱስ ነው እንደ ነፋስ ትቢያ በይድረስ
ተራራ በተኑት

**777.መክብበ**

መክብብ ሰማዕት አለቃ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው
ከመካከላችን አባርልኝ አርቅልን አስወግድልን

**778.ቅዱስ ጊዮርጊስ**

ቅዱስ ጊዮርጊስ አማላደን/2/ ከመድኃኔለም
አስታርቀን/2/
ማረን ይቅር አለን/2/ አማኑኤል ታረቀን/2/
ሹመት ለመፈለግ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ነገሥታት ዘንድ ሄዶ ›› ››
ጣዖት ሲያመልኩ አየ ›› ››
አምላኩ ተክዶ ›› ››
ክርስቲያን ነኝ የሚል ቅዱስ ጊዮርጊስ
በዓለም ሁሉ ጠፍቶ ›› ››
እኔ አምናለው አለ ›› ››
የአምላኩን ስም ጠርቶ ›› ››
የዓለም ግሣንግሱ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ጸባይዋ ሣይገዛህ ›› ››
ስለ ጌታ ፍቅር ›› ››
ከእናትህ ተለየህ ›› ››
የመፍጫው መሣሪያ ቅዱስ ጊዮርጊስ
በዓይነት ተደቅኖ ›› ››
እኔ አልፈራም አለ ›› ››
በአምላኩ ተማምኖ ›› ››

ተፈጭቶ እና ደቅቆ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ደብረ ይድረስ ሣለ ›› ››
እጸዋቱ ሁሉ ›› ››
ጊዮርጊስ ጊዮርጊስ አለ ›› ››

**779.ሕፃን ቂርቆስ**

ሕፃን ቂርቆስ ለዕሀርት ዘኢያፋርሆከ ነጎድጓድ/2/
ዮም ባርክ ማኅበረከ/2/ ለእለ አሐዱ አሐዱ/2/
**ትርጉም፡-** የእሳቱ ነጎድጓድ ያላስፈራህ ሕፃኑ ቂርቆስ
ሆይ የእያንዳንዳችንን ማኅበር ዛሬ ባርክ

780.ኦ **እስጢፋኖስ ሰማዕት**

ኦ እስጢፋኖስ ሰማዕት /2/
አክሊልን አገኘህ ከጌታ በእውነት /2/
የወጌልን ትምህርት ቀዳሜ ሰማዕት
ስለመገብካቸው ቀዳሜ ሰማዕት
አይሁዶች ወገሩህ ጨክኖ ልባቸው
በድንጋይ ሲወግሩት ቀዳሜ ሰማዕት
በጣም ተጨነቀ ቀዳሜ ሰማዕት
ለሚወግሩት ሰዎች ይቅርታን ጠየቀ /2/
አዝ . . .
የወንጌል በር ከፋች ቀዳሜ ሰማዕት
የተባልከው ቅዱስ ቀዳሜ ሰማዕት
ተመሠከረልህ ከእውነተኛው ንጉሥ
ሥራህ ያስደስታል ቀዳሜ ሰማዕት
እጅግ ድንቅ ሥራ ቀዳሜ ሰማዕት
በአንተ ተበተነ የወንጌል አዝመራ /2/
አዝ . . .
የዲቁናን ሥራ ቀዳሜ ሰማዕት
በክብር የፈጸምክ ቀዳሜ ሰማዕት
የሥላሴ ዙፋን ተከፍቶ ያየህ
የድንጋይ ሩምታ ቀዳሜ ሰማዕት
ያላዘናጋህ ቀዳሜ ሰማዕት
ቀዳሚው ሰማዕት እስጢፋኖስ ነህ /2/
አዝ . . .
ቀና ብሎ አየ ቀዳሜ ሰማዕት
ነፍሴን ተቀበለው በማለት ጸለየ
ጌታ ተቀበለው ቀዳሜ ሰማዕት
ቃሉንም ሰማለት ቀዳሜ ሰማዕት
ሰማያዊ አክሊል ወደ እርሱ ላከለት /2/

781. ኦ **ፍጡነ ረድኤት**

ፍጡነ ረድኤት /2/
የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊቀ
ሰማዕታት
ሰላም ለአንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት
የልዳው ፀሐይ ፍጡነ ረድኤት
በጨካኝ ንጉሥ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ ፍጡነ ረድኤት
ስቃይ ያልበገረህ ፍጡነ ረድኤት
አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሠህ/2/
አዝ . . .
የፈጣሪውን ስም ፍጡነ ረድኤት
ስለመሰከረ ፍጡነ ረድኤት
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሰይፍ ተመተረ
የስቃይ መሣሪያ ፍጡነ ረድኤት
ያላዘናጋህ ፍጡነ ረድኤት
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ /2/
አዝ . . .
ለእምነት ተጋዳይ ፍጡነ ረድኤት
ታማኝ ወታደር ፍጡነ ረድኤት
ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ስቃይ ቢያደርሱብህ ፍጡነ ረድኤት
በመታገስህ ፍጡነ ረድኤት
ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ስምህ /2/
አዝ . . .
ለሰማው ይደንቃል ፍጡነ ረድኤት
የአንተ ሰማዕትነት ፍጡነ ረድኤት
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉ ፍጥረት
ገድልህ ይናገራል ፍጡነ ረድኤት
ክብር እንደተሰጠህ ፍጡነ ረድኤት
ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖት /2/
አዝ . . .

782. **አርዓዮ ለቂርቆስ**

አርዓዮ ለቂርቆስ ግብረ ለደብተራ ወተናግሮ ግብራ
ለደብተራ /2/
ብርሃን በደመና/2/ እሙ እሙ ለሠማዕእት
እህቶሙለመላእክት/2/
ትርጉም፡- ለቂርቆስ የድንኳን ሥራ አሳየው በብርሃን
ምሰሶ ተነጋገረው የመላእክት እህታቸው የሰማዕታት
እናታቸው የደመና ብርሃንናት

783. **አፀደ ወይን**

አፀደ ወይን ዘያፈርህ አስካለ ሕይወት /2/
ከመ ጽጌሬዳ /4/ እስጢፋኖስ ምሉአ ፍቅር ከመ
ጽጌረዳ /2/

784. **ሰአለ**

ሰአለ ሥረይ ለኃጢአት ለእለ ወገርዎ /2/
ወይቤ ሥረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ
/2/

785. **ይቤላ ሕፃን ለእሙ**

ይቤላ ሕፃን ለእሙ ኢትፍርሂ እም /2/ ነበልባለ እሳት /2/
ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ዘአድኅኖሙ ውእቱ ያድኅነነ /2/
ሕፃኑ እናቱን አላት እናቴ ሆይ አትፍሪ /2/
የእሳቱን ነበልባል /2/
አናንያን አዛርያን ሚሳኤልንም ያዳናቸው እኛንም ያድነናል /2/

**786.አምላኮሙ ለክርስቲያን**

አምላኮሙ ለክርስቲያን ተመሲሎ ሰብአ መጽአ ኀቤየ ወይቤላ ቅዱስ ጊዮርጊስ /2/
አንሰ ኢኮንኩ አምላከ አላ ገብረ አምላክ አነ /2/
**ትርጉም:-**

**787.ገባሬ መንክራት**

ገባሬ መንክራት ጊዮርጊስ በአቁጽሎ ይቡስ ዓምድ/2/
ተራድአነ በገሀድ ተራድአነ /4/

**788.ጊዮርጊስ ግሩም**

ጊዮርጊስ ግሩም በመንፈስቅዱስ ኅቱም /2/
መዓዛ ቅዳሴከ ጥዑም ከመ ጽጌ ገዳም ጊዮርጊስ ግሩም /2/

**789.ጊዜ ዕረፍቱ**

ጊዜ እረፍቱ ለእስጢፋኖስ/2/
እም ልዕልና ወረዳ እግዚአብሔር/4/

## ለቤተክርስቲያን እና ለአባቶቸች የሚዘመሩ መዝሙራት

**790.አመ ትትሀነጽ**

አመ ትትሀነጽ ኢየሩሳሌም በእንቁ
ወሰንጴር ወበከርከዲን በዕንቁ ወሠንጴር/2/
አረፋቲሃኒ በኢየሩሳሌም ወማኀደፈዲሃኒ በወርቅ
ንጹሕ ወመርህባስ ለኢየሩሳሌም/2/

**791.ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ/2/**

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ/2/
ሀባ ሰላመከ ለኢትዮጵያ/2/
ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ/2/
ስጣት ሰላምን ለኢትዮጵያ

792. **ዝንቱ ኩሉ**

ዝንቱ ኩሉ ኮነ ኮነ በማኅደረ ስብሐት/2/
በደብረመድኃኒት/2/
በፈቃደ/4/ እግዚአብሔር /2/

**793.ሰላም ለክሙ**

ሰላም ለክሙ ኦ ማኅበራኒሁ ለክርስቶስ
እለ ተጋባእክሙ ውስተ ዛቲ ማኅደረ ስብሃት/2/
ጳጳሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት መሃይምናን
ወመሃይምንት ሕዝበ ክርስቲያን/2

794. **ባርከኒ**

ባርከኒ አባ መፍቀሬ ሕፃናት -------/2/
እስመ አንተ ሰባኬ ወንጌል ሐዲስ----/2/

795. **ከመ ትባርከነ**

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ ዘወርቅ/2/
ተዋነይ በጽድቅ /4/ --------ፓትርያርክ

**796.አባአባ**

አባ አባ ባርከኒ ------ ፓትርያርክ
ከመ ባርኮ አብርሃም ለይስሐቅ ወልዱ /2/

**797.ኦ አባ ቅዱስ**

ኦ አባ ቅዱስ እቀቦሙ /2/ ለስምከ ወበኃይልከ
እቀቦሙ/2/
ከመይኩኑ አሐደ ብነ ከማነ/2/ ከመ ይኩን/4/

798. **ከጌታዬ ፍቅር**

ከጌታዬ ፍቅር የሚለየኝ ማን ነው /2/
መከራ ችግር ሥቃይ ወይስ መራቆት ነው /2/
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም /2/

እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም /2/
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሠራው /2/
ግንቡ ንጹሕ ውኃ መሠረቱ ደም ነው /2/
ሳይነጋ ተራምደን እንግባ ቤታችን /2/
በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት /2/
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት /2/
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት /2/
ይኸው እዚህ አለ የሥላሴ ቤት /2/
ጠላት ቢተባበር ዲያብሎስ ቢያብር /2/
ሊለየን አይችልም ከእግዚአብሔር ፍቅር /2/

799. ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት /2/
አትመረመርም /2/ እጅግ ጥልቅ ናት /2/

በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ /2/
የእምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመጣ /2/
ሰው ሁሉ በክህደት/2/ ፈጣሪውን አጣ /2/

እንመሰክራለለን ፈጣሪያችን አለ
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ/2/
አንዳንዱ ቢክደው /2/ እየተታለለ /2/

እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት /2/
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የአማኑኤል እናት ናት /2/

800. ለዛቲ ቤት

ለዛቲ ቤት ሐነፃ ወልድ /2/
ወፈጸማ መንፈስቅዱስ /4/

801. ይትባረክ

ይትባረክ እግዚአብሔር /4/
ዘአልዓላ ለጽዮን እምኩሉ ዓለማት /4/

802. እንኳን ደህና

እንካን ደኅና መጣችሁ /2/
ወደ እኔ ወደ እናታችሁ
እጄን ዘርግቼ ስጠብቃችሁ

ወላጆቻችሁን እንድታከብሩ
አምላካችን መናገሩ /2/
እንድትጠብቁ ትእዛዙን
እምቢተኞች ባለመሆን /2/

አዝ . . .

የዕውቀት ገበያተኞች እንደመሆናችሁ
ምንም ጊዜ ሳይኖራችሁ /2/
እንደዚህ እኮ የምላችሁ
ቤተክርስቲያን ነኝ እናታችሁ /2/

አዝ . . .

ከሰኞ እስከ ዓርብ እየሠራን
እንጠያየቅ በሰንበት ቀን /2/

አዝ . . .

803. የድሆች መጠጊያ

የድሆች መጠጊያ ቤተ ክርስቲያን
ለመማር መጥተናል ሰምተን ቃልሽን /2/

ሰላም ሰላም የዘለዓለም ቤቴ /2/
ከአንቺ አልለይም እስከ ዕለተ ሞቴ

ሰላም ለአንቺ ይሁን ቤተክርስቲያን
በደሙ ያጸናሽ ኢየሱስ መድኅን /2/

አዝ . . .

ቤተ ክርስቲያን ሆይ የአማንያን እናት
ወደ አንቺ ቀርበናል እንድናገኝ ሕይወት /2/

አዝ . . .

ቅረቡ ምዕመናን በአንድነት ሆናችሁ
እጆቿን ዘርግታ ልትቀበላችሁ
ተነሥታለችና ቅድስት እናታችሁ

አዝ . . .

804. ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ እናታችን (2) ቤተክርስቲያን /2/
በደሙ የዋጀሽ (2) የዋጀሽ ኢየሱስ መድኅን /2/

805. ተዋሕዶ

ተዋሕዶ /2/ ሰማያዊት
የቀናች እምነት /2/ ሃሌ ሉያ
ተዋሕዶ /2/ መንፈሳዊት
የመንፈስ መብራት /2/ ሃሌ ሉያ
ተዋሕዶ /2/መለኮታዊ
ንጽሕት እምነት /2/ ሃሌሉያ
በአንቺ ስላመኑ /2/ ሰማዕታት
ተፈተኑ በእሳት/2/ ሃሌ ሉያ
በአንቺ ስላመኑ/2/ ቅዱሳን

ድል ነሱ ሰይጣን/2/ ሃሌ ሉያ
እንደወርቅ /2/ ፀርተው
አበራ ገድላቸው /2/ ሃሌ ሉያ
ክርስቲያኖች /2/ አስተውሉ
መዝኑ አስተውሉ /2/ ሃሌ ሉያ
ትኑርልን /2/ እምነታችን
ተዋሕዶ መክበሪያችን /2/ ሃሌ ሉያ

806. **ተዋሕዶ ንጽሕት**

ተዋሕዶ ንጽሕት ቅድስት እምነታችን /2/
ኑሪ ለዘለዓለም ተከብረሽ በሁላችን (2) /2/

810. **ተዋሕዶ ሃይማኖት**

ተዋሕዶ ሃይማኖት እንከን የሌላት /2/
እንከተላት /2/ እስከ ሞት /2/ በእውነት
ያለፍርሃት /2/

811. **ጽንው በተዋሕዶ**

ጽንው በተዋሕዶ እምነት /2/
መሠረት /2/ ናትና ሕይወት /2/

812. **እግዚአብሔር ይሀበነ**

እግዚአብሔር የሀበነ ልሳነ ጥበብ /2/
ከመ ናእምር ሕገ /2/ ለቤተክርስቲያን /2/
**ትርጉም** ፡- እግዚአብሔር ሆይ የቤተ ክርስቲያንን
ሕግ እናውቅ ዘንድ እውቀትን ስጠን

813. **በሃይማኖት**

በጭራሽ እንዳይደርቅ የሃይማኖት ሥሩ
መበርታት አለበት ሁሉም በተግባሩ
በሃይማኖት አለብን መጽናት
እንሁን በመንፈስ አንሁን ልበ መንታ
እንዲከፈትልን በሩን ስንመታ
አዝ . . .
ምግባራችን አምሮ በእምነት ከጸናን
ሲያበራ ይኖራል የሥራችን ብርሃን
አዝ . . .
ይብዛ ሰላማችን መልካም ሥራ እንሥራ
የመንፈስን ፍሬ ሁላችን እናፍራ
አዝ . . .

814. አንድ እምነት

አንድ እምነት ነው /2/ ጽኑ ሃይማኖት ነው /2/
ነቢያትን በትንቢት ሲያናግር የኖረው
አዝ . . .
አብርሃምን ለአምላክ ወገን ያደረገው
አዝ . . .
ከዕደ ረበናት ሦስናን ያዳነው
አዝ . . .

**815.ውድ ሃይማኖታችን**

ውድ ሃይማኖታችን የሁላችን ሕይወት
አንቺ ከምትጠፊ እኛ እንሁን መሥዋዕት /2/
ሰማይና ምድርን የፈጠረ እያለ
የሰው ልጅ ደፋሩ አምላክ የለም አለ /2/
በዝናብ አብቅሎ ሚመግብህን
አምላክ የለም ብለህ ካድከው ፈጣሪህን /2/
አእምሮ አለኝ ማለት አእምሮ ማጣት
እንክርዳድ ለመዝራት በሰው ጭንቅላት /2/
ይፍጨረጨራሉ ቀንና ሌሊት
ትእዛዙን ያክብር ሁሉም የሰው ልጅ /2/
ይህ ዓለም ጠፊ ነው ባያውቀው ነው እንጂ
ተው ንስሐ ግባ የሰው ልጅ ተመለስ
እንደልጅነትህ ኋላ ከምታለቅስ

816.ዋይ ዜማ

ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት
ቅዱሳን እንዘይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
እግዚአብሔር መልዓ ሰማያተ ወምድረ
ቅድሳተ ስብሐቲከ

# የምስጋና መዝሙር

817.ስምአኒ

ስምአኒ እግዚኦ ጸሎትየ
ወይብጽዓ ቅድሜከ ገአርየ

ወኢትሚጥ ገጽከ እምኔየ
በእለተ ምንዳቤየ አጽምዕ እዝነከ ኀቤየ
አመ ዕለተ እጼውአከ ፍጡነ ስምአኒ
**ትርጉም፡-** አቤቱ ስማኝ ጸሎቴን ጩኸቴም ወደአንተ ትድረስ ፊትህን ከእኔ ዘንድ አትመልስብኝ በመከራዬ ቀን ስማኝ ጆሮህንም ወደእኔ በጠራሁህም ዕለትም በፍጥነት ስማኝ

### 818.የሥላሴን መንበር

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት
አእላፍ መላዕክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን አባት
የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላዕክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ
ይህን ታላቅ ክብር ሊያዩ የታደሉ
በጽድቅ ሥራቸው በምድር ይታያሉ/2/

### 819.ሥላሴን አመስግኑ

ሥላሴን አመሥግኑ/2/
የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ/2/
በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ምስጋና ይገባል ከምንም በፊት
ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረ ጌታ
ምስጋና ይገባል ከጠዋት እስከ ማታ
ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰግኑት
መላእክት ከሰማይ የሚዘምሩልህ
እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን
በሰማይም በምድር እንጠራሃለን
ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ
ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ
ሥላሴ አምባዬ ክብሬም ናቸውና
ሁሌም ይመሩኛል በሕይወት ጎዳና

### 820. ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን /2/
ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን
ከሞት ወደ ሕይወት ያሸጋገረን
ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን/2/
የሰማዩን መንግሥት ርስቱን ለሰጠን
ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሰየን
ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል
በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል
ከዓለት የፈለቀ ውኃ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ
ስምህን ላመስገነው ከጠዋት እስከ ማታ
በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባሕር ወጀብ በበዛበት
ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት
በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን
የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ
የኢያቄም ስእለቱ የሐና እምነት
ለምኚልን ለእኛ ኪዳነምሕረት

### 821.ኩሉ ዘፈቀደ

ኩሉ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር /2/
በሰማይኒ ወበምድኒ ወበባሕርኒ/2/
ወበኩሉ ቀላያት /4/

### 822.ይትባረክ እግዚአብሔር

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ /2/
የአባቶቻችን አምላክ ይባረክ/4/

**823.ይትባረክ**

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኮሙ ለአበዊነ/2/

ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ/2/ እግዚአብሔር/2/

**824.እንደ እግዚአብሔር ያለ**

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለምና

እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና/2/

አዝ ...........

ባሕር ተከፈለ እሲኪታይ መሬቱ

ፈርዖን ወደቀ አልሠራም ትምክህቱ

ደካሞቹም ጸንተው ተራመዱ

ኃይለኞቹም ይኸው ተዋረዱ

አዝ ............

የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው

ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሳይነካው

ኃይለኞቹም ቢበረታቱብን

እንጸናለን በእርሱ ተደግፈን

አዝ ............

የተወረወረው የጠላታችን ጦር

ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚአብሔር

ለሥላሴ ይድረስ ምስጋናችን

ተሸነፈ አዳኝ ጠላታችን

አዝ ------------

ባሕር ላይ ሲራመድ ሞገስ አለው እርሱ

በግርማው ሲነሳ ጸጥ ይላል ነፋሱ

የድንግል ልጅ እኛ የምናመልከው

ከሀሊ ነው የለም የሚሳነው

**825.ልዑል እግዚአብሔር**

ልዑል /2/ ምስጋና ይገባሃል/2/

ለዚህ ዕለት ለዚህ ሰዓት በሰላም

በጤና አደረሰከን/2/

**826.እግዚአብሔር ብርሃኔና**

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው/2/

የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው/2/

አምላኬ መመኪያዬ ነው/2/

**827.እንደ አባቶቻችን**

እንደ አባቶቻችን እናቅርብ ምስጋና

ስሙን ለማመስገን ተፈጥረናልና/2/

ዲቦራና ባርቅ ማለዳ ሲቀኙ

ለምስጋና ቆመው ከአምላክ ሲገናኙ

የአሳፍም ልጆች ጸናጽሉን ይዘው

ይዘምሩ ነበር በአንድነት ሆነው

የዚህ ዓለም ጉድፍ ያልተጨመረበት

ንጹሑን ምስጋና ለአምላክ እንሰዋለት

በሰዓትት በማኅሌት ያሬዳዊ ዜማ

እንዘምር ሁላችን ድምጻችን ይሰማ

በምስጋና እንቅረብ ወደ ሰማዩ ክብር

ዳዊት በሃይማኖት ባለበት ማኅበር

ከበሮ ይመታ በገና ይደርደር

ለስሙ እንቀኝ በምሥጢር እንዘምር

የሰማይ ካህናት ሲዘምሩ አይቶ

ምሥጢር ተገልጾለት በመንፈስ ተቀኝቶ

በመዝሙረ ዳዊትን ሐዲስና ብሉይ

ይዘምር ነበረ ያሬድ ማኅሌታይ

**828.እናምናልን በአብ**

እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ

እናምናለን በመንፈስ ቅዱስ

ኸኸ ፍጹም ጥርጣሬ ሳይኖር አንድ

እግዚአብሔር ብለን/2/

የሥላሴን ቸርነት የሥላሴን ጥበብ

ልቡናችን ይረዳ ኅሊናችን ይማር

ኸኸ እንደ አምላክነቱ እንመነው/

ከእውነት ሁሉ የሚበልጥ ነው

በስም በአካል በግብር

ሦስትነቱን አምነን

በመለኮት አንድ አምላክ ብለን እናምናለን

እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ

እናምናለን በመንፈስ ቅዱስ

829.በበጎ ፈቃዱ

በበጎ ፈቃዱ ሁሉ በእርሱ ሆነ /2/
ነገር ሁሉ በእርሱ ተከናወነ/2/
ሰማይና ምድር ክብሩን ተናገሩ
ፈጥሮአቸዋልና እንዲገለጥ ክብሩ
በፈጠረው ፍጥረት የሚታወቅ እርሱ
እግዚአብሔር ይመስገን ስሙን አወድሱ
አልሆነም ያለ እርሱ ፍጹም አንዳች ነገር
ብንመረምረው በሰማይ በምድር
ፈቃዱ ነውና መልካምና በጎ
ፈጥሮ አሳይቶናል ሁሉን ውብ አድርጎ
ክረምትና በጋ ሌሊትና ቀን
ሁሉን አሳይቶ ጌታ አስተማረን
ያደረገው ሁሉ እንከን የሌለው
ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምሳሌም የለው
ያዘነውን ያውቃል ደስም ያለውን
ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ስለሚከወን
ችግርና ደስታ ለበጎ ነውና
ይህን ያስተማረ ይድረሰው ምስጋና

830.እልል በሉ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩም ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ
በኃጢያት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትዕዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ሳለን ጠላቶቹ ሳለን
ውለታው ግሩም ነው ክብር ለእርሱ ይሁን/2/
ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ሥጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰው ለመድኃኔዓለም/2/
ሕይወቱን የሠዋ እንደ አምላክ ማን አለ
ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩም አይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋር /2
ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአማላክ ስጦታ
ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ

831. እግዚአብሔርን አመስግኑት

እግዚአብሔርን አመስግኑት
ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት
እግዚአብሔርን አመስግኑት
ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት
ሰማይን ያለምሰሶ
ምድርንም ያለመሠረት
ያጸናው እርሱ ነው
ሥራህ ድንቅ ነው በሉት
የባሕርንም ጥልቀት የመጠነ
ዳርቻዋን የወሰነ
እግዚአብሔርን አመስግኑ
ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት
ማዕበል ነፋሱን የሚገስጽ
ፍጥረቱ ለስሙ የሚታዘዝ
ትጉህ እረኛ ድካም የሌለበት
እግዚአብሔርን ሥራህ ድንቅ ነው በሉት
ንጉሐ ባሕርይ ነው ሁሉን የሚገዛ
የነገሥታት ንጉሥ አልፋና ዖሜጋ
ዘለዓለም እርሱ ነው የማይለወጥ
እግዚአብሔር ሥራህ ድንቅ ነው በሉት
ጥበብን የሚሰጥ ጥበበኛ
ፍርድ የሚያደርግ እውነተኛ ዳኛ
እንደ እርሱ ያለ ከቶ አይገኝም
እግዚአብሔር ግሩም ነው ለዘለዓለም

832.ኢትግድፈነ

ኢትግድፈነ /2/ ወኢትመንነነ2/
አምላከ ሰላም ተራድአነ/2/
እግዝእትነ/2./ ነጽሪ ኀቤነ /2/
ሰላም ወልድኪ የሀሎ ምስሌነ /2/
እመቤታችን //2/ ተመልከች ወደእኛ /2/
የልጅሽ ቸርነት ይሁን መዳኛ/2/

833.የወደደኝ ጌታ

የወደደኝ ጌታ ምን አድርጌለት ነው
ብዘምርለት ያንስበታል ይኸው
ከውድቀቴ አንስተህ ድካሜን ያገዝከኝ
ሰባራውን ድልድይ ገጥመህ ያሳልፍከኝ/2/
በኢያሪኮ መንገድ ስለምን ቁጭብዬ
ብርሃን እጅግ ናፍቆኝ ከሰው ተገልዬ
የብርሃን ጌታ ወደ እኔ መጣና
ዓይኔን አበራልኝ በእጁ ዳሰሰና
ለብዙ ዘመናት ከአልጋ ላይ ተኝቼ
የሚረዳኝ አጣሁ ጠሉኝ ዘመዶቼ
የእኔ ጌታ አምላኬ ወደ እኔ መጣና
አልጋህን ተሸክም አለኝ ፈወሰና
አሥራ ሁለት ዓመት ደም የፈሰሰኝ
ምሥራቅ እየተፋ ሁሉም
ቢያንቋቋሽሹኝ
የጌታዬ ልብሱን ጫፉን ብዳብሰው
ኃይልም ከእርሱ ወጣ ደሜን ቀጥ
አደረገው
ሰካራም ዘማዊ ወንበዴ ነበርኩኝ
የአመጸኞች መሪ ደምን ያፈሰስኩሩ
ዛሬ ግን ታሪኬን ጌታ ቀይሮታል
ለኃያሉ ጌታ ምስጋና ይገባል

834.ለእኔስ ወደ እግዚእሔር

ለእኔስ ወደ እግዚአሔር መቅረብ
ይሻለኛል
መታመኛዬ እርሱ ነውና ይገባዋል ክብርና
ምስጋና/2/
ሕጉን እያሰቡን እንቅረብ ወደ እርሱ
ይምረናልና መሐሪ ነው እርሱ
በልባች ይንገሥ ይግባ ከቤታችን
የሕይወታችን ዋልታ እርሱ ነው
ተስፋችን/2/
ከቶ አላገኝም እርሱን የሚመስል
ነፍሴን የሚያከብራት የሚሠጠኝ ኃይል
በመከራ ሰዓት ከክፉ የሚያድነኝ
ከየት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ/2/
በለመለመ መስክ መሸሸጊያዬ ነው
በሰላም ወጥቼ ሰላም እገባለሁ
ተስፋዬ እርሱ ነው ይመራኛለና
ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምስጋና
ዘወትር አቀርባለሁ ለአምላኬ ምስጋና
ለእኔስ ይሻለኛል መቅረብ ወደጌታ
ጋሻዬ ነውና የነፍሴ አለኝታ
ስለዚህ አቀርባለሁ አልርቅም ከደጁ
ጠግቤ እኖራለሁ በበረከት እጁ /2/

835.ድንቅ አደርጎልኛል

ድንቅ አድርጎልኛል የሠራዊት ጌታ /2/
አልረሳኝም አምላክ አነሳኝ ከትቢያ
አዝ -------------
ድንቅ አድርጎልኛል በደሌን ሳይቆጥር
ድንቅ አድርጎልኛል ወደ ቤቱ ጠራኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ረክሼ ሳለሁ
ድንቅ አድርጎልኛል ልጅ ሆይ ና አለኝ
ድንቅ አድርጎልኛል በዳግም ምጽዐቱ
ድንቅ አድርጎልኛል መንግሥቱን ሊያወርሰኝ
አዝ ------------
ደንቅ አደርጎልኛል ከአንበሳ መንጋጋ
ድንቅ አድርጎልኛል ከጉድጓድ አወጣኝ

ድንቅ አድርጎልኛል በጠላቶቼ ፊት
ድንቅ አድርጎልኛል ግርማ ሞገስ ሰጠኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ምን እምልሳለሁ
ድንቅ አድርጎልኛል እንዲህ ለወደደኝ
አዝ ------
ድንቅ አድርጎልኛል ድንቅ አድርጎልኛል
ድንቅ አድርጎልኛል ጠላቶቼን ሁሉ
ድንቅ አድርጎልኛል ሲዋደዱብኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ማን ይደርስለታል
ድንቅ አድርጎልኛል እያሉ ሲሉኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ፈጥነህ ደረስክልኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ከሞት አዳንከኝ

## 836.ስሙ በክብር

ስሙ በክብር ክፍ ክፍ በሏልና
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረስው ምስጋና /2/
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረሰው ምስጋና /2/
ሕዝቡን እየመራ ያሻገረ
ባሕረ ኤርትራን የከፈለ
ጠላቶችን ውኃ ከዳናቸው
ሕዝብህም በደስታ እልል አለ
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ
ይድረሰው ምስጋና/2/

ፈረሰኛውና ፈረሶቹ
አልቻሉም ባሕሩን ለመሻገር
እርሱ ቆሞአልና ከፊታቸው
ድንቅን የሚሠራ እግዚአብሔር
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ
ይድረሰው ምስጋና

ጉልበቴ ነህ ኃይሌ ዝማሬዬ ብለው ተቀኙለት እነ ሙሴ
ከበሮውን ያዙ እነ ማርያም ሊያቀርቡ ምስጋና ለሥላሴ
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ
ይድረሰው ምስጋና

ተዋጊ ነው አሉት ድል አድራጊ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚራራ
ቀላያትን ከድኖ የሚያሰጥም
ልጆቹን በቃዴስ የሚመራ
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ
ይድረሰው ምስጋና

## 837.በገና አንሥተን

በገና አንሥተን መሰንቆን
እናመስግነው ስምህን
አንደ አምላካችን ማንም የለም
ይክበር ይመስገን ለዘለዓለም/2/

ዓለም ሞኝነት ይመስለዋል
ለአንተ መንበርከክ ይከብደዋል
ፍቅርህን ቀምሰን ዝም አንልም
እንዘምራለን ለዘለዓለም/2/

ሞኝነት ለእኔ መች ሆነና
ፊትህ ያቆመኝ ለምስጋና
እንድቀኝልህ ግድ የሚለኝ
ፍቅርህ ብቻ ነው የማረከኝ/2/

ፈውስን ስትሰጠን ስትባርከን
ፍቅርህን ልክህ ስትጎበኘን
ጉልበት ይጸናል በአንተ ጸጋ
ማነው የሚከፍልህ የአንተን ዋጋ

ስንዘምርልህ የሚስቁ
ብዙ ሜልኮሎች ዛሬም አሉ
የእኛ የሆነ ምንም የለም
አምላክ ስላንተ ዝም አንልም/2/

## 838.በመስቀል ተሰቅሎ

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለጸው

ምን ስጦታ አለን ለእርሱ የምንከፍለው
ምስጋና ነውና ከእኛ የሚፈልገው
ቸሩ አምላካችንን ተመስገን እንበለው
ዓለም እስኪደነቅ ድንቅ አድርጎልናል
እንዲህ ያለዋጋ ጸጋውን ሰጥቶናል
ትናንት ለእስራኤል ሞገስ የሆናቸው
ስሙን እናመስግን ዛሬም ከእኛ ጋር ነው
አፋችን ይመላ በታላቅ ምስጋና
ከኃጢአቱ ባሕር ተሻግረናል
ክቡር ሞስጉን አምላክ ቅዱስ እንበለው
ኢሳይያስም በክብር በራእይ እንዳየው
ከቶ ለእግዚአብሔር ምን ይከፈለዋል
ሁሉም የራሱ ነው ማን ምን ይሰጠዋል
አምስጋኝ ቢቀኝም ክብር ላራሱ ነው
እርሱ በባሕርዩ ዘለዓለም ምስጉን ነው
ሙሴም ዝም አላለም ዳዊትም አልተኛም
በጎቹ ዘመሩ ለመልካሙ እረኛ
ያሬድ ተመሠጠ ወደ ሰማይ ዓለም
እኛም ከእነርሱ ጋር እንዘምር ዘለዓለም

839.<u>ሳይገባኝ አምላክ</u>

ሳይገባኝ አምላክ ሳይገባን
ለዚህ ያደረሰከኝ እኔ ማነኝ/2/
ምን ያላደረክልኝ አለ ጌታ ለእኔ
ምንም ባሳዝንህ በምግባሬ
ኃጢአቴን ተመልክተህ ቸል ያላልከኝ
በሕይወቴ ብዙ ነገር ሠራኸልኝ
ውለታህ ብዙ ነው የአንተ ወሰን የለው
ተናግሬ እኔስ አልጨርሰው
ውድቀቴንም ድክመቴንም እኔ አውቃለሁ
የጠበቀኝ ቸርነትህ ምሕረትህ ነው
ለማይነገረው ፍቅርህ ግሩም ሥራህ
ልጆችህን የምትጠብቅ ከመከራ
ምን እንመልሳለን ለአንተ ለአምላካችን
ከመዋረድ አድነኸን ላከበርከን

840.<u>አምላካችን</u>

አምላካችን መድኃኔዓለም ነው
መመኪያችን መድኃኔዓለም ነው
በእልልታ እናመስግነው
በጨለማው መንደር ስንኖር ታሰረን
ከጥፋት ረግረግ ዲያብሎስ ዘፍቆን
በመስቀል ላይ ሆኖ ከሞት ያዳነን
ምስጋና ይድረሰው መድኃኒታችን
ከሞት ባሕር ወጣን በእርሱ ቸርነት
በድለን የነበርን አገኘን ምሕረት
በፍቅሩ አረጋጋን አደለን ሰላም
የሰላም ባለቤት መድኃኔዓለም
ራሱን ሰዋልን ለእኛ በደል ካሣ
ገና ጠላት ሳለን ኃጢአት በዓለም ነግሣ
ያንን የሞት ባሕር አሻግሮናልና
ውለታው ግሩም ነው ይድረሰው ምስጋና

841.<u>ዘመኔ በከንቱ</u>

ዘመኔ በከንቱ እንዳይፈጸም
መልካም እንድሠራ አርዳኝ መድኃኔዓለም
ኃጢአቴ በዝቶብኝ መኖር አቅቶኛል
በቤትህ ውስጥ ልጣል ሰላም ይሻለኛል
ድንገት ስትጠራኝ ግራ እንዳይገባኝ
በሕይወት ዘመኔ ለንስሓ አብቃኝ
አንተ የወሰንከው እድሜዬ ሲያበቃ
ለነፍሴ የሚቆም አድለኝ ጠበቃ/2/
በሞት ሣልገታ ሳይደክሞ ጉልበቴ
እንደምትወደው ልኑር መድኃኒቴ
በሰማይ መንግሥትህ አስበኝ አደራ
አቁመኝ በቀኝህ ከቅዱሳን ጋራ /2/

842.<u>እኔስ እዘምራለሁ</u>

እኔስ እዘምራለሁ ለሥላሴ /2/
ፈጥሮኛለና እና በሥጋ በነፍሴ

እኔስ እዘምራለሁ ለሥላሴ

ሥሉስ ቅዱስ ተብለህ የምትመሰገን

ሰውን ከመከራ ከሞት የምታድን

ነፍሴ ትገዛልህ ትንበርከክልህ

ቅዱስ ፈጣሪዬን አንተን ታምልክህ

በመሐሪነትህ ጠብቀህ ያኖርከኝ

በማዳን ችሎታህ ለዚህ ያደረስከኝ

ለአንተ ለአምላኬ ምስጋና አቀርባለሁ

ስምህን ለዘለዓለም ሁሌም እጠራለሁ

አብርሃም ለአምላኩ በቀና ቢታዘዝ

ሥላሴ ገቡና ቤቱን ባረኩለት

ሣራንም ጎበኟት በእርጅናዋ ጊዜ

ይስሐቅን ሰጧት ዘለዓለም ሥላሴ

843.<u>አማን በአማን</u>

አማን በአማን /2/

መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም/2/

ንግበር ሰብአ ብለው አማን በአማን

አዳምን ፈጥረውት ›› ››

በቸርነትና በፍቅር ጎበኙት

ሁሉን በእጅ አድርገው ሁሉን አስገዙለት

የፍቅር የደስታ አማን በአማን

የበረከት አባት ›› ››

መንግሥቱ ዘለዓለም ኅልፈት የሌለበት

በአፈ መላዕክት የሚመሰገኑት

የዚያን የደግ አባት አማን በአማን

የአብርሃምን ቤት ›› ››

እንደባረኩለት የእኛንም ባርኩልን

የቤታችን ዋልታ መሠረት ሁኑልን

በመከራ ጊዜ አማን በአማን

ከጭንቅ የሚያወጡኝ

ስሙን ሳመሰግን ትረካለች ነፍሴ

የእነሙሴን አምላክ የአብርሃሙን ሥላሴ

844.<u>እግዚአብሔርን ጠራሁት</u>

እግዚአብሔርን ጠራሁት በሐዘኔ ጊዜ

እግዚአብሔርን ጠራሁት በጭንቀቴ ጊዜ

አወጣኝ ከጭንቀት ከሐዘን ከትካዜ /2

የልመናዬን ድምጽ እርሱ ሰምቷልና

ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሏልና

በዘመኔ ሁሉ ስጠራው እኖራለሁ

ጎስቋላ ብሆንም ምስጋና አቀርባለሁ/2/

እንደ ቃልህ መሄድ መራመድ አቅቶኝ

የኃጢአቱ መንገድ ማዕበሉ ገፍቶኝ

ወደ እርሱ ስማጸን ደግሞም ስጸጸት

አላሳፈረኝም መጣ በምሕረት /2/

በበዛው ምሕረቱ ያለፈውን ትቶ

በፍቅሩ ጎበኘኝ አልተወኝም ከቶ

ሊቀበኝ ወዶ ፊቱን አበራልኝ

ማን ይቃወመኛል እግዚአብሔር ካለልኝ/2/

ኖኅን እንዳዳንከው እኛንም አድነን

ከቀስቱ እንድናመልጥ ምልክትን ስጠን

በትርህ ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑን

አንተ ከእኛ ጋር ነህ አንፈራም ክፉውን/2/

845.<u>ኑ ወደ ቤቴል</u>

ኑ ወደ ቤቴል ወደ ሰማያዊት/4/

ማደሪያ ነችና ዘለዓለማዊ ቤት ኑ ወደ

ሰማያዊት

እጆቿን ዘርግታ ሰማያዊት

ለመላው ዓለም ››

ኑ ወደ እኔ ስትል ››

ዓለም ዘለዓለም ››

ይህች ቤተ እግዚአብሔር ናት

መምህረ ወንጌል

የምትመግበን የሕይወትን ቃል

የሕይወት ቃል ወተት ሰማያዊት

እንዲህ የሚፈስባት ሰማያዊት

የሰማዕታት ገድል ››
የሚነገርባት ››
መሠረቷ ማይፈርስ ቅድስት ተዋሕዶ ናት
ተንተርሶ ያያት ሰማያዊት
ያዕቆብ በቤቴል ››
ዘይቱን የቀባት
የሕይወት መሠላል
ጉልላቷ ኢየሱስ
ከላይ ስለሆነ
እንገባለን እኛ በእርሱ ሰላመንን
የምስጋና መሥዋዕት ሰማያዊት
በልባች ይዘን ››
ጋሻ ጦር ጾማችን
ጸሎትን አንግበን
እንሠዋ መሥዋዕቱን በአንድነት ሆነን

## 846.ተነሡ እንዘምር

ተነሡ እንዘምር በአንድነት ሆነን በእልልታ/2/
ኸኸኸ ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር /2/
ለኃያሉ ጌታ ለልዑል እግዚአብሔር
አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሶአል
አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው /2/
አልጠገብ አለ ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት ያንተ ሥራ ያንገተ ልግስና
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና
ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተ ነህ
በሄድንበት ሁሉ ትከተለናለህ
ከእንቅፋት ከድንጋይ ትሰውረናለህ
ስለመልካም ሥራህ አለብን ውለት
ሰለማይነገረው የማዳን ስጦታ
ተመስገን እንበል ከጠዋት እስከማታ
ሌላ ምንም የለም የምንከፍለህ ጌታ
መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን ያውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እስከ ዘለዓለም ለስምህ እንዘምር
አዝ ------

## 847.ለምትቀር ዓለም

ለምትቀር ዓለም/2/
ለምትቀር ዓለም መታከት መድከም
በዓለም በረሀ ወድቀን እዳንጠፋ
መጽናት ገባልናል በፍቅር በደስታ
እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህን ይዘን
ድል ማድረግ አለብን የምትቀር ዓለምን
አዝ ----------
በሥጋዊ ምኞት በዓለም ተጠምደን
የአምላካቸንን ትዕዛዙን ጥሰን
ከፈጣሪያችን ፊት ከቤቱ እንዳንጠፋ
ወላዲተ አምላክ አንቺ ሁኝን ተስፋ
አዝ-------------
በሲያል በረሀ እንዳንቀር ወድቀን
ልንቆም ይገባናል በእምነት ተደግፈን
ጌታችን ሲመጣ በግራ ከመቆም
ካሁኑ እንዘጋጅ ነገ የእኛ አይደለም
አዝ -------
እንደ ሰማእታት ዓለምን በመናቅ
ጽድቅን እየሠራን ከክፋት በመራቅ
እንዘን አናልቅስ ስለበደላችን
በቀኙ እንዲያቆመን ቸሩ ፈጣሪያችን
አዝ ---------

## 848. ሰአሉ ለነ

ሰአሉ ለነ ቅዱሳን መላእክት/2/
ሰአሉ ለነ ጻድቃን ሰማዕታት
ኀበ አምላክ ምሕረት ሰአሉ ለነ
ለምኑልን ቅዱሳን መላእክት/2/

ለምኑልን ጻድቃን ሰማዕታት
ወደ አምላክ ምሕረት ለምኑልን
የመረጥከውን ማን ይከሳል
ያስቀምጥከውን ማን ይወስዳል
ለሚገባው ክብርን መስጠት
ታዝዟል እና በመጻሕፍት
ያከብርካቸውን ባሪያዎችህን
እንከብራልን ቅዱሳንህን /2/
ጽኑ መዳን እንዲይዙ
የሚላኩ የሚታዘዙ
ሠርክ በፊትህ እየቆሙ
ጥዑም ቅዳሴን እያሰሙ
በምስጋናቸው የሚየከብሩህን
እናከብራለን መላእክትህን/2/
ጤዛ ልሰው ዳዋ ጥሰው
ዋዕይ ቁሩንም ታግሰው
በየፍርክታው በየዱሩ
ሌጦ ለብሰው እየዞሩ
በሥርዓታቸው ያከበሩህን
እናከብራለን ጻድቃንህን/2/
እንደሚታረዱ በጎች ሆነው
አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው
ስለ ስምህ እየተጣሉ
ከአንበሳ ጋር እየታገሉ
በተጋድሏቸው ያከበሩህን
እናከብራለን ሰማዕታትን/2/
ከሕያው ቃልህ እየጠቀሱ
መናፍቃንን ድል እየነሱ
በገዛ ደምህ የዋጀሀትን
ቤተ ክርስቲያንን የጠበቋትን
በሕይወታቸው ያስደሰቱህን
እናከብራለን ቅዱሳንህን/2/

## 849.ስብሐት ለአብ

ስብሐት ለአብ3
ስብሐት ለአብ ለአኃዜ ኩሉ ዓለም
ስብሐት ለወልድ ለገበሬ ኩሉ ፍጥረት /2/
ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘያርዉ ክረምት በበዓመት/2/
ትርጉም፡- ምስጋና ይገባል ለአብ ዓለምን ሁሉ ለያዘ
ምስጋና ይገባል ለወልድ ዓለሙን ሁሉ ለፈጠረ/2/
ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስ በየዓመቱ
ክረምትን ለሚከፍት/2/

## 850.እውነተኛ ሰላም

እውነተኛ ሰላም ያለው ከቤትህ ነው
እርደኝ አልናወጽ እለምንሃለሁ/2/
ኃጢአቴን ሳስበው ልቤ ይጨነቃል
ከአንተ መለየቴ ነፍሴን አድክሟታል
ወደአንተ መልሰኝ እኔ እመለሳለሁ
እውነተኝ ሰላም ያለው ከቤትህ ነው
ለቅዳሴው ጸሎት ዘወትር እንዳልተጋሁ
በአደባባይ ቆሜ ስምህን እንዳልጠራሁ
ተሰነካክዬ ወድቄአለሁና
እርዳኝ አማኑኤል በሃይማኖት ልጽና
ዓይኔ ዕንባ ያመንጭ ላልቅስ ስለ ኃጢአቴ
የንስሓ ትሁን ቀሪዋ ሕይወቴ
በመዳኔ ሰዓት በዛሬዋ ዕለት
ፍቅርህን አስቤ መጣሁ ከአንተ ፊት
ጌታ ሆይ ጸጸቴን ዕንባዬን ተቀበል
አባትህ ነኝ በለኝ እኔም ልጅ ነኝ ልበል
ዘይት ሳላዘጋጅ ድንገት መጥተኽብኝ
በርህን በመዝጋት ከደጅህ አታስቀረኝ

## 851.ጌታ ሆይ ለስምህ

ጌታ ሆይ ለስምህ እዘምራለሁ
ልዑል ሆይ ለክብርህ እልል እላለሁ
በአንተ ደስ ይለኝል ሐሴት አደርጋለሁ /2/
የበዛው ምሕረትህ በእኔ ላይ ተገልጦ
የትናንቱ ስሜ በአንተ ተለውጦ
ሞገስ ስለሆንከኝ ከፊትህ ቆሚያለሁ
በአውደ ምሕረትህ ስምክን እጠራለሁ
ያለቀውን ነገር የተቆጠረውን

ትቀጥለዋለህ ለአንተ አይሳንህም
መቃብሩን ከፍተህ መግነዝ የምትፈታ
የሞትም ጌታ ነህ የድሆች አለኝታ
አንተ የመረጥከውን ማነው የሚከሰው
ያከበርከውንስ ማነው የሚቃወመው
በሰው ፊት የሚታይ ደም ግባት ባይኖረኝ
ጸጋህ ይበቃኛል እዘምራለሁኝ
እኔስ ቀንቻለሁ አምላኬ ለክብርህ
በልቡናዬ ውስጥ እስኪሳል መስቀልህ
የተጋረደውን አዚሙን አጥፋልኝ
ውለታህን አውቄ በአንተ ደስ እንዲለኝ

## 852ዓይኖቼ

ዓይኖቼ ማዳኑን አይተዋልና/2/
ይገበዋል /2/ ክብርና ምስጋና
ከሰማይ ወረደ ሰውን በማፍቀር
ኃያሉ ጌታችን ቸሩ እግዚአብሔር
በቤቴልሔም ዋሻ በዚያ በግርግም
ተወለደ ዛሬ መድኃኔዓለም
የተነበዩለት ብዙ ነቢያት
ከድንግል ተወልዶ አዳነን በእውነት
ከበደል ጉራንጉር አነሣን ከትቢያ
በአንድነት እንዘምር እንበል ሃሌ ሉያ
የተናቅን ስንሆን እኛን ሊያከብር ወድዶ
በፍቅር አከበረን እራሱን አዋርዶ
ምን አይነት ፍቅር ነው ፍጹም ምሕረት
የአምላክ መወለድ በከብቶች በረት
በንጽሕና ጸንተሽ ቤተ መቅደስ የኖርሽ
በኑቱም ድንግልና መድኃኒትን ወለድሽ
የዓለምን ኃጥአት የሚያስተሠርይ ጌታ
ተወልዷል ከድንግል የሰዎች አለኝታ

## 853.አደርገህልኛልና

አደርገህልኛልና በቸርነትህ/2/
አመስግንሃለሁ እልል እልል /2
ለዓለም ዓለም አማኑኤል
እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም /2/
ቀኑ ጨለሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደኩኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅኽልኝ የልቤን ትካዜ
አዝ -----
አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ
አዝ --------
ጥቂትዋን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ስጦታ
በቀንም በሌትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባሕርይህ እጹብ ለአንተ ሥራ
አዝ-----------
አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሀል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሠጥሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሠሮዬ ሞልቷል አይጎል እንደገና
አዝ -------

## 854የነገሥታት ንጉሥ

የነገሥታት ንጉሥ ቸሩ አባት
የጌቶቹም ጌታ በሰማያት
ከቶ እንደአንተ ማነው ሩኅሩኅ አባት/2/
አዝ ----------------
ቅዳሜ በአንተ ዘንድ ቸሩ አባት /2/
ምንም ቦታ የለው በሰማያት
ፍጹም ቸርነትህ ቸሩ አባት
የአንተ ባሕርይ ነው በሰማያት
ከቶ እንደአንተ ማነው ሩኅሩኅ አባት/2/
አዝ -----------

ምሕረትህ ለሰው ልጅ ቸሩ አባት
እጅጉን በዝታለች በሰማያት
ኃጢአት በበዛባት ቸሩአባት
ጸጋህ ትበዛለች በሰማያት
ከቶ እንደአንተ ማነው ሩኅሩኅ አባት/2/
አዝ ------
የትዕግሥት ብዛት ቸሩ አባት
እኔን ድንቆኛል በሰማያት
የኃጢአቴን ዋጋ ቸሩ አባት
መቼ ከፍለሽኛል በሰማያት
ከቶ እንደአንተ ማነው ሩኅሩኅ አባት/2/
አዝ -------
ስንበድል ስንቀጥፍ ችሩ አባት
አንተ ተደብቀን በሰማያት
አይተህ እንዳላየህ ችሩ አባት
በምሕረት አለፍከን በሰማያት
ከቶ እንደአንተ ማነው ሩኅሩኅ አባት/2/
አዝ ------

## 855.አድፈኒ

አድፈኒ እምተ ሰጥሞ ኪያየ ክቡድ/2/
ናሁ በላዕሌየ ተንሥአ ምገድ/2/
ሞገድ ናሁ በላዕሌየ ተንሥአ ሞገድ
አድነኝ እንዳልጠፋ በኃጢአት ወጥመድ /2/
እነሆ በእኔ ላይ ተነሥቶአል ሞገድ /2/
አድፈኒ ከገሃነም እሳት ጠፍቶ ከማይጠፋው
ከዚያ አስፈሪ አውሬ ከሚንቀላፋው
ከሰይጣን እሥራት ከዳግመኛ ሞት
እግዚአብሔር ሆይ ርዳኝ እንዳልቀር ከቤትህ
አዝ ---------
አድፈኒ
ማዕበሉ አወኮኝ እንዳልንገላታ
ሞገድ እንዳይጥለኝ ርዳኝ የእኔ ጌታ
ከክፉ ፈተና ከምማረርበት
ከዝሙት ከርኩሰት ፍቅር በሌለበት
አዝ ---------
አድፈኒ ከሐሜት ከስርቆት ከኃጢአት ባርነት
ከጨለማ መንገድ ሕይወት ከሌለበት
ከድፍረተ ኃጢአት አምላክ ከሚያዝንበት
ከተንኮል ከበቀል ቁጣ ከበዛበት
አዝ -------
አድፈኒ ዛሬ ካለሁበት ከኃጢአት ወጥመድ
በዚያ በምጽዓት ቀን በእኔ ከመርፈድ
የኃጢአት በሽታ አዳልጦ እንዳይጥለኝ
እግዚአብሔር አምላክ ሆይ አደራ ደግፈኝ
አዝ -------------

## 856.ዝምአትበሉ

ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ/2/
ቅዱስ /3/ ሥሉስ ቅዱስ በሉ
መላእክትም ሁሉ ምስጋናን ጀምሩ
ሥሉስ ቅዱስ በሉ
የሙሴ እህት ማርያም ከበሮውን እንሺ
በምስጋና መዝሙር እስራኤልን ጥሪው
አምላክን እናክብር እንዘምር በእልልታ
ከእኛ ጋር ይሆናል የሠራዊት ጌታ /2/
ፍጥረታትም ጨኸ ሰማያት ዘምሩ
ስለቅድስናው ሁላችሁ ዘምሩ
ዳዊት ሆይ ተነሣ ስልጽዮን ዘምር
ከበሮው ይመታ በገናው ይደርደር /2/
ወገኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር
ውለታው ብዙ ነው ለእኛ ያለው ፍቅር
ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በእልልታ
ለጌታ ለእግዚአብሔር ለሠራዊት ጌታ /2/

## 856.ስምህ በሁሉ ተመሰገነ

ስምህ በሁሉ ተመሰገነ
ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ
አንተን ማወደስ ያስደስተናል

ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል
አምላክ ተመስገን በሰማያት
ስምህ ይወደስ በፍጥረታት
ከሕፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ
አንተን ማመስገን ይሁን የእኛ እጣ/2/
በምግብ እጦት ብንሰቃይም
ማኅሌትህን አናቋርጥም
የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም
እንዘምራለን ለአምላካችን ስም/2/

ሰማዩ ዝናብ ደመና ቢያጣ
ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም
ቸርነትህን እንጠብቃለን
ከአንተ ደጅ ጌታ የት እንሄዳለን/2/

## 857.አንደበቴም ያወጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዓይኔ
በገባዖን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ
ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስትን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋር
በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ልዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ
አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣዖት እንድንሰግድ ነገሥታት ቢያውጁም
ሁሉ ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም
ጽናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኔዓለም

## 859.ወደ ቤተ እግዚአብሔር

ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ
ባሉኝ ጊዜ እኔን ደስ አለኝ/2/
የኃጢአት ሸክሜ ቀለለኝ/2/
እስቲ ላነሣሣው የዳዊትን መዝሙር
አምላኬን ላመስገን በደስታ በፍቅር
በልቤ እያሠብኩኝ ለኔ ያለውን ፍቅር/.2.
አዝ ------
የጥፋቱ ማዕበል ጎጆ መጠለያ
የጻድቁ የኖኅ የመርከብ አምሣያ
ቤተክርስቲያን ናት የእኛ መሸሸጊያ /2/
አዝ -----
ኃጢአት እሾህ ሆኖ ቁስሉ ሲወጋጋህ
ሞት ሲያንዣብብህ ሲጠወልግ ተስፋህ
ቤተክርስቲያን ሂድ መንገዷም አይጥፋህ /2/
አዝ -------------
የቅዱሳን ክብር የሚነገርባት
ድንግል ከነልጇ የምገትገኝባት
ይህች ቅድስት ስፍራ ቤተክርስቲያን ናት/2/
አዝ -------

## 860.እግዚአብሔር ሆይ

እግዚአብሔር ሆይ የሚረዳን የለምና
ከኛ አትራቅ ተስፋችን ነህና
አንተን አምነን ስንጠራህ አትለየን
አምላክ ሆይ ጠብቀን
አዝ --------
በአንተ ታምኛለው ዘላለም አልፈር
በጽድቅ ልመራ በፍቅር እንድኖር
ጆሮህን አዘንብልህ ፈጥነህ አድነኝ
መንገዴን አቅንተህ በሕይወት ምራኝ
አዝ -------
አምባና መጠጊያ መሸሸጊያ ሁነኝ
በድካሜ ጊዜ የለም የሚረዳኝ
የእውነት አምላክነህ አቤቱ ተቤዥን
ከአንተ በቀር ለእኛ ምንም ተስፋ የለን

አዝ----

የሕይወቴ ብርሃን መታመኛዬ ነህ
ዝም አትበለኝ አንተ አቤቱ ስጠራህ
በመከራዬ ቀን አቤቱ ሠውረኝ
በቃልህ እንድኖር በምሕረትህ ጎብኘኝ

አዝ -----

እንዳሸንፍ እርዳኝ የዓለምን ፈተና
ጠላቴ እንዲያፍር በእምነት እንድጸና
አንተ ተዋጋና እንዳልወድቅ እርዳኝ
ከጎኔ አትለየኝ ብርታትን ስጠኝ

አዝ -----

## 861.ብርሃን የለበሰው

ብርሃን የለበሰው በሰማያት ያለው/2/
እንደ እግዚአብሔር ከቶ ማንም የለም/2/

ውኆችን በእፍኙ የሠፈረ
ተራሮችን በሚዛን የመዘነ
ሰማይን በስንዝር የሚለካ
ዘመንን በዘመን የሚተካ/2/

አዝ -----

ከዓለም በፊት የነበረ
ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ
በምድር ክብብ የሚቀመጥ
ሁሉን ሲለውጥ የማይለወጥ /2/

አዝ ------

ዙፋኑ የጸና በሰማይ
ሁሉ የሚቻለው አዶናይ
ለመንግሥቱ ፍጻሜ የሌለው
አልፋና ዖሜጋ አምላክ ነው/2/

አዝ -------

ከሀሊ ኩሉ ሁሉንም የሚያውቅ
ፈታሄ በጽድቅ ሥራው ረቂቅ
ዓለምን የመላ ፈጥሮ የሚገዛ
መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ/2/

## 862.አሁንስ ተስፋዬ ማነው

አሁንስ ተስፋ ማነው/2/
እግዚአብሔር አይደለምን /2/

በአንደበቴ እንዳልስት መንገዴን ጠበቅህ
ለአፌ ጠባቂ እንዳለ አውቅሁ
ከኃጢአቴ ሁሉ አንተ አድነኝ
ለሰነፎች ስድብ ከቶ አታድርገኝ

የባሪያህን ጩኸት አቤቱ ስማኝ
የነጻ ልቦና አምላኬ ሆይ አድለኝ
በቃልህ ሰባብረው ድንጋዩን ልቤን
ሕግን እንድፈፅም ስጠኝ ፍቃድህን

ተስፋዬ ስለሆንክ ከማንም በላይ
ወደ እኔ ተመልከት አምላክ አዶናይ
ተስፋ ስላደረኩ አንተ አምላኬን
የልመናዬም ድምጽ ይሰማ አሁን

## 863.ሞት ነው ረሀብ

ሞት ነው ረሀብ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ /2/
ኃይሉ በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ጸጋው በእና ላይ አድሮ እንበረታለን

ከአንተ ርቀው ሸሽተው የሄዱ
ጠፋባቸው የጽድቅ መንገዱ
በሥጋዊ ጥበብ ሲፈልጉህ
በመታለል ስንቶቹ አንተን አጡህ

በተዋሕዶ የከበርከው ጌታ
መድኃኔዓለም ሁንልን መከታ
ስንደክም ምኞት ሲፈትነን
ኃይልን ሰጥተህ በእጆችህ ደግፈን
የዓለም ሰይፍ በእኛ ላይ ተሰሉአል
ሥጋችንን ሊቆርጠው አድብቷል
ኃይልን ስጠን እንድናሸንፈው
ጸጋህ ለእኛ የእምነት ጋሻችን ነው

ሐዋርያት ጸጋ በዝቶላቸው

ስለፍቅርህ ፈሰሰ ደማቸው
ዛሬም ለእኛ ጸጋህን አብዛልን
እንዳንደክም ፈተና ሲገጥመን
ጋሻ ሆነህ እንድትመክትልን
ቸር አምላክ ሆይ ወደ አንተ እንጮሃለን
ቢገጥመንም ችግር ወይ መከራ
አትለየን ጌታ ከእኛ ጋራ

### 864.ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሉያ በሰማያት ላለው
ዓለማትን ፈጥሮ ለሚገዛው
እንዘምራለሁ እቀኝለታለሁ
ጌትነቱን ክብሩን አደንቃለሁ
ገናና ነው ክብርን የተመላ
ድንቅ የሚያደርግ የለም ከእርሱ ሌላ
ጉልበት ሁሉ ለስሙ ይሰግዳል
ከአማልክት እርሱን ማን ይመስላል
ልብሱ ዘርፍ መቅደሱ ተሞልቶ
ስለክብሩ በገና ተቃኝቶ
ምስጋናችን በእጣኑ ጢስ ሲያርግ
ይመስጣል ያ የሰማዩን ሠርግ
ሲቀኝለት ዳዊት በማኅሌት
ቅዱስ ሲሉ ሱራፊል በኅብረት
ከዙፋኑ ምሕረት ይታወጃል
በምድራችን ሰላም ፍቅር ይሰፍናል
መሰወሪያው የእሳት ነበልባል ነው
ሠረገላው ነፋስ ደመና ነው
የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው
ለሚፈሩት ኃይልና ብርታት ነው

### 865.እንደአብርሃም እንሁን

እንደ አብርሃም እንሁን እንደሣራ/2/
እንግዳ እንቀበል በየተራ
የተራብ እናብላ እንደአብርሃም
የታረዘ እናልብስ እንደሣራ
ለሥጋ ሳናስብ እንደአብርሃም
እንጠቀም በነፍስ እንደሣራ
አዝ -------
የተጠሙ ይጠጡ እንደአብርሃም
ይብሉ የተራቡ እንደሣራ
እንደአብርሃም ቤት እንደአብርሃም
ሥላሴ እንዲገቡ እንደሣራ
አዝ --------
ይህችን አጭር ዘመን እንደአብርሃም
ካሁኑ ንቀን እንደሣራ
እንግዳ እንቀበል እንደአብርሃም
በድንካን ሆነን እንደሣራ
አዝ ---------
እንደ አባቶቻችን እንደአብርሃም
የዋሆች ሆነን እንደ ሣራ
እንግዳ እንቀበል እንደ አብርሃም
በማጠብ እግርን እንደ ሣራ

### 866.ኃይልን በሚሠጠኝ

ኃይልን በሚሠጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ/2/
ፈተና ቢገጠግመኝ ለበጎ ነው ብዬ አልፋለሁ/2/
በሠንሠለት አስረው በወኅኒ ቢጥሉኝ
መከራን አብዝተው እጅግ ቢያስጨንቁኝ
ለበጎ ነው ብዬ ተስፋ አድርጌሃለሁ
ይሁን አንተ ያልከው እገዛልሃለሁ
አዝ --------
ትናንትናም ዛሬም አንተ ያው አንተነህ
ፍቅርህ አይቀየር ወረትም የለብህ
ስምህን መጥራቴ ሞገስ ይሆነኛል
ጠላቴ ቢፎክር መቼ ያሸንፈኛል
አዝ ----------
በመከራው ብዛት ጉልበቴ ደከመ
ትካዜ ከብዶኛል ተስፋዬም ጨለመ
ነገር ቢሆን ባይሆን አንተን እንዳከብር

አድለኝ በጸጋ ጌታ የአንተን ፍቅር

አዝ ---------

ከሀገር ተጥቼ በዱር መሠደዴ

በባእዳን ሀገር ርቄ መሄዴ

ለበጎ ነውና መቼ ይከፋኛል

ፈጽሞ እንዳልጠፋ ፍቅርህ ይይዘኛል

አዝ ------

<u>867.ሰዎች እንዘምር</u>

ሰዎች እንዘምር ለአምላካችን

ከሞት ላወጣን ለአዳኛችን

እናመስግነው እንደአቅማችን

ምሕረት ለሠጠን ለሁላችን

አምላክ ተአምሩን የሠራብህ

ጬኸት ድምጽህን ለሰማልህ

በርጠሜዎስ ሆይ አትተወው

አዳኝ ጌታህን ተከተለው

እውርነቴን ላስቀረልኝ

ለዓይኔ ብርሃን የሠጠኝ

ሁሌም ከእርሱ ጋር እኖራለሁ

አዳኜን ትቼ የትእሄዳለሁ

አዝ ---------

በርጠሜዎስ ሆይ ታድለሃል

የመዳን ጸጋ ተሠጥቶሀል

እጹብ ድንቅ ነው የአምላክ ሥራ

እውር የሆነው ዓይንህ በራ

ይሄን ጌታዬን ምን ልበለው

ለውለታውስ ምን ልክፈለው

ስሙን ላወድስ ላመስግነው

ለአምላክ ክፍያ ይህ ብቻ ነው

አዝ -------

12 ዓመት ደም ሲፈስሽ

ሰዎች ሲንቁሽ ሲያንቋሽሹሽ

ማን ፈወሠሽ አንቺ ሴት

ያበቃሽ ማነው ለደኅነት

እምነትሽ አዳነሽ አለኝና

ኃይል ከእርሱ ወጣ የሚያጽናና

የጌታ ልብሱን ብዳብሰው

ደሜ ቀጥ አለ ላወድሰው

በቤተ ሳይዳ በአልጋ ስትኖር

በመጠመቂያው በወንዙ ዳር

ደውይ ስትሆን በሽተኛ

እንዴት ተፈወስክ አውጋን ለእኛ

አልጋ ታቅፌ ስንገላታ

መዳን ትሻለህ አለኝ ጌታ

አምላኬ እርሱ ፈወሰኝ

አልጋህን ይዘህ ሂድ አለኝ

<u>898.እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ</u>

እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ ቸርነት አድርገህ/2/

እድሜ ለንስሓ እንደ ሕዝቅያስ ሠጥተህ

ጠማማውን ልቤን በቃልህ አቃንተህ

አላውቀውም ብሎ ሲጠይቅ ያመፀው

ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሦስት ጊዜ የካደው

የጅረት ወንዝ ነው የሰጠሽው አንባ

ጴጥሮስ ተጸጽቶ ንስሓ እንዲገባ

ጽዋው እንዳይደርስኝ የይሁዳ እድል

ልጆች ሆኖ ውሎ ኃላ መኮብለል

ጴጥሮስ እድለኛ አልቅሶ ተማረ

በትዕቢቱ ይሁዳ እንዲወጣ ቀረ

ዘመኗን በሙሉ በዝሙት አቃጥላ

በንስሓ ጠራት ጌታ በገሊላ

ታድሳ ተነሣች በእንባዋ ብዛት

እግሩ ስር ተደፍታ ማርያም እንተ እፍረት

አመፀኛው ልቤ ዛሬስ መቼ ይተኛል

በኃጢአት በዝሙት በሥርቆት ይዋኛል

ወደ ቀድሞ ግብሩ እንዳይመለስ

ፍቅርህ በእኔ ሰርፆ ኃጢአቴን ደምስስ

በደላችን ሁሉ ስታስብ ትተህ
በምጽዓትህ ሰዓት ከጻድቃን ቆጥረህ
ነጭ ልብስ ለብሰን ሆነን ከአንተ ጋራ
በሩ ሳይዘጋ አስገባን አደራ

869.አትተወኝ አትጣለኝ

አትተወኝ አትጣለኝ/4/
ወድቄአለሁና ጌታ ሆይ አንሣኝ/2/
ቸሩ መድኃኒቴ የአልዓዛር ቤት
እራት
የኑሮዬ ጣዕም የሕይወቴ
መብራት
በኃጢአት ጭቃ ላይ
ወድቄአለሁና
ጌዬ ሆይ አንሣኝ እጅህን
ዘርጋና/2/
የሰጠኸኝ ክብር ይልጅነት ሥልጣን
እንደ ሶምሶን ዝሙት ከደሊላ ጋራ
አርቃኔን ቀረሁኝ ተላልፌ ሕግህን
አምላኬ ዘርጋልኝ የምሕረት እጅህን/2/
ዘወትር እየበደልኩ ከሕግህ ርቄ
በኃጢአት ጭቃ ላይ ክፉኛ ወድቄ
በበደል እሥራት ተይዣለሁና
አባቴ ሆይ ማረኝ መሐሪ ነህና/2/

870.ስለይማይነገር ስጦታው

ስላማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላላን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን
ስለማይነገረው ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ሕያው
እንድንሆን
ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር
ይመስገን ስለማይነገር ስጦታው
እግዚአብሔር ይመስገን
ንፋሱን ገስፆ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር
የዓለም ፈተና ሲበዛ እርሱ መጠጊያችን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ዳግሞ እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሣኤ ሰላምን ለሰጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ከሲዖል እሥራት ተፈተን ነጻ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

871.ቸርነትህ ብዙ

ቸርነትህ ብዙ ምሕረትህ ብዙ
በጉዞአችን ርዳን ጠባብ ነው መንገዱ
ድንቅ ነው አምላክ ሆይ ፍቅርህ
ለኛ ድንቅ ነው ለኛ
አንተ ነህ መልካም እረኛ
እስራኤል ወደቀ እስራኤል ተነሣ/2/
መንገድ አልቀናውም አምላኩን ቢረሣ/2/
የያዕቆብን አምላክ እግዚአብሔርን ይዞ/2/
ምን እንዳተረፈ አውቆታል በጎዞ /2/
አዝ --------
መንገዱ አይታክትም ጎዳናው የቀና /2/
እግዚአብሔር ከፊትም ከኋላም አለና /2/
እርሱ የሌለበት ቢመችም መንገዱ/2/
አቅጣጫው ወደ ሞት አይቀርም መውሰዱ/2/
አዝ -------
በመንገድ ዝለን ወድቀን መቼ ቀርተናል/2/
የያዕቆብ አምላክ ደግፎ አንስቶናል/2/
እግዚአብሔር ሲጠራን በቀደመው መንገድ/2/
ጉዞአችን ወዴት ነው በሞት ለመወሰድ/2/
አዝ ---------
አምላክ ሆይ ፍቅርህን በልባችን ሣለው /2/
እስከ ሞት በመስቀል የወደደን ማነው/2/
በበረሃው ጽናት ቢጸናብን ረሀቡ/2/
በረከት ሞላኸን ተረፈልን ምግቡ /2/
አዝ --------

## 872.ንዓ ንዓ አማኑኤል

ንዓ ንዓ አማኑኤል
ንዓ ንዓ መድኃኔዓለም
በፍሥሐ ወበሰላም
ና ወደኛ መድኃኔዓለም/2/
ቅዱስ ጌታ አማኑኤል
ቸር አምላክ መድኃኔዓለም
ለእኛ ብለህ አማኑኤል
ተሠቀልክ መድኃኔዓለም
ልትባርከን አማኑኤል
ና በሰርክ መድኃኔዓለም /2/
አዝ ------
ሥጋህና አማኑኤል
ደምህን መድኃኔዓለም
ብሉ ብለህ አማኑኤል
ሠጠኸን መድኃኔዓለም
ሕይወትህ ሆኖ አማኑኤል
አዳነን መድኃኔዓለም /2/
አዝ -----
በኃጢአት ሞት አማኑኤል
ወድቀን ሣለ መድኃኔዓለም
ከጥንት ሀገር አማኑኤል
ኑ አልከን መድኃኔዓለም
ምንስ እንበል አማኑኤል
ምን እናውራ መድኃኔዓለም
ግሩም ብቻ አማኑኤል
ያንተ ስራ መድኃኔዓለም/2/
አዝ -------

## 873.ኦ አንትሙ

ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን በከመ ተጋብእክሙ በዛቲ እለት /2/
ከማሁ ያስተጋባእክሙ በደብረ ጽዮን ቅድስት ወበኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም እጋእዚት/2/

ትርጉም፡- እናንተ የክርስቲያን ወገኖች ሆይ በዚህ ቀን እንደተሠበሠባችሁ ነጻ በምታወጣ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ይሰብስባችሁ

## 874.እንዘ ይብሉ

እንዘ ይብሉ ይዜምሩ በልሳን ዘኢያረምም/2/
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም/2/

## 875.እምኩሉ

እምኩሉ ይኄይስ በሥላሴከ ተአምኑ/2/
ወላዲትከ/2/ ወልድ ወላዲትከ ተማኅጸኑ /2/
ከሁሉ ከሁሉ ሥላሴን ነው ማመን ማመስገን /2/
ወልድን በወለደች/2/ ድንግል አማላጃችን በእርሷ እንማጸን/2/

## 876.ስብሐት ለሥላሴ

ስብሐት ለሥላሴ ለፈጣሬ ኩሉ ዓለም/2/
በመላእክቲሁ ስቡሕ ዘለዓለም/2/
በመላእክቲሁ እኩት ዘለዓለም/2/
ምስጋና ለሥላሴ ለዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ/2/
በመላእክቱ ነውና ሲመሰገን ኗሪ/4/

## 877.ስብሐት ለአምላክነ

ስብሐት ለአምላክነ ወመድኃኒነ/2/
ዘአድኀነኮ ኀሊናነ/4/

## 878.ለጌታዬ

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን እከፍለዋለው /2
ምስጋና ነው እንጂ /2/ ሌላ ምን እላለው/4/
ለመቤቴ ለድንግል ማርያም ስለውለታዋ ምን እከፍላታለሁ/2/
ላመስግናት እንጂ ሌላ ምን እላለው/4/

## 879.ሰለመ ሀበነ

ሰለመ ሀበነ /2/
አምላክነ/3/ ሰላመ ሀበነ/2/
ሰላምን ሥጠን /4/
አምላካችን /3/ ሰላም ሥጠን/2/

## 880.ሮላዌ

ኖላዊ ትጉኅ ዘኢትነውም /2/

ማኅበረነ /2/ እቀብ በሰላም /4/

881.ያከብረዋ

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት

በሰማያት ጻድቃን በውስተ ገነት/2

ወኲሉ ፍጥረት ዓሳት ወአናብርት/2/

እለውስተ ደይን ያእረፉ ባቲ

እስመ ባቲ አእረፈ እምኲሉ ግብሩ /2/

ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት /2/

ጻድቃን በገነት

ፍጥረታት በሙሉ አሳዎችና አንበሬዎች

በመቃብር ያሉ ያከብሯታል አምላክ /2/

በእርሷ እንዳረፈ ከሥራው ሁሉ

882.ሀበነ

ሀበነ እግዚኦ አዕምሮ አእይንተ አዕምሮ

ወትረ ኪያከ ይርአይ/2/

ወአእዛንነኒ ቃለ ዘባሕቲትከ ይስምዕ/2/

883.እንዘ ኢየምር

እንዘ የአምር እምቅድመ ኅሊና ዘይሄሊ ልበ

የአምር የአምር/2/

አርዓየ ኃይሎ በላዕሌነ ወጸገወነ ኸ

ሠናይቶ እግዚአብሔር/2/

884.ያልጠፋነው

ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው/2/

ምሕረቱ ከቶ አያልቅምና ርኅራኄው ከቶ

አያልቅምና ይገባዋል ክብርና ምስጋና/2/

885.ዘሰማይ ገብረ

ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድረ ሳረረ/2/

አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ/4/

ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና/2/

ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለአንተ ማን አለና /2/

886.አንሰ ወቤትየ

አንሰ ወቤትየ እግዚአብሔርሃ ናመልክ/2/

እስመ ቅዱስ ውእቱ እግዚአብሔር/4/

እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን/2/

እርሱ ቅዱስ ነውና እግዚአብሔር/2/

887.ሊተሰ

ሊተሰ ይኄይሰኒ ተሊወ እግዚአብሔር /2/

ወትውክልትየኒ/4/ ላዕለ እግዚአብሔር

ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል /2/

መታመኛዬ ነው/4/ እግዚአብሔር እርሱ ነው/2/

888.የአብ ጸጋ

የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስቅዱስ አንድነት/2/

ጸጋ በረከት ይደር በሁላችን ሕይወት /2/

889.አንቺ የወይን ሐረግ

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልማላሜሽ የበዛ

ምግብ ሆኖ ተሰጠን ፍሬሽ ለእኛ ቤዛ

በአንቺ ሰማይነት ድንግል የወጣው ፀሐይ

ብርሃን ነው(2) ለጻድቃን ስሙም አዶናይ

ፊደል ትመሥያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጂያለሽ

ለመላእክት የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ

የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኮከብ መገኛ

በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለእኛ

890.የአምላክ እናት

የአምላክ እናት ነይልን እኛ ልጆችሽን ባርኪን

ከአንዱ ልጅሽ(2) ፈጥነሽ አማልጅን(2

ስምሽን ሲጠሩ በሽተኞች ሁሉ

በአንቺ አማልጅነት ፈውስን ያገኛሉ(2)

በኃጢአት በሽታ ታምሞ የሚሰቃየው

የአዳም ዘር ተስፋው በአንቺ እኮ ነው(2)

ከሀዲው ቢበዛ አንቺን ቢረሳሽ

አንቺ አዛኝ ነሽ ጥላቻ የለስ (2)
ለጻድቃን አይደል ለኃጥአን ታለቅሻለሽ
በአማልጅነትሽ ዘውትር ታስቢለያሽ (2)

## 891.እንድናለን

እንድናለን እኛስ እንድናለን
እንድናለን ድንግል አንቺን ይዘን
እንድናለን በፍጹም ቸርነት እንድናለን
ስለወደደን እንድናለን
እንድንጠፋበት
ድንግልን ሠጠን
የልባችን ደስታ እንድናለን
እኛስ አግኝተናል
በአማልጅነቷ እንድናለን
ፈጣሪ ምሮናል እንድናለን
ምርኩዝ አንቺን ይዘን እድንናለን
ስንቃችን ሠንቀን
በድንግል መሪነት
ጽድቅን እንወርሳለን
የምታማልደን እንድናለን
ድንግልን ሠቶናል
የእሳቱን ባሕር
በእርሷ ተሻግረናል
የልባችን ደስታ እንድናለን
እኛስ አግኝተናል
በአማለጅነቷ
ፈጣሪ ምሮናል
መታወቂያችንን እንድናለን
እኛስ አግኝተናል
በተጠየቅን ጊዜ
የእርስዋ ነን ብለናል

## 892.ሰአሊ ለነ ቅድስት

ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን
እንደ ኤፍሬም እንደ አባታችን
ለምኚልን እመቤታችን
ተስፋቸው አንቺ ነሽ ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከ ዘለዓለም
ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው
በአንቺ ጸሎት ዳነች ሕይወታቸው
ስምሽን ሥልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃል ኪዳን ገባልሽ ዓለሙን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ
ዓለም ሥትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትደክም ሲከብዳት ኃጢአት
መንገድ ጠፍቶን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን
የልባችን ሐዘን እጅግ ከብዶብናል
ኃጢአታችን በዝቶ መቆም ተስኖናል
እንደ ኤልሳቤጥ እንደ ዘመድሽ
ደስ አሰኚን ይሰማ ድምጽሽ

## 893.ማርያምስ ተሀቱ

ማርያምሰ ተሀቱ እምትካት ውስተ ከርሱ/2
ለአዳም ከመባሕርይ ጸዓዳ
እስመ በእንቲአሃ ወበእንተ አዝማዲሃ
ተሰቀልኩ ዲበ ዕጽ ይቤ መድኃኔዓለም /2

ትርጉም

ማርያምማ ታበራለች ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ በአዳም ባሕርይ እርሷን ደስ ይበላት ብሎ ስለወገኖቿ ተሰቀልኩ አለ በእንጨት መስቀል ላይ መድኃኒዓለም

## 894.ዛሬም አለችኝ መማጸኛ

ዛሬም አለችኝ መማጸኛ /2/
አምላክ የሠጠን ለእኛ መዳኛ /2/
አዝ ---------
ዓለም የዳነባት ዛሬም አለችኝ መማጸኛ
የብርሀን እናት
ድንግል ተስፋችን ናት

የምንመካባት
በሷም ተማጽነን የምንድንባት
አዝ -------
የነዳያን ተስፋ ዛሬም አለችኝ መማፀኛ
ጸጋ ገንዘባችን
መጽናኛ የምትሆኝን
አንቺ ነሽ ኃይላቸው
ስምሽን ሲጠሩ
የምትደርሺላቸው
አዝ -------------
የማትፈርሺ መቅደስ ዛሬም አለችኝ መማፀኛ
የጸሎት ቤታችን >> >>
የእኛ መሸሸጊያ >> >>
ምርኩዝ ድጋፋችን >> >>
የማትተወን እኛን >> >>
እመቤት አለችኝ >> >>

## 895. እመአምላክ ሙሽራ ነሽ

እመአምላክ ሙሽራ ነሽ
ለቃል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ
ኸኸ/3/
12 ዓመት ቤተ መቅደስ የኖርሽ
የመመረጥ ጸጋ ከጌታ ያገኘሽ
አዝ ------
በአብሣሪው መልአክ ዕጹብ ድንቅ ዜና
ከሰማይ መጣልሽ አቋርጦ ደመና
በ6ኛው ወር ተልኮ ገብርኤል
ቤተመቅደስ ገባ ሊያበስራት ለድንግል
አዝ ---
በልዩ ሰላምታ ሰላም ለኪ አለሽ
የክርስቶስ እናት በጣም ደስ ይበልሽ
መላእክት በሰማይ ያመሰግኑሻል
ክብር ለአምላክ እናት ይድረሳት ይሉሻል
አዝ ----------
በማሕፀንሽ ቢያድር የሠራዊት ጌታ
ለመሆን ተመረጥሽ የአምላክ ቅድስት ቦታ
የፈጣሪ እናት መሆንሽን ተረድቶ
ሰላም ላንቺ ይሁን አለሽ እጅ ነሥቶ
አዝ -------

## 896. እንተ በምድር

እንተ በምድር ሥረዊሀ ወበሰማይ አዕፁቂሃ /2
ሐገረ ወይን /2/ ድንግል ሐረገ ወይን /2/
ትርጉም፡-
ደንግል ማርያም መሠረቶቿዋ በምድር ቅርንጫፎቿ
በሰማይ የሆነች ሐረግ ናት

## 897.ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መቼ እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ለአንቺ ምስጋና
ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር
ለዘመናትም ስጨነቅ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲሠቃየኝ
የዓለምን መድኅን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
በአሕዛብ ሀገር ስኖር ሸሽቼ
ደረሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰው ታድሞ
አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሠብኩት ሐሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተንኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀር
በእመአምላክ እኔ መቼም አላፍር
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ

ይህች ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋልሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ
መከራ አብዝቶ በያሰቃየኝ
አላቋርጥም የአንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
ክፉዎች ድርሰው ቢዝቱብኝ
መከራ አብዝተው ቢያሠቃዩኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ በያሠቃየኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም የአንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና

## 898.ዮም ፍሥሐ ኮነ

ዮም ፍሥሐ ኮነ (2)
በእንተ ልደታ ለማርያም /2/
በባርነት ሳለን ፍሥሐ ኮነ
ኃጢአት በዓለም ነግሶ
በድንግል መወለድ
ቀረልን አበሳ
እግዚአብሔር መረጠሽ ልትሆኚ እናቱ
ይኸው ተፈጸመ
የዳዊት ትንቢቱ
የሔዋን ተስፋዋ
የአዳም ሕይወት
የኢያቂም የሐና
ፍሬ በረከት
ምክንያተ ድኅነት
ኪዳነ ምህረት
ድንግል ተወለደች
የአምላክ እናት
በሔዋን ምክንያት ፍሥሐ ኮነ
ያጣነውን ሰላም >> >>
ዛሬ አገኘነው >> >>
በድንግል ማርያም >> >>
የምሥራች እንበል >> >>
ሐዘናችን ይጥፋ >> >>
ተወልዳለችና >> >>
የዓለም ሁሉ ተስፋ >> >>

## 899. ወእንዚ ትፈትል

ወእንዚ ትፈትል /2/ ወርቅ ወሜላተ ገብርኤል ግብተ/2/
ወይቤላ /2/ እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር

## 900.የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው

የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው የዳኑብሽ
የበላኤ ሰብእ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝት ማርያም ቅድስት /2/
አዝ ----------
በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽ ጽድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል/2/
አዝ -----
የእሳት ባሕር በንቺ ተሻግረዋል
ለሰማያዊው ክብር በቅተዋል/2/
አዝ -------
ነፍሳቸውም ጽድቅን አግኝታለች
ሕይወታቸውም በአንቺ ትድናለች
ድንግል ሆይ አትጣይኝ ትላለች/2/
አዝ ----------
እኔም በአንቺ እታመናለሁ
የአምላክ እናት አሳስቢኝ እላለሁ
በአማላጅነትሽ እድናለሁ/2/
አዝ -----------
እኛም በአንቺ እንታመናለን
የአምላክ አሳስቢ እንላለን

በአማላጅነትሽ እንድናለን;2/
አዝ -----------
ምእመናንም በአንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢ ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናሉ/2/
አዝ ------------

901 <u>አንቲ ዘበአማን</u>

አንቲ ዘበአማን /2/ ረከብኪ ጸጋ ክብረ ድንግል /2/
የዐቢ ክብራ ለማርያም
በይ እንግዲ ድንግል ዘበአማን ከእኛ አትሸሺ
ዘበአማን
የክርስቲያኑን ልብ ዘበአማን ትኅትናን አልብሺ
ያሬድ ጸናጽል ዘበአማን
የዘወትር ቅዳሴ -
የአባሕርያቆስ ዘበአማን
የዘወትር ቅሳሴ --
ርኅርኂተ ኅሊና ዘበአማን
የሐዋርያ ሞገስ ---
የመላእክት እህት ዘበአማን
ማኅደረ ሥሉስ
ሥሉስ ቅዱስ ተብሎ ዘበአማን
የሚመሰገነው -
የፍጥረታት ገዥ ዘበአማን
የአንቺ ልጅ እኮ ነው -
የምታምሪ ርግብ ዘበአማን
ሰላምን ያስገኘሽ ዘበአማን
ንጽሕናሽን አይቶ ዘበአማን
ወልድ መረጠሽ
አትርሺኝ ድንግል ሆይ ዘበአማን
እኛ ልጆችሽን
ከአምላክ አስታሪቂን ዘበአማን
እኛ ደካሞችን
ስለ በደላን ዘበአማን
ችላ ሳትይን ዘበአማን
ምሕረት አሠጪን ዘበአማን
ድንግል አትርሺን
የመመኪያችን ዘውድ ዘበአማን
እመብርሃን
ከልጅሽ አስታሪቂኝ ዘበአማን
እንዳንቀር ወድቀን

902. <u>በክብር ዙፋኑ</u>

በክቡር ዙፋኑ መርጦ ያስቀመጠሽ
ለእኛ ለኃጢአተኞች ተስፋችን አንቺ ነሽ
በፍጹም ትኅትና ቤተመቅደስ ያደግሽ
የአማኑኤል የጌታዬ የፈጣሪዬ እናት በምን እንመስልሽ
አዝ --------
ቃና ዘገሊላ ሠርግ ደግሠው
አንቺን ከነልጅሽ በክብር ጠርተው
ሰዎች ተረብሸው በጣም ተደናግጠው
ወይኑ በማለቁ በፍርሃት ተውጠው
አዝ ------
ወይኑ በመሀል ላይ ማለቁን ሰምተሽ
ድንጋጤአቸውን እምቤቴ አይተሽ
ወደ ልጅሽ ሄድሽ ብጠይቂላቸው
ጋኑን ውኃ ሙሉ ብሎ አዘዛቸው
አዝ ----------
የሚላችሁን አድርጉ ብለሽ
ሰዎቹን ከሀፍረት ከጭንቀት ፈታሽ
ድንግል እመቤቴ ቤዛዊተ ዓለም
በመከራ ደራሽ እንደአንቺ የለም
አዝ --------
ውኃውን ወደ ወይን አጣፍጦ ቀይሮ
የዶኪማስንም እፍረቱን ሠውሮ
እድምተኞች ሁሉ እስከሚደነቁ
አምላክ ከእነርሡ ጋር መሆኑን አወቁ
አዝ --------

903.ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ (2) ማርያም ሰላም ለኪ

ሰላም ለዝክርኪ ማርያም ለኪዳንኪ

ሰላም ለአንቺ ይሁን የኤልሣቤጥ ሰስታ ሰ.ለኪ

አምላክ የመረጠሽ ሰላም የፍጥረት አለኝታ ሰ.ለኪ

የልባችን ደስታ የተገለጸልሽ ሰ.ለኪ

የአማኑኤል እናት ምስጋና ይድረስሽ ሰ.ለኪ

ንጽሕተ ንጹሐን እንከን የሌለብሽ ሰላም ለኪ

መዓዛሽ ያማረ ጸጋን የተሞላሽ

ልቤ ተደሰተ ዜናሽን ሲሰማ ሰላም ለኪ

እኅቴ ሙሽራዬ የዳዊት ከተማ

ስምሽን ለልጅ ልጅ

እስቲ እኔ ልናገር

ሰ.ለኪ

ከአንቺ ያገኘሁት

አለ ብዙ ነገር

ሰ.ለኪ

ሰላም ለኪ ድንግል

እሰግድልሻለሁ

ሰ.ለኪ

የአንቺን ቅድስና

ለዓለም እነግራለሁ

ሰ.ለኪ

904.ድንግል ማርያም

የእኛ አማላጅ

ድንግል ማርያም የእኛ አማላጅ/2/

ከአብርሃም ዘር የተመረጠች

በድንግልና ጌታን ወለደች

መሰበ ወርቅ የመና ሙዳይ

ቤቴልሔም ሆይ እሙ ለፀሐይ

የካህናቱ ወርቅ ማዕጠንት

ይጣን መያዣ ነሽ ልዩ ፍጥረት

የመለኮት አትሮኖስ የከሩብ ተራራ

የወርቅ መቅረዝ የአሚናዳብ ሰረገላ

ንጹሕ የሠርግ ቤት የአብርሃም ድንኳን

የአምላክ ማደርያ ታቦተ ጽዮን

የአቤል የዋኅት የሴም ቸርነት

የዮሴፍ አጽናኝ ርግብ የዋህት

የአቤል ፀናፅል የጌድዮን ፀምር

የሠሎሞን ጥበብ የዳዊት መዘሙር

905.ተወልዳለችና

ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መደኃኒት

እናወድሳት እናመስግናት እንወደዳት/2/

የአዳምን ሕይወት /4/ ሽሽ

አዳም ሲሠደድ ከጥንት ርስቱ

ፊቱን ሸፈነው ጭንቀት ፍርሀቱ

እያለቀሰ ገነትን ሲያጣ

ተስፋ አንቺ ሆነሽው የመዳን እጣ /2/

ሊባኖስ ተራራ ተሠማ ዜና

ምሥራቅ ወለዱ ኢያቂም ወሐና

ዳግማዊት ሔዋን ምክንያተ ድኅነት

ልደታን ሰማን በቅድስት እለት

የልደትሽ ቀን ልደታችን ነው

በአንቺ ነውና ልጅ የተባልነው

ፋራን የተባልሽ ቅድስት ተራራ

በአንቺ መወለድ ዓለሙ በራ

906.ትውልድ ሁሉ

ትውልድ ሁሉ የሚማጸኑሽ

በመላእክት የተመሠገንሽ

ክብር አክሊሌ ሰላም ልበልሽ

ትውልድ ሁሉ ዓለም ሣይፈጠር

ትውልድ ሁሉ በለምጽ የነደደው

ይቀደስ ከንፈሬ

እንደ አባ ጊዮርጊስ

ላምስግንሽ ክብሬ

ዓይኖቼ ይታገሉ

ለውዳሴሽ ቀለም
የክርስቶስ እናት
የመድኃኔዓለም
ትውልድ ሁሉ አንቺን ለመዘከር
ይትጋ ኅሊናዬ
በውዳሴሽ ቅኔ
ይሙላ ልቡናዬ
ልቀበል በረከት
ስምሽን ጠርቼ
አንቺ ባለሽበት
ይቁሙ እግሮቼ

**907.አንቀፀ በርሃን**

አንቀፀ ብርሃን ድንግል ማርያም
ሰማያዊ ዙፋን የመድኃኔዓለም/2/
ሰማይና ምድር የማይችሉትን
ኸረ እንደምን ቻልሽው ፍህም መለኮትን/2/
የእሳት መጋረጃ ወዴት ተጋረደ
ልዑል በጥበቡ ካንቺ ተዋሐደ/2/
የኪሩቤል አምሳል እመብርሃን ናት
ሰማያዊ ንጉሥ የከተመባት
የመለኮት ዙፋን ድንግል በመሆን
ሚካኤል ገብርኤል ሰግደው ዘመሩልሽ
ሩፋኤል ራጉኤል ሰግደው ዘመሩልሽ

**908.ልዩ ክብር**

ልዩ ክብር የተሰጠሽ ንጽሕት ወቡርክት
የነብያት ሀገራቸው እህተ መላእክት
እናመስግናት /2/ እናወድሳት
ከሴቶች ሁሉ ደንግል ልዩ ናት
እናመስግናት ክብሯ የበዛ ነው
ፍጹም ነው ኪዳኗ
ለምና ታሰታርቀን
ርኅርኂተ ኅሊና
የክፉ ቀን ደራሽ
መሸሸጊያ ታዛ
የሰላም ሠገነት
የነፍሳችን ቤዛ
እናመሥግናት የተስፋ ፀሐይ ናት
>> >> ሽልማቴ ዘውዴ
>> >> የዓይኔ ብርሃን
>> >> አጽናኝ ናት ዘመዴ
>> >> የርግብ ምልክት
>> >> የአዲስ ዘመን ብሥራት
>> >> የድኅነት ዓርማ
>> >> ትንቢተ ነቢያት
እናመስግናት የአዳም በረከት
>> >> የዘለዓለም ቤቱ
>> >> የሐዘኑ መርሻ
>> >> ማረፊያ ርስቱ
ይገባታልና
ወዳሴና ክብር
ሆና ተገኝታለች
ሀገረ እግዚአብሔር
እናመሥግናት የልዑል ዘፋኑ
መንበረ ጸባኦት
የኪሩቤል ሞገስ
መንፈሳዊ ታቦት
በልዩ ዝማሬ
እንደ መላእክት
ስሟን እናወድስ
እንበላት ቅድስት

**908.እመብርሃን መመኪያአችን**

እምብርሃን መመኪያችን/2/
የአዳም ተስፋው አለኝታችን
እመብርሃን መመኪያችን
እመብርሃን የአባቶቻችን
ቃና ለዛቸው

በችግር ጊዜ
መንገድ መሪያቸው
ምን ብዬ ልጥራሽ
ላወድስሽ
የምግባር ደሀ
ባዶ ልጆሽ
እመብርሃን የቅዱሳኑ
ጣዕመ ዜማቸው
አንቺ ነሽና
ውብ ደርስታቸው
የእኛ ሥጦታ
የድል አክሊል ነሽ
በአማልጅነት
ለታመነብሽ
እምብርሃን የይስሐቅ መዓዛ
በፍኖተ ሎዛ
የያዕቆብ መሰላል
የአቤል የዋኅት
የሴት ቸርነት
የኢያሱ ሐውልት
የሕይወት ውኃ
የሳሙኤል ዘይት
ርግብ ሠናይት
ንግሥተ ሰማይ
እመብርሃን መልካሟ ርግብ
የኖሕ መልክቱ
የኀጥአን ተስፋ
የልብ ብርታቱ
ምሥራቻችን
ውስጣችን ያለሽ
በምድር በሰማይ
አምሳያም የለሽ

909.ቃልን ለመውለድ

ቃልን ለመውለድ ከአብ ዘንድ ሞገስን ያገኘሽ /2/
የሐና ልጅ ነሽ የኢያቄም እጹብ ድንቅ ነሽ /4/
እሾህ ኩርንችት ሆነ ኑሮዬ
የልጅሽ ፍጥረት ተጎሣቁዬ
ሞገድ ማዕበል እንዳይውጠኝ
ሰላላ ክንዴን ደግፊልኝ
ቆሜ ልሳለም በስዕልሽ ፊት
ፍቅር ትኅትናን እንድማርበት
ላደግድና ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት ልሁን ባርያሽ
የዳዊት ልጅ ሆይ ቁሚ ከጎኔ
ወደ መስቀሉ ይመልከት ዓይኔ
የሌዊ ልጅ ሆይ አይዞህ በይኝ
የሥጋ ድካም እዳይጎደኝ

910.እመብርሃን

ትምክህቴ መድኃኒቴ አንቺው ነሽ /2
እመብርሃን /4/ ምርኩዛችን
ሽክም የከበደኝ ደካም ነኝ እኔ
ረዳትም የለኝ ከአንቺ በቀር ለእኔ
እመአምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ
እመብርሃን (4) ምርኩዛችን
የኃጢአትን ቋጥኝ በጅርባዬ አዝዬ
እቀበዛበዛለሁ ተገፎ ጸጋዬ
በአንቺ እማጸናለሁ ነፍሴን በእጅሽ ጥዬ
ምርኩዝ መሠላሌ ጥላ ከለላዬ
እመብርሃን (4) ምርኩዛችን
ልዩነሽ እናቴ ማርያም ድንግል
ማን አዛኝ እንደአንቺ ግራ ቀኝ ቢባል
በአንቺ ላይ አረፉ ልቤ ተረጋጋ
የሕይወቴ ተስፋ በአንቺ ተዘረጋ
እምብሃን (4) ምርኩዛችን
ፍጽሞ አርቂልኝ የእኔን ክፉ ሽታ
በሽቱሽ መዓዛ አድይኝ እርካታ

የኪሩቤል እክናፍ የነፍሴ ዋስትና
ነይ ነይ እመቤቴ መርኩዛችን
እምብርሃን (4) ምርኩዛችን
ከፍቅርሽ ምስጋና ዝም እንዳልል ድንግል
አንደቤቴን ፍቺው ኅሊናዬም ይቁሥል
የፍቅርሽ ማእበል ይፍሰስ በሕይወቴ
በእቅፍሽ ድርጊኝ እንደልጅነቴ
እመብርሃን /4/ ምርኩዛቸን

## 911.<u>ኀሥዓ ልብየ</u>

ኀሥዓ ልብየ ቃለ ሠናየ /2/
ወአነ አይድእ ቅዳሴሃ ለማርያም /4/
እኔስ የማርያምን ውዳሴዋን እናገራለሁ
እንደ አባቴ ዳዊት በበገና እዘምራለሁ
ቀን ከሌሊት ሳልል ለምስጋና እተጋለሁ
ምርኩዜ ነሽና እመቤቴ በአንቺ እመካለሁ
ኦ እመቤቴ በእውነት እንወድሻለን
የእውነተኛ መብልን ክርስቶስን ወለደሽልን
ምክንያተ ድኂን ሆይ ድንግል ማርያም የአምላክ
መገኛ
በአማላጅነትሽ በመታመን እንጮሃለን እኛ
ምሕረትን አድይን ኪዳነምሕረት የዓለም መዳኛ
ስለቸርነትሽ እመቤቴ ለእኔ እናቴ ነሽ
ስለ ንግሥትነትሽም እምቤቴ ነሽ
ዝናባት ሳያጠጡት አየራትም ሳያሳድጉት
ሰማያዊ እንጀራ የሰጠሽን ቤተልሔማዊት
ቃና ዘገሊላ በሠርግ ቤት በዚያ ተገኝተሽ ሳለሽ
ውኃውን ወደ ወይን በአንቺ ምልጃ እንዳስለወጥሽ
ዛሬም የእኔ ሕይወት ወይኑ አልቆ ባዶ ሆኗልና
አንቺ የአምላክ እናት ንጽሕት ቅድስት ርኅርኂተ
ኅሊና
ሕይወቴን ቀድሰሽ እመቤቴ ሙይው በምስጋና

## 912. <u>የሐና ልጅ ነሽ</u>

የሐና ልጅ ነሽ የኢያቄም በረከት /2/
ድንግል /2/ ወላዲተ ቃል
የሐና ልጅ ነሽ የፀሐይ እናቱ
ድንግል የምሥራቅ ደጅ
ቅድስተ ቅዱሳን
የፍጥረት አማላጅ
ለእናቷ አንዲት ናት
ለወለደቻት
የእግዚአብሔር ሥጦታ
ምሳሌ ያላት
የሐና ልጅ ነሽ የጾም ጸሎት ፍሬ
የቅድስና ሀብት
ከአምላክ የተሠጠች
ንጽሕት እመቤት
ደመና በመሆን
ሕዝብን የጋረዳች
የኢያቄም በረከት
እመቤታችን ነች
የሐና ልጅ ነሽ በሊባኖስ አድባር
ዛሬ ደስታ ሆነ
መከላእክት ዘመሩ
እርቅም ተወጠነ
እኛም ደስ ይበለን
መዳናችን ቀርቧል
ከሐና ከኢያቄም
ንጹሕ ዘር ተገኝቷል
የሐና ልጅ ነሽ የሰላም ብሥራት ነሽ
የፍጥረታት ተስፋ
በአንቺ ቅድስና
ሐዘናችን ጠፋ
ምክንያት አንቺ ሆነሽን
ዓለም ሁሉ ዳነ
እግዚአብሔር ታረቀን
ሁሉ ባንቺ ሆነ

## 913. ማርያም ድንግል ምክሆን

ማርያም ድንግል ምክሆን ለደናግል
ይእቲኪ በቱ ምስአል ዘአስተዐፀቡ ታቀልል
ለኩሉ ፍጥረት ትተነብል በአክናፈ መላእክት
ትኬለል
ይእቲ ተዐቢ እም ኪሩቤል ወትፈደፋድ እም
ሱራፌል
**ትርጉም፡-**
ማርያም ድንግል መመኪያቸው የደናግል እርሷም
እኮ የምልጃ ቤት ናት የሚያሰጨንቀውን
የምታቃልል
ለፍጥረት ሁሉ ትማልዳለች በመላእክት ክንፎችም
ትጋረዳለች እርሷ ትበልጣለች ከኪሩቤል ደግሞ
ትበልጣለች ከሱራፌል

## 914.እሰይ ተከበረች

እሰይ ተከበረች በዛሬዋ ዕለት ድንግል ማርያም
የአምላክ እናት /2/
የምሥራች እልል በሉ የአዳም ልጆች ሁሉ
የምሥራች እልል በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ /2

## 915.መርያም ንፅይት

ማርያም ንጽሕት  ደንግል ማእምንት
ወላዲተ አምላክ ሰአሊተ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ
ሰአሊ ለነ ኀበ ክርስቶስ ወልድኪ ይሥረይ
ኃጢአተነ ሰአሊ ለነ ቅድስት
ትርጉም፡-ማርያም ንጽሕት ድንግል ታማኝ
አምላክን የወለድሽ የምሕረት አማላጅ ነሽ ለሰው
ልጅ ሁሉ/2/
ለምኝልን ከልጅሽ ከክርስቶስ ይቅር እንዲለን
ቅድስት ሆይ ለምኚልን/2/

## 916.የጽድቅ ብር ነሽ

የጽድቅ በር ነሽ የሙሴ ጽላት
አክሊለ ሰማዕታት ምዕራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንጹሕ አክሊላችን
ሐመልማለ ሲና እመቤታችን /2
እመቤታቸን ለእኛ መርኩዝ ነሽ
ከለላም ሆንሽ
የእሳት ሙዳይ
እሳት ታቀፍሽ
በብርሃን ተከበሽ
ወርቅ ለብሰሽ
ከሴቶች ሁሉ
አብ መረጠሽ
እመቤታቻን ድንግል ሆይ ልጆችሽ
ዘወትር ይጠሩሻል
ስምሽን ለልጅ ልጅ
ያሳስቡልሻል
በተሰጠሽ ጸጋ
በአማላጅነትሽ
ምሕረትን አሰጪን
ከመሐሪው ልጅሽ
እመቤታችን ያልታረሰች እርሻ
ዘር ያልተዘራባት
የሕይወትን ፍሬ
ሰጠችን የእኛ እናት
የተሠዋው መሲህ
እናቱን ወደዳት
በቀኙ ቆማለች
ድንግል እመቤት ናት
እመቤታችን የእውነት ደመና
ዝናብ የታየባት
ወዳናለች ድንግል
የታተመች ገነት
ክብር ለሆነችው
ኑ እንዘመርላት
ደስ ይበልሽ እንበል
ለብርሃን እናት

## 917.ለማርያም ድንግል

ለማርያም ደንግል መንበረ ተድላ (2)
ወሪዶ ገብርኤል ምደረ ገሊላ
ትወልዲ ወልድ ለድንግል ይቤላ
አዲስ ዜና ለማርያም ድንግል
ሰማያት ሠንጥቆ መጣ ገብርኤል
ድንግል ከአንቺ ጋር አምላክ ስለሆነ
ምክንያት አንቺ ሆነሽ ዓለም ሁሉ ዳነ
መዝገበ ጽድቅ ነሽ ምስጋና ይገባሻል
ሰማያዊ ጌታ ድንግል ሆይ ወልደሻል
መመኪያ ሞገስ ለእኛ ልትሆኝን
በስለት ወለዱሽ ሐናና ኢያቄም
በማይደክም ልሳን በመላእክት ዜማ
ትመሰገናለች የእኛ እናት በራማ
ጌታችን ተፀንሶ በማኅፀኗ ሳለ
የመላእክት ዝማሬ ትሠማ ነበር
የነቢያት ትንቢት ፍጻሜ አገኘ
ገብርኤል ተልኮ መድኃኒት ተገኘ
ንጹሕ ዘር ከሆነች ከእመቤታችን
በፍቃዱ ወርዶ ተወለደልን

## 918.ደስ ይበልሽ

ደስ ይበልሽ /2/ ማርያም ንጽሕት ድንግል
ደስ ይበልሽ ከሴቶቹ ሁሉ የተባረከሽ ነሽ /2
ሰላም እልሻለሁ ማርያም ደንግል
እንደ ብሥራታዊው እንደ ገብርኤል
ለአንቺ የተሰጠሽ ሁለት ድንግልና
አንደኛው በሥጋ ሌላው በኅሊና
አዝ -------
ከዓለም ሁሉ ሴቶች ንጽሕት በመሆንሽ
ሰማያዊው ምሥጢር የተገለጸልሽ
ለልዑል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ
የጌታችን እናት በጣም ደስ የበልሽ
አዝ -------
ማርያም ስትነበኛት ወደ ቤቷ ገብታ
ኤልሳቤጥ ዘመረች በመንፈስ ተሞልታ
በማኅፀኗ ያለው ዘለለ በደስታ
እኛንም ትጎብኘን ከጠዋት እስከ ማታ

## 919.ማርያም

ማርያም /3/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ /2
በአንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ /2/
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
አዝ ------
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበር
አዝ -------
ድንግል ተቀምጣ በቤተ መቅደስ
ሐር ወርቅ አስማምታ ስትፈትል ንግሥት
አዝ -------
ገብርኤል ሊያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ
አዝ ------
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

## 920.በምን በምን

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን/2/
ምሳሌ የላትም የላትም ክብሯን የሚመጥን/2
የሙሴ ጸላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሠላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እህት የሩኅሩኅን ርግብ /2/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መስንቆ የጌዴዎን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃን በር
ሆና የታገኘች የአምላክ ማኅደር/2
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግሥት

ችላ ተሸከመች በሁለት እጇ ይዛ
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ/2/
ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ የዛ
ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና /2

## 921.ድንግል እመቤቴ

ድንግል እመቤቴ የሕይወቴ ረዳት
የኑሮዬ ጣዕም ዋልታ መሠረት
እለምንሻለሁ/2/ ፍጹም በረከት/2/
ትኅትናሽ ሲታሰብ ድንግል እመቤቴ
በሰዎች ልቡና ድንግል እመቤቴ
ግርምትን ይፈጥራል
ልብ ይመስጥና
ጽዮን መጠጊያ ነሽ
የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል
እመብዙኃን
ከሚካኤል ጋር ድንግል እመቤቴ
ፈጥነሽ ደርሺልኝ
ቅዱስ ገብርኤል ይምጣ
ክበርሽን ያብስረን
ከድንግል ጋር ሆነህ
ዑራኤል ፈጥነህ ና
ሩፋኤል፤ ራጉኤል
ንዑ በደመና
በደማችን ሰርጿል
ፍቅሯ የማርያም
ምስክር ነን እኛ
እስከዘለዓለም
በአባቶችሽ ፈንታ
ልጆች ስላለን
ስምሽን ለልጅ ልጅ
እንዘክራለን

## 922. ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን

ሠላም ለኪ እምነ ጽዮን
ማርያም ቅድስት የሕይወት ብርሃን
ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
ሰላም ልበልሽ ተንበርክኬ
በንጽሕናሽ ተማርኬ
መርከብ የኖኅ አዳራሽ
ሰላም ለኪ ልበልሽ
ድንግል የአብርሃም ድንኳን
ሰላም /2/ ሐረገ ወይን
ያዕቆብ ያየሽ መሰላል
የሰሎሞን ክብር አክሊል
ጽላተ ሙሴ የኦሪት
የአሮን በትር መድኃኒት
የኖኅ ርግብ የኢያቄም
የነቢያት ተስፋ የአዳም
እሳተ መለኮትን ያየዝሽ
ልዑል አምላክን የወሰንሽ
ቤተ መቅደስ የልዑል
ሰላም ለኪ እም ወድንግል

## 923. የጌታዬ እናት ጸለየች

የጌታዬ እናት ጸለየች
ማርያምም እንዲህ እያለች/2/
ነፍሴ ጌታዬን ታከብረዋለች
መንፈሴም በአምላኬ ሐሴት ታደርጋለች
የእኔን የባሪያውን ትኅትና
የእስራኤል አምላክ ተመልክቷልና/2/
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል
እርሱ ታላቅ ሥራ አድርጎልኛል
ስሙም ቅዱስ ነው ምሕረቱም
ለትውልድ ትውልድ ለዘለዓለም/2/

ኃይልን አድርጓል ጌታ በክንዱ
ትዕቢተኞች ተዋረዱ
ገዢዎች ከዙፋን ስለተጣሉ
ትሁታን ደግሞ ከፍ ከፍ አሉ/2/
ባለጠጎችም ሲያጡ ሲራቡ
ድሆች በምሕረት ጥቂት ጠገቡ
ለአባቶቻችን እንደማለ
ምሕረቱን አስቦ እኛን ተቀበለ/2/

924.ቃል ኪዳን ግቢልኝ

በሄድኩበት ሂጂ እመቤቴ ይቀናል መንገዴ
ኑሮዬም ይሠምራል እመቤቴ አንቺን በመውደዴ
በያሬድ ውብ ዜማ እመቤቴ ሁሌ እጠራሻለው
በማለዳ ቆሜ እመቤቴ እለምንሻለሁ
ቃል ኪዳን ግቢልኝ እመ እግዚአብሔር /2/
የዋኅ ልብሽ ይርዳኝ ከአንቺ ጋር ልኑር
ፈጥነሽ ወደ ነይ እመቤቴ ከሰማይ ዳርቻ
ምሥጢሬን ሰሚ ነሽ እመቤቴ ድንግል አንቺ ብቻ
ሥላሴ የሠሩሽ እመቤቴ የማትፈርሺ መቅደስ
ሁሌ ጠዋት ማታ እመቤቴ አንቺን ላወድስሽ
ከምድር ብልጽግና እመቤቴ አንቺን እመርጣለሁ
ፍቅርሽን ልቀበል እመቤቴ ልቤን እስጣለሁ
ዕንቁ ስምሽ ለእኔ እመቤቴ ክብሬነው እላለሁ
እመቤቴ ብዬ እመቤቴ ችግሬን አልፋለሁ
ስምሽ ወለላ ነው እመቤቴ ከማር ይጣፍጣል
ከጥበባት ሁሉ እመቤቴ እጅግ ይደነቃል
ይታተም ምስጋናሽ እመቤቴ በሁለመናዬ
ሰአሊ ለነ ልበል እመቤቴ እንዲረዝም ዕድሜዬ

925. እሴብሕ ጸጋኪ

እሴብሕ ጸጋኪ አምላክነ ዘወለደኪ/2/
ንጉሥነ ዘወለድኪ
ውዳሴ ወግናይ አሥርቱ ቃላት
ቀድሞ ናት ድንግል ንጽሕት በእውነት
አዝ ----
ገብርኤል በቃሉ እያጫወታት
ዘኮንኪ ይሏታል ጽርሐ ቅድስት
አዝ -------
ናስተማስለኪ ተቅዋመ ማኅቶት
አንቺ እግዝእተ ኩሉ የሁሉ እመቤት
አዝ ------
ናስተማስለኪ በዕፀ ገነት
በትረ አሮን ጣትዋ የምትፈትልበት
አዝ -----
ለኪ ይደሉ እያሉ መቅደስ አስገቧት
መላእክት ወረዱ ሊያመሰግንዋት
አዝ ------
በመቅደስ እንድትኖር ስትሰጥ ብጽዓት
ዘካርያስ ነበር ሊቀ ካህናት
አዝ -----
ወሬ ሆኖ ቀረ የምቀኞች አድማ
ሆናለች እሷማ የልዑል ከተማ
አዝ -----

926.ታማልደናለች

ታማልደናለች /4/ ማርያም /2 ቤዛዊተ ዓለም/2/
ሚካኤል መልአከ ሊቀ መላእክት /2/
ዘአውረድከ (2) መና ከደመና(2)
ገብርኤል መልአክ አብሣሬ ትስብእት/2/
ዘአብሠራ /2/ ለማርያም ንጽሕት(2)
ሩፋኤል መልአክ ሊቀመላእክት(2)
ዘአብርሀ (2) ዓይኑ ለጦቢት(2)
ዑራኤል መልአክ ለእዝራ ነቢይ(2)
ዘአስተዮ (2) ጽዋዐ ልቡና(2)
ሰሎሞን ይቤላ /4/
ርግብየ ሠናይትየ ሰሎሞን ይቤላ /2
ገብረ መንፈስ ቅዱስ /4/
ሐዋርያ /2/ ዘእስክንድርያ(2)
ተክለሃይማኖት /4/
ሐዋርያ /2/ ዘኢትዮጵያ

ብርሃናት ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ
አዕማደ /2/ ቤተ ክርስቲያን /2

927.አብሰራ

አብሠራ ገብርኤል ሊቀ መላዕክት/2/
ኸኸ ወይቤላ /5/ ትወልዲ ወልደ /2/
**ትርጉም** ሊቀ መልአክ ቅ.ገብርኤል ልጅ
ትወልጀለሽ ብሎ ለእመቤታችን አበሠራት

928.ወይቤላ

ወይቤላ ውእቱ መልአክ ሰላም ለኪ /2/
ሰላመ ዚአየ የሀሉ ምስሌኪ/2/
የሀሉ ምስሌ

929.በዝመና ንጽሕኪ

በዝናበ ንጽሕኪ ሐረገወይን ፀገየ /2/
ወሮማን /2/ወሮማን ሐዋዘ ፈረየ/2/
እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺን የማይበት/2/
ምን ዓይን አለኝ /5/ ፍቅርሽ አይለየኝ/2/
ለአዳም ተስፋ የሆንሽው ማርያም እመቤቴ /2/
አማልጅን ቶሎ ብለሽ/3/ ሻልጠፋብሽ ልጅሽ /2/
የዳዊት መሰንቆ ነሽ የኢያሱ ሐውልት
በምን እንመስልሽ /3/ ወደርም የለሽ /2/
እመቤቴ ጥላዬ ሁኚልኝ ከለላዬ /2
ያለአንቺ ማን አለኝ /3/ አለሁሽ በይኝ /2/
አዳምና ሔዋን ከገነት ተሰደው/2/
ማርያም አንቺ ነሽ/3/ የመዳን ተስፋቸው
የእግዚአብሔር አብ ሙሽራ ወልድን የወለድሽ
የእግዚአብሔር መንፈስቅዱስ ንጽሕት አዳራሽ
የሰሎሞን አክሊል የታጠረች ተክል
የአሮን ካህን ልብስ/3/ የወርቅ ጸናጽል

930.ወደ ምሥራቅ እዩ

ወደ ምሥራቅ እዩ ወደ ፀሐይ መውጫ
ድንግልን ክበቢት እንበል ሃሌ ሊያ
ለአምላክ እናት ለአዛኝት እልል እንበል እንዘምርለት/2/
ወገኖች ተነሡ እናታችን መጣች
ሰሚን ስንጠራ መቼ ትቀራለች
የተከዘን ልታጽናና ነይ ስንላት ትመጣለችና/2/
የጽጌው ማኅሌት በጸሎት ሲጀመር
ማርያም ትመጣለች በደመና በአየር
ንዒ ስንል በሰዓታት
ልታባርከን ትመጣለች በእውነት/2/
ፍልሠታ ሲጀመር ቃል ኪዳን ገብታለች
የሌሊት ውዳሴን ንዒን ትሰማለች
ሕፃናቱን በበረከት ልትጎበኘን ትመጣለች በዕውነት
በፍጽም ቸርነት እንዲምረን ጌታ
በአማላጅነትሽ ሁኚልን መከታ
በእናታቸን አለኝታችን
እንድናለን ደንግል አንቺን ይዘን
ሃሌ ሃሌ ሉያ(2)
እስመ ዝንቱ ዑራኤል
እስመ ዝንቱ ለዓለም ብርሃኑ(2)

931.አዘክሪ ድንግል

አዘክሪ ድንግል አዘክሪ
ለልጅሽ አሳስቢ አዘክሪ
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን
ካንቺ መወለዱን አዘክሪ
በቤቴልሔም አዘክሪ
በጨርቅ መጠቅለሉን አዘክሪ
መኝታው ግርግም አዘክሪ
በዚያ በብርድ ወራት አዘክሪ
የገበሩለትን አዘክሪ
የአድግና የላም አዘክሪ
እስትንፋሳቸውን አዘክሪ
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን
በግብፅ በረሀ አዘክሪ
መሰደድሽን አዘክሪ
የኢሻዋውን ግልት አዘክሪ

ረሀብና ጥሙን አዘክሪ
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን
በመቃብሩ ዘንድ አዘክሪ
ባለቀሽው እንባ አዘክሪ
አሳስቢ ድንግል ሆይ አዘክሪ
ገነት አንድንገባ አዘክሪ
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን

932.እንደ ኤልሳበጥ

አንደ ኤልሳቤጥ ለመስግንሽ
ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት የእኛ እመቤት
አዛኝ ነሽ ከልብ ፍጹም የዋህት
ርኅራኄሽ ያስደስተኛል
ስለ ኃጢአቴ ምልጃሽ ይቀድማል
የሰላምታሽ ድምፅ ደስ ያሰኘኛል
ከትካዜዬም ያሳርፈኛል
ድምጽሽ ሲሰማኝ ልቤ ይረካል
ሐዘኔ ቀርቶ ፊቴ ይፈካል
በእናትነት አንቺን ለሰጠን
ቸሩ አምላካችን ይከበር ይመስገን
የሁሉ እቤት የሁሉ አጽናኝ
የዓለም መድኃኒት ከአምላክ አገናኝ
ዛሬም በልቤ ደስታ ጨምረሽ
እንደ ኤልሳቤጥ ሰላም ልበልሽ
ከሴቶች መካከል መርጦ ቀድሶሻል
ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉሻል
በልዩ ውዳሴ ያመሰግኑሻል
ድንግል ንግሥታችን በቀኝ ቆመሻል
የሰላምታሽ ድምጽ ልቤ ሲሰማ
ነፍሴን ደስ አላት ቀለላት ሸክሟ
ድንግል ለክብርሽ ስንበረከክ
እጅሽ ይዘርጋ ለመባረክ

933.ትኅትናሽ ግሩም ነው

ትኅትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም/2/
እናቱ ሆነሻል ለመድኃኔዓለም/2/
ንጽሕት ስለሆንሽ..... እመቤቴ /2/
እንከን የሌለብሽ ......እመቤቴ /2/
የፍጥረታት ጌታ....... እመቤቴ /2/
በአንቺ ያደረብሽ....... እመቤቴ /2/
የድንግል መመረጥ .....አምቤቴ /2/
ዜናው አስገረመኝ....... እመቤቴ /2/
እሳቱን ታቀፈች ......እመቤተ /2/
የማይቻለውን ........ እመቤቴ /2/
ምርኩዜ ልበልሽ............እመቤቴ/2/
ጥላ ከለላዬ እመቤቴ /2/
ጋሻዬ ነሽ አንቺ እመቤቴ
ለእኔ መመኪያዬ
በዓለም አንዳልጠፋ እመቤቴ
ሕይወቴ መሮብኝ እመቤቴ
እንደ ወይን አጣፍጭው እመቤቴ
ማርያም ድረሽልኝ እመቤቴ
የምሥራቅ ደጃፍ ነሽ እመቤቴ /2/
የሁላችን ደስታ
እሙ ለፀሐየ ጽድቅ እመቤቴ
የሁሉ ጠበቃ እመቤቴ
ድንግል የድል አክሊል እመቤቴ
ድንግል የጽድቅ ሥራ
ድንግል መሰላል ነሽ እመቤቴ
የተዋሕዶ ተስፋ እመቤቴ

934. ለማርያም

ለማርያም/2/
እንዘምራለን ለዘለዓለም/2/
የተዘጋች ደጅ ለዘለዓለም
ሕዝቅኤል ብሏል
ንጽሕት ናት በእውነት
በፍጹም ድንግል

አብነት አድርገን
እኛም እርሷን ለዘላለም
በፍጹም ፍቅር እንዘምራለን /2/
የዋህት ርግብ ለዘለዓለም
ሰላም አብሳሪ ለዘለዓለም
ጨለማ ሕይወቴ ለዘለዓለም
በርሃንን አብሪ ለዘለዓለም
እማጸንሻለሁ ለዘለዓለም
ድንግል ለነፍሴ ለዘለዓለም
አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ /2/
እጅግ የበዛ ነው ለዘለዓለም
ያለኝ ፍቀር ለዘለዓለም
አይወሰንም ለዘለዓለም
አይነገርም ለዘለዓለም
በእርሷ ደስ ይለኛል ለዘለዓለም
ሐሴት አደርጋለሁ ለዘለዓለም
ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ/2/

ነይ ነይ ስላት ለዘለዓለም
ቀንና ሌሊት ለዘለዓለም
አትለየኝም ለዘለዓለም
ለእኔስ ቅርቤናት
እጹብ እጹብ ብለው ለዘለዓለም
እመስገኗት ለዘለዓለም
ክብሯን ሊገልጹት ቢያጥራቸው ቃላት /2/

935.በሀጢያት ያደፈ

በኃጢአት ያደፈ ሆኗል ሰውነቴ
አብቂኝ ለንስሓ አማልጅኝ እናቴ
በኃጢአት ያደፈ በኃጢአት ብዛት
ልቤ ሲታወክ በኃጢአት ያደፈ
ተብትቦ ሳይጥለኝ በኃጢአት ያደፈ
የኃጢአቴ ድር በኃጢአት ያደፈ
በጣጥሰሽ ጣይልኝ በኃጢአት ያደፈ
የኃጢአቴን መጥመድ በኃጢአት ያደፈ
ድንግል ሆይ አማልጅኝ በኃጢአት ያደፈ
አርቂኝ ከዚህ ጉድ በኃጢአት ያደፈ
በኃጢአት ያደፈ መቆም አቅቶናል
በደሌ በዝቶብኝ በኃጢአት ያደፈ
እማፀንሻለሁ በኃጢአት ያደፈ
ልመናየን ስሚኝ በኃጢአት ያደፈ
ኃጢአቴን መሸከም በኃጢአት ያደፈ
እኔ አልቻልኩምና  በኃጢአት ያደፈ
እናቴ ሆይ ስሚኝ  በኃጢአት ያደፈ
ድንግል በጽሞና በኃጢአት ያደፈ

936.እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ወዳሴ
ታቀርባለች ዘውትር ነፍሴ/4/
ልቤ ተነሣሣ ተቀኝ ለክበርሽ
በፍጹም ትኅትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመብርሃን
የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና
ክብር ይገባሻል ዘወትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስራቆት
ያንን የእሳት ባሕር አሻግረኝ ድንግል  ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

937.ከሊባኖስ

ከሊባኖስ /2/ ከልጅሽ ጋር ነይ
እመ አዶናይ ከሊባኖስ ወደ እኛ ነይ
ጥበቃሽ ዘወትር ከሊባኖስ እንዳይለየኝ
በሔድኩበት ሁሉ ከሊባኖስ ማረፊያ ሁኚኝ

እኔን ባሪያሽን ከሊባኖስ ድንግል አትርሺኝ
በጽድቅ ሠሌዳ ከሊባኖስ ሰሜን ጻፊልኝ
ነፍሴና ሥጋዬን ከሊባኖስ አደራ እልሻለው
በልጅሽ ጽኑ ፍቅር ከሊባኖስ ተማጽኜሻለው
ከአንበሶች መኖሪያ ከሊባኖስ ከነብሮች ተራራ
መጥተሽ አስደስቺኝ ከሊባኖስ እናቴ ሙሽራ
የልብስሽ መዓዛ ከሊባኖስ የሊባኖስ ሽታ
ሮማን ናርዶስ ነው ከሊባኖስ እናቱ ለጌታ
እመቤቴ ስልሽ ከሊባኖስ ስምሽን ስጠራ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ከሊበኖስ ከቅዱሳንጋር
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ከሚካኤል ጋር
ፈጥነሽ ድረሺልኝ  ከገብርኤል ጋር
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ከዑራኤል ጋር

## 938.ያመስገናት

ያመሰገናት /3/ እዝራ በመሰንቆ
እናትነቷ ንጽሕናዋን አውቆ
ያመሰገናት /3/ ዳዊት በመዝሙር
አምባ መጠጊያችን የአምላክ ማኅደር
ያመሰገናት /3/ ኤፍሬም በውዳሴው
ለምኚልን አላት ፍቀሯ ስለገባው
ያመሰገናት/3/ አባ ሕርያቆስ
ምሳሌ ኣጣለት በመንፈስ ሲቀድስ
ያመሰገናት /3/ አባ ጊዮርጊስ
እናትነትዋን ፍቅሯን ሊያስታውስ
ያመሰገኗት /3/ ካህናት በክበሮ
ልብን በሚመስጥ በሐዘን እሮሮ
እናመስግናት /3/ ሆነን በአንድነት
እመቤታችንን እመምሕረት
አማላጃቸንን እመምሕረት

## 939ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያም እጮኸለሁ
ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወድሰኒ ልጄ በይኝ
በሠርክ ጸሎት ላይ ውዳሴ ማርያም
ዜማ ስናደርስ ውዳሴ ማርያም
ድንግል ትመጣለች ውዳሴ ማርያም
በቤተመቅደስ ውዳሴ ማርያም
የብርሃን ምንጣፍ ውዳሴ ማርያም
ከፊቷ ተነጥፏል ውዳሴ ማርያም
ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ ውዳሴ ማርያም
ያመሰግናታል ውዳሴ ማርያም
አባ ሕርያቆስም ውዳሴ ማርያም
ምስጋና ያደርሳል ውዳሴ ማርያም
የቅዳሴው ዜማ ውዳሴ ማርያም
ልብን ይመሰጣል ውሳሴ ማርያም
በጎ ነገር ልቤ ውዳሴ ማርያም
አወጣ እያለ ውዳሴ ማርያም
ዳዊት በገናውን ውዳሴ ማርያም
እየደረደረ ውዳሴ ማርያም
የንጽሕናችንን ውዳሴ ማርያም
መሠረት ነሽና ውዳሴ ማርያም
አንቺን ለማመስገን ውዳሴ ማርያም
ልቡናዬ ይብራ ውዳሴ ማርያም
ተፈሥሒ ድንግል ውዳሴ ማርያም
ኦ ቤተልሔም ውዳሴ ማርያም
ከአንቺ ተወለደ ውዳሴ ማርያም
መድኃኔዓለም ውዳሴ ማርያም
ቅዱሳኑ ሁሉ ውዳሴ ማርያም
ዙሪያሽን ከበዋል ውዳሴ ማርያም
አባ ጊዮርጊስም ውዳሴ ማርያም
ንዒ ድንግል ይላል ውዳሴ ማርያም
በወርቅ ዙፋን ላይ ውዳሴ ማርያም
ተቀምጠሽ ሳይሽ ውዳሴ ማርያም
ልቤ ተመሰጠ ውዳሴ ማርያም
ደንግል በግርማሽ ውዳሴ ማርያም

940. ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት /2/ ለነቢያት /2/
ሞገሶሙ ለሐዋርያት /4/
ትርጉም- ድንግል ሆይ የሐዋርያት ሞገስ
የነቢያት ትንቢት አንቺ ነሽ

941.ማርያም

ማርያም /2/ ድንግል ማርያም /2/
ርኅርኂተ ኅሊና /4/ ማርያም/4/

942.በመኑ በአምሣለ መኑ

በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ/2
እመቤቴ የእኛ አማላጅ አዛኝቷ  ኦ ድንግል
ምልዕተ ውዳሴ /2

43.ማርያም ተዐቢ

ማርያም ተዐቢ እምኩሉ ፍጥረት /2/
ኢያውአያ እሳተ መለኮት /4/
**ትርጉም፡-** ማርያም ትበልጣለች ከሁሉ ፍጥረት
/2/
ስለያዘች እሳተ መለኮትን/4/ (ስላላቃጠላት)

944.የኖኅ ቃል ኪዳኑ

የኖኅ ቃል ኪዳኑ ምልክት ዓርማው
የመዳኑ ምሥጢር የሰላም ተስፋው
እመቤቴ አንቺ ነሽ ቀስተደመናው/2/
አንቺ የአሮን በትር ሳይተክሏት ያደገች
የማክሰኞ እርሻ ያለዘር ያፈራች
የሲና ሐመልማል የተዋሕዶ ምሥጢር
ክብርት እምቤቴ ሀገረ እግዚአብሔር/2/
የዳዊት መሰንቆ ያሬድ ጽናጽል
የደካሞች ምርኩዝ የሰሎምን አኪሊል
ሰላሜ ተስፋዬ የሐዘኔ ደራሽ
የጽዮን ተራራ መሸሸጊዬ ነሽ/2/
የኤልሳዕ ማሠሮ ጨው የተገኘብሽ
የሕዝቅኤል ራዕይ ንጽሕት አዳራሽ
አንቺ የአዳም ተስፋ የመዳኔ ብስራት
አንቀጸ ብርሃን የአማኑኤል እናት/2/

945.ማህደረ መለኮት

ማኅደረ መለኮት የአምላክ እናት እመቤት
ስምሽን ጠርቶ ያፈረ ማነው
የአምላክ እናት ሥራሽ ግሩም ነው
ማኅደረ መለኮት ደጅሽ ላይ ቆሜ ስለምን
ማኅደረ መለኮት እመብርሃን ነይ ድንግል
ማኅደረ መለኮት መጽናኛዬ ነሽ ረዳቴ
ማኅደረ መለኮት ጋሻና ጦሬ መከታዬ
ማኅደረ መለኮት ስዘምርልሽ ደስ ይለኛል
ማኅደረ መለኮት ከልጅሽ ጸጋ ይሰጠኛል
አዝ --------
ማኅደረ መለኮት አሸብሸቡላት ለድንግል
ማኅደረ መለኮት ፍቀር ያላችሁ በእውነት
ማኅደረ መለኮት ትመጣለች ልትባርከን
ማኅደረ መለኮት ድንግል ሆይ ባርኪን ስንላት
ማኅደረ መለኮት አፌም ይከፈት ለዝማሪ
ማኅደረ መለኮት ለአምላክ እናት ለእመቤቴ
አዝ -------
ማኅደረ መለኮት ትምክህት ናት ለሁሉም
ማኅደረ መለኮት ጸዓዳ  ርግብ የሠላም
ማኅደረ መለኮት ምን ብዬ ልጥራሽ ላመስግንሽ
ማኅደረ መለኮት ከፍጥረት ሁሉ ነሽ የከበርሽ
ማኅደረ መለኮት በንጽሕና የተሸለምሽ
አዝ ---------

946.ማርያም ፊደል

ማርያም ፊደል የሁሉ መማሪያ /2/
በንጽሕና በንጽሕና ተጽፋለችና /2/

947.ሰላም ለኪ

ሠላም ለኪ /2/ ለኖኅ ሐመሩ
ሠላም ለኪ ለአሮን በትሩ
ሠላም ለኪ ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ
ሠላም ለኪ ለጌዴዎን ፀምሩ

ሠላም ለኪ የሰሎሞን መንበረ ክብሩ
ሠላም ለኪ ለፍሬ ስብሐት መጸሩ /2
እመ እግዚአብሔር ፀባኦት ሰላም
ለኪ/2/
ሠላም ለኪ ሰረገላሁ ለአሚናዳብ
ሰላም ለኪ መና ያለብሽ ንጹሕ መሶብ
ሰላም ለኪ ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ
የይስሐቅ መዓዛ /2/
እንዘ ንሴፎ ለበረከትኪ ዘምስለ
አምኃ ንሰግድ ለኪ/2/
ሠላም ለኪ ኅብስተ መና ዘእስራኤል
ሠላም ለኪ የሰማዕታት ንጹሕ አክሊል
ሠላም እፀ ጳጦስ ዘሲና
ሰላም ለኪ የኤልያስ መና
እንዘ ንሴፎ ለበረከትኪ ዘምስለ
አምኃ ንሰግድ ለኪ /2/

**948..አስታሪቂኝ**

አስታርቂኝ ድንግል ማርያም /2/
ከልጅሽ /3/ ከመድኃኔዓለም
አስታርቂኝ ኃጢአትን ሰርቼ
አስታርቂኝ ጫካ ውስጥ
ቆሜአለው
አስታርቂኝ ሥራዬ አሳፍሮኝ
አስታርቂኝ ዘወትር አነባለው
አስታርቂኝ ልጄ አዳም ብሎ
አስታርቂኝ አምላኬ ሲጠራ
አስታርቂኝ እነሆኝ ለማለት
አስታርቂኝ አንደበቴ ፈራ
አዝ ------------
አስታርቂኝ ሀብትን ተካፍዬ
አስታርቂኝ ከገዛ አባቴ
አስታርቂኝ ከቤቴ ኮበለልኩ
አስታርቂኝ ይሻለኛል ብዬ
አስታርቂኝ ገፍቼ ወጥቼ
አስታርቂኝ የቤቴን ገበታ
አስታርቂኝ ልበላ ተመኘሁ
አስታርቂኝ የእንስሳት ገፈራ
አዝ---------
አስታርቂኝ ወደ አባቴ ልሂድ
አስታርቂኝ አሁን ተነሥቼ
አስታርቂኝ ይቅርታ ልጠይቅ
አስታርቂኝ እግሩ ስር ወድቄ
አስታርቂኝ ልጅነቴ ቀርቶ
አስታርቂኝ አድርገኝ ባርያህ
አስታርቂኝ ከሞያተኞችህ
አስታርቂኝ እንደ አንዱ ቆጥረህ
አዝ ------
አስታርቂኝ ገና ሩቅ ሳለው
አስታርቂኝ አባቴ አይቶኝ
አስታርቂኝ ወደእኔ ሮጦ
አስታርቂኝ አቅፎ ነው የሳመኝ
አስታርቂኝ ጠፍቶ የነበረው
አስታርቂኝ ተገኘልኝ አለ
አስታርቂኝ ሞቶ የነበረው
አስታርቂኝ ደግሞ ሕያው ሆነ

**949. ደስ ይበለን**

ደስ ይበለን በጣም ደስ ይበለን/2/
በረከቱን ለኛ ስለሰጠን
በጨለማ ስኖር ደስ ይበለን
በኃጢአት ተከበን
የሕይወትን ብርሃን
ጽድቁን አበራልን
ወደ ምሥራቅ እንይ
ፀሐይ ወደአለበት
ጨለማው ልባችን
ጎህ እንዲገባበት

አዝ ------------
የፀሐይ እናቱ ደስ ይበለን
ማርያም እመቤቴ
እለምንሻለሁ
እስከ እለተሞቴ
የልቤ ማረፊያ
የዘለዓለም ቤቴ
አንቺ ነሽ ተስፋዬ
እፀ መድኃኒቴ
አዝ ----------
የግሸኗ ንግሥት ደስ ይበለን
የአምላክ እናት
ሆና ተገኝታለች
ለሚመኩባት
በልቼ ጠጥቼ
የምረካብሽ
ጎጆ ማረፊያ
ማርያም አንቺ ነሽ
አዝ ----------
ፀዓዳ እመቤቴ ደስ ይበልን
ሐመልማለ ሲና ደስ ይበለን
የሕዝቅኤል ደጃፍ
የሙሴ ደመና
የተዋበች እንቁ
የደጎች አዝመራ
በማኅፀንሽ ፍሬ
ሕይወታችን በራ

## 950.በሀዘኔ

በሐዘኔ ደራሽ ነሽ በጭነቀቴ
በችግሬ ደራሽ ነሽ
የአምላኬ እናት የጌታዬ እናት
ድንግል እመቤቴ ወላዲተ ቃል /2
መላካሚቱ ርግብ ድንግል እመቤቴ
ማርያም እናቴነሽ ድንግል እመቤቴ
ከፍጥረታት ሁሉ ድንግል እመቤቴ
ገናና ነው ክብርሽ ድንግል እመቤቴ
የሐዘኔ መጽናኛ ድንግል እመቤቴ
እንባን አባሽነሽ ድንግል እመቤቴ
አዝ ---------
ዋሻ መጠለያ ድንግል እመቤቴ
የዘለዓለም ቤቴ ድንግል እመቤቴ
መንገድ ስሄድ ስንቄ ድንግል እመቤቴ
መጠነሽ ምግቤ ድንግል እመቤቴ
እምአምላክ ስጠራሽ ድንግል እመቤቴ
ይጠፋል ረሀቤ ድንግል እመቤቴ
አዝ ------------
የእናትነትሽ ድንግል እመቤቴ
ፍቅርሽን አየሁት ድንግል እመቤቴ
ጎጆዬን ስትሞይው ድንግል እመቤቴ
ባዶ የሆነውን ድንግል እመቤቴ
አንቺ እያለሽልኝ ድንግል እመቤቴ
ምን እሆናለሁኝ ድንግል እመቤቴ
አዝ ------------

## 951.ባክኛለሁና

ባክኛለሁና በሥጋ ፈተና
የዚህ ዓለም ሐዘን ጫፍ የለውምና
ፈጥነሽ ወደ እኔ ነይ ከትንሿ ቤቴ
አጽናኚኝ እመአምላክ ድንግል እመቤቴ
ባሕሩ ትልቅ ነው ድንግል እመቤቴ
ትንሽ ናት መርከቤ /2/ ድንግል እመቤቴ
የመንገዴ መሪ ድንግል እመቤቴ
አንቺ ነሽ ወደቤ /2/ ድንግል እመቤቴ
በመንገዴ ብዝል ድንግል እመቤቴ
ዓለም ትስቃለች /2/ድንግል እመቤቴ
መመኪያ እመቤቱ ድንግል እመቤቴ
ወደየት ናት እያለች /2/ድንግል እመቤቴ

በቀቢጸ ተስፋ ድንግል እመቤቴ
እንዳልወደልቅብሽ ድንግል እመቤቴ
በቀንም በሌሊት ድንግል እመቤቴ
ተስፋዬ አንቺ ነሽ ድንግል እመቤቴ
የለም ያተረፍኩት ድንግል እመቤቴ
ወጥቼ ወርጄ /2/ ድንግል እመቤቴ
ትርፌ አንቺ ብቻ ነሽ ድንግል እመቤቴ
ጽዮን አማላጄ ድንግል እመቤቴ

## 952የገነት ደጃፍ

የገነት ደጃፍ ማርያም ነሽ
የወርቅ መሰላል ድንግል ነሽ
የአምላክ እናት ማርያም ነሽ
ክብርና ውዳሴ ለአንቺ ይገባሻል
አምላክ አንቺን ወዶ ባርኮ ቅድሶሻል
የተዘጋች በር የታተመች ገነት
ድንግል እና እናት ሰማያዊት ንግሥት
የመለኮት እናት እሳትን ያዘለች
የአደራ እናታችን እመቤታችን ናች
የሰማይ መላዕክት እያሸበሸቡ
ሰላም ለኪ ብለው ድንግልን ከበቡ
እኛም ክቡር ወዳሴ ዝማሬ ምስጋና
ለእርሷ እናቀርባለን ይገባታልና
እኔስ አነሳለሁ ስሟን ለዘለዓለም
ከሴቶች መካከል ከቶ እንደርሷ የለም
በድንግል ውዳሴ ነፍሴ ትረካለች
ምስጋና ሲጀመር ድንግል ትመጣለች

## 953. ማርያም እንወድሻለን

ማርያም እንወድሻለን/2/
ስለወለድሽ የሕይወት ምግብን /2/
ማርያም እንወድሻለን
ድክመቴን አትይ ማርያም
በኃጢአት መውደቄን ማርያም
ተስፋዬ አንቺ ነሽ ማርያም
እስከ እለተ ሞቴ ማርያም
ላልጠላሽ ምያለሁ ማርያም
ከስርሽ ላልጠፋ ማርያም
ገጸ በረከቴ ማርያም
የሕይወቴ ዋስትና ማርያም
የምእመናን ውበት ማርያም
ዘወድ እክሊላችው ማርያም
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ ማርያም
የመንገድ ስንቃቸው ማርያም
ምሥክር ነኝ ለአንቺ ማርያም
አንደ ነቢያቱ ማርያም
ስጦታ መሆንሽን ማርያም
ለአዳም ልጆች ሁሉ ማርያም
ሞገስና ጸጋ ማርያም
በጌታ ፊት ያለሽ ማርያም
ከሰይጣን መሸሻ ማርያም
ዋስ ጠበቃችን ነሽ ማርያም
እንዴት ነበር ያኔ ማርያም
ጌታን ስትወልጂው ማርያም
የእረኞቹ ደስታ ማርያም
የመላእክት ዝማሬ ማርያም

## 954.ለወዳሴሽ ልትጋ

ለውሳሴሽ ልትጋ ስምሽ ግርማ ያለው/2/
እመቤቴ ኸኸ እመቤቴ ስልሽ እውላለሁ
ከልቤ አቀርባለሁ ምስጋና ለስምሽ
መለመኛዬ ነው ጽኑዕ ቃል ኪዳንሽ
በሰላምታ ድምጽሽ ያልጸና ማን አለ
ጽንሱ በማኅፀን በደስታ ዘለለ
ማርና ወተት ነው የስምሽ ስያሜ
እመቤቴ ስልሽ ይቀላል ሸክሜ
ቅኔ ማኅሌቴ ሰዓታት መዝሙሩ
ያመሰግኑሻል ምድርና ጠፈሩ

እናቱ ነሽና አንቺ ለአዶናይ
ማለድኩኝ ከፊትሽ ይቅርታውን እንዳይ
ሰአሊነ ብዬ ይኸው ተምሬአለሁ
በአንቺ ተደግፌ ነገም እኖራለሁ
ነይ ነይ እልሻለሁ አንደ ካህናቱ
በሰዓታት ጸሎት ቆሜ በሌሊቱ
ዝም አልልም እኔ አወድስሻለሁ
የዓለምን መከራ እረሳብሻለሁ

955 <u>በምድራዊ</u>

በምድራዊ ሕይወት/2/ በፈተና ቦታ/2/
ድንግል ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ
ማርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ/2/

<u>956. በሐዘኔ በጭንቀቴ</u>

በሐዘኔ በጭንቀቴ መጽናኛዬ ነሽ ረዳቴ
እመአምላክ አደራ ድንግል እመቤቴ /2/
ለዓለም ተዘርግቶ እጄ ባዶ ሆናል
የራሴ ላይ አክሊል ተሽቀንጥሮ ወድቋል
ከኤልዛቤል ሽሽቼ መጣሁኝ ወደአንቺ
የጎሰቆልኩትን እኔን ተመልከቺ
የእግሬ መሰናልክ ለዓለም ደስታ ነው
ተስፋ ቢስ መሆኔ ለጠላቴ ድል ነው
የደስታ መመንጫ የኤሳቤጥ ዘመድ
አንዳልሠናከል ምሪኝ በመንገድ
ምድር ትለኛለች ተስፋ ቢስ ብቸኛ
ሳለቅስ ሳነባ አይታናለችና
ከቤተ መቅደሱ ለእኔ ዘመድ አለኝ
በሐዘኔ ሰዓት አይዞህ የምትለኝ
ከአመድ የወደቀ ትንሽ ገንዘብ አለሽ
ልብሽ ራርቶልኝ ፈልጊኝ አጥብቀሽ
እምነቴ እንዳይደክም እንዳልጠፋ ልጅሽ
አድጌአለሁና ከደጀ ሰላምሽ

<u>957.ማርያም ማርያም በሉ</u>

ማርያም /2/ በሉ
የተጨነቃችሁ ያዘናችሁ ሁሉ
ቅድስት ማርያምን አዘኝቷን ጥሩ
የጌታዬ እናትን አዛኝቷን ጥሩ
ነይ በሏት ትመጣለች /2/
ሐዘን ጭንቀት ትገላግላለች
ደንግል ማርያም ፀምረ ጌድዬን
የታቦት ተራራ ደንግል ማርያም
የአባ ጊዮርጊስ ደንግል ማርያም
የአርጋኖን ሙሽራ ደንግል ማርያም
በአዛኝነትሽ ደንግል ማርያም
ስንቅ የሆንሽኝ ደንግል ማርያም
ዛሬም ፈጥነሽ ስሚኝ ድንግል ማርያም
ድንግል አትርሺኝ ደንግል ማርያም
ድንግል ማርያም ብሥራተ ገብርኤል
የሚካኤል ፋና ደንግል ማርያም
አክሊለ ጊዮርጊስ ደንግል ማርያም
የሱራፌል ፋና ደንግል ማርያም
ነይ ፈጥነሽ ደረሺ ደንግል ማርያም
ተጨንቀናልና ደንግል ማርያም
ድንግል ማርያም ፍጥረታት በሙሉ
ያመሰግኑሻል ደንግል ማርያም
የሕይወታችን በር ደንግል ማርያም
ድንግል ናት ይሉሻል ደንግል ማርያም
እኛ እንጠራሻለን ደንግል ማርያም
ሲጨንቀን ሲጠበን ደንግል ማርያም
ለአንቺ ልጆች አድርጎ ደንግል ማርያም
ጌታ ስለሰጠን ደንግል ማርያም

<u>958. ማርያም ኩኒ</u>

ማርያም ኩኒ ለሕይወትየ ጸወኖ/2/
እስመ ተማኅጸንኩ አንሰ ተማኅጸንኩ/2/
በኪዳንኪ /2/ ተማኅጸንኩ
ማርያም ሁኚ ለሕይወቴ አምባ በምልጃሽ
እማጸንሻለሁ ተማጽኜሻለሁ/2/

በቃል ኪዳንሽ/2/ በሚያድነው ቃል ኪዳንሽ
አምላክ ስለሰጠሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
ጻድቃንን ለማትጋት ኃጥኡን ለማዳን
የምሕረትን ምጽዋት እለምንሻለሁ
ይቅርታን ለማግኘት እጄን ዘርግቻለሁ
የሊቀካህናቱ የክርስቶስ እናት
ለምኚልን ቅድስት ለኃጢአቴ ሥርየት
በሥጋም በነፍስም ይቅር አስብይኝ
ከበደሌ ዕዳ ንጹሕ አድርጊኝ
ማርያም በስምሽ በቃል ኪዳንሽ
አምኜ ቆሜአለሁኝ ኃጥኡ ባርያሽ
ንስሓ ሣልገባ እንዳልሞት አደራሽ
ለዚህ ዕድል አብቂኝ ከልጅሽ አማልጅሽ
በቃል ኪዳንሽ አምኜ ስጠራሽ
ድንግል አትለይኝ በረድኤትሽ
ፍቅርሽን በልቤ ጣዕምሽ በአንደበቴ
እንዲያድር አደርጊ ፅዩን እመቤቴ

959. <u>እመቤታችን</u>

እመቤታችን ማርያም ሀገራችንን ጠብቂልን
በምልጃሽ /2/
ከመናፍቃን ኪከሀድያን ከጠላት ሰይጣን ሠውሪሽ
አንድትጠብቂን በምልጃሽ/2/

960. <u>ሰላም ለኪ ማርያም እመአምላክ/2/</u>

ሰላም ለኪ ማርያም እመአምላክ/2
ወልድኪ ይዔውአኪ ውስተ ሕይወት
ወመንግሥተ ክብር/4/

961. <u>እስኪላግንሽ</u>

እስኪ ላግንሽ እመቤቴ ማርያም
እስቲ ላድንቅሽ ንጽሕት ቅድስት ማርያም
መመኪያ ርስቴ ነሽና እናቴ /2/
አዝ-----------------------
አዛኝት ማርያም ክብርሽ ልዩ ነው
ለተቸገረ ስምሽ ስንቅ ነው
መደኃኒቴ ነሽ እጠራሻለው
ከእግርሽ ወድቄ እሰግድልሻለው
አዝ ---------------------
የኤዶም ወንዝ የገናት ፈሳሽ
ምክንያተ ድኅነት ሰው የዳነብሽ
ንጹሑን በግ ጌታን ያስገኘሽ
አብርሃም ያየሽ እፀ ሣቤቅ ነሽ
አዝ ----------
እያሽበሽብኩ ልዘምርልሽ
ልዝረፍ ቅኔውን ነይ ላወድስሽ
የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስጋና አንቺ ነሽ
ዳዊት በመዝሙር የዘመረልሽ
አዝ -------
አእላፍ መላእክት ዙሪያሽን ከበው
ሲያመሰግኑሽ በሰማይ ያየው
እፁብ ድንቅ ነው ግሩም ተአምር
ዘርዝሬ አልጨርስ ያንቺን ክብር
አዝ---------

962.. <u>ናርዶስ ቀጺመታት</u>

ናርዶስ ቀጺመታት አሉ በልብሶችሽ መሀል/2/
የገነት <u>ሽቱ ነሽ</u>/2/2/ ማርያም ድንግል
የከበርሽ ነሽ አንቺ ከፍጥረት
መዓዛሽን ወድዷል ጌታ ፀባኦት
ጠላት እንዳይከሠኝ ከጎኔ ሁኚና
ነውሬን ሽፍኝው እናቴ ነሽና
አዝ ---------------
ገሊላዊት ድንግል የገነት ፈሣሽ
የቆሠለችውን ሕይወቴን ፈውሽ
ሰአሊ ለነ ቅድስት በቀን በሌሊት
ለአፊ ጥበብ ነሽ ቅኔ ማኅሌት
አዝ -----
ሁልጊዜ ድኅነትን የምንለምንሽ
ለእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘሽ

ክርስቲያኖች ሁሉ ተስፋ የሚያደርጉሽ
ለዓለም የሚበቃ ምልጃ ቃልኪዳንሽ
አዝ ----------------------

963.ልዑል ሠምራ

ልዑል ሠምራ ዳዊት ዘመራ/2/
በቤተመቅደስ ተወክፋዋ/2/
ልዑል መረጣት ዳዊት ዘመረላት/2/
በቤተመቅደስ ተቀበሏት/4/

964.እንዘ ዘልፈ

እንዘ ዘልፈ ትነበር ውስተ ቤተ እግዚአብሔር/2/
አስተርዓየ መልአከ ዘኢኮነ /2/ ከመቀዲሙ ኢኮነ /2/
ትርጉም:- ዘወትር በቤተ እግዚአብሔር
እየተቀመጠች
ሳለ እንደ ፊተኛው ያልሆነ መልአክ ታያት

965.መሶበ ወርቅ

መሶበ ወርቅ ዘመና እግዝእትና ማርያም ቅድስት
.2.
ቅድስተ ቅዱሳን ይብልዋ ካህናት /4/
ትርጉም መና ያለባት የወርቅ መሶብ የሆነችውን
እመቤታችንን ማርያምን ካህናት
ከቅዱሳን ይልቅ ቅድስት ነሽ እያሉ
ያመሠግኗታል፡፡

966. እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም ሆይ እለምንሻለሁ
ከልጅሽ አማልጅን /3/ ከፊትሽ ቆሜአለሁ
እባክሽ አማልጅኝ የአምላክ እናት ድንግል
ምን ጊዜም አይጠፋም/3/ ከአዳም ልጅ በደል
በደላች ብዙ ነው ልመናችን ትንሽ
ምሕረትን ጠይቂልን /3/ ድንግል ከልጅሽ

967.ወዳጄ ሆይ

ወደጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ
የታተመች ፈሳሽ እንከን የሌለሽ
የተዘጋች መቅደስ ንጹሕ አዳራሽ
ሕዝቅኤል ያየሽ የምሥራቅ በር
ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር
የልዑል ማደሪያው አማናዊት መቅደስ
ስለንጽሕናሽ ምስጋናን እናቅርብ
አዝ ----
ሁለቱንም የሆንሽ እናትና ድንግል
ማኅደረ መለኮት ወላዲተ ቃል
ያለዘርአ ብእሲ በኅቱም ድንግልና
አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና
አዝ ------
ምሥራቀ ምሥራቃት ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ
ጨረቃን የምታመስይ ፀሐይን የወለድሽ
የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሣሺ
ጽዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሺሺ
አዝ --------

968.የሰማይ የምድር

የሰማይ የምድር የአርያም ንግሥት
አንቺ ነሽ እመቤት የአምላክ እናት
ሽሽ ድንግል አማልጅኝ
ሽሽ ቅድስት ተራጂን
የሔዋን ተስፋዋ የአዳም ዘር ሕይወት
የድኅነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ ንጽሕት
የአሪት መጽናኛ የሐዲስ ኪዳን ብር
የወንጌል መሠረት የአምላክ ማኅደር
አዝ --------
የአብርሃም ድንኳን የምሥጢር ዋሻው
እናትና ድንግል ሁለቱን ሆንሽው
የኤፍሬም ውዳሴ የያሬድ ውብ ዜማ
የማትጠልቂ ፀሐይ የሃይማኖት ሻማ
አዝ --------

969.ማርያም ተዐቢ

ማርያም ተዐቢ እምኩሉ ፍጥረት /2/
ኢያውአያ እሳተ መለኮት/4/

ማርያም ትበልጣለች ከሁሉ ፍጥረት
ስለያዘች እሳተ መለኮት/4/
በመኑ በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስልኪ /2/
እምቤቴ የአምላክ እናት አዛኟ
ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ/2/

970. ነይ ነይ

ነይ ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ
የጻድቃን እመቤት
የመላእክት እህት/2/
ሁላችሁ እመኗት ከልብ አማላጅ ናትና
በእውነት እናመስግናት እናወድሳት
አማላጅ ኪዳነምሕረት/2/

971 **በልዑል መጠጊያ**

በልዑል መጠጊያ የሚኖር በልዑል መጠጊያ/2/
ይከልላል ከክፉ/2/
አንደበቱን ከኃጢአት ከልክሎ አምላኩን ካሰበ
ካልተመጻደቀ በሥራው ራሱን ካልካበ
ይከለላል ከክፉ/2/
ጨርቁን ማቁን ሳይል ራሱን ለአምላኩ ከሰጠ
በዓለም ምደራዊ ሀብት ተታሎ አምላኩን ካልሸጠ
ይከለላል ከክፉ /2/
እስከመጨረሻው ለመኖር በእምነቱ ከጸና
ካላፈገፈገ ከአምላኩ ሲገጥመው ፈተና
ይከለላል ከክፉ/2/

972 ወትቀውም ንግሥት

ውትቀውም ንግሥት /2/ በየማንከ /2
ኸኸ በአልበስ ወርቅ /3/ ዑጽፍት በአልባሰ ወርቅ /2/
ትርጉም፡- ንግሥቲቱ የወርቅ ልብስ ተጎናጽፋ በቀኝህ ትቆማለች

973. ስአሊ ለነ ማርያም

ስአሊ ለነ ማርያም ሰአሊለነ /2/
አክሊለ ንጹሐን /2 ሰአሊለነ /4
ለምኝልን ማርያም ለምኝልን /2
የንጹሐን አክሊል /2 ለምኝልን /4

974. ንጽሕተ ንጹሐን

ንጽሕተ ንጹሐን ከዊና ከመታቦት ዘዶር ዘሲና
ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግልና ነበረት/2/
ሲሣያ ኅብስተ መና ወስቴሃኒ ስቴ ጽሙና 2/
ትርጉም፡- ከንጹሐን ንጹሕ ሆና በሲና እንደነበረች ታቦት በንጽሕና በቤተ መቅደስ ውስጥ ኖረች ምግቧም ኅብስተ መና መጠጧም የጸጥታ መጠጥ ነበረ

**975.አቀድም አእኩቶቶ**

አቀድም አእኩቶቶ ለእግዚአብሔር /2/
በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ /2/

**976.ሰላም ሰላም**

ሰላም ሰላም /2/ ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑት ድኅነት ያሰጣል /2/
ደቀ መዛሙርቱ በሐሳብ ሲዋኙ
በጽኑ ጾማቸው ምልክት አገኙ
አዝ . . .
ለእኛ ወገኖችሽ ኃጢአት ላደከመን
ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን
አዝ . . .
ምሕና በኢያቄም እመቤታችን
በዚህች ቀን ባርኪልን ማኅበራችንን
አዝ . . .

**977.ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ**

ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ ይገባዋል ምስጋና
በሰላም በጤና ጠብቆናልና
እስከዚህችም ሰዓት አድርሶናልና
ይገባዋል ለአምላካችን ምስጋና

**978.ማን እንደ እርሱ**

ማን እንደ እርሱ እንደ እግዚአብሔር
ቸርነቱ ብዙ በሰማይ በምድር
ሞገድና ነፋስ የሚታዘዙለት
አብርሕት ቀላያት የመሰከሩለት

ጎቱም መቃብርን ሳይከፍት የተነሣ
ነፍሳትን ያዳነ ከሲዖል አበሳ
አዝ . . .
ፈዋሴ ድውያን ቸርነቱ ብዙ
የጸጋ ልብሳቸው ጽድቅን ለታረዙ
የተዋረዱትን ከፍ ከፍ የሚያደርግ
ለባልቴቷ ዳኛ ፈራጅ ለድሃ አደግ
አዝ . . .
የጠፋውን አዳም ሊፈልግ የመጣ
ከባርነት ዓለም ከጽልመት ያወጣ
ብርሃን ዘበአማን ጨለማን ያራቀ
ሰውን ከራሱ ጋር ሞቶ ያስታረቀ
አዝ . . .
በመከራ ሳሉ ሕዝቦቹን ያሰበ
ሥጋውና ደሙን ቆርሶ የመገበ
ከባቱ አበሳ ምሕረቱ የበዛ
ጌታችን እርሱ ነው የሁላችን ቤዛ
አዝ . . .

**979. ድንቅ ነው**

ድንቅ ነው ልዩ ነው ልዑል የእኛ ጌታ
ምስጋና ይድረሰው ከጠዋት እስከ ማታ /2/
የማይመረመረው በሰው ልጅ ኅሊና
ረቂቅ ባሕርይ ገናና ነውና
ያለ የነበረ ከዘመናት በፊት
ለዘለዓለም ኗሪ ፈጣሪ ዓለማት
አዝ . . .
በፍጥረቱ ሁሉ የሚመሰገነው
ኃያሉ ጌታችን በእውነት ግሩም ነው
በፍጹም ልዩ ነው የእርሱ ጌትነቱ
አልፋና ዖሜጋ ጽኑ ነው መንግሥቱ
አዝ . . .
በመላእክት ዓለም በሰማይ ከተማ
ለክብሩ ሲዘምር ማኅሌት ሲሰማ
ያለምንም እረፍት በቀንና ሌሊት
ንጹሐን መላእክት የሚያመሰግኑት
አዝ . . .
አዳምን ለማዳን ፍጹም በመውደዱ
የማይሞተው አምላክ ሞተ በፈቃዱ
ምሥጢሩ ረቂቅ ነው ለሰዎች አዕምሮ
ፍቅሩ ያስደንቃል ስናየው በአንክሮ
አዝ . . .

**980.መድኃኔዓለም ወሀቤ ሰላም**

መድኃኔዓለም ወሀቤ ሰላም /2/
ይክበር ይመስገን ለዘለዓለም /2/

**981.እስጢፋኖስ ሰማዕት**

እስጢፋኖስ ሰማዕት ሊቀ ዲያቆናት ለምዕመናን
የተሾምክ/2/
የአምላክህን ትዕዛዝ በሥራ የፈጸምክ/4/

**982.ኢየሱስ ክርስቶስ**

ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል ይጠብቀናል
እርሱ ለእኛ ደሙን ክሶልናል/4/

**983. ኢያቄም ወሐና**

ኢያቄም ወሐና እናት አባትሽ
ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት የሰጡሽ
መና ከሰማያት የወረደልሽ
ፍጹም ድንግል የሆንሽ ማርያም አንቺ ነሽ /2/
ኦ-ወላዲተ አምላክ ማርያም አንቺ ነሽ /እኛ ደሙን
ክሶልናል /2/

**984. መሶበ ወርቅ**

መሶበ ወርቅ ዘመና አጋእዚት ማርያም ቅድስት /2/
<u>ቅድስተ ቅዱሳን ይብልዋ ካህናት</u> (2) ይብልዋ /2/
**ትርጉም:-** መና ያለብሽ የወርቅ መሶብ ቅድስት
እመቤታችን ማርያምን ካህናት ከተለዩ የተለየች
ይሏታል።

**985. ወእንዘ ትፌትል**

ወእንዘ ትፌትል /2/ ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ
ገብርኤል ግብተ /2/
ወይቤላ ወይቤላ እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ
እግዚአብሔር

**986. እመቤታችን ለአንቺ**

እመቤታችን ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል/2/
ከሴቶች ሁሉ /3/ ተመርጠሻል
እያረጋጊት የሠማይ መላእክት /2/
ቤተ መቅደስ ኖረች /3/ አሥራ ሁለት ዓመት

አዝ . . .
ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈል/2/
በእርሷ ላይ አደረ /3/ አካላዊ ቃል
አዝ . . .
መንፈስቅዱስም እንዳልተለያት አውቆ
ሰገዳላት /3/ ዘካርያስ ታጥቆ
አዝ . . .
መንፈስቅዱስም እንዳልተለያት አውቃ/2/
ተሳለመቻት /3/ ኤልሳቤጥ ተደንቃ
አዝ . . .

**987. እመአምላክ ሙሽራ ነሽ**

እመአምላክ ሙሽራ ነሽ
ለቃል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ /2/ ኧኸ
አሥራ ሁለት ዓመት በቤተመቅደስ የኖርሽ
የመመረጥ ጸጋ ከጌታ አገኘሽ
በአብሣሪው መልአክ እጹብ ድንቅ ዜና
ከሰማይ መጣልሽ አቋርጦ ደመና
በስድስተኛው ወር ተልኮ ገብርኤል
ቤተ መቅደስ ገባ ሊያበሥራት ለድንግል
በልዩ ሰላምታ ሰላም ለኪ ያለሽ
የክርስቶስ እናት በጣም ደስ ይበልሽ
መላእክት በሰማይ ያመሰግኑሻል
ክብር ለአምላክ እናት ይድረሳት ይሉሻል
በማኅፀንሽ ቢያድር የሠራዊት ጌታ
ለመሆን ተመረጥሽ የአምላክ ቅዱስ ቦታ
የፈጣሪ እናት መሆንሽን ተረድቶ
ሰላም ለአንቺ ይሁን አለሽ እጅ ነሥቶ
ከፍጡራን ሁሉ አንቺ ትበልጫለሽ
ገብርኤል ተልኮ ደስታን አበሠረሽ
ምንኛ ድንቅ ነው ድንግል የአንቺ ብሥራት
ጌታን ትወልጃለሽ የሚል ቃልን መስማት
ይሁንልኝ ብለሽ ቃሉን የተቀበልሽ
ድንግል ሆይ እናቴ እጅግ ልዩ እኮ ነሽ

**988.ተልኮ መጥቶ**

ተልኮ መጥቶ ገብርኤል /2/
ደስ ይበልሽ አላት ለድንግል /2/
ሰላም ለኪ ማርያም /2/
ጸጋን የተመላሽ በፍጹም /2/
የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ /2/
የተባረከ ነው ቅዱስ /2/

**989.ማርያም ደስ ይበልሽ**

ማርያም/3/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
በአንቺ ስለአደረ የዓለም ሁሉ ጌታ/2/
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማ ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
አዝ . . .
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሣሪ ገብርኤል ነበረ
አዝ . . .
ድንግል ተቀምጣ በቤተመቅደስ
ሐርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል
አዝ . . .
ገብርኤል /2/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክ መወለድ ሥጋ በመልበስ
አዝ - - -
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ በመንክር ግርማ
አዝ . . .
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

**990.እመቤቴ ጥላ ከለላዬ**

እመቤቴ ጥላ ከለላዬ ረዳቴ የገነት ሙሽራ /2/
የገነት ሙሽራ /3/ ማርያም የልዑል ማደሪያ
መጣ በነቢያት ቃል አብ ተሰብኮ
በስድስተኛው ወር ገብርኤል ተልኮ
ቤተመቅደስ ሳለች ሳለች በፍጹም ትኅትና
ደሽ ይበልሽ አላት መልአኩ መጣና
በጥዑም ቃል እርሷን እያጽናና /2/
አዝ . . .
እኔ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል
ብላ ጠየቀችው በትኅትና ቃል
ገብርኤልም አላት አትፍሪ ማርያም

እግዚአብሔር ፍጹም ነው የሚሳነው የለም /2/
አዝ . . .
መንፈስ ቅዱስ ቀርቦ ይጸልልሻል
የልዑልም ኃይሉ በአንቺ ያድርብሻል
ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ
ይሆናል ዘለዓለም ዓለምን የሚዋጅ /2/
አዝ . . .
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች
በፍጹም ተዋሕዶ የአምላክ እናት ሆነች
ድንግል ማርያም በእውነት ልዩነች /2/
አዝ . . .

**991.አባ አቡነ**

አባ አቡነ አባ መምህርነ ተክለሃይማኖት /2/
እመ አዕላፍ ኅሩይ (2) ተክለሃይማኖት /2/

**992.. አንቺ ቤተልሔም / በመቀባበል /**

አንቺ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ መሬት
ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኃኒት
ለአዳም ክብር ሲሻ ቤተልሔም
ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም
ዛሬ ተወለደ ቤተልሔም
ከድንግል ማርያም ቤተልሔም
አዝ . . .
እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም
የምሥራቅ ነገሥታት ቤተልሔም
በከብቶች በረት ቤተልሔም
ተኝቶ ሳገኙት ቤተልሔም
አዝ . . .
እስራኤል ሕዝቤን ቤተልሔም
የሚጠብቃቸው ቤተልሔም
ከአንቺ ይወጣል ብሎ ቤተልሔም
እንደነገራቸው ቤተልሔም
አዝ . . .

**993.የጥበብ ሰዎች መጡ**

<u>የጥበብ ሰዎች መጡ</u> (2) ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደፋና /2/
ሰማይና ምድር የማይወስኑት /2/
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት /2/
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ /2/
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ /2/
አዝ . . .
ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ /2/
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ /2/
ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን /2/
ኩነኔን አጥፍቶ ክብርን ሊያወርሰን /2/
አዝ . . .
ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም /2/
ኀዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም /2/
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት/2/
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት /2/
አዝ . . .
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ /2/
የእስራኤል ንጉሥ ወዴት ነው እያሉ /2/
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ /2/
እጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ /2/
አዝ . . .

**994.ሣር ቅጠሉ ሰርዶው**

ሣር ቅጠሉ ሰርዶው ሰንበሌጥ ቁጤማው
በዚያች ወር በዚያች ቀን ለምልሞ የነበረው
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተሞልተው
ጌታ መወለዱን የምሥራች ሰምተው
እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ /2/
ያ ትጉህ እረኛ ሳለ በትጋት
ብርሃንን ለበሰ በእኩለ ሌሊት
ጥሪ ተደርጎለት ከሰማይ ሠራዊት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
አዝ . . .
የእረኝነት ሥራ ተንቆ እንዲቀር
ብሎ ሰው በልማድ ደንግጎ ነበር
አምላክ የመረጠው መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ
አዝ . . .
የተነበዩለት ነቢያት በሙሉ
ጌታ ተወለደ የምሥራች በሉ
ሰውን በመውደዱ ሰማያዊው ንጉሥ
ዶኾው ተወለደ እኛን ሊመቀደስ

አዝ . . .
የሩቅ ምሥራቅ ሰዎች ሰብአ ሰገል ሰምተው
ሊሰግዱለት መጡ በኮከብ ተመርተው
ዕጣንና ከርቤ ወርቁንም አመጡ
እንደየሥርዓቱ እጅ መንሻ ሰጡ
አዝ . . .
ስለተወለደ መድኅን የእኛ ተስፋ /2/
በደል ተወገደ ኃጢአትም ጠፋ /2/

**995.እሰይ እሰይ ተወለደ**

እሰይ እሰይ ተወለደ /2/
ከሰማየ ሰማያት ወረደ
ከድንግል ማርያም ተወለደ
እሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ ቸሩ አባታችን እሰይ እሰይ
መች ትገኝ ነበር እሰይ እሰይ ገነት ምድራችን እሰይ እሰይ
አዝ . . .
ብርሃን ወጣላቸው እሰይ እሰይ ለመላ ሕዝቦቹ እሰይ እሰይ
በጨለማ ጉዞ እሰይ እሰይ እንዲያ ሲሰላቹ እሰይ እሰይ
አዝ . . .
እንደ ጠል ወረደ እሰይ እሰይ ከሰማይ ወደ እኛ እሰይ እሰይ
ወገኖቹን ሊያድን እሰይ እሰይ ከኃጢያት ቁራኛ እሰይ እሰይ
አዝ . . .
እግዚአብሔር አብ ላከ እሰይ እሰይ አንድያ ልጁን እሰይ እሰይ
እርሱ ወዷልና እሰይ እሰይ እንዲሁ ዓለሙን እሰይ እሰይ
አዝ . . .

**996.ግነዩ ለእግዚአብሔር**

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር /2/
እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም /4/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ /2/
የዓለም ቤዛ ነውና የማኅፀንሽ ፍሬ /4/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ካንቺ ተወልዶ /2/
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ /4/
በድንግልናሽ የወለድሽው ክርስቶስ /2/
የድኩማኖች ብርታት ነው የህሙማን ፈውስ /4/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችን ፋቀ /2/
በቸርነቱ ጠብቆ ከበደል አራቀን /4/
ስምሽን የጠራ ዝክርህንም ያዘከረ /2/
በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ /4/
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ /2/
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ /4/
እመቤታችን እናታችን ማርያም /2/
የተማፀነሽ ይድናል ለዘለዓለም /4/
ድንግልናሽ ሳይለወጥ ወልድን የወለድሽ /2/
የጌታችን እናት ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ
የጌታችን እናት ማርያም ንጽሕት አንቺ ነሽ

**997.በጎል በጎል**

በጎል በጎል ሰበአ ሰገል /4/
በጎል ሰብአ ሰገል ሰገዱለት /4/
ፀሐይ /2/ ፀሐይ ሠረቀ /2/
ፀሐይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ /4/
አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ /4/
የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶልሽ
የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ
ድንግል ማርያም ንጽሕት ቅድስት /4/
የጌታ እናት ምስጋና ይገባሻል
ከሴቶች ሁሉ አንቺን መርጦሻል
እልል እልል ደስ ይበለን /2/
ወልድ ተወልዶ ነጻ ወጣን
ዮሐንስ ሲያጠምቀው ድል አገኘን

**998.አምላክ ለእኛ ብሎ**

አምላክ ለእኛ ብሎ ቃል ኪዳን የሰጣት /2/
የኃጥአን አማላጅ ድንግል ማርያም ናት /4/
እንደ አማለድሽው በላዔ ሰብእን /2/
እኛንም እባክህ አደራ አማልጅን /4/
ምሕረት እንድናገኝ ከአምላካችን /2/
አማላጅ ሁኚልን እመቤታችን /4/

ከአንቺ በተገኘው በመልካሙ ፍሬ /2/
ዓለም ተቀድሷል ነጻ ወጥቷል ዛሬ /4/
ስምሽ ግርማ ያለው ኪዳነምሕረት /2/
የሰዎች አማላጅ የጌታዬ እናት /4/
ካህናት በክበሮ ሲያመሰግኑሽ /2/
እኛም በእልልታ እንዘምርልሽ /4/

**999. አንቺ ነሽ ተስፋው**

አንቺ ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነምሕረት/2/
በተሰደደ ጊዜ ከገነት /2/

**1000.ሰላም ለኪ**

ሰላም ሰላም ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ /2/
የሕይወት መሠረት ሰላም ለኪ
የፍጥረት አለኝታ ሰላም ለኪ
ድንግል አደራሽን ሰላም ለኪ
ሁኝልን መከታ ሰላም ለኪ
አዝ . . .
በላዔ ሰብእ ዳነ ሰላም ለኪ
ብዙ ነፍስ አጥፍቶ ሰላም ለኪ
የአንቺን ስም ለጠራ ሰላም ለኪ
ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ ሰላም ለኪ
አዝ . . .
ተማጽነንብሻል ሰላም ለኪ
በአማላጅነትሽ ሰላም ለኪ
ድንግል ሆይ አደራ ሰላም ለኪ
አማልጅን ከልጅሽ ሰላም ለኪ
አዝ . . .
እኛ ብንከተል ሰላም ለኪ
በጎ ምግባርን ሰላም ለኪ
በሰላም በጤና ሰላም ለኪ
እንኖራለን ሰላም ለኪ
አዝ . . .

**1001. በዮናስ ስብከት**

ነነዌን ሊያቃጥል የወረደው እሳት /2/
ተመልሶ አረገ /2 በኀዘን በጸሎት /2/
ስለሆነ ከልብ የኀዘናቸው ምንጩ /2/
ነበር እንደ ራሔል እንባን እየረጩ /2/
የነነዌ ሰዎች ደስታን ያበሠረ /2/
ጋሻና ጦራቸው /2/ ጾም ጸሎት ነበረ /2/
እንኳን የሰው ልጆች እንስሳት ሳይቀሩ /2/
በዮናስ ስብከት /2/ ጾም ጸሎት ተማሩ /2/

**1002. የነፍሳችን ቤዛ**

የነፍሳችን ቤዛ የቅዱሳን ሀብት /2/
ጸጋን የሚያሰጠን ጾም ነው መድኃኒት /2/
የእስራኤል ልጆች በሙሴ ሲመሩ /2/
በፍጹም ጸሎት ባሕርን ተሻገሩ /2/
ቅዱሳን አባቶች ጾም ነው ጋሻቸው /2/
ወደ ሕይወት መንገድ የሚመራቸው /2/
ክፍላችን እንዲሆን ከቅዱሳን ጋራ /2/
ፍቅር ቤታችንን በጸሎት እንሥራ /2/
ልባችንም ይሁን የጸሎት ጎዳና/2/
የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድንወርስ በጤና /2/

**1003. ፍቅርና ሰላምን**

ፍቅርና ሰላምን ታፈራለች ጾም /2/
ፍጻሜ የሌለው <u>እስከ ዘለዓለም</u> /2/
የጾምንም ፍሬ ሁላችን አውቀን /2/
ለጸሎት እንትጋ <u>ፍሬው አይለፈን</u> /2/
አምላክ ተፈተነ በክፉ ጠላት /2/
ጾምን ሲመሠርት <u>ስለእኛ ሕይወት</u>/2/
አምላክ ተሸከመ ህመማችንን/2/
የሕይወትን ውኃ <u>ከጎኑ ሰጠን</u> /2/
ሕዝቦችህን ጠብቅ ከክፉ ፈተና /2/
ቅዱስ አምላካችን <u>ኃይላችን ነህና</u> /2/

**1004.ጾም ታድናለች**

ነቢዩ ዳንኤል በጾም ስላመነ /2/
ከአንበሶች ጉድጓድ ሕይወቱን አዳነ/2/
ኤልያስ የወጣ በእሳት ሠረገላ /2/
በጾም በጸሎት ነው አይደለም በሌላ/2/
የነፍስንም ቁስል ጾም ታድናለች /2/
የሥጋን ፍላጎት እያደከመች /2/
እስቲ ልብ እናድርግ እናስተውል ደግሞ/2/
ጌታ ለሐዋርያት ያላቸውን ቀድሞ /2/
ይህ ርኩስ መንፈስ ሊወጣ የሚችል/2/
በጾም በጸሎት ነው እንደ ወንጌሉ ቃል /2/

**1005.የአብርሐም አምላክ**

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ

ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ የሐሰት ምስክር
አቁመው ከሰሱት
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት
ጲላጦስ ገረፈው በሠንሠለት አሥሮ
በአይሁድ መካከል እንዲኖር ተከብሮ
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ
በችንካር ላይ ቆሙ ምንም አልሰለቹ
የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ
የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ

**1006.እም እቶነ እሳት**

እም እቶነ እሳት ዘይነድድ አንገፈነ /2/
ብርሃናተ ዘይትአጸፍ ተንሥአ ለነ /2/
ከሚነደው እሳት ከነበልባሉ አወጣን /2/
ብርሃናትን ተጎናጽፎ ተነሣልን /2/

**1007.የድሆች መጠጊያ**

የድሆች መጠጊያ ቤተ ክርስቲያን
ለመማር መጥተናል ስምተን ቃልሽን /2/
ሰላም ሰላም የዘለዓለም ቤቴ /2/
ከአንቺ አልለይም እስከዕለተ ሞቴ
ሰላም ለአንቺ ይሁን ቤተክርስቲያን
በደሙ ያጸናሽ ኢየሱስ መድኅን /2/
አዝ . . .
ቤተ ክርስቲያን ሆይ የአማንያን እናት
ወደ አንቺ ቀርበናል እንድናገኝ ሕይወት /2/
አዝ . . .
ቅረቡ ምዕመናን በአንድነት ሆናችሁ
እጆቿን ዘርግታ ልትቀበላችሁ
ተነሥታለችና ቅድስት እናታችሁ
አዝ . . .

**1008. ያከብርዋ ለሰንበት**

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት ጻድቃን
በውስተ ገነት /2/
ወኲሉ ፍጥረት ዓሣት ወአናብርት እለ ውስተ
ደይን ያዕረፉ ባቲ እስመ ባቲ አዕረፈ እም ኲሉ
ግብሩ /2/
ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት ጻድቃንም
በገነት /2/
ፍጥረታት በሙሉ ዓሳዎችና አንበሪዎች በመቃብር ያሉ
ያከብሯታል አምላክ በእርሷ እንዳረፈ ከሥራው ሁሉ /2/

**1009. ኲሎ ዘፈቀደ**

ኲሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር /2/
በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ ወበኲሉ ቀላያት
ቀላያት /2/
ትርጉም ፦ እግዚአብሔር በሰማይና በምድር
በባሕርም በፈሳሾችም ሁሉ የወደደውን አደረገ

**1010.የሥላሴን መንበር**

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሐል ሚካኤልንከፊት
አእላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩ ተመልከቱት የሰማዩን አባት /2/
የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ
ይህን ታላቅ ክብር ሊያዩ የታደሉ
በጽድቅ ሥራቸው ደምቀው ይታያሉ /2/
አዝ . . .
የቅዱሳን ኅብረት የቅዱሳን ሀገር
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር
ጽድቅና ርኅራኄ የተሞላ ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ /2/
አዝ . . .

**1011.ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ**

ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ ይገባዋል ምስጋና
በሰላም በጤና ጠብቆናልና
እስከዚህችም ሰዓት አድርሶናልና
ይገባዋል ለአምላካችን ምስጋና

**1012.ልዑል እግዚአብሔር**

ልዑል እግዚአብሔር /2/ ምስጋና ይገባሃል /2/
ለዚች ዕለት ለዚች ሰዓት በሰላም በጤና
አደረስከን

**1013. እናመስግን አማኑኤልን**

እናመስግን አማኑኤልን የሞተልንን ጌታ /2/

ሞትን በሞቱ ሻረልን እንዳንረታ /2/

**1014.ወደ ቤተ እግዚአብሔር**

ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሒድ ሲሉኝ /2/
እንደ ዳዊት እንደ ንጉሡ ተደሰትኩኝ /4/
መላእክት በሰማይ የሚያመሰግኑህ /2/
አምላካችን ፈቃድህ ይሁን እንዘምርልህ /4/
ሞትን አሸንፎ ለተነሣው ጌታ /2/
ዘምሩለት ተቀኙለት ጠዋትና ማታ/4/
በመስቀል ላይ ሆኖ ሲወጋ ጎኑን /2/
ውኃና ደም በአንድ ላይ ሆኖ ፈሰሰልን /4/
በውኃው ተጠምቀን ደሙን ጠጥተን
መንግሥቱን እንድንወርስ ስላደረገን
ስሙ ይመስገን የጌታችን
ስሙ ይመስገን የአምላካችን

**1015.ቅዱስ**

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር
ለአማልክት አምላክ እናቅርብለት ምስጋና
ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና
ለነገሥታት ንጉሥ እናቅርብለት
ምስጋና
የእስራኤል አምላክ ቅዱስ /3/
በጠራንህ ጊዜ ፈጥነህ ድረስ /3/
ተገዙ ለእግዚአብሔር ስሙንም ጥሩ
ድንቅ ሥራውንም ለአሕዛብ ንገሩ
በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ
ይመግባልና ሁሉን አስተካክሎ
አትወድምና የሰው ልጆችን ጥፋት
አቤቱ ጸሎቴን ስማ በያሬዳዊ ዜማ

**1016.ተናገሩ**

ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ /2/
ተአምሩን ለዓለም ንገሩ (2) ድንቅ ሥራውን
መስክሩ /2/

**1017.ለጌታዬ ለእግዚአብሔር**

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን
እከፍለዋለሁ /2/
ተመስገን ነው እንጂ /2/ ሌላ ምን እላለሁ /4/

**1018.የተዘጋች መቅደስ**

ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ
የታተመች ፈሳሽ እንከን የሌለሽ
የተዘጋች መቅደስ ንጽሕት አዳራሽ
ሕዝቅኤል ያየሽ የምሥራቋ በር
ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር
የልዑል ማደሪያ አማናዊት መቅደስ
ስለ ንጽሕናሽ ምስጋናን እናድርስ
አዝ . . .
ሁለቱንም የሆንሽ እናትና ድንግል
ማኅደረ መለኮት ወላዲተ ቃል
ያለ ዘርአ ብእሲ በጎኑም ድንግልና
አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና
አዝ . . .
ምሥራቀ ምሥራቃት ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ
ጨረቃን የምትመስይ ፀሐይን የወለድሽ
የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሳሺ
ጽዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሸሺ
አዝ . . .

**1019.ቀስተ ደመናው**

የኖኅ ቃል ኪዳኑ ምልክት ዓርማው
የመዳኑ ምሥጢር የሰላም ተስፋው
እመቤቴ አንቺ ነሽ ቀስተ ደመናው (2)
አንቺ የአሮን በትር ሳይተክሏት ያደገች
የማክሰኞ እርሻ ያለዘር ያፈራች
የሲና ሐመልማል የተዋሕዶ ምሥጢር
ክብርት እመቤቴ ሀገረ እግዚአብሔር (2)
አዝ . . .
ዳዊት መሰንቆ የያሬድ ጸናጽል
የደካሞች ምርኩዝ የሰሎሞን አክሊል
ሰላሜ ተስፋዬ የሐዘኔ ደራሽ
የጽዮን ተራራ መሸሸጊያዬ ነሽ (2)
አዝ . . .
የኤልሳዕ ማሰሮ ጨው የተገኘብሽ
የሕዝቅኤል ራእይ ንጽሕት አዳራሽ
አንቺ የአዳም ተስፋ የመዳኑ ብሥራት
አንቀጸ ብርሃን ነሽ የአማኑኤል እናት(2)
አዝ . . .

**1020.ሰላም ለኪ**

ሰላም ለኪ /2/
ለኖኅ ሐመሩ ሰላም ለኪ

ለአሮን በትሩ ሰላም ለኪ
ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ
ለጌዴዎን ፀምሩ ሰላም ለኪ
ለሰሎሞን መንበረ ክብሩ ሰላም ለኪ
ለፍሬ ስብሐት መዖሩ ሰላም ለኪ
ለፍሬ ስብሐት መዖሩ
እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ
ሰላም ለኪ
ሠረገላሁ ለአሚናዳብ ሰላም ለኪ
መና ያለብሽ ንጹሕ መሶብ ሰላም ለኪ
ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ ሰላም ለኪ
የይስሐቅ መዓዛ ሰላም ለኪ
የይስሐቅ መዓዛ
እንዘ ንሴፊዎ ለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ ንሰግድ ለኪ /2/
ሰላም ለኪ
ኅብስተ መና ዘእስራኤል ሰላም ለኪ
የሰማዕታት ንጹህ አክሊል ሰላም ለኪ
ዕፀ ጳጦስ ዘሲና ሰላም ለኪ
የኤልያስ መና ሰላም ለኪ
የኤልያስ መና
እንዘ ንሴፊዎ ለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ ንሰግድ ለኪ /2/

**1021.የወርቅ መሰላል ነሽ**

ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ
መሰላል ነሽ የወርቅ መሰላል ነሽ
ሰውና አምላክን ያገናኘሽ
አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ /2/
አሽልቦት እንቅልፍ ተኝቶ ከጤዛ
ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርስ መሰላል
ምሳሌሽን አየን ማርያም ድንግል
አዝ . . .
መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ከሰማይ /2/
እንደ ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ላይ
ተስፋ አድርጎ ሲኖር የሰላሙን ዘመን
ይኸው ተፈጸመ በአንቺ በእናታችን
አዝ . . .
በአንቺና በልጅሽ ሆነልን ሰላም /2/
በአንቺ ተፈጸመ የያዕቆብ ሕልም
ሰውና መላዕክት ተለያይተው ሲኖሩ
በልጅሽ መወለድ በአንድ ላይ ዘመሩ
አዝ . . .

**1022.አንቺ የወይን ሐረግ**

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ /2/
ምግብ ሆኖ /2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለእኛ ቤዛ /2/
ኧኸ
በአንቺ ሰማይነት ድንግል የወጣው ፀሐይ /2/
ብርሃን ነው /2/ ለጻድቃን ስሙም አዶናይ /2/ ኧኸ
ፊደል ትመስያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ /2/
ለመላእክት /2/ የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ /2/
ኧኸ
የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኮከብ መገኛ /2/
በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለእኛ /2/
ኧኸ
አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ 22/
ምግብ ሆኖ /2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለእኛ ቤዛ /2/ ኧኸ

**1023.እናታችን ጽዮን**

እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና
መጠጊያ ማረፊያ ጥላችን ነሽና
ከገነት ብንወጣ ማረፊያ ሆንሽን
የምሕረት ደመና ውኃ ሰጠሽን
የሕይወት እንጀራ አመጣሽልን
በአሥራትም በአደራ ለአንቺ ተሰጠን
አዝ . . .
የኤልሳቤጥ አጽናኝ የጭንቅ ቀን ደራሽ
የኃጢአታችን ብዛት ዳገት ሳይሆንብሽ
ምሥራችን ደስታ ይዘሽልን መጣሽ
ማርያም ስንልሽ ደረሽልን ፈጥነሽ
አዝ . . .
ውለታሽ ብዙ ነው ከልብ የማይጠፋ
ስምሽ መጽናኛ ነው አዝኖ ለተከፋ
በእንተ ማርያም ብሎ ለለመነ
የሰማይ የምድሩም ማንም አልጨከነ
አዝ . . .
በትራችን አንቺ ነሽ የምትደግፊን
ባሕረ እሳትን የምታሳልፊን

ጽርሐ ሥላሴ ነሽ ማኅደረ መለኮት
ሁል ጊዜ አንጠግብሽም እንላለን ብጽእት
አዝ . . .

**1024.መሠረተ ሕይወት**

መሠረተ ሕይወት ማርያም በረድኤት ነይ /2/
ምሕረት ቸርነትን ይዘሽ ከሰማይ (2)
ማርያም ድንግል በረድኤት ነይ

**1025.እንተ በምድር**

እንተ በምድር ሥረዊሃ ወበሰማይ አዕፁቂሃ /2/
ሐረገ ወይን /2/ ድንግል ሐረገ ወይን /2/
**ትርጉም** :- እመቤታችን ሥሯ በምድር
ቅርንጫፏ በሰማይ የሆነ የወይን ሐረግ ናት

**1026.ማርያም ንጽሕት**

ማርያም ንጽሕት ድንግል ማእምንት ወላዲተ
አምላክ ሰአሊተ ምሕረት ለዉሉደ ሰብእ /2/
ሰአሊ ለነ ኀበ ክርስቶስ ወልድኪ ይሥረይ
ኃጢአተነ ሰአሊ ለነ ቅድስት /2/
ማርያም ንጽሕት ድንግል ታማኝ አምላክን
የወለድሽ የምሕረት አማላጅ ለሰው ልጆች /2/
አማልጅን ከልጅሽ ከክርስቶስ ይቅር እንዲለን
ቅድስት ሆይ ለምኚልን /2/

**1027.የኪዳን ጽላት**

የኪዳን ጽላት የተሠወረ መና ያለብሽ ደብተራ
ድንካን አንቺ ነሽ /2/
ይኸውም መና የተባለው /2/ በድንግል ማርያም
ያደረው የእግዚአብሔር ልጁ ነው /2/

**1028.ማርያም ተአቢ**

ማርያም ተዐቢ እም ኵሉ ፍጥረት /2/
ኢያውአያ እሳተ መለኮት /4/
**ትርጉም** :-

**1029.እምነ እምነ ንኢ**

እምነ እምነ ንኢ /4/
በሰላም /2/ ንኢ ማርያም /2/
አምላክ ንአ ንአ /2/
በሰላም /2/ አምላክ ንአ /2/
**ትርጉም** :-

**1030.የጠሩሽ**

የጠሩሽ አንቺን ተማጽው የዳኑብሽ
የበላኤ ሰብእ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት
በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽም ጽድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አውቀዋል /2/
አዝ . . .
የእሳት ባሕርን በአንቺ ተሻግረዋል
የሰጣይንን ጦር በአንቺ ድል ነሥተዋል
ለሰማያዊው ክብር በቅተዋል /2/
አዝ . . .
ተስፋቸውንም ጽድቅን አግኝታለች
ሕይወታቸውም በአንቺ ትድናለች
ድንግል ሆይ አትጣይን ስላለች /2/
አዝ . . .
እኔም በአንቺ እታመናለሁ
የአምላክ እናት አትርሺኝ እላለሁ
በአማላጅነትሽ እድናለሁ /2/
አዝ . . .
እኛም በአንቺ እንታመናለን
የአምላክ እናት አሳስቢ እንላለን
በአማላጅነትሽ እንድናለን /2/
አዝ . . .
ምዕመናንም በአንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢ ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናሉ /2/
አዝ . . .

**1031.ነይ ነይ**

ነይ ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ የጻድቃን እመቤት
የመላእክት እህት /2/
ሁላችሁ እመኗት ከልብ አማላጅ ናትና በእውነት
እናመስግናት እናወድሳት አማላጅ ኪዳነምሕረት /2/

**1032. በምድራዊ ሕይወት**

በምድራዊ ሕይወት /2/ በፈተና ቦታ /2/
ማርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ
ድንግል ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ /2/

**1033.ኪዳነ ምሕረት እመቤት**

ኪዳነ ምሕረት እመቤት
ለዓለም ሁሉ መድኃኒት
ቅድስተ ቅዱሳን ብፅዕት
አንቺ ነሽ ለአምላካችን እናት
ጌታችን ፈጠረሽ ልዩ አድርጎ
በሚያስደንቅ ምሥጢሩ ተዋሕዶ
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ
ያለ ሕማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ
እናትነት ድንግልና
አስተባብረሽ ይዘሻልና
ድንግልም እናትም እመብርሃን
ንጽሕተ ንጹሐን እኛን አማልጂን

**1034.ማርያም ድንግል**

ማርያም ማርያም ድንግል ማርያም /2/
ርኅርኅተ ኅሊና /4/ ማርያም /2/

**1035.ማርያም ፊደል**

ማርያም ፊደል የሁሉ መማሪያ /2/
በንጽሕና በንጽሕና ተጽፋለችና /2/

**1036.ማኅደረ መለኮት**

ማኅደረ መለኮት /2/
ማርያም እመ ብዙኃን /4/
**ትርጉም** :- የመለኮት ማደሪያ የሆንሽ እመቤታችን
ማርያም የብዙኃን እናት ነሽ

**1037.በመኑ**

በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ /2/
እመቤቴ የእኔ አማላጅ አዝኝቷ ኦ ድንግል
ምልዕተ ውዳሴ
**ትርጉም** :-ማን በተመሰለው ምሳሌ እመስልሻለሁ
እመቤቴ የእኔ አማላጅ አዛኝቷ ምስጋናን የተመላሽ
ነሽ::

**1038.በምን በምን እንመስላት**

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን /2/
ምሳሌ የላትም የላትም ክብሯን የሚመጥን /2/
የሙሴ ጽላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሠላል የአብርሃም ድንካን
የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እህት የሩኅሩኃን ርግብ /2/
አዝ . . .
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌዴዎን ጸምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃን በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር /2/
አዝ . . .
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግሥት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ /2/
አዝ . . .
ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን ድረስሽ ምስጋና /2/
አዝ . . .

**1037.የመላእክት እህት**

የመላእክት እህት የሰማዕታት እናት የጻድቃን እመቤት
/2/
ለምኝልን /2/ ከልጅሽ ማርያም ድንግል /2/

**1038.እመቤታችን**

እመቤታችን ማርያም ማኅበራችንን ጠብቂልን በምልጃሽ
/2/
ከመናፍቃን ከከሃድያን ከክፉ መንፈስ ሰውረሽ
እንድትጠብቂን በምልጃሽ /2/

**1039.ይዌድስዋ**

ይዌድስዋ መላእክት /2/ ለማርያም /2/
በውስተ ውሳጤ መንጦለዕት ወይብልዋ በሐኪ ማርያም
ሐዳስዩ ጣዕዋ /2/
**ትርጉም** :- በመጋረጃ ውስጥ መላእክት ማርያምን
ያመሰግኗታል ሰላምታ ይገባሻል ማርያም አዲሲቷ
እንቦሳ ይሏታል

**1040.የአርያም ንግሥት**

የሰማይ የምድር የአርያም ንግሥት
አንቺ ነሽ እመቤት አምላክ እናት
ኧኸ /2/ ድንግል አማልጅን
ኧኸ /2/ ቅድስት ተራጅኝ
የሔዋን ተስፋዋ ለአዳም ዘር ሕይወት

የድኅነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ ንጽሕት
የኦሪት መጽናኛ የአዲስ ኪዳን በር
የወንጌል መሠረት የአምላክ ማኅደር
አዝ . . .
የአብርሃም እርሻ የምሥጢር ዋሻው
እናትና ድንግል ሁለቱን ሆንሽው
የኤፍሬም ውዳሴ የያሬድ ውብ ዜማ
የማትጠልቂ ፀሐይ የሃይማኖት ሻማ
አዝ . . .
የሰማይ የምድር የአርያም ንግሥት
አንቺ ነሽ እመቤት አምላክ እናት
አዝ . . .

**1041.ድንግል አማልጅን**

ድንግል አማልጅን ከአምላካችን
እንዳንሞት በነፍስ በሥጋችን
አደራ ድንግል ጠብቂን ልጆችሽን

**1042.ታማልደናለች**

ታማልደናለች /4/
ማርያም /2/ቤዛዊት ዓለም /2/
ሚካኤል መልአክ ሊቀ መላእክት /2/
ዘአውረደ /2/ መና ከደመና/2/
ገብርኤል መልአክ አብሣሬ ትስብዕት
ዘአብሠራ /2/ ለማርያም ንጽሕት /2/
ሩፋኤል መልአክ ሊቀ መላእክት /2/
ዘአብርሃ /2/ ዓይኑ ለጦቢት /2/
ሰሎሞን ይቤላ /2/ ርግብየ ሠናይትየ
ሰሎሞን ይቤላ
ርግብየ ሰናይትየ ሰሎሞን ይቤላ
ዑራኤል መልአክ ለዕዝራ ነቢይ /2/
ዘአስተዮ /2/ ጽዋዐ ልቡና
ገብረ መንፈስ ቅዱስ /4/
ሐዋርያ /2/ ዘእስክንድርያ /2/
ተክለ ሃይማኖት /4/
ሐዋርያ /2/ ዘኢትጵያ /2/
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ /2/
አዕማደ /2/ ቤተክርስቲያን /2/

**1043.መልአከ ሰላምነ**

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ዑራኤል /2/
ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም
**ትርጉም ፡-** የሰላም መልአክ ቅዱስ ዑራኤል ስለ እኛ
ለምንልን ጸሎታችንንም በመድኃኔዓለምፊት አሳርግልን

**1044.ኃያል ኃያል**

ኃያል ኃያል /2/
ሰዳዴ ሳጥናኤል /2/
ኃያል ገባሬ ኃይል
ባሕራን ያዳነው
ተላፊኖስን የረዳው /2/
መልአኩ ሚካኤል ነው
የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው
አዝ . . .
ከዕደ እረበናት /2/
ሦስናን ያዳናት
ሚካኤል መልአከ ምሕረት
አዝ . . .
ዲያቢሎስን ያዋረድከው
በእሳት ሰይፍ የቀጣኸው
ሚዛንህ ትክክል ነው /2/
ሚካኤል ሥራህ ድንቅ ነው
አዝ . . .
በኀዘን በትካዜ ያለሁትን ብላቴና
አጽናናኝ አረጋጋኝ /2/ ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና
አዝ . . .

**1045. የጻድቃን ከተማ**

የጻድቃን ከተማ ሆነች መንግሥትህ
አምላክ የፈጠርካት ለወገኖችህ /2/
የአራዊት ድምጽ የሌሊቱ ግርማ
በትዕግሥት አለፈ ያን ሁሉ ጨለማ /2/
ሀብት ንብረትን ተድላን ሁሉ ናቁ
መንግሥትን ብቻ ለማየት ናፈቁ /2/
ቅዱሳን እጆችህ ሰውን የፈጠሩ
ለሰው ልጆች ሲሉ በሐብል ታሠሩ /2/
ይህንን ሁሉ ነፍስ ቅዱሳንም አይተው
በኀዘን አለፈ መላ ሕይወታቸው /2/
ምሕረትህ የበዛ ቸሩ አምላካችን

በምሕረትህ ኀብኛት ኢትዮጵያን /2/

**1046. ጻድቃን ቡሩካን**

ጻድቃን ብሩካን ዓለምን ንቃችሁ
የክርስቶስን ፈለግ የተከተላችሁ
በመንግሥተ ሰማይ እጥፍ ነው ዋጋችሁ
ሰአሉ ለነ አስተምሕሩ ለነ
እስመ በጸሎተ ጻድቅ ትጸኀን ወኢትማስን ሀገረ
ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስ ዲያቆን
ወቅዱስ ጊዮርጊስ መክብበ አሜን
ምስለ ኢየሉጣ ወቂርቆስ ሕፃን
አዝ . . .
እሥራ ወአርባእቱ ካህናተ ሰማይ
ዐጠንተ መንበሩ ለአምላክ አዱናይ
መንበረ ጸባኦት በላዕላይ
አዝ . . .
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘእም አቅሌሲያ
ወተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ
ወማርቆስ አብ ዘእስክንድርያ

**1047.ምስጋና ጀመረ**

ምሥጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ማኅሌታይ ያሬድ ዘኢትዮጵያ
ምሥጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ይበል /3/ ሃሌ ሉያ
ጥዑመ ልሳን ያሬድ /3/
ዘኢትዮጵያ
ብሉይን ከሐዲስ ሐዲስን ከብሉይ
አስተባብሮ ይዞ ያሬድ ማኅሌታይ
ምሥጢር ተገልጦለት ከምድር እስከ ሰማይ
አዝ . . .
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሥጢር እያስማማ
ምስጋና ጀመረ በእነዚህ ከተማ
ለቅድስት ሥላሴ በሦስት ዓይነት ዜማ
አዝ . . .
በገና ጸናጽል ሲመታ ከበሮ
ዜማው ሲንቆሮቆር በሰው ልጆች ጆሮ
የያሬድ ዝማሬ ያድሳል አዕምሮ
አዝ . . .
ምእመናን እናቅርብ ለአምላክ ምስጋና
በእዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና
ዜማውን ከያሬድ ተምረናልና
አዝ . . .

**1048.መዓርዒረ ቃል**

ኦ መዓርዒረ ቃል /2/
አበ ኢትዮጵያ ዘውገ ሱራፌል
የይስሐቅ አበባ መዓርዒረ ቃል የታውክልያ ፍሬ
መዓርዒረ ቃል
በኢትዮጵያ ፈካ ደምቆ ሊታይ ዛሬ
ከካህናተ ሰማይ መዓርዒረ ቃል ከሱራፌል ጋራ
መዓርዒረ ቃል
ስውር ምሥጢር አየህ በምድር ልታፈራ /2/
አዝ . . .
የሰላም መምህር መዓርዒረ ቃል የቅኔ ባለቤት መዓርዒረ ቃል
ከሰማይ ገባህ በትዕግሥትህ ብዛት
ሱራፌል ኪሩቤል መዓርዒረ ቃል የሰማይ መላእክት
መዓርዒረ ቃል
በአንተ ተደነቁ ቢያዩህ በሰማያት/2/
አዝ . . .
የብርሃን ፀዳል መዓርዒረ ቃል የዓለም ሽልማት
መዓርዒረ ቃል
ለምድር ሰገነት ነህ ለኢትዮጵያም አባት
የመላእክት አምሳል መዓርዒረ ቃል የዓለም ማኅቶት
መዓርዒረ ቃል
ልዩ ነህ ቅዱስ ነህ ያሬድ የእኛ አባት /2/
አዝ . . .
ባህር ምስጋናህ መዓርዒረ ቃል ምሥጢር ማዕበል
መዓርዒረ ቃል
እንደ ጊዮን ሞልቶ ሁሌ ይታያል
እንዴትስ ይደንቃል መዓርዒረ ቃል የአንተ ስጦታህ
መዓርዒረ ቃል
ዕፁብ ነው ! ድንቅ ነው ! ምስጋና ይድረስህ /2/
አዝ . . .
መዓዛ ቅዱሳን መዓርዒረ ቃል ሞገሰ ምዕመናን
መዓርዒረ ቃል
በኢትዮጵያ አበራ የዜማህ ወጋገን

የሕያዋን ሕያው መዓርዒረ ቃል የቅዱሳን
መኩሪያ መዓርዒረ ቃል
ትኮራብሀለች እናት ኢትዮጵያ /2/
አዝ . . .
ቤተ ክርስቲያን መዓርዒረ ቃል በአንተ ደመቀች
መዓርዒረ ቃል
በዜማ ስልቶችህ ኮርታ ተመካች
መቅረዞቿም ፈኩ መዓርዒረ ቃል ሕንፃዋም
ደመቀ መዓርዒረ ቃል
ቅጽሯም እሳት ሆነ ጠላቷም ወደቀ
አዝ . . .2/

**1049.ኦ ፍጡነ ረድኤት**

ኦ ፍጡነ ረድኤት /2/
የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊቀ
ሰማዕታት
ሰላም ለአንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት
የልዳው ፀሐይ ፍጡነ ረድኤት
በጨካኝ ንጉሥ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ ፍጡነ ረድኤት
ስቃይ ያልበገረህ ፍጡነ ረድኤት
አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሥህ/2/
አዝ . . .
የፈጣሪውን ስም ፍጡነ ረድኤት
ስለመሰከረ ፍጡነ ረድኤት
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሰይፍ ተመተረ
የስቃይ መሣሪያ ፍጡነ ረድኤት
ያላዘናጋህ ፍጡነ ረድኤት
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ /2/
አዝ . . .
ለእምነት ተጋዳይ ፍጡነ ረድኤት
ታማኝ ወታደር ፍጡነ ረድኤት
ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ስቃይ ቢያደርሱብህ ፍጡነ ረድኤት
በመታገስህ ፍጡነ ረድኤት
ሲወሳ ይኖራል ዘላለም ስምህ /2/
አዝ . . .
ለሰማው ይደንቃል ፍጡነ ረድኤት
የአንተ ሰማዕትነት ፍጡነ ረድኤት
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉ ፍጥረት
ገድልህ ይናገራል ፍጡነ ረድኤት
ክብር እንደተሰጠህ ፍጡነ ረድኤት
ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖት /2/
አዝ . . .

**1050.ኦ እስጢፋኖስ ሰማዕት**

ኦ እስጢፋኖስ ሰማዕት /2/
አክሊልን አገኘህ ከጌታ በእውነት /2/
የወንጌልን ትምህርት ቀዳሜ ሰማዕት
ስለመገብካቸው ቀዳሜ ሰማዕት
አይሁዶች ወገሩህ ጨክኖ ልባቸው
በድንጋይ ሲወግሩት ቀዳሜ ሰማዕት
በጣም ተጨነቀ ቀዳሜ ሰማዕት
ለሚወግሩት ሰዎች ይቅርታን ጠየቀ /2/
አዝ . . .
የወንጌል በር ከፋች ቀዳሜ ሰማዕት
የተባልከው ቅዱስ ቀዳሜ ሰማዕት
ተመሠከረልህ ከእውነተኛው ንጉሥ
ሥራህ ያስደስታል ቀዳሜ ሰማዕት
እጅግ ድንቅ ሥራ ቀዳሜ ሰማዕት
በአንተ ተበተነ የወንጌል አዝመራ /2/
አዝ . . .
የድቁናን ሥራ ቀዳሜ ሰማዕት
በክብር የፈጸምክ ቀዳሜ ሰማዕት
የሥላሴ ዙፋን ተከፍቶ ያየህ
የድንጋይ እሩምታ ቀዳሜ ሰማዕት
ያላዘናጋህ ቀዳሜ ሰማዕት
ቀዳሚው ሰማዕት እስጢፋኖስ ነህ /2/
አዝ . . .
ቀና ብሎ አየ ቀዳሜ ሰማዕት
ነፍሴን ተቀበለው በማለት ጸለየ
ጌታ ተቀበለው ቀዳሜ ሰማዕት
ቃሉንም ሰማለት ቀዳሜ ሰማዕት
ሰማያዊ አክሊል ወደ እርሱ ላከለት /2/
አዝ . . .

**1051.ወደ ሕይወት መንገድ**

ወደ ሕይወት መንገድ ይመራኛል ጌታ
በጨለማው መንገድ እንዳልንገላታ
ፈጣሪ ብቻ ነው ሕይወቴና ክብሬ

ለእርሱ ደስ ይለኛል ባቀርብ ዝማሬ
ጉልበት ሁሉ ላንተ በፍርሃት ይሰግዳል
ምሕረትን አድለን ፈጣሪ ቸል አትበል
የምህረትን ወኃ የተጠሙ ሁሉ
ከኃያሉ ጌታ ከአንተ ይረካሉ
በምሕረትህ ማረን አቤቱ ፈጣሪ
ለፍጥረታት ሁሉ ነህና መሐሪ /2/
ሰላምን አድላት ለኢትዮጵያ
እጆቿን ዘርግታ ስትል ሃሌ ሉያ /2/

**1052.የሰው ልጅ በኃይልህ**

የሰው ልጅ በኃልህ ፈጽሞ አትመካ /2/
አንድ አምላክ አለና በኃይሉ ኃይልን የሚለካ /2/
ኃይል እንደ ሶምሶን ከአምላክ ቢሰጥ እንጂ /2/
በጉልበት መመካት ለማንም አይበጅ /2/
ሰናክሬም ቢነሣ በሕዝቅያስ ላይ /2/
የደረሰበትን አልሰማህም ወይ /2/
ጎልያድ በኃይሉ ዳዊትን ቢንቀው /2/
አዋረደው እንጂ ኃይሉ መች ጠቀመው /2/
እንደ ዳታንና እንደ አቤሮን አይሆንም በግድ /2/
ተመርጦ ነው እንጂ ለክብር በአምላክ ፈቃድ /2/
አዝ . . .
ክህነትን ለአሮን ሕግንም ለመሴ /2/
ከሰው ሁሉ መርጠው ሰጣቸው ሥላሴ /2/
አዝ . . .

**1053.እግዚአብሔርን ጥራ**

እግዚአብሔርን ጥራ በመከራ ጊዜ
ያድንሃልና በኀዘን በትካዜ
ጋሻና ጦሬ ብለህ ምርኩዜ
እግዚአብሔርን ጥራ
አመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ
በእኩለ ሌሊት እንዳመሰገነህ ነቢዩ ዳዊት
በንጹሕ ልቡና እንደ መላእክት
እግዚአብሔርን ጥራ
በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ
እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ
ጠብና ክርክር እንዲወገዱ
እግዚአብሔርን ጥራ
እምነትን ከሥራ አስተባብረህ ከልብ
በወጣጥነትህ ፈጣሪህን አስብ
ሥራህም በሰው ፊት ይብራ እንደ ፀሐይ ይብራ እንደ ኮከብ
እግዚአብሔርን ጥራ
በቤተ ክርስቲያን ጸሎት በድንግል ኪዳን
አቤቱ ጠብቃት ኢትዮጵያን
ለሕዝቧም ስጣቸው ፍቅር አንድነትን
እግዚአብሔርን ጥራ
እለምንሃለሁ አምላኬ ሆይ አንዲት ነገር
ከቤትህ ገብቼ በደስታ እንድኖር
ከባለማሎችህ ከአብርሃም ከይስሐቅ ከያዕቆብ ጋር
እግዚአብሔርን ጥራ
ኑሮዬ ሲጨልም ግራ ሲገባኝ
ያለ ፈጣሪዬ ዘመድም የለኝ
ስወድቅ የሚያነሳኝ የሚደግፈኝ
እግዚአብሔርን ጥራ
ደርሶልኛልና በመከራ ቀን
አከብረዋለው ቅዱስ አምላኬን
እጆቼንም ይዞ የሚመራኝን
እግዚአብሔርን ጥራ
እግዚአብሔርን ጥራ በመከራ ጊዜ
ያድንሃልና በኀዘን በትካዜ
ጋሻና ጦሬ ብለህ ምርኩዜ

**1054.ይህንን ጉባኤ**

ይህንን ጉባኤ ባርክልን ጌታችን /2/
ሰላም ስጠን ፍቅርን ስጠን ዛሬ ለሁላችን /2/

**1055.ቃልህ ሲነገር ልስማ**

ቃልህ ሲነገር ልስማ ጌታሆይ እባክህ /2/
ልቤን ክፈተው /4/ የልድያን ልብ እንደከፈትከ

**1056.ሰዓሊ ለነ ማርያም**

ሰአሊ ለነ ማርያም ሰአሊ ለነ
አክሊለ ንጹሐን /3/ ሰአሊ ለነ
ለምኝልን ማርያም ለምኝልን
የንፀጹሐን አክሊል /3/ ለምኝልን

**1057. ወደ ምሥራቅ እዩ**

ወደ ምሥራቅ እዩ ወደ ፀሐይ መውጫ
ድንግልን ክበቧት እንበል ሃሌ ሉያ
ለአምላክ እናት ለአዛኝት /2/

እልል እንበል እንዘምርላት /2/

ወገኖች ተነሡ እናታችን መጣች

ስሟን ስንጠራ መቼ ትቀራለች

የተከዘ ልታጽናና ነይ ስንላት ትመጣችና /2/

የፅጌው ማኅሌት በጸሎት ሲጀመር

ማርያም ትመጣለች በደመና አየር

ንዒ ስንል በሰዓታት ልትባርከን

ትመጣለች በእውነት /2/

አዝ ----------------

ፍልሠታ ሲጀመር ቃል ኪዳን ገብታለች

የሌሊት ውዳሴን ንዒን ትሰማለች

ሕጻናትን በበረከት ልትጎበኝ

ትመጣለች በእውነት /2/

አዝ ----------------

በፍጹም ቸርነት እንዲምረን ጌታ

በአማላጅነትሽ ሁኚልን መከታ

እናታችን አለኝታችን እንድናለን

አዝ ----------------

ሃሌ ሃሌ ሉያ/2/

እስመ ዝንቱ ዑራኤል

እስመ ዝንቱ ለዓለም ብርሃን/2/

## 1058. ለምኚ ድንግል

ለምኚ ድንግል ለምኚ /2/

ለኃጥአን /3/ አይደለም ለጻድቃን /2/

ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ

» አዛኝ እሩሩ ነሽ

» የጌታዬ እናት

» ጸጋን የተሞላሽ

» የአምላክ ማደርያ

» ለምነሽ አስምሪን

» አማናዊት ጽዮን

» ከእኔ አትለይኝ

ለምኚ ሐዘንሽ አዘኚ

» ለእኔ ይሁን ድንግል

ለምኚ የተንከራተትሽው

» በሀገረ እስራኤል

» ትእግሥትሽን ሳየው

» ልቤ ይመሰጣል

» የሐዘን እንባ ጎርፍ

» ዓይኔን ይሞላዋል

ለምኚ በቀራኒዮ አንባ

» በዚያ የፍቅር ቦታ

» በእግረ መስቀሉ ስር

» ከክርስቶስ ጌታ

» ለእኛ ተሰጥተሻል

» እናት እንድትሆኝን

» ልጆችሽ ነንና

» ምልጃሽ አይለየን

ለምኚ አንደበቴን ጌታ

» በምስጋና ሙላው

» ደስ ይበልሽ ብዬ

» እኔም ላመስግናት

» አንደበቴን ጌታ

» በምስጋና ሙላው

» ደስ ይበልሽ ብዬ

» እኔም ላመስግናት

## 1059.መዓዛ አፈዋት

መዓዛ አፈዋት ማርያም /2/ ጽጌ መንግሥት ቡርክት /2/

ጽጌ ጽጌ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሀ ወአጽብሀ /2/

## 1060.እሴብሕ ጸጋኪ

እሴብሕ ጸጋኪ ኦ እግዝእትየ ማርያም

እጽ ልምልምት ወፍሬ ጥዕምት /3/

ሐረገወይን /3/ አንቲ ማርያም

አጸደ ወይን /3/ አንቲ ማርያም

ትመስሊ ፊደለ ወትወልዲ ወንጌለ ወታገምሪ መስቀለ

አዝ----------------

ትመስሊ ሰማየ ወትወልዲ ፀሐየ ወታገምሪ አዶናየ

አዝ------------------

ትመስሊ መሶበ ወትወልዲ ኮከበ ወታጸግቢ ርሁበ

አዝ----------------

ትመስሊ መቅደሰ ወትልዳ ንጉሠ ወታገምሪ መንፈስ ቅዱስ

አዝ----------------

ትመስሊ ታቦተ ወትወልዳ ጽላተ ወታገምሪ
መለኮተ

አዝ----------------

ትመስሊ ደመና ወትወልዳ ሕብሰተ መና መታገም
ጥኢና

አዝ----------------

ትመስሊ ገራህተ ወታፈርሂ ስዊተ ወታጸድቂ
ነፍሳተ

አዝ----------------

ትመስሊ ስሂነ ወትወልዲ መድኅነ ወትፌውሲ
ድውያነ

አዝ----------------

ትመስሊ ምሥራቀ ወትወልዲ መብረቀ ወታለብሲ
ርሁቀ

አዝ----------------

ለአብ መርዓቱ ለወልዱ ወላዲቱ ለመንፈስ ቅዱስ
ጽርሐ ቤቱ

አዝ----------------

**.1061. ኦ ሚካኤል**

ኦ ሚካኤል /2/ ሊቀ መላእክት
በኃጢአት እንዳንወድቅ እንዳንሞት ፈጥነህ
ተራዳን አጽናን በእምነት /2/

ለያዕቆብ ነገድ ሚካኤል
ለእስራኤል »
ጠባቂአቸው ነህ »
መላእክ ኃይል »

ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል የእኛ
አባት /2/

ነጸብራቃዊ ሚካኤል
ተክህኖ ልብስ »
ሐመልማለ ወርቅ »
ዓይኑ ዘርግብ »

ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል
የእኛ አባት /2/

በስእል ፊት ሚካኤል
እቆማለሁ »
ፈጥነህ ተራዳን »
አለሁ በለኝ »

ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል
የእኛ አባት /2/

**1062.. ቅዱስ ሚካኤል**

ቅዱስ ሚካኤል /3/ ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ሥጋዬ
ፈጥነህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ

አንተ ስለሆንክ ሚካኤል
ያአምላክ ባለሟል »
ልመናን ፈጥኖ »
ከአምላክ ያቀርባል »

የዋህ መልአክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው /2/

ደዌ የጸናበት ሚካኤል
በአንተ ይድናል »
በአደባባይህ »
ምስክር ሆኗል »

ከቤቱ መጥቶ የተማጸነ
በቃልኪዳንህ ሕይወቱ ዳነ /2/

ከአምላክ ተሰጥቶህ ሚካኤል
ክብርህ ያበራል »
ለጎስቋላው ሰው »
መጠጊያ ሆኗል »

ትልቅ ትንሹ ደሃው ሀብታሙ
ለምኖ አግኝቷል ከአምላክ በስሙ /2/

በብሉይ ኪዳን ሚካኤል
ከአምላክ ተልከህ »
ሕዝበ እስራኤልን »
ነጻ ያወጣህ »

ምሐዲስ ኪዳንም ድንቅ ሥራ አለህ
በተአምራትህ ትፈውሳለህ /2/

ባለ መድኃኒት ሚካኤል
ያቃተውን »
ፈዋሽ ጸበልህ »
ሆኖኛል ኃይል »

እንደ መፃጉዕ ድኅነት አገኘን
ፈውሰኸኛል በአንተ ተመካን /2/

**1063.. ሚካኤል አማልደን**

ሚካኤል አማደን ከአምላካችን /2/
እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን
አደራህን አማልደን ከአምላካችን

**1064.. አንተ ቅዱስ ሚካኤል**

አንተ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት የአምላክ
ባለሟል /2/
አገራችንን ጠብቅልን ዛሬም በአማላጅነትህ ፈጥነህ
ድረስላት ለኢትዮጵያ /2/

**1065. ፈተና ቢገጥማት**

ፈተና ቢገጥማት /2/ ቅድስት አፎምያ
ሚካኤል /2/ ብላ ስትጠራ /2/ ፈጥኖ አዳናት
ከጭንቅ ከመከራ /2/
ነውና እምነቷ /2/ ጽኑ ከምግባሯ
ሚካኤል መጣላት /2/ ተአምሩን ሊሠራ
ሚካኤል መጣላት /2/
ለአፎምያ ተአምሩን ሊሠራ
ፍጡነ ረድኤት መጣላት /2/ ገስግሶ /2/
እንደ ኃያልነቱ ኃይሉን አፈራርሶ /2/
በመጣበት ሄደ ተመልሶ
በእምነት ለጠሩህ /2/ ጸንተው በኃይማኖት
ቶሎ ይደርስልናል ፍጡነ ረድኤት /2/
ሚካኤል ሊቀ መላእክት

**1066.የኃያላን ኃይል**

የኃያላን ኃያል /2/ ልዑል እግዚአብሔር /2/
ተአምራተ ብዙ በሰማይ /2/ በምድር /4/
ለአብና ለወልድ /2/ ለመንፈስቅዱስ /2/
መስገድ ይገባናል በሥጋ /2/ በነፍስ /4/
ለእግዝእትነ ማርያም /2/ ለአምላክ እናት /2/
መስገድ ይገባናል የጸጋ /2/ ስግደት /2/
ለጻድቁ አባት /2/ ለተክለሃይማኖት /2/
መስገድ ይገባናል የጸጋ /2/ ስግደት /2/
ለጻድቁ አባት /2/ ለአቡነ አረጋዊ /2/
መስገድ ይገባናል የጸጋ /2/ ስግደት /4/

**1067.ንአ ንአ አማኑኤል**

ንአ ንአ አማኑኤል ንአ ንአ መድኃኔዓለም
በፍሥሐ ወበሰላም ና ወደ እኛ መድኃኔዓለም
ቅዱስ ጌታ አማኑኤል ቸር አምላክ
መድኃኔዓለም
ለእኛ ብለህ አማኑኤል ተሰቀልክ
መድኃኔዓለም
ልትባርከን አማኑኤል ና በሰርክ
መድኃኔዓለም /2/
ሥጋህና አማኑኤል ደምህን መድኃኔዓለም
ብሉ ብለህ አማኑኤል ሰጠኸን መድኃኔዓለም
ሕይወት ሆኖ አማኑኤል አዳነን /2/
መድኃኔዓለም
በኃጢአት ሞት አማኑኤል ወድቀን ሳለን
መድኃኔዓለም
ከጥንት ሀገር አማኑኤል ኑሩ አልከን
መድኃኔዓለም
ሞገስ ልበል አማኑኤል ሞገስ ላውራ
መድኃኔዓለም
ግሩም ብቻ አማኑኤል የአንተ ሥራ /2/
መድኃኔዓለም

**1068.እግዚአብሔር ብርሃኔና**

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው /2/
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማን ነው /2/
አምላኬ መመኪያዬ ነው /2/

**1069.ኦ. ድንግል ደስ ይበልሽ**

ኦ.ድንግል ደስ ይበልሽ
ቅድስት ደስ ይበልሽ
ገብርኤል በቃሉ ደስታን ያሰማሽ
ኦ. ንጽሕት ደስ ይበልሽ
የዘለዓለም አምላክ እናት ስለሆንሽ
ኦ.ንጽሕት ደስ ይበልሽ
ከፍጡራን ሁሉ  በላይ ስለሆንሽ
ኦ.ንጽሕት ደስ ይበልሽ
የነገሥታት ንጉሥ ዙፋን ስለሆንሽ
ኦ.ንጽሕት ደስ ይበልሽ
የድኅነቴ ዓርማ ልዩ ምልክቴ
ለእኔም ነሽ እናቴ እመቤቴ
የድኅነቴ ዓርማ ልዩ ምልክት

ልዩ ነሽ እናቴ እመቤቴ
የምታማልጅን ከቸሩ አባታችን
ለእኛም እናታችን እመቤታችን/2/
የምታማልጅን ከቸሩ አምላካችን
ለእኛም እናታችን አስታራቂያችን
ስለ ውድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጵያ
ለልጆችሽ አሳሳቢ ብለሽ ሀሌ ሉያ
ድንግል ሆይ አሳሳቢ ብለሽ ሀሌ ሉያ
ስለ ውድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጵያ
ለልጂሽ አሳሳቢ ብለሽ ሀሌ ሉያ

**<u>1070.እናት አለኝ</u>**

እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ የምታፅናናኝ
እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ
የተቀኘላት እዝራ በመስንቆ
እናትነቶን ንጽሕናዋን አውቆ
ያመሰገናት ዳዊት በበገና
አትለየኝም እናቴ ናትና /2/
ሳለቅስ ስተክዝ ወድቄ ከፊቷ
አቅፋ አፅናናችን እኔን ከደረቷ
አላት ኪዳን ሁሌ ለሀጥዐን
ትማፀናለች በዕንባ ዝክር ልጆን/2/
የአዳም ተስፋ ናት ድንግል እናታችን
መርጦ ያደረባት ክርስቶስ ጌታችን
ታማልዳለች ዛሬም ለዘለዓለም
የአምላክ እናት የፍጥረታት ሰላም/2/

**<u>1071.ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም</u>**

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም
ድንግል ማርያም/2/
ንጽሕተ ንጹሐን ማርያም
ድንግል ማርያም /2/
ታማልዳለች ከልጆ ከመድኃኒዓለም /2/
ታማልዳለች ከልጆ /2/ ከመድኃኔዓለም
ታማልዳለች /4/ ልጁ ሆይ
ይቅር በል እያለች
አባቶቻችን ነቢያት ወሐዋርያት/2/
ጻድቃን ወሰማዕታት
ያማልዳሉ በእውነት ያማልዳሉ /2/
ያማልዳሉ በእውነት /2/ ያማልዳሉ
ያማልዳሉ /4/ አምላክ ይቅር በል እያሉ
ሰባቱ ሊቃናት መላእክት ሚካኤል ወገብርኤል
ሩፋኤልና ፋኑኤል
ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ
ሰባቱ ሊቃናት መላእክት አፍኒን ራጉኤልና ሳቁኤል
ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ
ያማልዳሉ ከክፉም ይጠብቃሉ /2/
ያማልዳሉ ከክፉም /2/ ይጠብቃሉ
ያማልዳሉ /4/ ከክፉም ይጠብቃሉ
በዱር በገደል በበረሃ በዋሻም ያሉ /2/
ያማልዳሉ በእውነት ያማልዳሉ /2/
ያማልዳሉ በእውነት /2/ ያማልዳሉ
ያማልዳሉ /4/ አምላክ ይቅር በል እያሉ

**1072. <u>ዓለምን ለማዳን</u>**

ዓለምን ለማዳን የተሰቀለው
ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው /2/
ጌታችን ተሰቅሎ ቢያዩት መላእክት
በዝማሬ ፈንታ አለቀሱለት
ሚካኤል ዝም አለ ገብርኤል ገረመው
<u>አምላኩ እርቃኑን ተሰቅሎ ስላየው</u> /2/
ነፍሱን ለወዳጁ የሚሰጥ ቢገኝም
ለጠላቱ የሚሞት በጭራሽ አይኖርም
ጠላቶቹ ስንሆን ለእኛ የሞተው
<u>ክርስቶስ ልዩ ነው ወደርም የሌለው</u> /2/
ዕውርን ቢያበራ የሞተን ቢያስነሳ
በመመስገን ፈንታ ሆነበት አበሳ
ሰማያዊው ዳኛ ሊፈረድበት
<u>ተከሶ ቀረበ በጲላጦስ ፊት</u> /2/
በጸሎተ ሐሙስ እለት እራት የሆነው
ዓርብ በመስቀል ላይ የተሰቀለው
ፍቅር አስገድዶት ለእኛ የሞተው
<u>መልካሙ እረኛችን መድኃኔዓለም ነው</u>/2/

**1073. <u>እንዲህ አለው ጴጥሮስ</u>**

እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስን
ምሥጢር ገሃድ ሲሆን በዚ የ በተራራ

በአንድ ላይ እንኑር ሦስት ዳስ እንሥራ
አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ
ተለወጠ ገጹ ከመ ፀጌሬዳ
ወርዶ ከለላቸው ደመና ጸዓዳ
ከሰማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ሲል
ኤልያስም ሄደ በሰረገላው
ሙሴም ከመቃብር ወደ መኖሪያው
ስለአስደነቃቸው ግሩም ታመራቱ
ይህን ምሥጢር አይተው ተሰነባበቱ

**1074.መልእክተ ወንጌል**

መልእክተ ወንጌል በደሙ የጻፈ
ስቃዩን ታግሶ ችሎ ያሣለፈ
በርሃብ በግርፋት በግዞት አብዝቶ
በገድል በትሩፋት ጠላትን ድል ነሥቶ
ንዋየ ኅሩይ ነው ለዓለም ያበራ
ሐዋርያው ጳውሎስ ለጽድቅ የተጠራ /2/
እንቅልፋን እያጣ ሌት ተቀን ሳይታክት
የኂላውን ትቶ ተጓዘ ወደፊት
በድካም ተጠምዶ በገድል እያረሠ
ከደማስቆ እስከ ሮም ቃሉን አዳረሠ
እውነትን መናገር ከቶ ያላፈረ
ሕዝብን ከአሕዛብ በአንድ ያስተባበረ
አምላኩ እንዳይናቅ ከልቡ የተጋ
ጸንቶ የተጓዘ ለምትበልጠው ጸጋ
በሮም አደባባይ ሰማዕት የሆነ
የተዋሕዶ አርበኛ ለአምላክ የታመነ
በጣዕመ ስብከቱ ዓለሙን አጣፋጦ
አክሊል ተቀዳጀ ሳይታክት ዕሮጦ

**.1075. ንሴብሖ**

ንሴብሖ /2/ ለአምላክ ዕዝራ /2/
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ስለፍቅርህ ልጀምር ማኅሌት
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
ስመለከት ወደሰማይ በጨረቃ ብርሃን
ግርማ ለብሴ አስገረመኝ የአምላኬ ዙፋን
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይደለን በመንፈስ እንዘምር
እልል እንበል በምስጋና ጸጋውን እንጨምር
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
አዕዋፍ በማለዳ መዝሙር ሲዘምሩ
በቋንቋቸው የአንተን ክብር በምሥጢር ሲያወሩ
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ
ክበሮ ሆይ ጸናጽል ሆይ ለምስጋና ተነሥ
በማለዳ ለጌታን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሖ ለአምላክ ዕዝራ

**1076.. .ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን**

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን /2/
ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን
ከሞት ወደ ሕይወት ያሸጋገረን
ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንል ደስ ይበለን/2/
የሰማዩን መንግሥት ርስቱን ለሰጠን
ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሰየን
ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል
በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል
ከዓለት የፈለቀ ውኃ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ
ስምህን ላመስገነው ከጠዋት እስከ ማታ
በቃዴስ በረሀ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባሕር ወጀብ በበዛበት
ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት
በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ
የኢያቄም ስለት የሐና እምነት
ለምኝልን ለእኛ ኪዳነምሕረት77..ወዳሴ
ማርያም

ወዳሴ ማርያም እጮኸለሁ
ደንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወድሰኒ ልጄ በይኝ
በሠርክ ጸሎት ላይ ውዳሴ ማርያም
ዜማ ስናደርስ ውዳሴ ማርያም
ድንግል ትመጣለች ውዳሴ ማርያም
በቤተ መቅደስ ውዳሴ ማርያም
የብርሃን ምንጣፍ ውዳሴ ማርያም
ከፊቷ ተነጥፏል ውዳሴ ማርያም
ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ ውዳሴ ማርያም
ያመሰግናታል ውዳሴ ማርያም
አባ ሕርያቆስም ውዳሴ ማርያም
ምስጋና ያደርሳል ውዳሴ ማርያም
የቅዳሴው ዜማ ውዳሴ ማርያም
ልብን ይመሰጣል ውሳሴ ማርያም
በጎ ነገር ልቤ ውዳሴ ማርያም
አወጣ እያለ ውዳሴ ማርያም
ዳዊት በገናውን ውዳሴ ማርያም
እየደረደረ ውዳሴ ማርያም
የንጽሕናችንን ውዳሴ ማርያም
መሠረት ነሽና ውዳሴ ማርያም
አንቺን ለማመስገን ውዳሴ ማርያም
ልቡናዬ ይብራ ውዳሴ ማርያም
ተፈሥሒ ደንገል ውዳሴ ማርያም
ኦ ቤተልሔም ውዳሴ ማርያም
ከአንቺ ተወለደ ውዳሴ ማርያም
መድኃኔዓለም ውዳሴ ማርያም
ቅዱሳኑ ሁሉ ውዳሴ ማርያም
ዙሪያሽን ከበዋል ውዳሴ ማርያም
አባ ጊዮርጊስም ውዳሴ ማርያም
ንዒ ድንግል ይላል ውዳሴ ማርያም
በወርቅ ዙፋን ለይ ውዳሴ ማርያም
ተቀምጠሽ ሳይሽ ውዳሴ ማርያም
ልቤ ተሰወረ ውዳሴ ማርያም
ድንግል ተሰወረ ውዳሴ ማርያም
ደንግል በግርማሽ ውዳሴ ማርያም

1078.. ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት /2/ ለነቢያት /2/
ሞገሰሙ ለሐዋርያት /4/
ትርጉም፡- ድንግል ሆይ የሐዋርያት ሞገስ የነቢያት
ትንቢት አንቺ ነሽ

1079..ማርያም

ማርያም /2/ ድንግል ማርያም /2/
ርኅርኅተ ኅሊና /4/ ማርያም/4/
**ትርጉም**፡- ለሰዎች አዛኝ ልብ ያላት እመቤቴ

1080.በመኑ በአምሳለ መኑ

በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስልኪ/2
እመቤቴ የእኛ አማላጅ አዛኝቷ ኦ ድንግል
ምልዕተ ውዳሴ /2

1081.ማርያም ተዐቢ

ማርያም ተዐቢ እምኩሉ ፍጥረት /2/
ኢያውዓያ እሳተ መለኮት /4/
**ትርጉም**፡- ማርያም ትበልጣለች ከሁሉ ፍጥረት /2/
ስለያዘች እሳተ መለኮትን/4/
(ስላላቃጠላት)

1082.ተወልዳለችና

ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መደኃኒት
እናወድሳት እናመስግትናት እንውደዳት/2/
የአዳምን ሕይወት /4/ ኸኸ
አዳም ሲሠደድ ከጥንት ርስቱ

ፊቱን ሸፈነው ጭንቀት ፍርሃቱ
እያለቀሰ ገነትን ሲያጣ
ተስፋ አንቺ ሆነሽው የመዳን እጣ /2/
ሊባኖስ ተራራ ተሠማ ዜና
ምሥራቅ ወለዱ ኢያቄም ወሐና
ዳግማዊት ሔዋን ምክንያተ ድኅነት
ልደትዋን ሰማን በቅድስት እለት
የልደትሽ ቀን ልደታችን ነው
በአንቺ ነውና ልጅ የተባልነው
ፋራን የተባልሽ ቅድስት ተራራ
በአንቺ መወለድ ዓለሙ በራ

1083. የዕለት የዓመት

የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ
ከዚህ ካደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ
አቀርብልሃለሁ የክብር ሰላምታ የአክብሮት
ሰላምታ
ኑ እናመስግን ከልባችን
የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ላደረሰን
ሁላችንን /2/
የሰው ልጆች እድሜ ጥንቱንም ሲጀመር
ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር
አንድ ቀን አይሞላም እንደአንተ አቆጣጠር /2/
አዝ . . .
ስለዚህ አምላክ ሆይ ክቡር ነው ቅዱስ ነው
ወደአንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው
ደካማ ነውና ሰው እድሜ ከራበው /2/
አዝ . . .

1084. አበባዮሽ

እሰይ ደስ ደስ ይበላችሁ/2/
ቅዱስ ዮሐንስ መጣላችሁ
ደስ ደስ ይበላችሁ
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን/2/
ጌታ አለ ብለን ደስ ብሎን
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን/2/

ድንግል አለች ብለን ደስ ብሎን
አበባዮሽ ቅድስት/2/
ባለእንጀሮቼ ቅድስት
ቁሙ በተራ ›ቅድስት ›
በጎ ምግባርን ››ቅድስት
በእምነት እንሥራ ቅድስት ››
ዛሬ ነው ቀኑ ቅድስት ›
መመለሻችን ቅድስት ››
ይቅር እንዲለን ቅድስት ››
ቸሩ አምላካችን ቅድስት ››
አደይ የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ በራ/2/
ድንግል ማርያምን ቅድስት
እንለምናት ቅድስት
ምሕረት የሚያሠጥ ቅድስት
ቃልኪዳን አላት ቅድስት
ጭንቀት ይርቃል ቅድስት
ይቀርባል ሰላም ቅድስት ›
ስሟ ሲጠራ ቅድስት
የድንግል ማርያም ቅድስት
አደይ የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ በራ/2/
በሕገ ልቡና ጥንቱን
ፈጣሪን አውቀሽ ጥንቱን
ሕገ ነቢያት ከአለም
ቀድመሽ ተቀበልሽ ከአለም
በብሉይ ኪዳን ለጌታ
መሥዋዕት አቀረብሽ ለጌታ
ተስፋ ካደረጉት ከአይሁድ
ከእስራኤል ቀድመሽ ከአይሁድ
ሕገ ወንጌልን በፊት
ይዘሽ ተገኘሽ በፊት
ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ ትልቅ ጸጋ አለሽ/2/
ስለፈጸምሽ ሦስቱን ሕግጋት የፈጣሪሽን
ካለፈው ስህተት ሁላችን

እንድንመለስ ሁላችን
አዲሱ ዓመት ለሁሉ
መጣ ማቴዎስ ለሁሉ
ይህም ያልፍና በጊዜ
ይመጣል ማርቆስ በጊዜው
ሌላው ይተካል በጊዜው
ዘመነ ሉቃስ በጊዜው
ወልደ ነጎድጓድ በጊዜው
ሲደርስ ዮሐንስ በጊዜው
በየዓመቱ መጥምቁ
ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ
አደይ የብርሃን የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ
አበራ2/
ኢትዮጵያ ባህል ቋንቋሽ የሚያኮራሽ/2/
ዘመኑ አልፎ ቅድስት
ሲሄድ ማቴዎስ ቅድስት
አዲሱ ዘመን ቅድስት
ሲመጣ ማርቆስ ቅድስት
እድሜን ጨምሮ ቅድስት
ለሠጠን ጤና ቅድስት
ለመድኃኔዓለም ቅድሰት
ይድረስ ምስጋና ቅድስት
አደይ የብርሃን ጮራ በማርቆስ በራ
እቴ አበባ እቴ አበባዬ አዬ ቅድስት እናቴ
እቴ አበባ ስትለኝ ከርማ አዬ ቅድስት እናቴ
መከረችኝ ደግማ ደጋግማ አዬ ቅድስት
እናቴ
ቃሉን ሰማው አድምጥው ብላ እዬ ቅድስት
እናቴ
አዬ ቅድስት እናቴ አዬ ቅድስት እናቴ/2/
ይሸታል የእጣኑ ጢስ ሲታጠን ከመቅደሱ
በመላእክት ዜማ ካህናት ሲቀድሱ ሲታጠን
ከመቅደሱ/2/

ከብረው ይቆዩን ከብርው
ከዓመት ዐውደ ዓመት ደርሰው
በእምነት በምግባር ጸንተው
ነጽተው ንስሓ ገብተው
ለሥጋ ወደሙ በቅተው
ከብረው ይቆዩ ከብረው
ከብረው ይቆዩ ከብረው
ከዓመት እስከ ዓመት ደርሰው
ቅን ታዛዥ ልጅን ወልደው
ትጉት ሰው አክባሪ ሆነው
የፍቅርን ሸማ ለብሰው
ከብረው ይቆዩ ከብረው
አበባው ለምለም ቁጤማው ለምለም
ኢትዮጵያ እንደአንቺ የለም
አበባው ለምለም ቁጤማው ለምለም
ተዋሕዶ እንደአንቺ የለም
አበባው ለምለም ድንግል ማርያም
ያለ አንቺ እመቤት የለም

### 1085. የአዋጅ ነጋሪ ቃል

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሀ አየለ
የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካክሉ እያለ
ምስክርነቱን ዮሐንስ ካስረዳን
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን
የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
ዐውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም
ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንጥረግ ሁላችን
ማለፊያ እንዲሆነን ወደ አምላካችን
አዝ . . .
ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርኅራኄ በእኛ ላይ ይስፋፋ
ሥጋና ደምህን በክብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆን አምላክ ተማጽነናል
አዝ . . .

ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም አንጻን አደራህ
በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህ
አዝ . . .

1086..ቡሄበሉ

ቡሄ በሉ ቡሄ በሉ ልጆች ሁሉ
የእኛማ ጌታ የዓለም ፈጣሪ የሰላም አምላክ
ትጉት መሐሪ በደብረ ታቦር የተገለጸው
ፊቱ እንደፀሐይ በርቶ የታየው የድንግል
ማርያም አንዱ ልጇ ነው
ድምጽህን ሰማና በብሩህ ደመና/2/
የቡሄው ብርሃን ለእኛ አበራልን
ያዕቆብ ዮሐንስ እንዲሁም ጴጥሮስ
አምላክን አዩት ሙሴ ኤልያስ
አባትም አለ ልጄን ስሙት
ቃሌ ነውና የወለድኩት
አዝ --------
ኪዳነምሕረት /2/
ባርኮ የሠጠሽ ኢትዮጵያን አስራት
ጭንቀት ይርቃል ይቀርባል ሰላም
ስሟ ሲጠራ የድንግል ማርያም
አዝ -----
በተዋሕዶ ወልድ የከበረው
የእግዚአብሔር አብ ልጅ ወልደ ማርያም ነው
ቡሄ በሉ ቡሄ በሉ
የአዳም ልጆች ብርሃን ተቀበሉ
አዝ -----
ኢትዮጵያዊያን ታሪክ ያላችሁ
ባሕላችሁን ያዙ አጥብቃችሁ
ብርሃንን አብሩ ችቦ ይዛችሁ
ምሥጢር ስላለው ደስ ይበላችሁ
አዝ ----

አባቶቻችን ያወረሱን
የቡሄን ትርጉም የሣወቁን
እንድንጠብቀው ለእኛ የሠጡን
ይሄ ነውና ያስረከቡን
አዝ ------
የድንግል ማርያም አስራት የሆንሽ
ቅዱሳን ጻድቃን የሞሉብሽ
በረከታቸው ያደረብሽ ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ነሽ
አዝ ------
ታቦር አርሞንኤም ብርሃን ታየባቸው
ለቅዱስ ተራራ ስምህ ደስ አላቸው
ሰላም ሰላም የታቦር ተራራ
ብርሃነ መለኮት በአንቺ ላይ አበራ
አዝ -----
ለሐዋርያት የላከው መንፈስ
ዛሬም በእኛ ላይ ጸጋውን ያፍስስ
በጥሩ ምግባር እንድንታደስ
በቅን ልቡና በጥሩ መንፈስ
አዝ -----
የሰማይ መላእክት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
የሚያመሰግኑት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
የአዳም ልጆች ሁሉ ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
ሁሉ የሚማጸኗት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
የዓለም አማላጅ ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
ድንግል ማርያም ናት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
እንዲሁ እንዳላችሁ በፍቅር አይለያችሁ በፍቅር
ለዓመቱ በሰላም በፍቅር ያድርሳችሁ በፍቅር
ክርስቶስ በቀኙ በፍቅር ያቁማችሁ በፍቅር
የመንግሥቱ ወራሽ በፍቅር ያድርጋችሁ በፍቅር እንዲሁ
እንዳለን እኛን አይለየን እኛን
ለዓመቱ በሰላም እኛን ያድርሰን እኛን
አማኑኤል በቀኙ እኛን ያቁመን እኛን
የመንግሥቱ ወራሽ እኛን ያድርሰን እኛን

የቅዱሳን መላእክት የጻድቃን ሰማዕታት
ረድኤት በረከት ይደር በሁላችን
በሁላችን በሁላችን ይደር በሁላችን /2/

1087. **ምስክረነቱን ገለጸ**
ምስክርነቱን ገለጸ ቂርቆስ ሕፃን/2/
በእሳት ተፈተኖ አለፈኸኸ ፈተና ደስ
ይበለን/2/
ቂርቆስ ኢየሉጣን ሁለቱም በአንድ ልብ ምን
ጨከኑ/2/
ተቃቅፈው ሲገቡ ወደ እሳት ጋኑ/2/
ሕፃኑ እና እናቱ በእሳት ውስጥ ሲዋኙ
ያለ ምንም ፍርሀት/2/
ገብርኤል ተላከ እነርሱን ለማውጣት /2/
በርዶና ቀዝቅዞ የእሳቱ ነበልባል በጌታችን
መስቀል /2/
ሁለቱም ሰማዕታት ተጎናጸፉ ድል/2/

1088. **መጥመቀ መለኮት**
መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ /2/
መንገድ ጠረገ ለኢየሱስ መምጫው
ሊደርስ
ተክለሃይማኖት በጸሎት/2/
ተክለሃይማኖት በጸሎት የእኛ አባት
ገብረመንፈስቅዱስ ሐዋርያ /2/
ኪንሒሳ መጥተው ጸለዩላት ለኢትዮጵያ
ዜና ማርቆስ በጽኑ እምነት/2/
ፀሐይ አቆሙ እንደ ኢያሱ በደብረ
ብሥራት/2/
እመቤታችን ድንግል ማርያም /2/
ምሕረት አስጭን ከመለኮት
ከመድኃኔዓለም
መስቀሉን ይዞ በፈረስ/2/
ከዘንዶ አስጣላት ቤሩታዊትን ቅዱስ ጊዮርጊስ

1089. **ጊዮርጊስ ብርሃኑን**
ጊዮርጊስ ብርሃኑን አበራ/2/
ዱድያኖስ አፈረ ከጣዖቱ ጋራ
ጊዮርጊስ ብርሃኑን አበራ /2/
ለዲያብሎስ ያልሠገደ ጀግናው ጊዮርጊስ
ደግሞ ባይን ታየ ክብሩ ሲወደስ
ከሞት አፍ ያወጣት ቤሩታይትን
በሰማእቱ ገድል ድል ሆነ ሠይጣን
ቅዱሱ ሰማዕት ጊዮርጊስ አባታችን
አሳየ ሥልጣኑን ከሞት እንደሚያድን
መድኃኒት ክርስቶስ የገለጠው ብርሃን
እኛም እንድንድን ከዘመኑ አውሬ
እስቲ እንግለጽለት ክብሩን በዝማሬ
ተዋሕዶ አበራ ደግሞ እንደገና
ደራጎን ድልሆኖ ሞቶ ቀርቷልና
ለአሸናፊ ጌታ ለእግዚአብሔር ልዑል
ምስጋና እናቅርብ እንበል እልል
ጊዮርጊስ አበራ ብሃን/2/
ሠው በላውም አውሬ ሞተ ደራጎን/2/
ጊዮርጊስ አበራ ብርሃን

**1090.ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት**
ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት /2/
<u>አትመረመርም</u> /2/ እጅግ ጥልቅ ናት/2/
በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ /2/
የእምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመጣ /2/
<u>ሰው ሁሉ በክህደት</u>/2/ ፈጣሪውን አጣ/2/
እንመስክራለለን ፈጣሪያችን አለ
እንመስክራለን አማኑኤል አለ/2/
<u>አንድአንዱ ቢክደው</u> /2/ እየተታለለ /2/
እንመስክራለን ድንግል አማላጅ ናት /2/
እንመስክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የአማኑኤል እናት/2/

<u>1091. ስአሊ ለነ ማርያም</u>
<u>ስአሊ ለነ ማርያም ስአሊ ለነ /2/</u>

**የደብረ ታቦር**

**1091.ደብረ መቅደሱ**

ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር

ማርያም ሰላም/2/

ሰላም ለላዕየኪ አዳም/4/

ናዝሬት ሠላም ዘአሕጉር

እም ደብረታቦር ሰላም/2/

ሰላም ለላዕየከ አዳም/4/

**1092. አሐደ ሌከ**

አሐደ ለከ ወአሐደ ለሙሴ/2/

ወአሐደ ለኤልያስ ንግበር ማኅደረ/4/

አንዱንም ለአንተ አንዱንም ለሙሴ/2/

አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ ቤትን/4/

**1093.አማን በአማን**

አማን በአማን /4/

ተሰብሐ በደብረታቦር/4/

**1094.በስመ ዚአከ**

በስመ ዘአከ ይትፌሥሑ ዮም/2/

ታቦር ወአርሞንኤም /4/

ታቦር ወአርሞንኤም /23/

ታቦር ወአርሞንኤም/4/

**1095.በደብረ**

በደብረ በደብረ ታቦር /2/

ሰባሕኩከ በደብር /4/

**1096. ቡሄ በሉ**

ቡሄ በሉ ቡሄ በሉ ልጆች ሁሉ

የእኛማ ጌታ የአለም ፈጣሪ የሰላም አምላክ

ትኑት መሐሪ በደብረ ታቦር የተገለጸው

ፊቱ እንደፀሐይ በርቶ የታየው የድንግል

ማርያም አንዱ ልጇነው

ድምጽህን ሰማና በብሩህ ደመና/2/

የቡሄው ብርሃን ለእኛ አበራልን

ያዕቆብ ዮሐንስ እንዲሁም ጴጥሮስ

አምላክን አዩት ሙሴ ኤልያስ

አባትም አለ ልጄን ስሙት

ቃሌ ነውና የወለድኩት

አዝ --------

ኪዳነምሕረት /2/

ባርኮ የሠጠሽ ኢትዮጵያን አስራት

ጭንቀት ይርቃል ይቀርበላ ሠላም

ስሟ ሲጠራ የድንግል ማርያም

አዝ -----

በተዋሕዶ ወልድ የከበረው

የእግዚአብሔር አብ ልጅ ወልደ ማርያም ነው

ቡሄ በሉ ቡሄ በሉ የአዳም

ልጆች ብርሃን ተቀበሉ

አዝ -----

ኢትዮጵያዊያን ታሪክ ያላችሁ

ባሕላችሁን ያዙ አጥብቃችሁ

ብርሃንን አብሩ ችቦ ይዛችሁ

ምሥጢር ስላለው ደስ ይበላችሁ

አዝ ----

አባቶቻችን ያወረሱን

የቡሄን ትርጉም የሣወቁን

እንድንጠብቀው ለኛ የሠጡን

ይሄ ነውና ያስረከቡን

አዝ ------

የድንግል ማርያም አስራት የሆንሽ

ቅዱሳን ጻድቃን የሞሉብሽ

በሀብታቸው ያደረብሽ ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ነሽ

አዝ ------

ታቦር አርሞንኤም ብርሃን ታየባቸው

ለቅዱስ ተራራ ስምህ ደስ አላቸው

ሰላም ሰላም የታቦር ተራራ

ብርሃነ መለኮት በአንቺ ላይ አበራ

አዝ -----

ለሀዋርያት የላከው መንፈስ
ዛሬም በእኛ ላይ ጸጋውን ያፍስስ
በጥሩ ምግባር እንድንታደስ
በቅን ልቡና በጥሩ መንፈስ
አዝ -----
የሰማይ መላእክት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
የሚያመሰግኑት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
የአዳም ልጆች ሁሉ ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
ሁሉ የሚማጸኗት ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
የዓለም አማላጅ ደጋግመው በደስታ ደጋግመው
ድንግል ማርያም ናት ደጋግመው በደስታ
ደጋግመው
እንዲሁ እንዳለችሁ በፍቅር አይለያችሁ በፍቅር
ለዓመቱ በሰላም በፍቅር ያድርሳችሁ በፍቅር
ክርስቶስ በቀኙ በፍቅር ያቁማችሁ በፍቅር
የመንግሥቱ ወራሽ በፍቅር ያድርጋችሁ በፍቅር
እንዲሁ እንዳለን እኛን አይለየን እኛን
ለዓመቱ በሰላም እኛን ያድርሰን እኛን
አማኑኤል በቀኙ እኛን ያቁመን እኛን
የመንግሥቱ ወራሽ እኛን ያድርገን እኛን
የቅዱሳን መላዕክት የፃድቃን ሠማዕታት
ረድኤት በረከት ይደር በሁላችን
በሁላችን በሁላችን ይደር በሁላችን /2/

1097. ወሪዶሙ

ወሪዶሙ እምደብር እም ደብረታቦር አዘዞሙ
ኢይንግር/2
እስከ አመ ይትፌጸም በእድሜሁ ዘርእዩ
በደብር/2/

1098 እንዲህ አለው ጴጥሮስ

እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስን
ምሥጢር ገሀድ ሲሆን በዚያ በተራራ
በአንድ ላይ እንኑር ሦስት ዳስ እንሥራ
አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ
አንዱን ለጴጥሮስ
ተለወጠ ገጹ ከመ ጽጌረዳ
ወርዶ ከለላቸው ደመና ጸዓዳ
ከሰማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ሲል

ኤልያስም ሔደ በሠረገላው
ሙሴም በመቃብር ወደ መኖሪያው
ስላስደነቃቸው ግሩም ተአምራቱ
ይህን ምሥጢር አይተው ተሰነባበቱ

1099.የታቦር ተራራ

የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይበልሽ /2/
እግዚአብሔር መለኮቱን ስለገለጸብሽ /2

## በተክለ ሳዊሮስ ሰ/ት/ቤት የሚጠኑ የዓመቱ ያሬዳዊ ዜማዎች /ወረቦች/

### ዐውደ ዓመት

**እስመ ለዓለም**

በመንፈስ የሐውር ወበኃይለ ኤልያስ አልቦ
ዘየዐብዮ ለዮሐንስ

**ዝማሜ**

ሃሌ ሉያ ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል
ትሰመይ አርኮ ለመርዓዊ ትሰመይ
ወአዝማዱ በሥጋ ትሰመይ ተፈኖከ ታርዉ
አናቅጸ ጽድቅ

**ጽፋት**

ተፈኖከ ታርዉ አናቅጸ ጽድቅ/3/
ወአዝማዱ በሥጋ ትሰመይ ተፈኖከ ታርዉ
አናቅጸ ጽድቅ
ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ አርኮ
ለመርዓዊ ትሰመይ
ወአዝማዱ በሥጋ ትሰመይ ተፈኖከ ታርዉ
አናቅጸ ጽድቅ
በመንፈስ የሐውር ወበኃይለ ኤልያስ አልቦ
ዘየዐብዮ ለዮሐንስ

**ሰላም**

ተሰአልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ

ዮሐንስ ክቡር ነቢየ ልዑል ብእሴ ሰላም
ዘንብረቱ ገዳም/2/

**ወረብ**

ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል/2/
አርኮ ለመርዓዊ ትሰመይ/2/
ነቢየልዑል/2/

**ርዕሰ ዐውደ ዓመት**

ርዕሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ ወላዴ መጥቅዕ /2/
ወላዴ መጥቅዕ/ 2/ ወአበቅቴ/4/

**ዐውደ ዓመት**

ዐውደ ዓመት ለባርኮ ባርኮ ዐውደ ዓመት/2/
ንዒ ማርያም በምሕረት ወሳህል/2/

## የመስቀል ወረብ

**በመስቀሉ**

በመስቀሉ ወበቃሉ/2/
አእበዮሙ ለአበዊነ/4/

**ዝንቱ**

ዝንቱ መስቀል ቤዛነ መድኃኒትነ/2/
ዝንቱ መስቀል ቤዛነ መድኃኒትነ/4/

**እምገቦ**

እምገቦከ ውኂዘ ነቅዐ ማየ ዘቀደሶ ለፈያታ/2/
ለነዳይ ምስካይ መስቀልከ እግዚኦ ለነዳይ ምስከይ/2

**ኃይለ መስቀሉ**

ኃይለ መስቀሉ አብርሃ/2/ ለኢትዮጵያ/2/
እስመ መስቀል ሞዓ ሞተ ተሞዓ/2/

**ተሰአልከ/ጽፋት/**

ተሰአልከ እግዚኦ ሃሌ ሉያ መስቀል ብርሃን
ለኩሉ ዓለም መሠረተ ቤተክርስቲያን
ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም መስቀል ለእለ
ነአምን መድኅን

**የስደት ወረብ**

ረሀበ ወጽምዐ አዘክሪ ድንግል ረሀበ ወጽምዓ /2/
ምንዳቤ ሐዘን አዘክሪ ድንግል/2/

**ብክዩ**

ብክዩ ኅዙናን ኀልየክሙ ስደታ ለማርያም/2/
ማርያም ተዐይን ባህቲታ ውስተ አድባረ ግብጽ ከመ ያፍ/2/

**እንዘ ተሐቅፊዮ**

እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ/2/ ጽጌ ጸዓዳ ወቀይሕ/2/
ንዒ ርግብየ ምስለ ገብርኤል ወንዒ ሡናይትየ ምስለ ሚከኤል/2/

**ትመስል**

ትመስል እምኪ ማርያም ዕለት ሣልስተ ወርኃ ብዕተ ትመስል እም/2/
ዘወለደት ጽጌ/3/ ወፀሄየ ዓለም/2/

**የጥቅምት 27 መድኃኔዓለም**

**አባ አባ**

አባአባ ባርከኒ መብአ ጽዮን በትረ ማርያም/2/
ከመ ባርኮ አብርሃም ለይስሐቅ ወልዱ/4/

**ወበ ጽጌያተ**

ወበጽጌያተ ምድር አሠርጎከ /2/
ወበመስቀልከ ለጻድቃን አብራህከ /4/

**መድኃኔዓለም**

መድኃኔዓለም እግዚአብሔር ኀደረ ላዕሌሃ/2/
ኪያሃ ዘሠምረ ማኅደረ ስብሐት
ኪያሃ ዘሠምረ ደብረ መድኃኒት/2/

**ኅዳር 12 ቅዱስ ሚካኤል**

አንተኑ ሚካኤል መና መና ዘአውረድከ/2/
ወአንተኑ ለእስራኤል መና ዘአውረድከ/2/

**ሰፊሆ**

ሰፊሆ ክነፊሆ /2/
ክነፊሆ ይጼልል ዲቤነ /4/

**ነዋ ሚካኤል**

ነዋ ሚካኤል መልአከክሙ/2/
ይስአል ለክሙ በእንተ ምሕረት/4/

**ውእቱ ሚካኤል**

ውእቱ ሚካኤል መልአከ ኃይል ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር/2/
ይስአል ለነ ረዳኤ ይኩነነ ይስአል ለነ አመ ምንዳቤ /2/

## ኅዳር 21 ጽዮን ማርያም

**ጽፋት**

አይ ይእቲ ዛቲ እንተ ታስተርኢ እምርሁቅ ከመ ማኅቶት ብርሀት ከመፀሐይ ሙሴኒ ርእያ ሀገር ቅድስት እዝራኒ ተናገራ ዳዊት ዘመራ

**ሙሴኒ ርእያ**

ሙሴኒ ርእያ/2/ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያ/2/
እዝራኒ ተናገራ ተናገራ ዘመራ ዳዊት/2/

**እዝራኒ**

እዝራኒ ተናገራ/2/
ተናገራ ዳዊት ዘመራ ተናገራ ዘመራ ዳዊት/2/

**አብርሂ**

አብርሂ /2/ ጽዮን አብርሂ/2/
ዕንቁ ዘጳዝዮን ዘነረየኪ ሰሎሞን ንጉሥ/2/

**እንተ ክርስቶስ**

እንተ ክርስቶስ መሠረት ፀሐየ ጽድቅ ያበርህ ለኪ ፀሐየ ጽደቅ/2/
በስብሐት ሥርጉት በስብሐት ሥርጉት ማኅደረ ስብሐት/2/

## የልደት እና የጥምቀት ወረብ

**አንገርጋሪ**

ውእቱ ኢየሱስ በቤተልሄም ዘይሁዳ አዋልደ ጢሮስ አሜሀ ይሰግዳ ሰብአ ሰገል አምጽኡ ሎቱ ጋዳ ወይትሐሠያ አዋልደ ይሁዳ

**ዝማሜ**

ሃሌ ሉያ ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርቶስ እምቅድስት ድንግል ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዘሎቱ ሰብአ ሰገል ሰገዱ ሎቱ አማን መንክር ስብሐተ ልደቱ

**ወረብ /ውእቱ ኢየሱስ/**

ውዕቱ ኢየሱስ/3/ እምቅድስት ድንግል/2/
በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ/2/

**ሰላም**

ተሰአልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ/2/ ዮም ተወልደ እግዚእ ወመድኅን በፍሥሀ ወበሰላም

**አማን በአማን**

አማን በአማን/4/
መንክር ስብሐተ ልደቱ /4//ጥምቀቱ/

**አንፈራዖ**

አንፈራዖ ሰብአ ሰገል/4/
አምኃሆሙ አምጽኡ መድምመ/2/

**ውስተ ማህፀነ**

ውስተ ማኅፀነ ድንግል ኅደረ ማኅፀነ ድንግል/2/
ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ ሰማይ ወምድር በማይ ተጠምቀ/2/

**ርእይዎ**

ርእይዎ ኖሎት/2/ አእኩትዎ መላእክት/2/
ዮም ሰማያዊ በጎል ሰከበ ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል/2/

**ሃሌሉያ**

ሃሌ ሉያ መጽአ ወልድ ውስተ ዓለም ሃሌ ሉያ ውስተ/2/
ወለብሰ ሥጋነ ሰብአ ኮነ በአርዓያ ዚአነ /2/

**ወወለደት**

ወወለደት ወልደ ዘበኩራ/2/
መንጦላእት ደመና ሰወራ/4/

**ሖረ ኢየሱስ**

ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ/2/
ከመ ያጥምቆ/2/ ፈለገ ዮርዳኖስ/2/

## ጥር 21 አስተርእዮ ማርያም

**ዘድንግል**

ዘድንግል መናሥግት ኢያሪሆ/2/
ኢያሪሆ ዘኪሩቤል ኢርእዮ
ኢያሪሆ ኢርእዮ ዘኪሩ/2/

**ጊዜ ዕረፍታ**

ጊዜ ዕረፍታ ለማርያም ጊዜ/3/ እረፍታ ለማርያም/2/

ወረደ ወልድ ዲበ እም ዲበ ልዕልና ወረደ/2/

**እስመ እምዘርዓ**

እስመ እምዘርዓ ዳዊት ዘመጽአ/2

በቤተልሔም ዘይሁዳ

በቤተልሔም እንዘ ይሁዳ/2

**<u>የዘመነ መርዓዊ እና የቃና ዘገሊላ ወረብ</u>**

**በቃና ዘገሊላ/2/**

በቃና ዘገሊላ

ዘገሊለ ከብከብ ኮነ/4/

**ተአምረ**

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ/2/

በቃና ዘገሊላ ዘገሊላ ከብከብ ኮነ/4/

**አሐዱ**

አሐዱ አከል ገብረ ሥላሴ ወመርዓቱ ወለተ ማርያም/2/

ዘአስተጻመረ/2/ እግዚአብሔር/2/

**ወእመአኮ**

ወእመአኮ ከመወሬዛ ኃየል/2/

ትዌድሶ መርዓት እንዘ ትብል/4/

**አንሶሰወ**

አንሶሰወ ከመሰብ እሙነ ኮነ/2/

ተቀበሉ መርዓዊ መድኃኒነ ወረደ/4/

**ዘድንግል መናስግተ**

ዘድንግል መናሥግተ ኢያሪሆ/2/

ኢያሪሆ ዘኪሩቤል ኢርእዮ

ኢያሪሆ ኢርእዮ ዘኪሩብ

**የመጋቢት27 መድኃኔዓለም**

መስቀል ብርሃነ ለኩሉ ዓለም/2/

ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም/2/

**በለኒ መሐርኩከ**

በለኒ መሐርኩከ/2/ በእንተ መርያም/2/

እስመ አልቦ ዘእንበሌከ ዘይሜሕር ቃለ መድኃኔዓለም/2/

**መርሕ በፍኖት**

መርሕ በፍኖት ሞገሰሙ ለጻድቃን ሞገስ/2/

ዝንቱ መስቀል ለአዳም ዘአግብኦ ውስተ ገነት/2/

**ተዘከረነ እግዚኦ**

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ/2/

በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን ዲበ እጸ  መስቀል ቅዱስ/2/

**<u>የሆሣዕና ወረብ</u>**

**በትፍሥሕት**

በትፍሥሕት ወበሐሴት/2/

ይሁቦሙ ኃይል ወሥልጣን/4/

**ደቂቅኒ**

ደቂቅኒ ይጸርሑ ወሕዝብኒ ኪያሁ ይሴብሕ/2/

ወይብሉ ሆሣዕና በአርያም ቡሩክ አንተ መድኃኔዓለም/2/

**<u>የትንሣኤ ወረቦች</u>**

አማን በአማን/2/

ተንሥአ እምነ ሙታን/4/

**ትንሣኤከ**

ትንሣኤከ ለእለ አመነ

ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ/4/

**ወምድርኒ**

ወምድርኒ ትገብር ፋሲከ/2/

ተሀጺባ በደመ ክርስቶስ/4/

**ፋሲከ**

ፋሲከ/6/

ተዝካረ ትንሣኤሁ ለመድኃኒነ/4/

**ተንሥአ**

ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታን/2/

ተንሥአ ወፈትሆሙ ለሙቁሐን/4/

**የዕርገት ወረብ**

**ጽፋት**

ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ዕርገቱ ለክርስቶስ

እምድኅረ ተንሥአ እሙታን በአርብዓ ዕለት በይባቤ

ወበቃለ ቀርን አማን መንክር ስብሐተ ዕርገቱ

**አማን በአማን**

አማን በአማን/2/
መንክር ስብሐተ ዕርገቱ/4/

**ዘየአምን ብየ**

ዘየአምን ብየ በትንሣኤየ ወበዕርገትየ/2//
ቦ ዘለዓለም ሕይወት/4/

**ዐርገ**

ዐርገ በስብሐት/2/ ውስተ ሰማያት/2/
ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት/2/

**አንትሙሰ**

አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም/2/
እስከ ትለብሱ ኃይል እም አርያም/4/

## የግንቦት ልደታ ወረብ

**ጽፋት**

ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደታ ለማርያም እምሐና
ወኢያቄም ከመትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃን አማን ተወልደት እመብርሃን

**አማን በአማን**

አማን በአማን/2/
እመብርሃን ተወልደት/4/

**ዮም ፍሥሐ**

ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደታ ለማርያም/2/
አማን አማን በአማን ተወልደት/2/ እመብርሃን/2/

**እስመ እበውእ**

እስመ እበውእ ውስተ መካን ማኅደረ ስብሐት ቤተ እግዚአብሔር/2/
በቃለ አሚን ወበትፍሥሕት ደምጹ እለይገብሩ በዓለ ልደት ለማርያም/2/

**እምሐና**

እምሐና ወኢያቄም/4/

አላ በሩካቤ ዘበሕግ/2/

**ኢያቄም ወለዳ**

ኢያቄም ወለዳ ኢያቄም/2/
ዳዊት ዘመዳ ኢያቄም ወለዳ/4/

**ሐመልማላዊት**

ሐመልማላዊት/6/
ሙሴ ዘርእያ/2/ በደብረ ሲና ደብረሲና ማኅደረ ስብሐት/2/

**ኮነ ዮም**

ኮነ ዮም/2/ በእንተ ልደታ ለማርያም/2/
ከመትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃነ
ነቢያተ ከመ ትቤዙ/2/

**ኦ ማርያም**

ማርያም መንክር ልደትኪ ወእጹብ ግብርኪ/2/
ጾርኪ/3/ ዓምደ እሳት መድኃኔዓለም/2/

## የሰኔ ቅዱስ ሚካኤል ወረብ

**ባሕራንኒ**

ባሕራንኒ ባሕራን ይቤ ዘነገደ ባሕር/2/
ርኢኩዎ/2/ ለሚካኤል ወሰዕንኩ ጠይቆ/2/

**መልአከ ሰላምነ**

መልአከ ሰላምነ/4/
ሊቀ መላእክት ሚካኤል ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ/2/

**አመ ይሰቅልዎ**

አመ ይሰቅልዎ አይሁድ ለእግዚእ/2/
ሚካኤል አርመመ ወገብርኤል ተደመ/2/

**ወረዶ**

ወረዶ እመስቀሉ/2/
እመስቀሉ አብርሃ ለኩሉ እመስቀሉ ለኩሉ አብርሃ/2/

## የደብረ ታቦር ወረብ

**ወረዶ**

ወረዶሙ እምደብር እምደብረ ታቦር አዘዞሙ ኢይንግር/2/
እስከ አመ ይትፌጸም በእድሜሁ ዘርእዩ በደብር/2/

**አማን በአማን**

አማን በአማን አማን በአማን/2/

ተሰብሐ በደብረ ታቦር ተሰብሐ በደብረ/2/

**ደብረ መቅደሱ**

ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ማርያም ሰላም/2/

ሰላም ለላዕየከ አዳም/4/

ናዝሬት ሰላም ዘአሕጉር እምደብረ ታቦር ሰላም/2/

ሰላም ለላዕየኪ አዳም/4/

## ነሐሴ 16 ወረብ

**ተበሃሉ**

ተበሃሉ በሰማየት/2/ እለ ኪያኪ አፍለሱ/2/

ማርያምሰ እንተ በምድር ታንሶሱ/2/

**ዕርገታ**

ዕርገታ ውስተ ሰማያት ወበአታ ውስተ ገነት/2/

በስብሐት ለማርያም ሐዋርያት ገነዝዋ በስብሐት/2/

## የሥላሴ ወረብ

**ስብሐት ለአብ**

ስብሐት ለአብ ለአኃዜ ኩሉ ዓለም/2/

ስብሐት ለወልደ ለገባሬ ኩሉ ፍጥረት

ስብሐት ለመንፈስቅዱስ ለዘያርኑ ክረምተ በበዓመት/2/

## የቅዱስ ገዮርጊስ ወረብ

**አማን በአማን**

አማን በአማን አማን በአማን/2/

ጊዮርጊስ ትሩፈ ገድል/4/

**ውስተ አዘቅት**

ውስተ አዘቅተ ወገሩ ለጊዮርጊስ አዘቅተ አከሙ ወገሩ/2/

ቅዱስ ጊዮርጊስ/2/ ሞኦሙ ለፀሩ/2/

## የገብረ መንፈስ ቅዱስ ወረብ

**ግሩማን መላእክት**

ግሩማን መላእክት/2/ ሱራፌል ወኪሩቤል እለ አክናፊሆሙ ነበልባል/2/

ወረዱ ዮም ተቀበሉ ከመብሂል አማን ገባሬ ኃይል/2/

## የዘወትር ወረብ

**ንሴብሖ**

ንሴብሖ/2/ ለእግዚአብሔር/2/

ስቡሐ ዘተሰብሐ/4/

**አንሰ**

አንሰ ወቤትየ እግዚአብሔርሃ ናመልክ/2/

እስመ ቅዱስ ውእቱ እግዚአብሔር/4/

**እግዚአብሔር አስተጋብኦሙ**

እግዚአብሔር አስተጋብኦሙ እምበሐውርት እምጽባሕ ወእምዓረብ ወመስዕ ወባሕር በማኅደረ ስብሐት/2/

በዕፀ መስቀሉ አተቦሙ በጸሎታ ለማርያም/2/

**ሃበነ እግዚኦ**

ሀበነ እግዚኦ አእምሮ አእይንተ አእምሮ ወትረ ኪያከ ይርአይ/2/

ወአእዛንነኒ ቃለ ዘባሕቲትከ ይስምአ/2/

**ኢይታጸዉ**

ኢይታጸዉ አናቅጽኪ ክቡራት ዕንቁ መሠረትኪ/2/ኦ

ሰናይት ሠላማዊት ሠናይት ማኅደረ ስብሐት/2/

**ሊተሰ**

ሊተሰ ይኄይሰኒ ተሊወ እግዚአብሔር/2/

ወትውክልተየኒ/2/ ላዕለ እግዚአብሔር/2/

**ሰላም ለክሙ**

ሰላም ለክሙ ኦ ማኅበራኒሁ ለክርስቶስ እለ ተጋብአእክሙ ውስተ ዛቲ ማኅደረ ስብሐት/2/

ጳጳሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት መሃይምናን ወመሃይምንት ሕዝበ ክርስቲያን/2/

**ይቤሎሙ ኢየሱስ**

ይቤሎመ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ንዑ ስምዑኒ እንግርክሙ ተለዉ ድኅሬሁ ወተምኅሩ ምግባረ ዚአሁ ወይቤሎሙ ሰላም ለክሙ ሰላመ ዚአየ እሁብክሙ

**ወረብ**

ኢየሱስ(3) ክርስቶስ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ንዑ ስሙዑኒ እንግርክሙ (2)

ተለዉ ድኅሬሁ ወተምህሩ ምግባረ ዘአሁ ወይቤሎሙ ሰላም ለክሙ ሰላመ ዚኢየ እሁበክሙ/2/

ንዑም ጸመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ እስመ ከማሁ አዘዘዘነ/3/

ንዑም ጸመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ እስመ ለሊሁ መድኃኒነ ጸመ

ሃሌ ሉያ /2/ እናመስግነው አምላካችንን ከዳግማዊ ሞት ያዳነን ከሰይጣን ባርነት ያወጣን እናመስግነው አምላካችንን በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን የገለጸልን አጥብቀን ብንሸሸው አብዝቶ የፈለገን እናመስግነው አምላካችንን ምንም ቢበዛ ኃጢአታችን በምሕረቱ የጎበኘን እናመስግነው አምላካችንን ዛሬም በመንግሥቱ እንዲያስበን እንደፈያታ ዘየማን እናመስግነው አምላካችንን እርሱ ነውና መድኃኒታችን

እግዚኦ እግዚእነ እግዚአብሔር ተሰሃለነ ለአግብርቲከ እስመ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌከ ስብሐት ወአኮቴተ ንፌኑ ለስምከ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘእብጻእከነ እስከ ዛቲ ሰዓት በብዘወኃ ሣህልከ

<u>**ቁም ዜማ**</u>

- እግዚኦ እግዚእነ እግዚአብሔር ተሠሃለነ ለአግብርቲከ እስመ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእበሌከ ስብሐተ ወአኮቴት ንፌኑ ለስምከ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአብጻከነ እስከ ዛቲ ሰዓት በብዝኃ ሣህልከ
- አንተ አቡነ ወአንተ እምነ ውስተ ቤትከ ዘአጸንእከነ ከመ ቀደሙ በአርዓያከ ወበአምሣልከ ፈጠርከነ በፈቃድከ ለወንጌልከ መከ ነገርከነ ወመሀርከነ ይእዜኒ እግዚእ እግዚኦ ባርክ ጉባኤነ /ማኅበረነ/ ወሀሎ ማእከሌነ

<u>**ትርጉም:-**</u> አንተ ነህ አባታችን እንዲሁም እናታችን በቤትህ ውስጥ ያሳደከን በአርዓያህና በምሣሌህ ስለፈጠርከን በወንጌልህም ቃል እንደነገርከንና እንዳስተማርከን አቤቱ ዛሬም ባርከው ጉባኤያችንን /ማኅበራችንን/ ደግሞም ተገኝ በመካከላችንን:-

--------------------//---------------------

**ሐዲስ ሐዋርያ**

ሐዲስ ሐዋርያ ተክለ ሃይማኖት
በብርሃን መስቀሉ አሰጠን በረከት
በአማላጅነትህ ይታደለን ጸጋ
ሁሉን ከሚችል አልፋና ያሜጋ

የሥላሴ መዝገብ የምሥጢር ሰሌዳ
ተጽፎብህ ያለ የምስጋና ጋዳ /እጅ መንሻ/
አንተ ታላቅ መሪ እውነተኛ እረኛ
ለኢትዮጵያ ጴጥሮስ ነህ ለበጎቹ ዳኛ

አዝ . . .

የምንጠጣው ውኃ የምንበላው ምግብ
ተበክሏልና በዘንዶ በእባብ
በመስቀሉ ባርከው መርዝነቱ ይጥፋ
ቀናዒው ተክለ አብ የሁላችን ተስፋ

አዝ . . .

የትኅትና አባት የጽድቅ መምህር
እጅግ የበዛ ነው የተሰጠህ ክብር
መከራና ችግር ሲገጥመን ኀዘን
ፈጥነህ ድረስና በክንፍህ ጋርደን

አዝ . . .

በመንፈሳዊው ገድል ጸንተሃል በእምነት
ከአምላክ ተሰጠህ የጽድቅ አክሊላት
በሞትህም ከበርክ አገኘህ እረፍት
እኛንም በምልጃህ አግባን ገነት

**መሠረተ ዜማ**

መሠረተ ዜማ <u>ወጠነ</u> /2/ ያሬድ ካህን (2)
<u>ያሬድ /3/ ያሬድ ካህን</u> /2/ ጥዑመ ልሳን (2)

**ትርጉም:-** የዜማን መሠረት ጀመረ ያሬድ ካህን ያሬድ ካህን ድምጹ ያማረ ነው

**ዜኖኩ ጸድቀከ**

ዜናኩ ጽድቀከ ወነገርኩ አድኅኖተከ ከሠትኩ ቃላቲከ ለሕዝብከ ኢትዮጵያ /2/
በጸጋሁ ለመንፈስቅዱስ ወመሀርክዎሙ አነ ይቤ ያሬድ ጥዑመ ልሳን (2)

ጽድቅህን ነገርኩ አዳኝነትህን አስተማርኩ
ቃላትህንም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነገርኩ (2)
እኔም በመንፈስቅዱስ ጸጋ አስተማርካቸው አለ
ያሬድ ጥዑመ ልሳን (2)

**ኢትዮጵያ**

ለኢትዮጵያ /2/
አሠርገዋ/3/ ለኢትዮጵያ

**ወተቀበልዎ**

ወተቀበልዎ መላእክት በስብሐት ወበማኅሌት /2/
ወአብጽሀዎ ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት /2/

**ገብረ መንፈስ ቅዱስ**

ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘይሠርር በአክናፉ /2/
ኀበ ዓምደ ወርቅ /2/ ስሙ ጽሑፍ /2/

**ጥምቀተ አንጽሐ**

ጥምቀተ አንጽሐ ሕጽው ወንግሥት ለእሊሃሁ
እም ሀበ ፊሊጶስ ድህረ ተጠምቀ ለሊሁ /2/
ሰላማ አቡነ አንጽሐ ለነ በቅድሜሁ ለመድኃኒነ
ምሥጢረ ደሙ ወሥጋሁ /2/

**ሑሩ ወትልዎ**

ይቡሎ መንፈስቅዱስ ለፊልጶስ ሑር ወትልዎ
ለዝንቱ ሰረገላ ዘአፍራስ/2/
ፊልጶስ መሀሮ ለባኮስ በእንተ ክርስቶስ
ወአጥመቆ በማየ ጥምቀት ሐዲስ /2/
አለው መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ሂድና ተከተለው
ይህንን የአፍራስ ሠረገላ /2/
ፊልጶስ አስተማረው ለባኮስ ስለክርስቶስ
አጠመቀው በማየ ጥምቀት ሐዲስ /2/

**አስተዳሎከ ፍኖተ**

ፊልጶስ ለሰላማ አስተዳሎከ ፍኖተ ድኅረ
ተወፈየነ በእደዊከ ጥምቀት /2/
እስመ በሰላማ (2) ነሣእነ ዘቁርባነ ሥርዓተ /2/

**እሉ ውስተ አድባር**

ኤሉ ውስተ አድባር ወበዓታት /2/
ኤሉ ውስተ አድባር ወበአታት /4/

**ኀዲጎ ብዕሲቶ**

ኀዲጎ ብዕሲቶ መኒኖ መንግሥቶ /2/
ዘፈለሰ ዘፈለሰ ዘፈለሰ መኒኖ መንግሥቶ /2/

**ዳኅንኑ ዘስኩ**

ዳኅንኑ ዘስኩ አረጋዊ አቡክሙ ጻድቅ መንኑ ዝስኩ
ብእሲ ዘይን ዕድዎ በምግባረ ሠናይ
**ትርጉም፡-**

**የጻድቃን መዓዛ**

የጻድቃን መዓዛ ደስ ይላል እንደ ጽጌረዳ /2/
ያድነናል (3) ከኃጢአት ፍዳ /2/

**መዓዛ አፈዋት**

መዓዛ አፈዋት ማርያም ማርያም ጽጌ መንግሥት
ቡርክት /2/
ጽጌ ጽጌ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሃ ወአጽብሐ /2/

**<u>እስመአልብነ</u>**

እስመ አልበነ ረዳኢ በጊዜ ምንዳቤ ወሐዘን/2/
እስመ ዘእንበሌከ ባእደ ኢነአምር/4/

**<u>አማን በአማን</u>**

አማን በአማን /4/
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም

**<u>ስምዒ ጸሎተነ</u>**

ስሞዒ ጸሎተነ ወባርኪ ጉባኤነ(2)
ማርያም (3) ወላዲተ አምላክ (2)

**<u>895.ይዌድስዋ መላእክት</u>**

ይዌድስዋ መላክት /2/ ለማርያም /2/
ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ
በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ በዕዋ (2)

**<u>እመቤታችን በቀኝ ቆማለች</u>**

እመቤታችን በቀኝ ቆማለች
የብርሃን ልብሷን ተጎናፅፋለች
ሰአሊነ ምሕረት መዝገበ ፀሎት
አቁራሪተ መዓት የጌታዬ እናት /2/
አዝ -----------

እመቤታችን የብርሃን ልብስሽ
\>> \>> ነይ ተድናጽፌሽ

›› ›› ሰዓታቱን ስናደርስ
>> >> ንኢ ስንልሽ
>> >> በሠጠሽ ቃል ኪዳን
>> >> እንድታስምሪን
>> >> እንለምነሻለን
>> >> ከእግርሽ ስር ወድቀን
አዝ --------
እመቤታችን ከኪሩቤል ድንግል
አንቺን ትበልጫለሽ
ከሦስቱ አካል አንዱን
እመቤታችን ወልድን ስለወልደሽ
ስለዚህ ድንግል ሆይ እመቤታችን
እንወድሻለን
ዘወትር ጠዋት ማታ
እንማልዳለን
አዝ -----------
እመቤታችን ለስም አጠራሩ
ክብር ይግባውና
እናት እንድትሆኚኝ
ሽልሞናልና
ስምሽን ስንጠራ
ሰዎች ያዝኑልናል
ሞገሴ ነሽና
ይድረስሽ ምስጋና
አዝ ---------
እመቤታችን ድንቅ ድንቅ ነገር
ነቢያት ተናገሩ
ሀገረ እግዚአብሔር
ድንግል ናት እያሉ
ሁለተኛው አዳም
ከአንቺ ተወለደ ›
የተዘጋው ደጃፍ
ባንቺ ተከፈተ

አዝ --------
**<u>እንደ ወይን/2/ እንደ ዘለላ/2/</u>**
እንደ ወይን/2/ እንደ ዘለላ/2/
ስምሽ የጣፈጠ ተአምርሽ ያማረ/2/
ያማረ ደንግል ማርያም/2/
**<u>ወእንዘ ትፈትል/2/ ወርቀ ወሜላተ</u>**
ወእንዘ ትፈትል/2/ ወርቀ ወሜላተ
አስተርአያ ገብርኤል ግብተ/2/
ወይቤላ/2/ እስመ ረከብኪ ሞገሰ ኸኸ በኀበ
እግዚአብሔር /2/
**<u>ሐመልማለ ወርቅ/4/</u>**
ሐመልማለ ወርቅ/4/
ማርያም/3/ ሐመልማለ ወርቅ/2/
የወርቅ ልማላሜ/4/
ማርያም /3 የወርቅ ልማላሜ/2